መመሪያ ቁጥር 1073/2017

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ

DIRECTIVE NO. 1073/2025

FEDERAL PUBLIC PROCUREMENT DIRECTIVE

ግንቦት 2017 ዓ.ም

May/ 2025

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ
2. ትርጓሜ
3. የተፈፃሚነት ወሰን

ምዕራፍ ሁለት

ተግባርና ኃላፊነት

4. የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት
5. የመንግሥት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት
6. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት
7. የግዥ ሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት
8. የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ስለማቋቋም
9. የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት
10. ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም
11. ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት
12. የመንግስት መ/ቤቶች የሲስተም አስተዳዳሪ ተግባርና ኃላፊነት

ምዕራፍ ሦስት

መሠረታዊ የመንግስት የግዥ ድንጋጌዎች

ክፍል አንድ

የግዥ ዕቅድ ዝግጅት

13. የግዥ ዕቅድ ስለማስጀመር
14. የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ ማሰባሰብና ማደራጀት
15. የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት
16. የግዥ ዕቅድ ይዘት

Contents

Chapter One

General Provisions

1. Short Title
2. Definitions
3. Scope of Application

Chapter Two

Duties and Responsibilities

4. Duties and Responsibilities of the Ministry of Finance
5. Duties and Responsibilities of the Public Procurement Authority
6. Duties and Responsibilities of Heads of Public Bodies
7. Duties and Responsibilities of the Procurement Unit
8. Establishment of Procurement and Disposal Endorsing Committees
9. Duties and Responsibilities of Procurement and Disposal Endorsing Committees
10. Establishment of Ad-hoc Procurement Evaluation Committees
11. Duties and Responsibilities of Ad-hoc Procurement Evaluation Committees
12. Duties and Responsibilities of the System Administrator of the Public Body

Chapter Three

Basic Provisions of Public Procurement

Section One

Procurement Planning

13. Initiation of the Procurement Plan
14. Identification, Collection, and Organization of Procurement Needs
15. Preparation of the Procurement Plan
16. Content of the Procurement Plan

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

17. የግዥ ዘዴ መምረጥ
18. የግዥ መፈፀሚያ ጊዜ ስለመወሰን
19. የግዥ ዕቅድ ስለመመርመር
20. የግዥ ዕቅድ ስለማፅደቅ እና ስለማሻሻል
21. ዓመታዊ የግዥ ዕቅድን ይፋ ማድረግ
22. የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ ዝግጅት

ክፍል ሁለት

የመንግሥትኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት

23. የመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ግዥ የግንኙነት ዘዴ
24. የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ላይ ስለሚደረግ ምዝገባ
25. የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት አጠቃቀም

ክፍል ሦስት

ልዩ አስተያየት

26. የልዩ አስተያየት ጠቅላላ ድንጋጌዎች
27. በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች የሚደረግ ልዩ አስተያየት
28. ለኢትዮጵያውያን አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች የሚሰጥ ልዩ አስተያየት
29. ኢትዮጵያውያን አባል ለሆኑባቸው የሽርክና ወይም የእሽመሩ ማህበር የሚደረግ ልዩ አስተያየት
30. በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት የሚደረግ ልዩ አስተያየት
31. በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካል ጉዳተኞች የሚደረግ ልዩ አስተያየት
32. በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ የነጋዴ ሴቶች ማህበራት የሚደረግ ልዩ አስተያየት
33. ለቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች የሚደረግ ልዩ አስተያየት
34. የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት ብቻ የሚሳተፉበት ግዥ
35. የልዩ አስተያየት አፈፃፀም

17. Selection of the Procurement Method
18. Determination of Procurement Execution Timelines
19. Review of the Procurement Plan
20. Approval and Amendment of the Procurement Plan
21. Publication of the Annual Procurement Plan
22. Development of Project Procurement Strategies

Section Two

Electronic Procurement System

23. Communication Protocols for e-Government Procurement
24. Registration on the e-Procurement System
25. Use of the e-Government Procurement System

Section Three

Preferences in Public Procurement

26. General Provisions on Preferences
27. Preference for Locally Manufactured Goods
28. Preference for Ethiopian Service Providers, Consultants, and Contractors
29. Preference for Ethiopians in Joint Ventures or Consortiums
30. Preference for Small and Micro Enterprises in Manufacturing
31. Preference for Associations of Persons with Disabilities in Manufacturing
32. Preference for Women's Trading Associations in Manufacturing
33. Preference for Technological Innovation Products
34. Exclusive Procurement for Job-Creation Manufacturing Enterprises

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

35. Implementation of Preferences

ክፍል አራት

የግዥ ሰነዶችን ስለመያዝ እና ይፋ ስለማድረግ

36. የግዥ ሰነዶችን ስለመያዝ
37. የግዥ ሰነዶችን ይፋ ስለማድረግ
38. ግዥዎችን በድረ-ገጽ ይፋ ስለማድረግ

ክፍል አምስት

የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት መስፈርቶች

39. ተወዳዳሪዎች ማሟላት ያለባቸው የቅድመ ብቃት መስፈርቶች
40. የጥቅም ግጭት
41. የመንግስት መ/ቤት የቀድሞ ሰራተኞች በጨረታ ስለሚሳተፉበት አግባብ
42. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች በጨረታ ስለሚሳተፉበት አግባብ

ክፍል ስድስት

የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

43. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ስለማዘጋጀት

ክፍል ሰባት

ዘላቂነት ያለው የግዥ ሥርዓትን ተፈጻሚ ስለማድረግ

44. የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና
45. የአካባቢ ጥበቃን ታሳቢ ያደረገ የመንግስት ግዥ
46. የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ያደረገ መንግስት ግዥ

ክፍል ስምንት

የመንግሥት ግዥ ሥነ-ምግባር

47. ጠቅላላ
48. ምስጢርን መጠበቅ
49. የጥቅም ግጭትን ስለማስወገድ

35. Implementation of Preferences

Section Four
Procurement Records and Disclosure

36. Record-Keeping Requirements
37. Disclosure of Procurement Documents
38. Publication of Procurement Information on Websites

Section Five
Pre-qualification of Candidates

39. Pre-qualification Criteria
40. Conflict of Interest
41. Participation of Former Public Officials in Tenders
42. Participation of Public Enterprises in Tenders

Section Six
Technical Specifications

43. Preparation of Technical Specifications

Section Seven
Sustainable Procurement

44. Life Cycle Cost Analysis
45. Environmentally Sustainable Procurement
46. Socially Responsible Procurement

Section Eight
Public Procurement Ethics

47. General Ethical Principles
48. Confidentiality Obligations
49. Avoidance of Conflicts of Interest
50. Fairness

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

50. ፍትሐዊነት
51. ግልጸኝነት
52. ብቃት

ምዕራፍ አራት

የግዥ ዘዴዎች

53. የግዥ ዘዴ ዓይነቶች

ክፍል አንድ

ግልጽ ጨረታ

54. ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ
55. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ
56. የዓለም ዓቀፍ ግልጽ ጨረታ አፈጻጸም
57. ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች

ክፍል ሁለት
በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ

58. በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ አፈፃፀም
59. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ
60. የሁለት ደረጃ ጨረታ
61. የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ

ክፍል ሶስት
ውስን ጨረታ

62. የውስን ጨረታ አፈጻጸም
63. በተገደበ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ
64. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ
65. ልዩ ፍላጎትን ለማሟላት በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ

ክፍል አራት
በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ

66. የቀጥታ ግዥ አፈጻጸም
67. በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ ላይ ስለሚደረግ ድርድር

51. Transparency
52. Competence

Chapter Four
Procurement Methods

53. Types of Procurement Methods

Section One
Open Tendering

54. National Competitive Bidding
55. International Competitive Bidding
56. Execution of International Competitive Bidding
57. Other International Procurements

Section Two
Selective Tendering

58. Execution of Selective Tendering
59. Pre-Qualification Tendering
60. Two-Stage Bidding
61. Request for Expressions of Interest

Section Three
Limited Tendering

62. Execution of Limited Tendering
63. Restricted Bidding
64. Request for Quotations
65. Procurement via Request for Quotation for Specific Needs

Section Four
Direct Procurement

66. Preconditions for Direct Procurement
67. Negotiation in Direct Procurement

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ክፍል አምስት
በልዩ ሁኔታ የሚፈፀም ግዥ

68. በልዩ ሁኔታ ግዥን ስለመፈፀም
69. የልዩ ሁኔታ ፈቃድ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥ ላይ መከተል የሚገባቸው መርሆዎች
70. የልዩ ሁኔታ ፈቃድ ጥያቄ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት
71. በልዩ ሁኔታ ፈቃድ ጥያቄ ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓቶች

ምዕራፍ አምስት
የግዥ ስልቶች

72. የግዥ ስልት ዓይነቶች

ክፍል አንድ
ስትራቴጂያዊ ግዥ

73. የስትራቴጂያዊ ግዥ አፈፃፀም

ክፍል ሁለት
በማዕቀፍ የሚፈጸም ግዥ

74. የማዕቀፍ ግዥ ጠቅላላ ድንጋጌዎች
75. የማዕቀፍ ግዥ ሁኔታዎች
76. በማዕቀፍ ግዥ የሚሳተፉ አካላት ተግባርና ኃላፊነት
77. የማዕቀፍ ግዥ ጨረታ ሥነ-ሥርዓት
78. የማዕቀፍ ስምምነት ስለመፈረም
79. የማዕቀፍ ውል ስለመፈረም

ክፍል ሦስት
የጋራ ግዥ

80. የጋራ ግዥ ቅድመ-ሁኔታዎች
81. የጋራ ግዥ አፈጻጸም

Section Five
Exceptional Circumstances

68. Procurement under Special Permission
69. Principles and Criteria for Granting Special Permissions
70. Procedures for Submitting Requests for Special Permission
71. Procedures for Responding to Special Permission Requests

Chapter Five
Procurement Approaches

72. Types of Procurement Approaches

Section One
Strategic Procurement

73. Execution of Strategic Procurement

Section Two
Framework Agreements

74. General Provisions
75. Execution of Framework Agreements
76. Duties and Responsibilities of Involved Parties
77. Tender Procedures
78. Signing of Framework Agreements
79. Signing of Framework Contracts

Section Three
Joint Procurement

80. Prerequisites for Joint Procurement
81. Execution of Joint Procurement

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ክፍል አራት
በሊዝ ስምምነት የሚፈፀም ግዥ

82. በሊዝ ስምምነት የሚፈፀም ግዥ አፈጻጸም

ክፍል አምስት
በራስ ኃይል የሚከናወን ሥራ

83. በራስ ኃይል የሚከናወን ሥራ ግዥ አፈጻጸም

ክፍል ስድስት

የተርንኪ ግዥ

84. የተርንኪ ግዥ አፈፃፀም

ክፍል ሰባት
የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ

85. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ ግዥ አፈጻጸም
86. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ ሥነ-ሥርዓት
87. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ አቅራቢዎች ምዝገባ
88. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ የግምገማ ሂደት

ምዕራፍ ስድስት
የግንባታ ሥራ ግዥ አፈፃፀም
ክፍል አንድ
የግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መስፈርቶች
ክፍል አንድ

89. የግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መስፈርቶች
90. የግንባታ ሥራ የአፈፃፀም ምዘና
91. የግንባታ ሥራ ግዥ አጠቃላይ ልምድ
92. የግንባታ ሥራ ግዥ ተዛማጅ የሥራ ልምድ
93. የግንባታ ሥራ ግዥ የፋይናንስ አቋም
94. ዓመታዊ የተርንኦቨር መጠን

Section Four
Procurement through Lease Agreements

82. Execution of Lease-Based Procurement

Section Five
Force Account

83. Execution of Procurement via Force Account

Section Six
Turnkey Procurement

84. Execution of Turnkey Procurement

Section Seven
Electronic Reverse Auction

85. Implementation of Electronic Reverse Auctions
86. Tender Procedures for Electronic Reverse Auctions
87. Registration of Suppliers for Reverse Auctions
88. Evaluation Procedures for Reverse Auctions

Chapter Six
Procurement of Construction Works
Section One
Qualification Criteria

89. General Qualification Criteria
90. Performance Evaluation
91. Overall Experience
92. Relevant Experience
93. Financial Standing
94. Annual Turnover
95. Professional Qualifications and Competence

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

95. በግንባታ ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና ብቃት
96. ለግንባታ ሥራዎች የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ማሟላት
97. ከአንድ በላይ ንዑሳን የግንባታ ስራዎች (lots) በተካተቱበት ግዥ ላይ የልምድ አያያዝ

ክፍል ሁለት

ለተለያዩ የግንባታ ሥራ ዓይነቶች የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

98. ለህንፃ ግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት
99. ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት
100. የመንገድ ኘሮጀክቶች አመዳደብ በንጣፍ ዓይነት
101. ለመንገድ ኘሮጀክቶች የግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት
102. ለግድብ ግንባታ ሥራ እና ለመስኖ ግንባታ ሥራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

ምዕራፍ ሰባት
የጨረታ ሥነ-ሥርዓት

103. የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ
104. የጨረታ ሰነድ
105. የተጫራቾች መመሪያ
106. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ
107. የጨረታ ቅፅና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ
108. አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች
109. የብቃትና የማጣጣማ መስፈርት አዘገጃጀት
110. ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ስለመወሰን
111. ስለ ናሙና አቀራረብ
112. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ
113. የጨረታ ቋንቋ
114. የመጫረቻ ዋጋ
115. የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ
116. የጨረታ ማስከበሪያ
117. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ
118. የጨረታ አከፋፈት

96. Construction Equipment
97. Consideration of Experience in Multi-Component Works

Section Two
Minimum Requirements for Construction Works

98. Minimum Requirements for Building Construction
99. Minimum Requirements for Bridge Construction
100. Road Project Classification
101. Minimum Requirements for Road Construction
102. Minimum Requirements for Dam and Canal Construction

Chapter Seven
Bid Procedures

103. Bid Advertisement
104. Bid Documentation
105. Instructions to Bidders
106. Technical Specifications
107. Bid Form and Price Schedule
108. General and Special Conditions of Contract
109. Evaluation and Qualification Criteria
110. Bid Floating Period
111. Submission of Samples
112. Clarifications and Amendments to Bid Documents
113. Language of the Bid
114. Bid Price
115. Validity Period of Bids
116. Bid Security
117. Submission of Bids
118. Bid Opening
119. Preliminary Evaluation

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

119. የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት ግምገማ እና ማወዳደር
120. ዝርዝር ግምገማ
121. የዋጋ ግምገማ ስለማከናወን
122. የሒሳብ ስህተቶችን ስለማረም
123. የተሰበረ የጨረታ ዋጋ
124. ያልተመጣጣነ የጨረታ ዋጋ
125. ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ውይይት እና በመ/ቤቱ ስለሚጠየቅ ማብራሪያ
126. ጨረታን ማፅደቅ
127. የጨረታ ውጤትን እና አሸናፊነት ማሳወቅ
128. ድህረ-ብቃት ግምገማ

ምዕራፍ ስምንት
የግዥ ውል አስተዳደር እና የውል አለመግባባቶችን ስለመፍታት

129. አጠቃላይ ድንጋጌዎች
130. የግዥ ውል አዘገጃጀት
131. የውል ቅድመ ሁኔታዎች
132. ውል መፈረም
133. የተዋዋይ አካላት ኃላፊነት
134. ውልን ይፋ ስለማድረግ
135. ውል ስለማሻሻል
136. የውል ማስከበሪያ
137. ውልን ተፈፃሚ ስለማድረግ
138. የውል አፈፃፀምን መከታተል
139. የቅድመ ክፍያ አከፋፈል
140. የዋጋ ማስተካከያ
141. ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ
142. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ
143. ለምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ
144. ርክክብ እና ፍተሻ
145. ክፍያ ስለመፈጸም
146. ውል ማጠናቀቅ
147. የጉዳት ካሳ
148. ውልን ስለማቋረጥ
149. ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች
150. ማስታወቂያዎች እና የፅሑፍ ግንኙነቶች

Section Eight
Contract Management and Dispute Resolution

120. Detailed Evaluation
121. Financial Evaluation
122. Rectification of Arithmetic Errors
123. Abnormally Low or Exaggerated Prices
124. Disproportionate Bid Prices
125. Clarifications and Negotiations
126. Endorsement of Bids
127. Notification of Results and Contract Award
128. Post-Qualification Review

129. General Provisions
130. Drafting of Procurement Contracts
131. Contract Preconditions
132. Contract Signing
133. Responsibilities of Contracting Parties
134. Disclosure of Contract
135. Contract Amendments
136. Performance Security
137. Contract Enforcement
138. Contract Monitoring
139. Advance Payment
140. Price Adjustment
141. Price Adjustment – Construction
142. Price Adjustment – Framework Agreements
143. Price Adjustment – Consultancy Services
144. Delivery and Inspection
145. Payment Settlement
146. Contract Closure
147. Liquidated Damages
148. Termination of Contract
149. Force Majeure
150. Written Notices and Communications

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

151. የውል አለመግባባቶችን ስለመፍታት

ምዕራፍ ዘጠኝ
የአቤቱታ እና ይግባኝ አቀራረብና አወሳሰን ሥርዓት
ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች
152. አቤቱታን ወይም ይግባኝን ስለማቅረብ
ክፍል ሁለት
አቤቱታን ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ስለማቅረብ
153. አቤቱታን ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ስለማቅረብ
154. አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ
155. የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ አፈጻጸም ሂደትን ማገድ ስለመቻላቸው
156. የአቤቱታ የሚጣራበት ሂደት እና ውሳኔ አሰጣጥ
ክፍል ሦስት
ለቦርዱ የሚቀርብ ይግባኝ
157. ይግባኝ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ ስለማቋቋም
158. ከቦርድ አባልነት ስለመሰናበት፤
159. የቦርዱ ሥልጣን እና ተግባር
160. የቦርዱ የአሰራር ሥነ-ሥርዓት
161. ቦርዱ ስለሚሰጠው ውሳኔ
162. ቦርዱ ውሳኔውን እንደገና ስለሚያይበት አግባብ
163. ይግባኝ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ስለማቅረብ

ምዕራፍ አስር
የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት እና የሚጣራበት ሥርዓት
164. ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርብ የጥፋተኝነት ሪፖርት
165. የጥፋተኝነት ሪፖርት አቀራረብ
166. ባለሥልጣኑ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች
167. ባለስልጣኑ ውሳኔውን እንደገና ስለሚያይበት አግባብ
168. መረጃን ስለማቅረብ

151. Dispute Settlement Mechanisms

Chapter Nine
Complaints and Appeals
Section One
General Provisions

152. Complaints, Appeals, and Offense Reporting

Section Two
Lodging Complaints

153. Submission to the Head of the Public Body
154. Timeframe for Lodging Complaints
155. Authority to Suspend Procurement
156. Review and Decision-Making Process

Section Three
Appeal to the Complaint Review Board

157. Establishment of the Review Board
158. Resignation of Board Members
159. Powers and Duties of the Board
160. Board Procedures
161. Board Decisions
162. Review of Board Decisions
163. Appeal to Regular Courts

Chapter Ten
Offense Reporting Procedures

164. Submission of Offense Reports to the Authority
165. Process for Submitting Offense Reports
166. Authority's Decision-Making
167. Review of Decisions
168. Submission of Evidence

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ምዕራፍ አስራ አንድ
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

169. ለመንግሥት መ/ቤቶች ስለሚቀርብ የሒሳብ ሰነድ
170. የተሻሩ መመሪያዎች
171. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ
172. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

Chapter Eleven
Miscellaneous Provisions

169. Submission of Financial Documents to Public Bodies
170. Repealed Directives
171. Transitional Provisions
172. Effective Date of the Directive

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

መመሪያ ቁጥር 1073/2017
የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ

የመንግስት ግዥ የቁጥጥር ሥርዓትን በማጠናከር የመንግስት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም እንዲያስገኝ፣ ፍትሐዊ፣ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ለወጣው ገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘት የሚያስችል እንዲሆን ለማድረግ፣

ግዥን ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሐዊ እና ከሙስና የጸዳ እንዲሆን ሊያግዝ የሚችል እና አዋጁን በአግባቡ ሊያስፈጽም የሚችል እንዲሁም ተቀባይነት ካላቸው ዓለም አቀፍ የግዥ ሥርዓቶች ጋር የተናበበ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 አንቀጽ 87(2) እና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 26 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ምዕራፍ አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1073/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የተለየ ትርጉም ካልተሰጣቸው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ"** ማለት የዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ የምክር አገልግሎት ወይም ከምክር ውጪ የሆነ አገልግሎት ሊያሟላ የሚገባውን ጥራት፣ አቅም፣ ዓይነት፣ ደረጃ፣ የአካባቢ ተቀባይነት፣ የቴክኒክ ዕርዳታ፣ ድህረ ሽያጭ

DIRECTIVE NO. 1073/2025
FEDERAL PUBLIC PROCUREMENT DIRECTIVE

Whereas, in order to strengthen the government procurement control system, ensure that public funds are used efficiently to maximize benefits, and build a fair, competitive, and value-for-money procurement system;

Whereas, recognizing the need for a procurement directive that promotes transparency, efficiency, fairness, and accountability, and aligns with internationally accepted procurement practices;

Now therefore, the Ministry of Finance, pursuant to the power vested to it under Article 87(2) of the Public Procurement and Property Administration Proclamation No. 1333/2024 and Article 26 of Proclamation No. 1263/2021, hereby issues this Directive.

CHAPTER ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Directive may be cited as the "Federal Public Procurement Directive No. 1073/2025."

2. Definitions

Unless otherwise provided for the purpose of implementing this Directive, terms and expressions used herein shall have the meanings assigned to them under the Proclamation. In addition, the following terms shall have the following meanings:

1) **"Technical Specification"** means a document that describes the quality, capacity, type, level, environmental compatibility, technical support, and post-sale services required for goods, works,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አገልግሎቶችን ጨምሮ በሁሉም ተጫራቾች መካከል ፍትሐዊ ውድድርን ሊያስገኝ በሚያስችል መልኩ የሚገልጽ ሰነድ ነው፤

2) "አዋጅ" ማለት የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 ነው፤

3) "የግዥ ሥራ ክፍል" ማለት የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንደስራ ባህሪያቸው የሚኖራቸው የውስጥ አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤት የግዥ ዕቅድ የሚያዘጋጅና ግዥ የሚፈጽም የሥራ ክፍል ነው፤

4) "ጠቅላላ ዋጋ" ማለት ለአንድ ግዥ አፈጻጸም ታክስን ጨምሮ ማናቸውም ሌሎች ወጪዎችን በማካተት በመንግስት መስሪያ ቤቱ ለሚፈፀም ግዥ የሚከፈል ዋጋ ነው፤

5) "በማናቸውም ተመሳሳይ ውል" ማለት አዕምሮአዊ ንብረቶችን ለመጠቀም የሚደረግ ውልን፣ የንግድ ስም እና ስያሜን ለማከራየት የሚደረግ ውልን እና ሌሎች ተመሳሳይ ውሎችን ያካትታል፤

6) "የሊዝ ስምምነት" ማለት የመንግሥት መ/ቤቶች በግዥ ምትክ ወጪ ሊቆጥቡ የሚችሉ፣ ተለዋዋጭነት እና የቅርብ ጊዜ ቴክኖሎጂን መጠቀም የሚያስችሉ ንብረቶችን በኪራይ ለተወሰነ ጊዜ ማግኘት የሚችሉበት ውል ነው፤

7) "የጨረታ ማስከበሪያ" ማለት ተጫራቾች በጨረታው ተሳታፊ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ውል እስከሚፈረምበት ጊዜ ድረስ የሚያሲዙት ዋስትና ነው፤

8) "እገዳ" ማለት ኩባንያዎችን ወይም ማናቸውም ግለሰብ በዚህ ህግ መሰረት በማንኛውም ግዥና ሽያጭ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ባለመሆናቸው የታገዱ አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የማካተት ተግባር ነው፤

9) "ውል" ማለት በግዥ ፈፃሚው አካል እና በአቅራቢው መካከል ያለውን ስምምነት የሚያመለክት የጽሁፍ ሰነድ ነው፤

10) "የውል ማስከበሪያ" ማለት የውል ስምምነት በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን ለማረጋገጥ አቅራቢው ለመ/ቤቱ የሚሰጠው በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ነው፤

consultancy, or non-consultancy services, in a manner that facilitates fair competition among all bidders.

2) **"Proclamation"** means the Federal Government Procurement and Property Administration Proclamation No. 1333/2024.

3) **"Procurement Unit"** means the unit responsible for preparing and executing procurement activities in accordance with the Public Body's internal organizational procedures, ensuring coordination with the financial plan and timely and effective budget preparation.

4) **"Total Price"** means the total amount payable by a Public Body for the procurement, including taxes and all other associated costs.

5) **"Any Similar Contract"** means agreements for the use of intellectual property, trade name and brand licenses, or other comparable contractual arrangements.

6) **"Lease Agreement"** means a contract under which a Public Body may acquire property for a defined period through rental, enabling recognition of the expense as equivalent to a purchase and facilitating the use of modern technology.

7) **"Bid Security"** means a guarantee submitted by a bidder from the time of participation until contract award.

8) **"Debarment"** means the exclusion of companies or individuals from participating in any procurement or sales process under this law due to non-qualification or misconduct.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

11) **"የጋራ መጠቀሚያ ዕቃ እና አገልግሎት"** ማለት በባለስልጣኑ የሚለዩ ሆነው ግዥው ለዚሁ ዓላማ በተቋቋመው መ/ቤት በኩል በማዕከል የሚፈጸም ነው፤

12) **"ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍትዌር"** ማለት ፈቃድና አካላዊ ቅጅን የሚይዝ እንዲሁም ለወደፊት ማጣቀሻ እና ለአዲት ዓላማ የግዥ ሂደቶችን የሚያሳይ እና መዝገቦችን የሚያስቀምጥ ዕቃ ነው፤

13) **"የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሐራጅ ጨረታ"** ማለት ተጫራቾች ዋጋን በመቀነስ የሚወዳደሩበት ሂደት ሲሆን መንግስት መ/ቤቱ አነስተኛ ዋጋ ላቀረበው አቅራቢ ውሉን የሚሰጥበት የግዥ ስልት ነው፤

14) **"ቁልፍ ሠራተኛ"** ማለት የድርጅቱን ዋና ስራዎች የማከናወን ኃላፊነት እና በእነዚህ ሥራዎች ላይ ቀጥታ ወሳኝ ሚና ያላቸውን ግለሰቦች የሚያካትት ሲሆን በድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤትም ሆነ በፕሮጀክት ጽ/ቤቶች የሚሰሩ ሆነው የድርጅቱን ዋና ስራ አስፈፃሚዎች እና ዋና ሥራ ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎችን ያካትታል፤

15) **"ኤሌክትሮኒክ ግዥ"** ማለት የመንግስት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በመጠቀም ዕቃዎችን፣ ከምክር ውጪ የሆኑ ሌሎች አገልግሎቶችን፣ የምክር አገልግሎትና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ግዥ የሚፈጸምበት ሥርዓት ነው፤

16) **"የታገዱ አቅራቢዎች ዝርዝር"** ማለት ጥፋት በመፈጸማቸው ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግስት ግዥ ወይም ሽያጭ እንዳይሳተፉ የታገዱ አቅራቢዎችን ዝርዝር የያዘ መረጃ ነው፤

17) **"ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ"** ማለት የመንግስት መ/ቤቶች የታቀዱ የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸው የዕቃዎች፣ ከምክር ውጪ የሆኑ ሌሎች አገልግሎቶች፣ የምክር አገልግሎት እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ግዥ መቼ እና እንዴት እንደሚፈጽሙ የሚገልጽ ሰነድ ነው፤

18) **"ተቆጣጣሪ አካላት"** ማለት ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ተግባራትን ለመቆጣጠር በህግ ስልጣን የተሰጣቸውና ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም የቁጥጥር ሥራ የሚያከናውኑ ተቋማት ማለት ሲሆን፤ ፍትህ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ዋና

9) **"Contract"** means a written agreement concluded between the procuring entity and the supplier.

10) **"Performance Security"** means an unconditional guarantee submitted by the supplier to ensure fulfillment of contractual obligations.

11) **"Common User Goods and Services"** means items designated by the Authority to be centrally procured by a responsible body.

12) **"Marketable Software"** means a licensed tool with a tangible copy capable of documenting procurement processes, supporting future referencing, and audit functions.

13) **"Electronic Reverse Auction"** means a procurement method in which bidders reduce prices competitively and the contract is awarded to the lowest bidder.

14) **"Key Employee"** means an individual responsible for executing the organization's core operations, including professionals at main or project offices and executives managing essential functions.

15) **"Electronic Procurement"** means a digital platform used by Public Bodies to procure goods, works, consultancy, and non-consultancy services.

16) **"List of Debarred Suppliers"** means a register of suppliers prohibited from participating in public procurement or sales for a defined or indefinite period due to violations.

17) **"Annual Procurement Plan"** means a document that outlines the timing and manner in which a Public Body will conduct procurements necessary for program implementation.

18) **"Oversight Bodies"** means entities legally authorized to monitor procurement and

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አዲተር፣ የፌዴራል ስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን፣ የግዥ አፈጻጸምና ንብረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ እና ተመሳሳይ ሚና ያላቸውን ሌሎች አካላትን ይጨምራል፤

19) "ጽሁፍ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት ማናቸውም ሰነድ፣ ማስረጃ፣ ወይም ማስታወቂያ በጽሁፍ እንዲሆን ከተጠየቀ ይህ ሰነድ፣ ማስረጃ ወይም ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ መልክ ከቀረበ ወይም ከተቀመጠ፣ ተደራሽ ከሆነ፣ እና በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል የሚችል ከሆነ የጉዳዩን አቀራረብ አስመልክቶ የተጠየቀው እንደተሟላ ይቆጠራል።

20) በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ጾታ ያገለግላል፤

3. የተፈፃሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል በፌዴራል መንግሥት በጀት የሚተዳደር ወይም በተቋቋመበት ሕግ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ተቋም ተብሎ የተሰየመ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት በሚፈጽመው ግዥ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን፣ በማዕከል የሚፈጸሙ የመድሐኒት አቅርቦቶችና የሕክምና መሣሪያ ግዥዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

3) የመንግስት ጤና ተቋማት ይህን መመሪያ መሰረት በማድረግ የመሠረታዊ መድኃኒቶች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ግዥው በማዕከል በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት መፈጸም የማይቻል ሲሆን ነው።

4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) አፈፃፀም "መሠረታዊ መድኃኒት" ማለት በዋነኛነት የህብረተሰብ ጤናን ከመጠበቅ አኳያ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እና በማንኛውም ጊዜ ከክምችት መጥፋት የሌለባቸውን መድኃኒቶች ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ በሚኒስቴሩ በሚዘጋጅ የመድኃኒት ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ማንኛውም መድኃኒት ነው።

property administration activities, including the Ministry of Justice, the Federal Auditor General, the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission, the Ministry of Finance, the Public Procurement and Property Administration Authority, the Complaint Handling and Decision Board, and other similar institutions.

19) **"Written Form"** means any record, evidence, or communication required by this Directive to be in writing; if such documentation is presented or stored electronically and can be retrieved for future use, it shall fulfill the requirement.

20) Words importing the masculine gender shall include the feminine.

3. Scope of Application

1. This Directive shall apply to procurement conducted by any federal government entities financed in whole or in part by the federal budget or established by law and designated as federal Public Bodies or institutions.

2. Notwithstanding Sub-Article (1), this Directive shall not apply to procurements related to state owned enterprises, centralized procurement of medicines and medical devices.

3. Public health institutions may procure essential medicines under this Directive provided that such procurement was not possible to execut centrally through the Ethiopian Pharmaceuticals Supply Service as outlined in Sub-Article (2).

4. For purposes of Sub-Article (3), "essential medicines" means those prioritized for public health, consistently available, and listed in the pharmaceutical register issued by the Ministry.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ምዕራፍ ሁለት

ተግባርና ኃላፊነት

4. የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ ከተሰጡት ሥልጣን እና ኃላፊነቶች በተጨማሪ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡ -

1) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ለመጠቀም እንደ አስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ የክፍያ ተመን ይወስናል፤
2) በአዋጁ መሠረት የተለየ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ለሚያስፈልጋቸው መ/ቤቶች የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት፤
3) በአዋጁ አንቀጽ 12(2) መሠረት ከባለስልጣኑ በሚቀርብለት የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም ሥርዓትና አተገባበር ጥናት እንዲሁም በጥናቱ ላይ ተመስርቶ ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን መሠረት በማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፤

5. የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ ከተሰጡት ሥልጣን እና ኃላፊነቶች በተጨማሪ ባለስልጣኑ የሚከተሉትን ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖሩታል፤

1) የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ መተግበሪያዎችን የማዋቀር፤ በየጊዜው ወቅታዊ የማድረግ እና የመንግሥት መ/ቤቶች የሚፈጽሟቸው ግዥዎች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተከትለው እንዲፈጸሙ ያደርጋል፤
2) የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ሲስተም አስተዳዳሪ የመንግስት መ/ቤቶች መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል እንዲሁም በተቋማት ተለይተው የሚቀርቡትን ሲስተም አስተዳዳሪዎችን ይመዘግባል፡፡
3) የንግዱ ማህበረሰብ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ምዝገባውንም ያስተዳድራል፤

CHAPTER TWO

DUTIES AND RESPONSIBILITIES

4. Duties and Responsibilities of the Ministry of Finance

In addition to the responsibilities assigned by the Proclamation, the Ministry of Finance shall:

1. Collaborate with relevant institutions to determine and impose a reasonable usage fee for the electronic procurement system, where deemed necessary.
2. Prepare tailored procurement directives for Public Bodies with specialized needs on the basis of the Proclamation.
3. Issue decisions in accordance with Article 12(2) of the Proclamation to improve procurement procedures and enhance the system based on studies and recommendations submitted by the Authority.

5. Duties and Responsibilities of the Authority

In addition to the powers and responsibilities granted by the Proclamation, the Authority shall have the following duties and responsibilities:

1. Ensure that the Government Electronic Procurement System is properly configured and regularly updated, and that all procurements undertaken by Public Bodies are conducted through this system.
2. Issue user licenses to government agencies and register the system administrators designated by each institution.
3. Facilitate access to the Government Electronic Procurement System for the business community and manage the registration of private sector users.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

4) ዕቃዎች፣ ከምክር ውጪ የሆኑ ሌሎች አገልግሎቶች፣ የምክር አገልግሎትና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እንደ ባህሪያቸው በመለየት ምደባና ዝርዝር ካታሎግ ያዘጋጃል፤

5) ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የሚገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ወቅታዊ የተጠቃለለ የግዥ መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን ለሕዝብ ተደራሽ ያደርጋል፤

6) መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን፣ ቅጾችንና ሌሎች የግዥ ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፤

7) እንደአስፈላጊነቱ ለመንግስት መ/ቤቶች ከግዥና ንብረት ሽያጭ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ለማከናወን ውል የገባ ሶስተኛ ወገን የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን እንዲጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፤

8) ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር የመንግስት የልማት አጋሮች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ እንዲጠቀሙ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሚጠቀሙበትን አግባብ ይወስናል፤

9) የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓቱ ለትግበራው የሚረዱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን ለአቅራቢዎች፣ ለመንግስት መ/ቤቶች፣ ለተቆጣጣሪ አካላት፣ ለፋይናንስ ተቋማት እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያሰራጭ እና ይፋ የሚያደርግ መሆኑን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፤

10) የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱ ጨረታ አየር ላይ የሚውልበትን የመጀመሪያ ቀንና ሰዓት በራሱ የሚያስጀምር ስለመሆኑ፣ እንዲሁም የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በራሱ የሚዘጋ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

11) የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓቱ የአቅራቢዎችን የውል አፈጻጸም ደረጃ መረጃ የሚይዝ መሆኑን፣ እንዲሁም መረጃው የመንግስት መ/ቤቶች ለግዥ ጨረታ ግምገማ እንዲጠቀሙ በሚያስችል መልኩ ተደራሽ መሆኑን ይከታተላል፤

12) የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓቱ ቁልፍ የግዥ የአፈጻጸም አመላካቾችን መረጃ ለመያዝ እናየተለያዩሪፖርቶችን ለመቀመር በሚያስችልመልኩ የተዘጋጀ መሆኑን ያረጋግጣል፣

4. Develop a comprehensive catalog of goods, non-consultancy services, consultancy services, and construction works, classified according to their characteristics.

5. Organize and analyze procurement data collected through the electronic system and ensure that relevant, up-to-date information is accessible to the public.

6. Prepare and regularly update standard bidding documents, forms, and other procurement-related templates.

7. Grant authorization, as necessary, for third parties contracted by Public Bodies to utilize the electronic procurement system to perform procurement and asset disposal-related activities.

8. In consultation with the Ministry, authorize government development partners to use the electronic system and determine the terms and modalities of their usage.

9. Monitor and ensure that the electronic procurement system disseminates and discloses relevant procurement information to suppliers, Public Bodies, oversight agencies, financial institutions, and other stakeholders involved in the procurement process.

10. Monitor and verify that the electronic procurement system automatically initiates the official bid opening date and time, and automatically closes submissions at the designated deadline.

11. Ensure that the electronic procurement system maintains data on supplier performance, and that this information is readily accessible to Public Bodies for use in evaluating procurement bids.

12. Ensure that the system is capable of capturing key performance indicators related to procurement and generating relevant analytical reports.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2025

13) ከሚኒስቴሩ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በመንግሥት ግዥ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን የኤሌክትሮኒክ የአሰራር ሥርዓትን መዘርጋት፤

14) ባለስልጣኑ በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት አጠቃቀም ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የደህንነት ተጋላጭነት እና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎችን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል፤

15) ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ለኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱ ትግበራ አግባብነት ካላቸው የመንግስት ተቋማት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ ሥራዎችን ያከናውናል፤

16) በመንግሥት ግዥ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ፖሊሲና ዕቅድ እንዲኖር ማድረግ፣ የተቋሙን እና የሰው ኃይል አቅም ለማጎልበት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ እና የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት፤

17) ለመንግሥት ግዥ አፈፃጸም የሚያገለግል የመረጃ ማሰራጫ እና ክምችት ሥርዓት ማቋቋም፣ ማጎልበት፣ መጠበቅ እና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤

18) በፌደራል እና በክልል መንግስታት መካከል የተጣጣመ የመንግሥት ግዥ ሥርዓት እንዲኖር የሚያስችል ሥራዎችን እንዲሠራ ያደርጋል፤

19) ለመንግስት ግዥ ዕድገት ከሚሰሩ እና በዘርፉ ለመሳተፍ ፍላጎት ካላቸው አካላት ጋር ተቋማዊ ግንኙነት በመፍጠር በትብብር ይሠራል፤

20) የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችን የበጀትና ሌሎች የፋይናንስ መረጃዎችን ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ጋር ማቀናጀት የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

21) ባለስልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር መ·ያተኞች ሊኖራቸው የሚገባውን ዕውቀትና ክህሎት መወሰን፣ የመ·ያ ብቃት የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ መ·ያተኞችን መመዝገብና መቆጣጠር፣ የግዥ መ·ያተኞች ማህበር እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም የሚቋቋመው የመ·ያተኞች ማህበር በሕግ

13. In collaboration with the Ministry and other relevant entities, establish and maintain an operational electronic procurement system applicable to all government procurements.

14. Coordinate with appropriate institutions to implement preventive measures aimed at mitigating security vulnerabilities and operational risks associated with the use of the electronic procurement system.

15. In consultation with the Ministry of Finance, coordinate with relevant government institutions and stakeholders to ensure the effective implementation of the electronic procurement system.

16. Develop and implement a policy and strategic plan for capacity building in government procurement, conduct research to enhance institutional and human resource capacities, and deliver training programs.

17. Establish, maintain, and update a comprehensive data dissemination and storage system that supports the implementation of government procurement.

18. Facilitate the harmonization of public procurement systems between the federal and regional governments.

19. Establish institutional relationships and cooperate with entities that are engaged in or seeking to contribute to the development of public procurement in Ethiopia.

20. Facilitate the integration of budgetary and other financial data from federal government offices with the electronic procurement system.

21. In collaboration with relevant stakeholders, determine the necessary knowledge and qualifications for procurement professionals, issue professional certification, register and supervise procurement professionals, and support the establishment of a professional association.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

የሚሰጠውን ኃላፊነት መውጣት በሚችልበት አቋም ላይ ሲደርስ እንደሁኔታው ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲያከናውን ውክልና መስጠት።

6. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የሚከተሉትን ተጨማሪ ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1) የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች በዘርፉ በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ፣ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
2) የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች ጥሩ ሥነ- ምግባር ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤
3) የግዥ ስራን እንዲፈፅም የሚደራጀው የስራ ክፍል ስራውን በቡድን ለማከናወን የሚያስችል አደረጃጀት ያለውና ግልፅ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ማረጋገጥ፤
4) በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3 እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 በተቀመጠው መሰረት የፕሮጀክት ግዥዎች ከመፈፀማቸው በፊት የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥና አፈጻጸሙን መከታተል፤
5) በአዋጁ አንቀጽ 7(1) መሠረት የተመላከቱትን የመስሪያ ቤቱን ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ማቋቋም፤
6) በግዥ ስራ እና በግዥ አፅዳቂነት ለተመደቡ ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች የመንግስት ግዥ ስርዓትን በሚገባ እንዲያውቁ የሚያስችል ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
7) ለግዥ ስራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የስራ ክፍሉም ሆነ አፅዳቂ ኮሚቴው ስራቸውን በተገቢው ስለመወጣታቸው ክትትል ማድረግ፣ እንደአስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤
8) ውስብስብ ለሆኑ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11

Upon the association's readiness and legal authorization, delegate the aforementioned responsibilities to the association.

6. Duties and Responsibilities of the Heads of Public Bodies

Without prejudice to Article 5 of the Proclamation, the head of the Public Body shall have the following additional duties and responsibilities:

1. Ensure that personnel assigned to procurement responsibilities possess the necessary educational qualifications, work experience, and certification of professional competence as required.
2. Ensure that individuals assigned to procurement roles are of good conduct.
3. Ensure that the procurement unit is organized to support teamwork and operates in accordance with standard operating procedures.
4. Ensure that a project procurement strategy and a corresponding implementation follow-up strategy are developed in accordance with Article 5(3) of the Proclamation and Article 22 of this Directive prior to initiating project-related procurements.
5. Establish a procurement endorsing committee in accordance with Article 7(1) of this Directive to review and approve the Public Body's procurements.
6. Ensure that all procurement personnel and members of the procurement endorsing committee receive training sufficient to understand and apply government procurement procedures.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

የተመለከቱትን ተግባራት የሚያከናውን ከግዥ የስራ ክፍል፣ ለሚፈጸመው ግዥ ተፈላጊ ልምድና እውቀት ያላቸው፣ ከተጠቃሚ የስራ ክፍል ወይም ከሌሎች የስራ ክፍሎች እና እንደአስፈላጊነቱ ከመ/ቤቱ ውጭ የሚመጡ ባለሙያዎችን ያካተተ ጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ ማቋቋም፤

9) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተመላከቱት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የመ/ቤቱን የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ዕቅድ መርምሮ ማፅደቅ፤

10) በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ መፅደቅ የማያስፈልጋቸውን ግዥዎች ማጽደቅ ወይም ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

11) ከዕጩ ተወዳዳሪዎች አንዲሁም ከተጫራቾች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ መስጠት፤

12) የውል ሰነድ መፈረም፣ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ውል የመፈረም ውክልና መስጠት፣ በውሉ መሠረት ግዥው መፈፀሙን መከታተል፤

13) ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ እስከ ሐምሌ 30 ድረስ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓቱን ተከትሎ የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ ወይም በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ይፋ መደረጉን ማረጋገጥ፤

14) ዓመታዊ የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት በመ/ቤቱ የተከናወኑ ግዥዎችን በሙሉ ያካተተ እና እስከ አዲሱ በጀት ዓመት ነሀሴ 30 ቀን ድረስ ተዘጋጅቶ የተላከ መሆኑን ማረጋገጥ፤

15) ለአዲት ሥራው የሚያስፈልጉ መረጃና ማስረጃ በሚፈለገው ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ፣ ለተመደቡት አዲተሮች አገልግሎት የሚሆን የስራ ቦታ እንዲመቻች ማድረግ፣ እና ስለተፈፀሙት ግዥዎች አካሔድ ሊያስረዳ የሚችል ኃላፊ ወይም ባለሙያ እንዲመደብ ማድረግ፤

16) በግዥ አዲት ግኝቶች ላይ ከባለስልጣኑ በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ተገቢ ማስተካከያ የማድረግ እና የተደረጉ ማስተካከያዎችንም ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፤

17) ያለ በቂ ምክንያት ለአቅራቢዎች መክፈል የሚገባው ክፍያ እንዳይዘገይ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ፤

18) በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 9 መሠረት የቀጥታ ግዥ ለመፈጸም የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉና ለመ/ቤቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙ

7. Monitor the performance of the procurement unit and the endorsing committee, and take corrective actions where necessary.

8. Establish an ad-hoc evaluation committee to handle procurements requiring complex technical assessments, including representatives from the procurement unit, beneficiary or related work units, and, where necessary, external professionals.

9. Review and approve the Public Body's procurement plan, ensuring compliance with this Directive and the Proclamation.

10. Approve procurements not requiring endorsement by the committee or delegate authority for such approvals.

11. Review and decide on complaints submitted by bidders or prospective bidders.

12. Sign contracts or delegate authority for contract execution and oversee contract performance.

13. Ensure that the annual procurement plan is finalized by the 30th of Hamle (July 30) and published on the electronic procurement platform.

14. Ensure that the annual procurement performance report is prepared and submitted by the 30th of Nehasé (August 30).

15. Provide auditors with the necessary documentation and support, including workspace and expert explanations as required.

16. Implement corrective measures based on findings from procurement audits and report back to the Authority.

17. Monitor and prevent unjustified delays in payments to suppliers.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

መሆኑን በማረጋገጥ፣ በቀጥታ ግዥው እንዲፈጸም ይወስናል አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

19) የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ተከትሎ የግዥ አፈጻጸምተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችል የተሟላ መዋቅር፣ የሲስተም አስተዳደርና ሌሎች አስፈላጊ የሰው ሃይል መመደቡን ያረጋግጣል፣

20) የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል እንዲፈፅም ለተቋቋመው አካል የሚቀርቡ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዥ ፍላጎት ከመ/ቤቱ ዕቅድ እና በጀት ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ በወቅቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

21) የመ/ቤቱ የግዥ ተግባራት ይህን መመሪያ እና የአጠቃቀም ማንዋሎችን መሰረት በማድረግ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ተከትሎ እንዲፈጸሙ መደገፍ እና መቆጣጠር፣

22) በግዥ ሂደት የሚሳተፉ የመ/ቤቱ የስራ ክፍሎች፣ ኮሚቴዎች፣ ቡድኖችና ባለሙያዎች፣ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አተገባበር ረገድ ከመ/ቤቱ ጋር የሥራ ግንኙነት ያላቸው የውጭ አካላት የሚኖራቸውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችሉ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ውስጥ የተመዘገቡ እና በየስራ ድርሻቸው የተመደቡ መሆኑን ማረጋገጥ፣

23) የመንግሥት መ/ቤቱ ግዥውን በሶስተኛ ወገኖች የሚፈጽም ሲሆን፣ ሶስተኛ ወገኖች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም የግዥ ተግባራትን እንዲፈጽሙ ውክልና መስጠት፣ እና

24) ከመ/ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ለአቅራቢዎች የተፈጸሙ ክፍያዎችን የተመለከተ መረጃዎችን ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት እንዲደርስ ማድረግ፡

:

7. የግዥ ሥራ ክፍል ተግባር እና ኃላፊነት

በአዋጁ የተሰጡት ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግሥት መ/ቤቱ የግዥ የስራ ክፍል ቀጥሎ የተገለጹት ተጨማሪ ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) የመ/ቤቱን ፍላጎት በማሰባሰብ የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ማዘጋጀት እና የተጠቃለለውን ዓመታዊ ሪፖርት እና ሌሎች ሰነዶችን በማዘጋጀት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፣

18. Decide on and oversee direct procurements, ensuring that the conditions under Article 5(9) of the Proclamation are met and that such procurements are economically justifiable.

19. Ensure the Public Body has in place an appropriate organizational structure, system administration, and qualified personnel to facilitate e-procurement.

20. Ensure timely submission of requirements for common user items to the central procurement body designated for framework procurements.

21. Supervise the implementation of procurement activities through the electronic procurement system in line with this Directive and related manuals.

22. Ensure that work units, committees, teams, experts, and external entities interacting with the Public Body are registered on the electronic system and assigned appropriate roles.

23. Delegate authority to third parties to conduct procurement via the electronic system as needed.

24. Ensure that information on payments made to suppliers is submitted to the appropriate tax authority.

7. Duties and Responsibilities of the Procurement Unit

In addition to the responsibilities assigned by the Proclamation, the Procurement Unit shall:

1. Collect procurement needs, prepare procurement plans, and compile quarterly and annual performance reports for

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 4th of June 2025

2) ከሌሎች መ/ቤቶች ፍላጎት ጋር በጣምራ የሚፈፀሙ ግዥዎችን እና በሦስተኛ ወገን የሚከናወኑ ግዥዎችን ይለያል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
3) ግዥያቸው በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ በማዕከል እንዲፈጸሙ በባለስልጣኑ የተወሰኑትን በመለየት የሚፈለጉ መረጃዎች ተሟልተው ግዥውን እንዲፈፅም ስልጣን ለተሰጠው ተቋም በወቅቱ ይልካል፣
4) በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሰ) እና (ሸ) እና በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው በስተቀር ማንኛውም የመንግስት ግዥ በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ላይ ከተመዘገቡ እና የባንክ ሂሳብ ካላቸው አቅራቢዎች የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል፣
5) ከጠያቂ የስራ ክፍል ጋር በመተባበር የጨረታ ሰነድ አዘጋጅቶ ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ኮሚቴው በሚሰጡ አስተያየቶች መሠረት የጨረታ ሰነዶችን ያስተካክላል፣
6) በአዋጁ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የጨረታ ሰነዱን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ ይገልፃል፣ እንደአስፈላጊነቱ በመ/ቤቱ ድረ ገጽ ላይ ይጭናል፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አዋጁንና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተከትሎ ማብራሪያ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣
7) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመጫረቻ ሰነድ መቀበያ ሳጥን ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል፣ጨረታ ይከፍታል፣ እስተቻለ ድረስ የግዥ ጠያቂው ክፍል እና የውስጥ ኦዲት ተወካይ በጨረታ አከፋፈት ስነ-ስርዓቱ ላይ እንዲገኙ ይጋብዛል፣
8) የጨረታ ማስከበሪያ ይቀበላል፣ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ በጨረታ ሰነዱ በተገለጹት ሁኔታዎች መሠረት የጨረታ ማስከበሪያውን ለመንግስት ገቢ ያደርጋል ወይም ተመላሽ ያደርጋል፣
9) ከተጫራቾች የሚቀርቡ የመጫረቻ ሰነዶችን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ የግዥ ሰነዶችን በጥንቃቄ ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ከሚመለከታቸው ሕጋዊ አላካት ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል፣
10) የመጫረቻ ሰነዶችን በቡድን በመሆን ይገመግማል ወይም እንዲገመገሙ ያደርጋል፣ የግዥው መጠን በዚህ መመሪያ ከተጠቀሰው በላይ በመሆኑ ምክንያት የግምገማ ውጤቱ ለግዥ የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ መፅደቅ ያለበት ከሆነ ለኮሚቴው ያቀርባል፣

submission to the head of the Public Body.

2. Identify and coordinate joint procurements with other public bodies and procurements carried out by third parties.

3. Gather and submit data for framework procurements to be carried out centrally designated by the Authority.

4. Ensure that all procurements—except those exempted under Article 34(1)(h) and (i) of the Proclamation—are conducted through registered suppliers on the electronic system with valid bank accounts.

5. Prepare bid documents in collaboration with the requesting work unit, submit them to the endorsing committee, and revise them as necessary based on feedback.

6. Upload bid documents to the electronic system and the Public Body's website, and respond to queries as per Article 50(2) of the Proclamation.

7. Manage the bid submission process, open bids, and involve the procurement initiator and internal audit unit where feasible.

8. Secure bid securities and process forfeitures or returns based on bid document provisions.

9. Maintain and safeguard submitted bid documents and other essential procurement records; respond to authorized information requests.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ከኮሚቴው በሚሰጠው አስተያየት መሠረት ያስተካክላል ወይም እንዲስተካከል ያደርጋል፣

11) የጨረታው ውጤት እና የአሸናፊነት ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ለተጫራቾች ያሳውቃል፣ እንዲሁም በተመሳሳይ ጊዜ የጨረታውን ውጤት ይፋ ያደርጋል፣

12) የመጫረቻ ሰነድ በግዥ የስራ ክፍል ሲገመገም መረጃዎች በትክክል መገልበጣቸውን፣ የሂሳብ ስሌት በትክክል መሰራቱን ወይም አንድን ተጫራች ሊጠቅም ወይም ሊጎዳ የሚችል ማንኛውም ተግባር አለመፈፀሙን ያረጋግጣል፣

13) በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚፀድቁ ግዥዎችን በሚመለከት ከኮሚቴው ለሚቀርቡ የማብራሪያ ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣል ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

14) ከመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ውክልና መሠረት በዚህ መመሪያ ላይ ከተጠቀሱት የገንዘብ ገደቦች በታች የሆኑ ግዥዎችን ያፀድቃል፣

15) የተለየ የውል አስተዳደር የሥራ ክፍል ከሌለ በስተቀር የውል ረቂቅ ያዘጋጃል፣ እንዳስፈላጊነቱ በተዘጋጀው ረቂቅ ላይ ከአቅራቢዎች ጋር ይደራደራል፣ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሠረት ውል ይፈርማል ወይም፣ በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ እንዲፈረም ያደርጋል፣ የመንግስት መ/ቤቱ በውል ስምምነቱ መሰረት ግዴታውን መወጣቱን እና የውል መብቱ መከበሩን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

16) በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀሙ ግዥዎች ተላታፊ የሚሆኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ይመርጣል፣ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 27 (4) መሰረት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን መጠቀም በማይቻልበት ሁኔታ የዋጋ ማቅረቢያ ይሰበስባል፣

17) የዋጋ ማቅረቢያን ጨምሮ የሚፈፀሙ ግዥዎችን በሚመለከት በአሸናፊነት የሚመረጡት የአቅራቢዎች ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን ያረጋግጣል፣

18) በአዋጁ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 3 በተገለጸው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመ/ቤቱን የግዥ አፈጻጸም ሂደት አስመልክቶ መረጃ እንዲሰጠው ጥያቄ ለሚያቀርብ አካል የተጠየቀውን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ይሰጣል። ሆኖም መረጃውን የመስጠት ሂደት መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ

10. Conduct or facilitate bid evaluations and, where thresholds are exceeded, submit evaluation reports to the endorsing committee for review and amendment as necessary.

11. Notify bidders and publicly disclose results through the electronic procurement system.

12. Ensure the accuracy of arithmetic calculations and impartial evaluation of bids.

13. Clarify information requested by the endorsing committee during procurement approvals.

14. Approve procurements within delegated thresholds.

15. Where no dedicated contract administration unit exists, draft, negotiate, and sign contracts (within delegated limits), monitor performance, and ensure contract compliance.

16. For procurements conducted through request for quotations, select eligible bidders and collect quotes when the electronic system is unavailable, in line with Article 27(4) of the Proclamation.

17. Confirm that winning bid prices align with market conditions.

18. Respond promptly to requests for procurement information, except where restricted under Article 19(3) of the Proclamation. If additional costs are incurred, the requester shall bear such costs.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

የሚዳርገው ከሆነ መረጃ ፈላጊው ወጪውን እንዲሸፍን መደረግ ይኖርበታል፣ እና

19) የተለየ የውል አስተዳደር የሥራ ክፍል ከሌለ በስተቀር፣ በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የውል አፈጻጸም መከታተያ ሠነድ በማዘጋጀት የዋጋ ማቅረቢያን ጨምሮ ከመ/ቤቱ ጋር ውል የገቡ አቅራቢዎች ያላቸውን አፈጻጸም መገምገምና መረጃዎችን አደራጅቶ በመያዝ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል::

8. የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1) ከ3 (ሦስት) ያላነሱ አባላት ያሉት የመ/ቤቱን ግዥዎችን እና የሚወገዱ ንብረቶችን ሽያጭ መርምሮ የሚያፀድቅ ከሦስት ዓመታት የማይበልጥ የአገልግሎት ዘመን የሚኖረው (የሚኖራቸው) አንድ ወይም ከአንድ በላይ የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይቋቋማል::

2) የኮሚቴው አባላት የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፣

   ሀ) በተቻለ መጠን በመ/ቤቱ ውስጥ በከፍተኛ ኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ፣

   ለ) ከተለያየ የሙያ ዘርፍ የተውጣጡ እና በመ/ቤቱ ስራ የተሻለ ዕውቀት እና ልምድ ያላቸው፣

   ሐ) ጥሩ ሥነ-ምግባር ያላቸው እና የዲስፕሊን ወይም የወንጀል ጥፋት ሪከርድ የሌለባቸው::

3) የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አባላትን የአገልግሎት ዘመን ለአንድ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ማራዘም ይችላል፣

4) ለግዥ ስራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የስራ ክፍሉም ሆነ አፅዳቂ ኮሚቴው ስራቸውን በተገቢው ሁኔታ ስለመወጣታቸው ክትትል ማድረግ፣ እንደአስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ::

19. Unless there is a dedicated contract administration unit, prepare a contract performance monitoring report for suppliers under contract, including those procured through request for quotation, and submit it to the head of the Public Body.

8. Establishment of a Procurement and Disposal Endorsing Committee

1. A procurement and disposal endorsing committee with a minimum of three (3) members shall be established by the head of the Public Body. The committee's term shall not exceed three years.

2. Members of the committee shall meet the following criteria:

   a) Preferably be senior officials of the Public Body;
   b) Represent diverse professional backgrounds with relevant knowledge and experience;
   c) Be of good character and free from disciplinary or criminal records.

3. The head of the Public Body may renew a member's term once, if appropriate.

4. The head of the Public Body shall monitor procurement activities and ensure that the procurement unit and endorsing committee perform their duties effectively, taking corrective measures as needed.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

9. የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1) በግዥ ስራ ክፍል የሚዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ በዚህ መመሪያ የተመላከቱትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መዘጋጀቱን በማረጋገጥ አስተያየቱን ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡
2) በግዥ ስራ ክፍል የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በዚህ መመሪያ የተመላከቱትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፡፡
3) አዋጁ አንቀጽ 34 መሠረት ከሚፈጸሙ ግዥዎች ወይም በዚህ መመሪያ በዋጋ ማቅረቢያ ከሚፈፀሙ ግዥዎች ውጭ ያሉትን ሌሎች ግዥዎችን የሚከተሉትን የማጣራት ስራዎችን በማከናወን ከግዥ የስራ ክፍል የሚቀርብለትን የግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፣ እንዲስተካከል ወይም እንዲሰረዝ ያደርጋል፣

ሀ/ ግምገማው በወጣው የጨረታ ሰነድ መሠረት መሰራቱን፣

ለ/ የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችና አሰራሮችን የጠበቀ መሆኑን፣

ሐ/ በግዥ ውሳኔ ሀሳቡ ላይ ለመድረስ የተከናወኑት ዝርዝር ግምገማዎችና አጠቃላይ የግዥ ሂደቱ መ/ቤቱ ለሚከፍለው ክፍያ ተመጣጣኙን ለማስገኘት የሚያስችሉ መሆኑን ማረጋገጥ፣

9. Duties and Responsibilities of the Procurement and Property Disposal Endorsing Committee

Without prejudice to the powers and responsibilities vested in it by the Proclamation, the Procurement and Disposal Approval Committee shall have the following detailed powers and responsibilities:

1. To verify that the annual procurement plan prepared by the Procurement Unit is consistent with the requirements set forth in this Directive and to submit its observations to the Chief Executive of the Public Body.
2. To ensure that the bidding documents prepared by the Procurement Unit are in conformity with the standards and requirements prescribed under this Directive.
3. To review, approve, amend, or annul evaluation reports submitted by the Procurement Unit—except those related to procurements conducted pursuant to Article 34 of the Proclamation or through the Request for Quotation method under this Directive—by undertaking the following verification tasks:

   a) Confirm that the evaluation was conducted in accordance with the criteria and instructions contained in the issued bidding documents;
   b) Verify that the evaluation process complies with the applicable provisions and procedures set forth in the Proclamation and this Directive;
   c) Ensure that the evaluations and the overall procurement process are sufficiently robust to justify the procurement decision in light of the financial obligations of the Public Body.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

4) በቀረበው የግዥ ግምገማ ሪፓርት ላይ የሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት የኮሚቴው ውሳኔ ምክንያታዊ መሆን አለበት፣

5) አዋጁን፣ የአፈጻጸም መመሪያውን እና ሌሎች በባለስልጣኑ የሚወጡ የአፈጻጸም ሥርዓቶች በተሻለ ሁኔታ ሊፈጸሙ የሚችሉበትን አሰራር የመ/ቤቱን የበላይ ኃላፊ ያማክራል፣

6) በኮሚቴው ስለተከናወኑ የግዥ ተግባራት፣ ስላጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳቦች የሚገልጽ ሪፖርት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፣

7) በመ/ቤቱ የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት ሂደት ውስጥ በኮሚቴው ስለተወሰኑ ውሳኔዎች በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ፣ በባለስልጣኑ ወይም በሌላ ስልጣን ባለው አካል ሲጠየቅ ማብራሪያ ይሰጣል፣

8) በአቅራቢው ያልተሟላው የውል ግዴታ በመ/ቤቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ተጨማሪ ወጪ እንደማያስከትል እና በአቅራቢው ቸልተኝነት ምክንያት የተፈፀመ አለመሆኑን በማረጋገጥ የውል ማስከበሪያው ለአቅራቢው እንዲመለስለት ውሳኔ ይሰጣል፤

9) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ግዥውን በስራ አመራር ቦርድ እንዲያፀድቁ በሚኒስትሩ ሲፈቀድ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፣ እና

10) የአፅዳቂ ኮሚቴው ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖራቸው ዝርዝር የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት እንዲሁም የስብሰባ ስነ-ስርዓት በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 1 ላይ ተመልክቷል።

4. Ensure that any decision rendered by the Committee on a procurement evaluation report is justifiable and supported by reasonable grounds.

5. Consult the Chief Executive of the Public Body regarding procedures for the optimal implementation of the Proclamation, this Directive, and any other operational guidelines issued by the Authority.

6. Report on procurement activities carried out by the Committee, highlight challenges encountered, and submit proposed solutions to the Chief Executive of the Public Body.

7. Provide explanations to the Chief Executive, the Authority, or any other competent oversight body upon request concerning decisions taken by the Committee during the procurement performance reporting process.

8. Approve the release of performance guarantees to suppliers, provided it has been confirmed that any unfulfilled contractual obligations by the supplier have not caused damage or incurred additional costs to the Public Body, and that such failure was not due to the supplier's negligence.

9. Where authorized by the Minister under Article 7(5) of the Proclamation, the Board of Directors shall assume the duties and responsibilities of the Procurement Approval Committee as described in this Article.

10. The specific roles and responsibilities of the Chairperson and Secretary of the Committee, as well as the procedures governing meetings, shall be stipulated in Annex 1 of this Directive.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

10. ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1) በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ውስብስብ ለሆኑ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች ከግዥ የስራ ክፍል፣ እንዲሁም ለሚፈጸሙ ግዥዎች ተፈላጊ የቴክኒክ ልምድና ዕውቀት ያላቸው ከተጠቃሚ የስራ ክፍል፣ ከሌሎች የስራ ክፍሎች እና እንደአስፈላጊነቱ ከመ/ቤቱ ውጭ የሚመጡ ባመ·ያዎችን ያካተተ ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይቋቋማል።

2) ኮሚቴው ሊኖረው የሚገባው የአባላት ቁጥር እንደ ግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን እና ውስብስብነት በበላይ ኃላፊው ወይም ግምገማው በግዥ የስራ ክፍል የሚከናወን ሲሆን በግዥ ስራ ክፍል ኃላፊው የሚወሰን ሆኖ ከሶስት ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፤

3) ከግዥ የሥራ ክፍል የሚመረጡ ባለሙ·ያዎች ወይም የገምጋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢና አባላት በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 2 መሠረት የጥቅም ግጭት የሌለባቸው መሆኑን በመግለጽ የሥነ ምግባር ደንቡን መፈረም አለባቸው።

4) የስብሰባው ሥነ ሥርዓት፣ የግምገማው ዘዴና ሂደት በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን አባሪ ቁጥር 3 ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል።

5) ኮሚቴው እና ከግዥ ሥራ ክፍል የሚመረጡ ባለሙ·ያዎች በግምገማ ወቅት ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ።

11. ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቋቋመው ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል።

1) በተጠቃሚ የስራ ክፍል ወይንም በግዥ የሥራ ክፍል የተዘጋጀውን የግዥ ዝርዝር መግለጫ (ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ፣ ቢጋር እና ዝርዝር የግንባታ ሥራዎች) እንዲሁም የመገምገሚያ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ግምገማ ያከናውናል፣

2) በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶችና የግምገማ ዘዴ መሠረት በማድረግ ከግዥ የሥራ ክፍል

10. Establishment of an Ad-Hoc Procurement Evaluation Committee

1. Pursuant to Article 5(4) of the Proclamation, the head of the Public Body may establish an ad-hoc procurement evaluation committee for complex procurements, including experts from relevant internal and external units.

2. The number of members shall be determined by the head of the Public Body or the Procurement Unit, based on the value and complexity of the procurement. The committee shall have no fewer than three members.

3. Any expert from the Procurement Unit participating in the evaluation shall disclose conflicts of interest and recuse themselves in accordance with Annex 2 of this Directive.

4. Meeting procedures and evaluation methods shall follow Annex 3 of this Directive.

5. Committee members and Procurement Unit experts shall be held accountable for all actions taken during the evaluation.

11. Duties and Responsibilities of the Ad-Hoc Procurement Evaluation Committee

The ad-hoc procurement evaluation committee established by the head of the public body pursuant to Article 10 shall:

1. Conduct technical evaluations in accordance with the specifications, terms of reference, and evaluation criteria prepared by the user unit or Procurement Unit.

2. Verify the initial evaluation report against the bid criteria and evaluation method.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

የሚቀርብለትን የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማውን ማረጋገጥ፣

3) የቴክኒክ እና እንደአስፈላጊነቱ የድህረ ግምገማዎችን ማከናወንና አንድን ተጫራች ሊጠቅም ወይም ሊጎዳ የሚችል ማንኛውም ተግባር አለመፈፀሙን ማረጋገጥ፣

4) በዚህ መመሪያ የሚቋቋመው ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ዋጋ እና ተዛማጅ ምዘናወችን ማከናወን የለበትም።

5) ግምገማውን ጨረታው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ በማጠናቀቅ ለግዥ የስራ ክፍል ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፣

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ግምገማውየማይጠናቀቅ ከሆነ ጨረታው ጸንቶ መቆያ ጊዜ እንዲራዘም ለግዥ የሥራ ክፍል ቀደም ብሎ ማሳወቅ አለበት፣

7) የቴክኒክ ግምገማውን ውጤት ወይም ሪፖርትበቃለ-ጉባኤ ይዞ ለግዥ የሥራ ክፍል ያቀርባል፣

8) ከሚመለከታቸው አካላት ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል፤

9) እንዳስፈላጊነቱ የግዥው ርክክብ ሲካሄድ በቴክኒክ መስፈርቱ መሰረት የቀረበ መሆኑን ያረጋግጣል፣

10) ሌሎች በበላይ ኃላፊው የሚሰጡትን ኃላፊነትና ተግባራት ያከናውናል።

12. የመንግስት መ/ቤቶች የሲስተም አስተዳዳሪ ተግባርና ኃላፊነት

1) ለመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት አገልግሎት የሚውሉ ተቋማዊ አደረጃጀት እና የተቋሙን ጠቅላላ መረጃ ይመዘግባል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣

2) ከግዥ ጋር የተገናኘ ኃላፊነት ያላቸው የመ/ቤቱ የስራ ክፍሎች፣ ኮሚቴዎች፣ ቡድኖችና ባለሙያዎች በመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱ ላይ እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣

3) በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጥ ትዕዛዝበዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ 2 የተጠቀሱ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ከግዥ ጋር በተያያዘ የተሰጣቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ የስራ ድርሻ ይመድባል፣

4) በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ኃላፊነት ወይም ውክልና መሠረት ከመንግስት መ/ቤቱ ግዥጋር የተያያዙ ተግባራትንለማከናወንውል የገባ ሶስተኛ ወገን ወይም ሌሎች

3. Conduct technical and post-qualification reviews to ensure fairness and impartiality.

4. Ad-hoc procurement evaluation committee shall not conduct price and related evaluations.

5. Submit final technical evaluation results to the Procurement Unit before the expiry of bid validity.

6. If unable to complete the evaluation on time, notify the Procurement Unit to request an extension of the bid validity.

7. Submit technical evaluation reports and meeting minutes to the Procurement Unit.

8. Provide explanations to concerned parties upon request.

9. Ensure goods or services to be delivered comply with technical specifications.

10. Carry out additional tasks as assigned by the head of the Public Body.

12. Duties and Responsibilities of the System Administrator of the Public Body

The system administrator shall:

1. Register and maintain institutional structure and all relevant data in the electronic government procurement system.

2. Ensure that procurement-related units, committees, teams, and personnel are registered in the system.

3. Assign system roles to officials and ensure they perform procurement duties as instructed by the head of the Public Body.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ከውጭ ለሚመጡ አካላት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም ተግባራቸውን ለመወጣትእንዲችሉ ግዥ መፈጸም የሚያስችል ኃላፊነትን ይሰይማል፣ ይከታተላል።

ምዕራፍ ሶስት

መሠረታዊ የመንግስት ግዥ ድንጋጌዎች

ክፍል አንድ

የግዥ ዕቅድ ዝግጅት

13. የግዥ ዕቅድ ስለማስጀመር

1) ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በሥሩ የሚገኙ ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች ያላቸውን የግዥ ፍላጎት ከመ/ቤቱ የሥራ ፕሮግራም፣ ጊዜ፣ እና በጀት ጋር በማመሳከር እንዲያቀርቡ የግዥ የሥራ ክፍል ኃላፊው በኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት አማካኝነት ማስጀምር አለበት።

2) ለዚህ የመመሪያው ክፍል አፈፃፀም "የሥራ ክፍሎች" ማለት እንደ አግባብነቱ በመንግሥት መ/ቤቱ ማዕከል ደረጃ የሚገኙ ሥራ አስፈፃሚዎች፣ ዳይሬክቶሬቶች፣ መምሪያዎች፣ የሥራ ሂደቶች እና ሌሎችም ሲሆኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል።

3) መ/ቤቶች በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸሙ ግዥዎች የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዥ ዕቅድ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችን በማዕከል ግዥ የሚፈጽመው መ/ቤት በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

4) የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዥ ዕቅድን ግዥውን በማዕከል ለሚፈጽመው መ/ቤት በወቅቱ ባለመላካቸው ለሚፈጠሩ የአፈጻጸም ክፍተቶች የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል።

4. Facilitate procurement activities managed by third parties or external bodies and, when authorized, grant them system access for procurement execution.

CHAPTER THREE

BASIC PROVISIONS OF PUBLIC PROCUREMENT

SECTION ONE

PREPARATION OF THE PROCUREMENT PLAN

13. Preparation of the Procurement Plan

1. The Head of the Procurement Unit of any Public Body shall initiate through the electronic procurement system to enable user departments to submit their procurement needs in alignment with the Public Body's work plan, timeline, and budget.

2. For the purpose of this Directive, "Work Units" means executives, directorates, departments, work processes, and other administrative structures at the central or branch level of a Public Body.

3. Entities involved in framework agreements for the procurement of common user items shall strictly adhere to the procurement plan of the Public Body responsible for centralized procurement and ensure timely delivery of items in accordance with the approved schedule.

4. The head of the Public Body shall be accountable for any performance shortfalls resulting from failure to provide common user items in a timely manner to the Public Body responsible for centralized procurement.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

14. የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ ማሰባሰብና ማደራጀት

1) የግዥ ሥራ ክፍል በመንግስት መ/ቤቱሥር ከሚገኙ ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች የግዥ ፍላጎቶች በማሰባሰብ ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን መፈጸም አለበት፡-

ሀ/ በመ/ቤቱ የሚገኙ ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፣

ለ/ ከተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች የቀረበውን ፍላጎት በግዥ ዓይነት፣ ብዛት እና ግምታዊ ነጠላ ዋጋ፣ የጥራት ደረጃ እና የገበያ አማራጭ በማየት መለየት፣

ሐ/ መ/ቤቱ ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራና አገልግሎቶችን መለየት፣

መ/ የቀረበው ፍላጎት በቂ አቅራቢ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ማጣራት፣

ሠ/ በመ/ቤቱ በተደረገ ጥናት በተገኘ የገበያ መረጃ ለየግዥው የሚያስፈልገውን የዋጋ ግምት ማወቅ፣ እና

ረ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎቹ እና ተገቢው ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች መዘጋጀቱን ወይም ወደፊት የሚዘጋጅ መሆኑን ማረጋገጥ።

2) በማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት የሚገኙ ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች በተሰበሰበው እና በተደራጀው መረጃ መሰረት የግዥ ፍላጎታቸውን ማዘጋጀት አለባቸው። የግዥ ፍላጎታቸውን በሚያዘጋጁበት ጊዜ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡-

ሀ/ ፍላጎቱ በመ/ቤቱ ውስጥ ባለ እና ጥቅም ላይ ባለልዋለ ሌላ ሐብት ወይም ንብረት ሊሟላ የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

14. Identifying, Collecting, and Organizing Procurement Needs

1. The Procurement Unit shall gather procurement needs from user departments and perform the following functions to identify annual procurement requirements:

a) Request all Work Units to submit their annual procurement needs;

b) Review submissions considering type, quantity, estimated unit price, required quality, and available market alternatives;

c) Identify goods, construction works, and services to which the Public Body assigns priority;

d) Confirm the availability of sufficient suppliers in the market;

e) Establish cost estimates through market assessment or reliable price references; and

f) Ensure that technical specifications are available or will be developed by knowledgeable experts.

2. Work Units in any Public Bodies shall base their procurement need submissions on accurate and organized data. The Procurement data ensuring the following:

a) The requested item is not already in stock or substitutable by existing property;

b) The item or service is available in the market;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ለ/ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ ምርት ወይንም አገልግሎት ሊሟላ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ/ የግዥ ፍላጎቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ እሴቶችን ያላካተተና መሥሪያ ቤቱን ለአላስፈላጊ ወጪ የማይዳርግ መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ/ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ታስበው የሚፈጸሙ ግዥዎች በሚሆኑበት ጊዜ የግዥ ፍላጎቱ ወደፊት የሚፈጠርን የፍላጎት ዕድገት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፣

ሠ/ አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ መደበኛ አቅርቦት ወይም ደረጃ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣ እና

ረ/ የግዥ ፍላጎቱ የማህበረሰቡን የአካባቢ ደህንነት እና ጥበቃ የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ።

3) የግዥ ሥራ ክፍል ከተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች የተሰባሰበውን ፍላጎት ከገበያ ጥናት የሚገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የግዥ ፍላጎታቸውን ማደራጀት አለባቸው፡-

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃ፣ አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ግዥ በአንድ ላይ የሚፈጸምበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከ50 (ሃምሳ) በመቶ በላይ ድርሻ ያለውን የግዥ ዓይነት መሠረት በማድረግ ማደራጀት፣

ለ/ ተቀራራቢ እና ተመሳሳይ ፍላጎቶችን በአንድ ላይ ማሰባሰብ፣

ሐ/ በአንድ ላይ ለሚፈፀሙ ግዥዎች በቂ አቅራቢ በገበያ ላይ መኖሩን ወይም ግዥው በሚኖረው የአቅራቢ ዓይነት በተለያየ ምድብ በመክፋፈል በቂ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ/ ግዥው ለአፈጻጸም አመቺ እና ክልካይ ሁኔታዎች የሌሉበት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሠ/ ለሀገር ውስጥ አምራቾች፣ የሴት ነጋዴዎች እና አካል ጉዳተኞች ማህበራት እንዲሁም ለጥቃቅንና አነስተኛ የስራ ዕድል ፈጠራ ማህበራት

c) Unusable or unnecessary items are excluded to prevent wasteful expenditure;

d) Long-term procurement needs consider anticipated demand growth;

e) Unless emergency situation happens, the needs can be satisfied under standard market supply conditions; and

f) The procurement needs does not compromise community or environmental safety.

3. Based on the consolidated needs and market information, the Procurement Unit shall organize :

a) In accordance with Article 30(4) of the Proclamation, classify combined procurements in to goods, services, and construction works based on the component representing more than 50% of the value;

b) Consolidate similar or identical needs;

c) Ensure sufficient market competition or divide procurement into lots to increase competition;

d) Structure procurement to support efficiency and eliminate prohibitive requirements; and

e) Promote participation by local manufacturers, women-owned businesses, associations of persons with disabilities, small and micro enterprises,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

የመወዳደር ዕድልን በሚያሰፋ መልኩ አንዲሁም የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን በሚያሰፍን መልኩ ግዥው እንዲደራጅ ማድረግ።

15. የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት

1) የግዥ ሥራ ክፍል ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤት እና ለመስሪያ ቤቱ ተጠሪ የሆኑ አካላት የታቀዱ የሥራ ዝርዝሮችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ግዥ በወቅቱ ለመፈፀም የሚያስችል ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ማዘጋጀት አለበት።
2) በግዥ ሥራ ክፍል የሚዘጋጀው የግዥ ዕቅድ የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መሆን አለበት።

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን የመንግስት ግዥ መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣

ለ/ የግዥ ዕቅዱ የመ/ቤቱን የሥራ ዕቅድ ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር የተጣጣመ ለማድረግ፣ እንዲሁም ውጤታማ የሆነ የበጀት ዝግጅት እንዲኖር ለማድረግ፣

ሐ/ የቁጥቁጥ ግዥን በመከላከል፣ እንዲሁም ውድድርን በማስፋት የመሥሪያ ቤቱን የግዥ አፈጻጸም ጊዜና ወጪ ቆጣቢ ማድረግ፣ እና

መ/ በግዥ አፈጻጸም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን መለየት እንዲሁም ከፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂው ጋር በተገናዘበ መልኩ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ።

16. <u>የግዥ ዕቅድ ይዘት</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 መሠረት የሚዘጋጀው የግዥ ዕቅድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፦

ሀ/ የግዥውን ዓይነት፣

ለ/ የግዥውን መጠን፣

ሐ/ የግዥውን መግለጫ፣

and initiatives that enhance community benefits.

15. Preparing the Procurement Plan

1. The Procurement Unit, any Public Body, and any entity accountable to the Public Body shall prepare an annual procurement plan that enable them to execute the planned activities using the electronic procurement system, based on the approved work plan of the Public Body.

2. The procurement plan prepared by the Procurement Unit shall enable for the execution of the following goals:

a) Reflect the principles of public procurement as outlined in Article 4 of the Proclamation;
b) Align with the Public Body's operational and financial plans to support efficient budget management;
c) Avoid fragmented procurement and promote timeliness, competition, and cost-effectiveness; and
d) Identify potential risks during the execution of the procurement and having the necessary preparation that are aligned with the project strategic procurement.

16. Content of the Procurement Plan

1. The procurement plan to be prepared under Article 15 of this Directive shall contain the following elements:

a) Type of procurement;
b) Quantity of procurement;
c) Technical specifications;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

መ/ ለግዥው የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን፣ በጀት እና የፋይናንስ ምንጭ፣

ሠ/ ለግዥው ተስማሚ የሆነ የውል ዓይነት፣

ረ/ ዋና ዋና የግዥ አፈጻጸም ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ የሚያመለክት መርሐ-ግብር፣ እና

ሰ/ ሌሎች እንደ መ/ቤቱ ባህሪ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን፡ ፡

2) የመንግስት መ/ቤቶች የሚያዘጋጁት ዕቅድ ግዥን በጥቅል ወይም በማዕከል ለመፈጸም በሚያስችል መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

17. የግዥ ዘዴ መምረጥ

1) የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ለእያንዳንዱ የግዥ ዓይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በዕቅዱ ላይ ማመልከት አለባቸው፡፡

2) የመንግስት መ/ቤቱ የግዥ ዕቅዱን በሚያዘጋጅበት ወቅት የሚታወቁ የግዥ ፍላጎቶች ሁሉ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ መካተታቸውን እና ለእያንዳንዱ ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ መመረጡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

18. የግዥ መፈፀሚያ ጊዜ ስለመወሰን

1) የመንግስት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱን በመጠቀም በግዥ ሂደቱ ውስጥ ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑበት ጊዜ መወሰን አለባቸው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን በሚወስኑበት ወቅት የሚከተሉትን እና እንደሚፈፀመው የግዥ ዓይነት ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል፡፡

ሀ/ ግዥው በሚከናወንበት ጊዜ ከመስሪያ ቤቱ የሥራ ፕሮግራም ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣

d) Estimated financial cost, budget, and source of funding;

e) Appropriate contract type;

f) Schedule for major procurement activities and timelines; and

g) Any special considerations relevant to the Public Body.

2. The procurement plan to be prepared by Public Bodies shall be structured to enable bulk or centralized procurement where appropriate.

17. Selection of the Procurement Method

1. The Public Body shall identify the appropriate procurement method for each procurement during the planning phase, selecting from the methods permitted under the Proclamation and this Directive.

2. The procurement plan shall include all known procurement needs and indicate the appropriate procurement method for each.

18. Determining the Procurement Execution Time

1. The Public Body shall schedule key procurement activities during the execution of the procurement using the electronic procurement system.

2. When determining the execution timeframe under sub-article 1 of this Article, the following and other issues appropriate to the types of procurement shall be considered:

a) During the execution of the procurement, alignment with the operational work plan;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

ለ/ በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚኖርበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፣

ሐ/ በዚህ መመሪያ በተገለጸው መሠረት ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ጊዜን የጠበቀ እና አስከተቻለ ድረስ ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃ ተጨማሪ ጊዜ የሰጠ መሆኑን፣ እና

መ/ በተለይ ውስብስብ ለሆኑ እና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ላላቸው ግዥዎች በቂ የሰነድ ማዘጋጃ፣ መገምገሚያ እና ማፅደቂያ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለየግዥ ዓይነቱ የሚወሰነው ጊዜ የግዥ አፈጻጸም ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን ከሚያስፈልገው ጊዜ የረዘመ እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

b) Taking in to consideration of market supply conditions;

c) Observance of minimum floatation period as determined under this Directive and, if necessary, grant for extended bid preparation to attract competitive participation; and

d) For high-value or complex procurements, provision of adequate time for preparation, evaluation, and decision-making.

3. Without prejudice to sub-article 1 of this Article, the time allocated for each procurement must be appropriate and no longer than necessary for completion of the procurement process.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

19. የግዥ ዕቅድ ስለመመርመር

1) በአዋጁ አንቀጽ 7 (4) መሰረት የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በመሥሪያ ቤቱ የግዥ ሥራ ክፍል የተዘጋጀውን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በመመርመር ዕቅዱን በተመለከተ ያለውን ማናቸውንም አስተያየቶች ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል።
2) የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው የግዥ ዕቅዱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ ስለመዘጋጀቱ ይመረምራል፣

ሀ/ የግዥ ፍላጎቶች ከመ/ቤቱ ፕሮግራሞች እና ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር የሚጣጣም መሆኑን፣

ለ/ እያንዳንዱን ፍላጎት ለማሟላት ከግዥ የተሻለ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን፣

ሐ/ ዕቅዱ ግዥን በጥቅል ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ መዘጋጀቱን፣

መ/ የግዥ ዕቅዱ በአዋጁና በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት መዘጋጀቱንና በገበያ ጥናት የተደገፈ መሆኑን፣እና

ሠ/ ከመሥሪያ ቤቱ ልዩ ባህርይ አንፃር ሊሟሉ የሚገባቸውን ሌሎች ሁኔታዎች መሟላታቸውን።

20. የግዥ ዕቅድ ስለማፅደቅ እና ስለማሻሻል

1) የግዥ ሥራ ክፍሎች ያዘጋጁትን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቅርበው ማፅደቅ አለባቸው።
2) የመንግሥት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከግዥ የሥራ ክፍሎች የቀረበለት የግዥ ዕቅድ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ለግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች አፅዳቂ ኮሚቴ መላክ አለበት።
3) የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች አፅዳቂ ኮሚቴው የግዥ ዕቅዱን በመመርመር ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አስተያየቱን መላክ አለበት።

19. Reviewing the Procurement Plan

1. In accordance with Article 7(4) of the Proclamation, the Procurement Endorsing Committee shall review the draft procurement plan submitted by the Procurement Unit and provide feedback to the head of the Public Body.
2. The Committee, when reviewing the plan, shall verify it was prepared taking the following considerations in to account:

a) Alignment of procurement needs with operational and financial plans;
b) That procurement is the most effective solution for meeting identified needs;
c) That opportunities for consolidated procurement have been considered;
d) That the plan is based on market assessment and adheres to the Directive and the Proclamation; and
e) Other special conditions have been taken into account based on the unique features of the Public Body.

20. Approval and Amendment of the Procurement Plan

1. The Procurement Unit shall submit the procurement plan to the head of the Public Body for formal approval.
2. The head shall refer the plan Submitted to it from the Procurement Unit on the basis of sub-article 1 of this Article to the Procurement and Property Disposal Committee for comment.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

4) የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የመ/ቤቱን የግዥ ዕቅድ መርምሮ ማፅደቅ አለበት፤

ሀ/ የግዥ ዕቅዱ ከመ/ቤቱ የስራ ፕሮግራሞች እና ከፋይናንስ ዕቅድ ጋር መጣጣሙን፣ እንዲሁም ውጤታማ የሆነ የበጀት ዝግጅት እንዲኖር በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ መሆኑን፣

ለ/ በጥቅል ሊፈፀሙ የሚችሉ ግዥዎች አንድ ላይ መሰብሰባቸውን፣

ሐ/ ባለስልጣኑ በሚወስነው መሠረት ከሌሎች መ/ቤቶች ግዥዎች ጋር በማዕቀፍ ስምምነት ሊፈጸሙ የሚችሉ ግዥዎችን መለየታቸውን፣ መረጃዎቹ ተሟልተው ግዥውን እንዲፈፅም ስልጣን ለተሰጠው መ/ቤት በወቅቱ የተላኩ መሆኑን፣ እና

መ/ ዕቅዱ የመ/ቤቱን የግዥ ፍላጎቶች በሙሉ ያካተተ እና ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ የኮሚቴውን አስተያየት ማግኘቱን።

5) የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የመ/ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ሂደት በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሠረት መመራቱን ለማረጋገጥ አፈጻጸሙን መከታተል አለበት፡
:

6) በግዥ የሥራ ክፍሎች የተዘጋጀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት ካገኘና ለባለስልጣኑ ከተላከ በኋላ የመንግስት መ/ቤቶች የሚፈጽሟቸው ግዥዎችን መከፋፈል ወይም በዕቅዱ ከተገለጸው ውጭ መፈጸም አይችሉም።

7) የመንግስት መ/ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት እና በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲታመንበት የግዥ ዕቅዳቸውን በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽሉ ይችላሉ።

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በተገለጸው መሠረት የተሻሻለው የግዥ ዕቅድ የመጀመሪያው ዕቅድ

3. The Committee shall review the plan and return its comments to the head of the Public Body.

4. The head of the Public Body shall grant approval after verifying the fulfillment of the conditions:

a) The plan is aligned with operational and financial frameworks and facilitates efficient budgeting;

b) Consolidated procurements are grouped;

c) Procurement through Framework agreement are identified and the information are compiled and reported to the institution designated for such procurement in accordance with the decision of the Authority; and

d) All procurement needs are covered and reviewed by the Procurement Endorsing Committee.

5. The head shall ensure that the procurement execution process is continuously monitored against the approved plan.

6. The procurement plan prepared by the Procurement Unit after once approved and submitted to the Authority, the procurement plan shall not be altered or executed outside the approved framework.

7. The Public Bodies may revise the plan any time as needed, subject to the head's authorization.

8. When a revision of the plan is made in accordance to sub-artice 7 of this Article,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ለተላከላቸው በመ/ቤቱ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እና ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት::

21. ዓመታዊ የግዥ ዕቅድን ይፋ ማድረግ

1) የአዋጁ አንቀጽ 27 (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት መ/ቤቶች በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ከግዥ ዕቅድ ጋር በተገናኘ የሚያከናውኗቸው ማናቸውም ተግባሮች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም መሆን አለበት::

2) የመንግስት መስሪያ ቤቶች ዓመታዊ የግዥ ዕቅዳቸውን እስከ ሐምሌ 30 ድረስ አዘጋጅተው በማጠናቀቅ በኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት በመጠቀም እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለባቸው::

22. የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ ዝግጅት

1) የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከአስቸኳይ ፕሮጀክቶች በስተቀር በፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር አዋጅ ቁጥር 1210/2012 ተከትሎ ለሚዘጋጁ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ ማዘጋጀት አለባቸው::

2) የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂው የፕሮጀክት ጽንሰ ሃሳብ ሰነዱ አካል ተደርጎ በቅድሚያ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን የፕሮጀክቱን ዓላማ ለማሳካት፣ እንዲሁም የመንግስት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚገባውን ፋይዳ በሚያስገኝ መልኩ መዘጋጀት አለበት::

3) የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂው ቢያንስ ፕሮጀክቱን ለማሳካት የሚያስችሉ የግዥ ፍላጎትና ዓይነት፣ የገንዘብ መጠን፣ በግዥው ወቅት ሊያጋጥም የሚችለውን ስጋትና

All revisions shall be communicated to relevant Work Units and the Authority.

21. Publicizing the Annual Procurement Plan

1. Subject to Article 27(4) of the Proclamation, Public Bodies shall ensure that all activities related to the procurement plan are carried out through the electronic procurement system in accordance with the Proclamation and this Directive.
2. Public Bodies shall prepare and finalize the annual procurement plan by July 30 of the Ethiopian calendar and shall make it public through the electronic Government Procurement (e-GP) system and on the official website of the respective Public Body.

22. Preparation of Project Procurement Strategy

1. Public Bodies, with the exception of emergency projects, shall prepare a project procurement strategy for projects governed by the Federal Government Projects Administration and Management Proclamation No. 1210/2020.
2. The project procurement strategy shall be prepared in advance as part of the project concept document aiming to ensure the achievement of the project's objectives and to maximize the value for money in the use of government funds invested in the project.
3. The project procurement strategy shall include, at a minimum, the procurement needs and types required for the project, the estimated financial resources, the potential risks and mitigation methods during procurement, the results of market

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ማቅለያ መንገዶች፣ የገበያ ጥናት፣ አማራጭ የግዥ ዘዴ እና የውል ዓይነት ማካተት አለበት።

4) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚዘጋጅ የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ በሚመለከተው አካል ከጸደቀበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በመ/ቤቱ እና በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ላይ ለህዝብ ተደራሽ መደረግ ይኖርበታል።

ክፍል ሁለት
የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት

23. የመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ግዥ የግንኙነት ዘዴ

1) ከመንግሥት ግዥ ጋር በተያያዘ በባለስልጣኑ፣ በመንግሥት መ/ቤቶች፣በዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ በተጫራቾች እና በአቅራቢዎች፣ በፋይናንስ ተቋማት እና ሌሎች በዚህ መመሪያ በተገለጹት አካላት መካከል እንዲሁም እርስ በእርስ የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በኤሌክትሮኒክ ስርዓቱ በተደገፈ የግንኙነት ዘዴ መሆን አለበት።
2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም "ግንኙነት" ማለት የግዥ ዕቅድ ይፋ ማድረግ፣ የጨረታ ማስታወቂያን፣ የጨረታ ሰነድ ሽያጭን፣ ማሻሻያ እና የማብራሪያ አቀራረብን፣ የቅድመ ጨረታ ስብሰባዎችን፣ የጨረታ መክፈቻ ሥነ-ስርዓቶች፣ የጨረታ ግምገማ ውጤት እና አገላለጽ፣ አቤቱታ አቀራረብ እና ምላሽ አሰጣጥን፣ ይግባኝን እንዲሁም በውል አስተዳደር ወቅት ያሉና ሌሎች ተያያዥ ግንኙነቶችን ያካትታል።
3) በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም የሚቀርብ ማንኛውም ሰነድ ፊርማና ማህተምን በተመለከተ የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ አዋጅ ቁጥር1071/2010 እና የኤሌክትሮኒክስ ትራንዛክሽን አዋጅ ቁጥር 1205/2012 እንደየ አግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።
4) ከመንግስት ግዥ ጋር በተያያዘ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ ተግባርና ኃላፊነት የተሰጣቸው የሥራ ክፍሎች፣ ኮሚቴዎች፣ ቡድኖችና ሠራተኞች ሥራቸውን የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱን ተጠቅመው ማከናወን አለባቸው።
5) በአዋጁ አንቀጽ 27 (4) በተደነገገው መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ሚኒስቴሩ በሚሰጠው ውክልና

assessments, alternative procurement methods, and the types of contracts to be used.
4. Pursuant to this Article, once the project procurement strategy is approved by the responsible body, it shall be published within one month on the Public Body's platform and through the government electronic procurement system for public access.

Section Two
Electronic Procurement System

23. Electronic Government Procurement Communication Method

1. Any communication related to government procurement, involving the Authority, Public Bodies, bidders, contractors, suppliers, financial institutions, and other entities mentioned in this Directive, shall follow a standardized communication procedure supported by the electronic procurement system.
2. For the implementation of Sub-Article 1 of this Article, "**Communication**" includes activities such as publishing procurement plans, bid announcements, contract award notices, pre-bid meetings, bid opening procedures, evaluation results and award notifications, lodging and resolving complaints and appeals, contract administration, and other related communications.
3. Pursuant to the Proclamation and this Directive, all document signatures and stamps related to electronic procurement shall comply with the Electronic Signature Proclamation No. 1071/2018 and the Electronic Transaction Proclamation No. 1205/2020.
4. Work units, committees, teams, and employees involved in government procurement shall perform their duties using the electronic procurement system in accordance with the Proclamation and this Directive.
5. Whenever Public Bodies face circumstances in which electronic procurement systems cannot

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

መሠረት ግዥውን ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ የግዥ ሥርዓት ለመፈፀም የባለስልጣኑን ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ባለስልጣኑ የመንግስት መ/ቤቶች ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ የግዥ ሥርዓት እንዲፈጽሙ ሲፈቅድ ተጫራቾች በጨረታ እንዳይሳተፉ ያልታገዱ መሆኑን በማረጋገጥ መሆን አለበት።

7) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 አፈፃፀም **"የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ"** ማለት ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ በኔትወርክ መቋረጥ ወይም በሌሎች ተገዳኝ መሰረተ ልማቶች የአቅርቦት ችግር ግዥውን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መፈፀም የማይቻል መሆኑን ባለስልጣኑ ሲያምንበት ወይም በባለስልጣኑ የመረጃ ቋት ላይ እክል ሲያጋጥም ወይም ባለስልጣኑ በኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱ ላይ ማንኛውም ሥጋት የተከሰተ መሆኑን ሲረዳ፣ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ሥራ ላይ የማይውልባቸው ሁኔታ ነው።

24. በኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ላይ ስለሚደረግ ምዝገባ

1) የመንግስት መ/ቤቶች፣ እንዲሁም ተቆጣጣሪ አካላት አግባብነት ባለው ሕግእና በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱን ተጠቅመው ለመወጣት እንዲችሉ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ መመዝገብ አለባቸው።

2) የፋይናንስ ተቋማት ከግዥ ጋር የተያያዙ የዋስትና፣ የክፍያ እና ተያያዥ ስራዎችን ለማከናወን እንዲችሉ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ መመዝገብ አለባቸው።

3) በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ጨረታ ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው የንግዱ ማህበረሰብ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ መመዝገብ፣ መረጃዎቻቸውን በማንኛውም ጊዜ ወቅታዊ ማድረግ እና እንደሁኔታው ምዝገባቸውን ማደስ አለባቸው።

be used due to technical issues or other constraints, they must obtain approval from the Authority, based on the delegation provided by the Minister, to use a non-electronic procurement method.

6. Based on Sub-Article 5 of this Article, when the Authority permits Public Bodies to conduct procurement through non-electronic systems, they shall ensure that suppliers who participate are not debarred from bidding.

7. For the implementation of Sub-Article 5 of this Article, the phrase **"circumstances in which electronic procurement systems cannot be used"** refers to situations where the procuring entity experiences network disruptions or other fundamental infrastructural issues that prevent the use of electronic procurement including instances where the Authority deems electronic procurement infeasible, where there are data access restrictions, or where critical system failures occur, or in any other circumstances in which electronic procurement systems are rendered inoperable.

24. Registration on the Electronic Procurement System

1. Government offices and regulatory bodies shall register on the electronic procurement system to fulfill their assigned responsibilities and duties in accordance with applicable laws and this Directive.
2. Financial institutions shall register on the electronic procurement system to facilitate procurement-related transactions, including the provision of guarantees, processing of payments, and other financial services.
3. The business community interested in participating in government electronic procurement processes must register on the electronic system, ensure their information remains current, and renew their registration as necessary.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

25. የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት አጠቃቀም

1) ማንኛውም በመንግስት ግዥ የሚሳተፍ ተጫራች ማናቸውንም ከፋይናንስ ተቋማትየሚቀርቡ ክፍያዎች እና ዋስትናዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመጠቀም የቀረበ መሆኑን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
2) ባለሥልጣኑ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ውስጥ ማንኛውም ስህተት ወይም ግድፈት ወይም ስጋት የተከሰተ መሆኑን ሲረዳ ያለቅድሚያ ማስታወቂያ በማንኛውም ጊዜ አገልግሎቱን በከፊል ወይም በሙሉ ሊያርም ወይም ሊያሻሽል ወይም ሊያቋርጥ ይችላል፤ሆኖም የተወሰደውን እርምጃ ወዲያውኑ ሥርዓቱን ሲጠቀሙ ለነበሩ ተቋማት ማሳወቅ አለበት፡፡
3) ባለሥልጣኑ ላልተጠናቀቁ የግዥ ሂደቶች፣ የመጫረቻ ሰነድ ማስገቢያ ጊዜ በቂ አለመሆን ፣ ለመረጃ መረብ መቋረጥ፣ የተጠቃሚዎች መለያ መጥፋት፣ የድረ-ገጽ መቆራረጥ ወይም መዘጋት፣ አግባብ ባልሆነ አጠቃቀም ወይም በቸልተኝነት ለሚፈጠር ጉዳት፣ ወይም በሌላ በተጠቃሚዎች ተግባር ለሚፈጠሩ ጉዳቶች ኃላፊነት አይወስድም፡፡
4) የመንግስት መ/ቤቶች ጨረታው አየር ላይ በሚቆይበት ጊዜ በራሳቸው የጥንቃቄ ጉድለት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት ለሚፈጠር የጊዜ መቆራረጥወይም የመረጃ ተደራሽነት ችግር ማካካሻ እንዲሆን ችግሩ ከደረሰበት ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ የሚሆን የጊዜ ማራዘሚያ መስጠት አለባቸው፡፡
5) ማንኛውም የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ተጠቃሚና አስተዳዳሪ ጨረታ ከመከፈቱ በፊት የተጫራቾችን መረጃና ማንነት ማግኘት የለበትም፡፡
6) ለግዥ እና ውል አስተዳደር ተግባራት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የሚገለጹ ገደብ የተቀመጠላቸው ጊዜዎች አቆጣጠር በባለስልጣኑ የመረጃ ማዕከል የመረጃ ቋትየጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
7) ማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ተጠቃሚ የተጠቀመውን ኮምፒውተር ትክክለኛውን አሰራር ተከትሎ በመዝጋት ለሌላ ተገልጋይ ጥቅም ላይ እንዳይውል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

25. Utilization of the Electronic Government Procurement System

1. Any bidder participating in public procurement shall be responsible for ensuring that payments and guarantees issued by financial institutions are submitted through the electronic procurement system using the designated format.
2. When the Authority detects any errors, discrepancies, or system failures within the electronic system, it may suspend, modify, or terminate the service at any time without prior notice. However, affected institutions shall be informed of such actions immediately.
3. The Authority shall not be held responsible for procurement processes that remain incomplete due to insufficient submission time, network failures, lost user accounts, website downtime, misuse, negligence, or damages resulting from users' actions.
4. Government offices shall proportionally extend submission deadlines if auctions experience delays or accessibility issues due to their own negligence or inaction during the bid listing period.
5. Prior to the opening of a procurement auction, neither users nor administrators of the electronic procurement system shall have access to bidder information or identities.
6. Time constraints for procurement and contract management processes, as displayed within the electronic procurement system, shall be enforced based on the schedule established by the relevant information center.
7. Any user of the electronic procurement system shall log out of their computer securely to prevent unauthorized access by another user.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ክፍል ሦስት
ልዩ አስተያየት

26. የልዩ አስተያየት ጠቅላላ ድንጋጌዎች

በዋጋ ማቅረቢያ እና በቀጥታ ግዥ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር በማናቸውም ግዥ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 21 መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ከምክር ወጪ ለሆኑ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች፣ በውጭ ሀገር ድርጅቶች እና በአገር በቀል ድርጅቶች መካከል ለሚመሰረት ጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽመ·ር ማህበር ወይም በማምረት ስራ ላይ ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት፣ ለአካል ጉዳተኞች እና የነ,ጋዴ ሴቶች ማህበራት እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች ልዩ አስተያየት ይደረጋል።

27. በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች የሚደረግ ልዩ አስተያየት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 26 መሰረት በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች የሚደረገው ልዩ አስተያየት በዋጋ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተመላከተው መሠረት ተፈጻሚ መደረግ አለበት፤
2) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት ተፈፃሚ የሚደረገው ጨረታ የወጣበትን ዕቃ ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ወጪ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመላከተውን የተጨማሪ እሴት ምጣኔ በተመሰከረለት ኦዲተር በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲቀርብ ይሆናል። በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርበው የኦዲት ሪፖርት ተጫራቹ ጨረታ ከወጣበት አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጨረታ በወጣበት ዕቃ ዓይነት ላይ የተጨመረውን የእሴት መጠን ማሳየት አለበት።
3) የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚያወጣው ማንኛውም ጨረታ ላይ ለመወዳደር የኦዲት ሪፖርት እንዲቀርብ የሚጠየቅ ከሆነ የሚቀርበው የኦዲት ሪፖርት ከሒሣብ አያያዝ እና የኦዲት ቦርድ የጸና የኦዲት ፍቃድ በተሰጠው ባለሙ·ያ ወይም ድርጅት የተዘጋጀ መሆን አለበት።

Section Three
Preference

26. General Provisions on Preference

Except for procurements conducted through a request for quotation or direct procurement, preference shall be granted pursuant to Article 21 of the Proclamation to goods produced in Ethiopia; non-consultancy service providers, consultants, and contractors of Ethiopian nationality; consortium, partnerships, or joint ventures formed between domestic and foreign enterprises; small and micro enterprises engaged in manufacturing; associations of persons with disabilities; women traders' associations; and outputs of technological innovation.

27. Preference for Goods Produced in Ethiopia

1. In accordance with Article 26 of this Directive, preference for goods produced in Ethiopia during price competition shall be implemented pursuant to Sub-Article 3 of this Article.
2. This preference applies to the procurement of manufactured goods for which a bid is issued based on total expenditure, an additional value assessment shall be presented in accordance with Sub-Article 4, supported by an audit report from a certified auditor verifying the domestic value added in Ethiopia. The audit report shall demonstrate the amount of value added within one year from the contract date.
3. Where an audit report is required for participation in any public procurement bid, it must be prepared by a licensed audit professional or organization certified by the Accounting and Audit Board.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

4) በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች የሚሰጠው ልዩ አስተያየት መጠን እና ሊሟላ የሚገባው የታከለ እሴት መጠን፤

ሀ) ለመድኃኒት እና የህክምና መሣሪያዎች ፤

የተጨማሪ እሴት መጣኔ	የልዩ አስተያየት መጠን
20%- 35%	20%
36%- 50%	21%
51% -65%	22%
66%- 80%	23.5%
81% - 100%	25%

ለ) ሌሎች ዕቃዎችን ለማቅረብ ፤

የተጨማሪ እሴት መጣኔ	የልዩ አስተያየት መጠን
20%- 35%	10%
36%- 50%	11%
51% -65%	12%
66%- 80%	13.5%
81% - 100%	15%

5) የተጨማሪ እሴት በትክክል የታከለ ስለመሆኑ የመንግስት መ/ቤቱ አስፈላጊውን ማስረጃ በማስቀረብ እና በመገምገም የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

6) የልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ለመሆን በማሰብ የታከለ እሴት የተጋነነ፣ የተጭበረበረ ወይም የሀሰት መረጃዎችን ያቀረበ ተጫራች በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ተጠያቂ መሆን አለበት።

7) ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ጋር በተገናኘ የተጋነነ፣ አሳሳች የሆነ ወይም የተጭበረበረ ሰነድ ያዘጋጀ ወይም እንዲዘጋጅ የተባበረ አዲተር በወንጀል ጥፋት ተጠያቂ እንዲደረግ

4. The preference margins and corresponding domestic value addition requirements shall be as follows:

a) **For pharmaceutical and medical device suppliers:**

Rate of Added Value	Preference Margin
20%- 35%	20%
36%- 50%	21%
51% -65%	22%
66%- 80%	23.5%
81% - 100%	25%

b) **For suppliers of other goods:**

Domestic Added Value	Preference Margin
20%- 35%	10%
36%- 50%	11%
51% -65%	12%
66%- 80%	13.5%
81% - 100%	15%

5. Public Bodies shall verify the proper application of domestic value addition by reviewing supporting documentation and conducting necessary assessments.

6. Any bidder who submits false, exaggerated, or misleading information to obtain undue benefit shall be held accountable under the provisions of the Proclamation and the enforcement mechanisms outlined in this Directive.

7. In relation to sub-article 3 of this Article, if a document suspected to be false, exaggerated, or

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

የመንግሥት መ/ቤቱ ለፍትሕ አካላት ጥቆማ ማድረግ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በፋይናንስ ሪፖርት እና አዘገጃጀት አዋጅ በተደነገገው መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ የመንግሥት መ/ቤቱ ለሂሳብ አያያዝእና አዲት ቦርድ ሪፖርት ማድረግ አለበት::

8) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 አፈጻጸም "የታከለ እሴት" ማለት ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጭ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፣ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም::

9) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመላከተው ቢኖርም ከዚህ በፊት በአዲት ሊረጋገጥ የሚችል የማምረት ሥራን ያልሰራ ወይም ምርት ለማምረት አዲስ ፋብሪካ የገነባ ድርጅት ወይም ጨረታውን ካሸነፈ በኋላ ምርቱን አምርቶ ለማቅረብ የሚወዳደር ተጫራችን በተመለከተ የልዩ አስተያየቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ተጫራቹ በሚጫረትበት ዕቃ ላይ ያመረተው ናሙና ከጥሬ ዕቃው ጀምሮ እስከ ምርት ድረስ የተጨመረ እሴት መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመላከተው የተሟላ ስለመሆኑ በኦዲተር ሊረጋገጥ ይገባል::

10) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አምራች ዘርፎች ያላቸውን የአገር ውስጥ የተጨማሪ እሴት ምጣኔ ወቅታዊ ጥናትን ለሚኒስቴሩ እና ለባለስልጣኑ ያቀርባል:: ሚኒስቴሩ በጥናቱ ላይ ተመርኩዞ እንደ አግባብነቱ በተለያዩ ዘርፎች ለሚገኙ አምራቾች የሚሆን የሀገር ውስጥ የታከለ እሴት ምጣኔ ሊያወጣ ይችላል::

28. ለኢትዮጵያውያን አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች የሚሰጥ ልዩ አስተያየት

1) የመንግሥት መ/ቤቶች ለኢትዮጵያውያን አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች በአዋጁ አንቀጽ 21 (1) (ለ) በተቀመጠው መሠረት ልዩ አስተያየት መስጠት አለባቸው::

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት በዋጋ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት በሚከተለው መሠረት ተፈፃሚ መደረግ አለበት፤

   ሀ/ ለግንባታ ሥራ እና ለምክር አገልግሎት ግዥዎች 7.5% (ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ)፣

misleading is prepared or co-prepared by an auditor and is used in misconduct, the Public Body must report the matter for criminal prosecution and also notify the Accounting and Audit Board in accordance with the Financial Reporting and Audit Proclamation.

8. For the purposes of Sub-Article 3, "**domestic value added**" refers to the difference between the total production cost and the cost of imported raw materials, supplies, and foreign services. Indirect taxes applied in the production process shall not be considered part of domestic value addition.

9. Notwithstanding Sub-Article 3, preference may also be granted to bidders who have not previously produced the goods under the bid, newly established factories, or bidders who intend to produce the goods after being awarded the contract. The domestic value addition must be verifiable by an auditor and determined according to Sub-Article 4.

10. Without prejudice to Sub-Article 2 of this Article, the Ministry of Industry shall conduct regular studies on sector-specific domestic value addition thresholds and submit recommendations to the Authority and the Minister. Based on these findings, the Ministry may set appropriate value addition benchmarks for different manufacturing sectors.

28. Preference for Ethiopian Service Providers, Consultants, and Contractors

1. In accordance with Article 21(1)(b) of the Proclamation, preference shall be granted to Ethiopian national service providers, consultants, and contractors.

2. The preferences to be granted under sub-article 1 of this Article is in price competition and shall be implemented as follows:

   a) 7.5% for procurement of construction works and consultancy services.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ለ/ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎት ግዥዎች 3% (ሦስት በመቶ)::

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ለግለሰብ ተጫራቾች ተፈፃሚ የሚሆነው ተጫራቹ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ከሆነ ወይም በትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ ብቻ ነው::

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተፈቀደው ልዩ አስተያየት የሕግ ሰውነት ለተሰጣቸው አካላት ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል፡

ሀ/ ድርጅቱ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መ/ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣

ለ/ ከድርጅቱ አክሲዮን ወይም የካፒታል ድርሻ ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በላይ በኢትዮጵያውያን የተያዘ ሲሆን፣

ሐ/ ከድርጅቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በላይ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣ እና

መ/ ከድርጅቱ ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ 40% (አርባ በመቶ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ::

5) የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች የሚወዳደሩበትን ሥራ ቢያሸንፉ ከሥራው ጠቅላላ ዋጋ ከ20 ከመቶ የማያንስ ዋጋ ያለውን ሥራ ለጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት በመስጠት ለማሰራት ግዴታ የገቡ ከሆነ በጨረታው ለዋጋ ከተያዘው ነጥብ ተጨማሪ 2 ከመቶ ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል::

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው ልዩ አስተያየት አፈፃፀም በመደበኛው የጨረታ ሰነድ በገርገር በሚመለከተው አግባብ መሆን አለበት::

29. ኢትዮጵያውያን አባል ለሆኑባቸው የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽመር ማህበር የሚደረግ ልዩ አስተያየት

1) የመንግስት መ/ቤቶች ከዚህ በታች የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ተከትለው ኢትዮጵያውያን አባል የሆኑባቸውየሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽመር ማህበራት ዕቃዎችን፣ ከምክር አገልግሎት ውጭ የሆነ

b) 3% for procurement of non-consultancy services.

3. The preference under Sub-Article 2 shall apply only to individual bidders who are Ethiopian citizens or foreign nationals of Ethiopian descent by birth.

4. The preference granted under sub-article 2 of this Article for legally recognized entities shall apply only if all of the following conditions are satisfied:

   a) The organization is established under Ethiopian law and headquartered in Ethiopia.
   b) More than 50% of its shares or capital are owned by Ethiopian nationals.
   c) More than 50% of its members of the board of directors are Ethiopian nationals.
   d) At least 40% of its key employees are Ethiopian nationals.

5. When a local contractor has entered in to a commitment to subcontract at least 20% of the project value to small and medium enterprises in the event of becoming a winner of the bid, it shall receive an additional 2% preference during price evaluation.

6. The procedures for implementing the additional preference under Sub-Article 5 shall be in accordance to with the standard bidding documents.

29. Preference for Ethiopians who Are Members of Partnerships, Consortium or Joint Ventures

1. Public Bodies shall give preference to consortium, partnerships, or joint ventures that include Ethiopian nationals as members when competing with foreign bidders in tenders for the supply of goods, non-consultancy services,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲሁም፣ በአማካሪነት እና በሥራ ተቋራጭነት ለመሥራት ከውጭ አገር ተጫራቾች ጋር በሚሳተፉበት ማንኛውም ጨረታ በአዋጁ አንቀጽ 21 (1) (ሐ) መሠረት ልዩ አስተያየት መስጠት አለባቸው።

2) የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ አንቀጽ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያውያን አባል የሆኑባቸው የሽርክና ወይም የእሽመር ማህበራት በሚወዳደሩበት ዓለም አቀፍ ጨረታ ላይ 3.5 % ልዩ አስተያየት መስጠት አለባቸው።

3) በጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽመር ማህበር **በዚህ** አንቀጽ ለግንባታ ሥራ እና ለምክር አገልግሎት ግዥዎች የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል፡-

ሀ/ ከሚፈጸመው የግንባታ ሥራ ወይም የምክር አገልግሎት ጠቅላላ መወዳደሪያ ዋጋ ውስጥ የሀገር በቀል ድርጅት ቢያንስ 40% (አርባ በመቶ) መጠን የያዘ ከሆነ እና

ለ/ ከቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ 40% (አርባ በመቶ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ።

4) ለጥምረት ወይም ለሽርክና ወይም ለእሽመር ማህበር በዚህ አንቀጽ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት በዕቃ ግዥዎች ወቅት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል፡-

ሀ/ የሚፈፀመው የዕቃ ግዥ በቴክኒክ ረገድ ውስብስብ በመሆኑ የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚገኝበት መሆኑ በመንግሥት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲረጋገጥ፤

ለ/ ከሚፈፀመው የዕቃ ግዥ ጋር በተያያዘ እንደ ተከላ፣ ገጠማ፣ ሙከራ እና ፍተሻን ጨምሮ ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎቶች መስጠት የሚያስፈልግ ሲሆን እና እነዚህም በአገር በቀል ድርጅቱ በኩል የሚፈጸም ከሆነ፣

ሐ/ ከሚፈጸመው የዕቃ ግዥ ጠቅላላ መወዳደሪያ ዋጋ ውስጥ የሀገር በቀል ድርጅት ቢያንስ 40% (አርባ በመቶ) መጠን የያዘ ከሆነ፣

መ/ በጥምረት፣ በሽርክና፣ እና በእሽመር ማህበር አባላት መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት የአገር በቀል ድርጅቱ የድህረ ሽያጭ አገልግሎቶችን እና

consultancy services, and construction works, in accordance with Article 21(1)(c) of the Proclamation, and subject to the conditions outlined below.

2. Public Bodies shall grant a 3.5% price preference to consortium, partnerships, or joint ventures that include Ethiopian nationals when participating in international tenders.

3. A price preference shall be granted to such consortia, partnerships, or joint ventures for the procurement of construction works and consultancy services if the following conditions are met:

   a) The share of local partners accounts for at least 40% of the total bid value of the construction work or consultancy services.
   b) At least 40% of the key employees are Ethiopian nationals.

4. A price preference shall be granted for the procurement of goods to consortia, partnerships, or joint ventures that meet all the following conditions:

   a) The Head of the Public Body has determined that the goods are technically complex and require knowledge and technology transfer.
   b) The goods require installation, commissioning, testing, inspection, and related services, which can be performed by the local partners.
   c) The share of local partners is at least 40% of the total bid value.
   d) In accordance with the internal agreement among the members, the local partner is assigned responsibility for after-sales and related services required by the Public Body.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ሥራዎችን እንዲያከናውን እና ለመንግስት መ/ቤቱ ኃላፊነትን የሚወስድ ስለመሆኑ ተገቢውን ውክልና የሚሰጥ ከሆነ፣እና

ሠ/ የዕቃውን ገጠማ፣ አጠቃቀም፣ ጥገና እና ተያያዥ አገልግሎቶችን በተመለከተ ለመንግስት መ/ቤቱ ተገቢው ስልጠና በማን፣ መቼ እና እንዴት እንደሚሰጥ በጥምረት፣ በሽርክና፣ እና በእሽሙር ማህበር አባላት መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት የተመላከተ ከሆነ።

5) በውጭ አገር ሥራ ተቋራጭ እና በአገር በቀል ሥራ ተቋራጭ መካከል የሚመሰረት ጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበር የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጭ የሚወዳደርበትን ሥራ ቢያሸንፍ ከሥራው ጠቅላላ ዋጋ ከ20 ከመቶ የማያንስ ዋጋ ያለውን ሥራ ለጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት በንዑስ ተቋራጭነት በመስጠት ለማሰራት ግዴታ የገባ ከሆነ በጨረታው ለዋጋ ከተያዘው ነጥብ ተጨማሪ 2 ከመቶ ልዩ አስተያየት ይደረግለታል።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው ልዩ አስተያየት አፈፃፀም በመደበኛው የጨረታ ሰነድ በዝርዝር በሚመለከተው አግባብ መሆን አለበት።

7) ለዚህ የመመሪያው አንቀጽ አፈፃፀም **"ጥምረት"** ወይም **"የእሽሙር ማህበር"** ማለት አንድን የተወሰነ ፕሮጀክት ወይም የንግድ ዓላማ ለመፈፀም በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ኩባንያዎች፣ ድርጅቶች ወይም ነጋዴዎች መካከል የተቋቋመ ጊዜያዊ የትብብር ጥምረት ሲሆን የተለየ ህጋዊ አካል ሳይኖረው የጋራ ሥራን ለማከናወን እና የጋራ ኃላፊነትን በመጋራት ሥራውን ለመፈፀም ተሳታፊዎች ሀብታቸውን፣እውቀታቸውን እና አቅማቸውን እንዲያሟሉ የሚያስችል ጊዜያዊ ትብብር ነው።

8) ለዚህ የመመሪያው አንቀጽ አፈፃፀም "የሽርክና ማህበር" በንግድ ሕጉ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል።

30. በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት የሚደረግ ልዩ አስተያየት

1) የመንግስት መ/ቤቶች ከዚህ በታች የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ተከትለው በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ያመረቱትን ዕቃዎች ለማቅረብ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር በሚሳተፉበት

c) For medical devices, the agreement among the members must specify which party is responsible for providing training to the Public Body, and indicate the timing and method of delivery.

5. If a consortium, partnership, or joint venture formed between foreign and domestic entities is awarded a domestic construction contract, and at least 20% of the total contract value is subcontracted to a domestic small and medium sized enterprise, an additional 2% preference shall be applied to the bid price.

6. The application of the preference granted under Sub-Article 4 shall be clearly specified in the standard bidding documents.

7. For purposes of this Directive, **a "Joint Venture"** or **"Consortium Association"** refers to a temporary collaboration between two or more companies, organizations, or traders formed for a specific project or commercial purpose. This arrangement does not create a separate legal entity, but establishes joint responsibility through the pooling of resources, expertise, and capabilities to execute the project.

8. For the purpose of this Article, the term **"Consortium Association"** shall carry the meaning provided under the Commercial Code.

30. Preference for Micro and Small Enterprises Engaged in Manufacturing

1. In accordance with Article 21(1)(d) of the Proclamation, Public Bodies shall give preference to goods supplied by micro and small enterprises (MSEs) competing in

Uploaded on the website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ማንኛውም ጨረታ በአዋጁ አንቀጽ 21 (1) (መ) በተቀመጠው መሠረት ልዩ አስተያየት መስጠት አለባቸው።

2) በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አነስተኛና ጥቃቅን ማህበራት ዕቃዎችን ለማቅረብ ከሌሎች የውጭ አገር እና የአገር ውስጥ ተጫራቾች ጋር በሚሳተፉበት ማንኛውም ጨረታ 3% (ሦስት ከመቶ) ልዩ አስተያየት ይሰጣቸዋል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተፈቀደው በተጨማሪ ከዚህ በታች የተመለከቱ ልዩ አስተያየቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ፤

ሀ/ ግዥው በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚፈፀም ሲሆን በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈጻሚ ይደረጋል።

ለ/ በጨረታ ማስከበሪያ እና በውል ማስከበሪያ ምትክ ማህበራቱን ካደራጃቸው የመንግስት ተቋም የሚሰጥ የጨረታ ማስከበሪያ የድጋፍ ደብዳቤ እና የውል ማስከበሪያ ደብዳቤ ማህበራቱ ሊያቀርቡ ይችላሉ። በዚህ መልኩ የሚቀርበው የድጋፍ ደብዳቤ ዋስትና የተሰጠበትን የገንዘብ መጠን በመጥቀስማህበራቱን ባደራጃቸው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የተፈረመ መሆን አለበት። በተጨማሪም መተማመኛ ቅጽ በዚህ መመሪያ አባሪ 4 መሠረት ሞልተው ማቅረብ አለባቸው።

ሐ/ ጥቃቅንና አነስተኛ ማሕበራቱ ልዩ አስተያየት ተደርጎላቸው ከሌሎች ተጫራቾች ጋር እኩል ነጥብ ቢያመጡ ቅድሚያ ያገኛሉ።

መ/ ማህበራቱ የተቋቋሙበትን የሕጋዊነት ማስረጃ በማቅረብ የጨረታ ሰነድ ያለ ክፍያ በነፃ ይሠጣቸዋል።

4) በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አነስተኛና ጥቃቅን ማህበራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟሉ ነው፤

ሀ/ አግባብነት ባለው የአነስተኛና ጥቃቅን የሥራ ዕድል ፈጠራ ሕግ መሰረት የተቋቋሙ መሆን አለባቸው፤

ለ/ ለጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራቱ ልዩ አስተያየት የሚደረግላቸው የራሳቸው የሆኑ የሥራ ውጤት

tenders, subject to fulfillment of the conditions set forth below.

2. Public Bodies shall grant a 3% price preference to MSEs engaed in manufacturing competing against both international and domestic bidders.

3. In addition to the preferences under Sub-Article 2, the following special considerations apply:

   a) In international tenders, only the preferences specified under Sub-Article 1(a) and (b) of Article 27 shall apply.

   b) Instead of bid security and performance secutiry, MSEs may submit support and contract commitment letters issued by their sector's regulatory authority during bid and contract execution. These letters must include the guaranteed financial amount and be approved by the appropriate office. A reliability form must also be completed in accordance with Annex 4 of this Directive.

   c) Where MSEs receive scores equal to those of other bidders, they shall be prioritized during evaluation.

   d) MSEs shall submit legal documentation of their establishment in order to receive bidding documents free of charge.

4. The preference granted under Sub-Articles 2 and 3 applies only if all of the following conditions are met:

   a) The enterprise must be established under the Micro and Small Enterprise Development and Job Creation legislation.

   b) The MSE's shall be eligible for the preference only when the offer

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ምርቶችን ለማቅረብ ብቻ ሲሆን፣ የራሳቸው የሥራ ውጤት ያልሆኑ ሽቀጣሽቀጥ ወይም የፋብሪካ ውጤቶችን የማቅረብ ፈቃድ የተሰጣቸው ከሆነ ልዩ አስተያየት አይደረግላቸውም።

ሐ/ ጥቃቅን እና አነስተኛ ማህበራቱ የልዩ አስተያየት ተጠቃሚ የሚሆኑት የሚወዳደሩበት የግዥ መጠን እስከ ብር አስር ሚሊዮን ብቻ ሲሆን፣ የግዥ መጠኑ ከዚህ የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን ልዩ አስተያየት ሳይሰጣቸው እንዲወዳደሩ ይደረጋል።

መ/ በጨረታ የሚሳተፉት ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ካደራጃቸው ተቋም የሚከተሉትን ሠነዶችን እና ማስረጃዎችን ማቅረብ አለባቸው፤

i. የመልካም ሥራ አፈፃፀም ማስረጃ፣

ii. ፈቃዳቸውን ለሌላ ሦስተኛ ወገን ያላስተላለፉ፣ በጥቃቅን ወይም በአነስተኛ ብቻ ተደራጅተው የቆዩ መሆኑን እና ሌሎች መረጃዎችን የሚገልጽ የድጋፍ ደብዳቤ፣

31. በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካል ጉዳተኞች ማህበራት የሚደረግ ልዩ አስተያየት

1) በአዋጁ አንቀጽ 21 (1) (መ) በተቀመጠው መሠረት በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካል ጉዳተኞች ማህበራትያመረቱትንዕቃዎች ለማቅረብ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር በሚሳተፉበት ማንኛውም ጨረታ በዋጋ ውድድር ወቅት 3% (ሦስት ከመቶ) ልዩ አስተያየት ይሰጣቸዋል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት የሚወዳደሩበት ግዥ በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚፈፀም ሲሆን በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈጻሚ ይደረጋል።

3) የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ልዩ አስተያየት ተደርጎላቸው ከሌሎች ተጫራቾች ጋር እኩል ነጥብ ቢያመጡ ቅድሚያ ያገኛሉ።

4) ለአካል ጉዳተኞች የተፈቀደው የልዩ አስተያየት በማህበር ተደራጅተው የማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ እና ምርታቸውን ለሚያቀርቡ ማህበራት ብቻ ተፈፃሚ ሲሆን፣ ተቀጣሪ ሰራተኞችን ሳይጨምር የማህበሩ

enterprise's own manufactured products. Enterprises that supply goods produced by others are ineligible.

c) The preference is applicable only to procurements with a total value of up to ETB 10 million. MSEs may participate in tenders more than of this value, but without preference.

d) Participating MSEs must submit the following from the relevant government authority:

i. Certificate of good performance; and

ii. A letter confirming that their license has not been transferred and they are operating solely as MSEs.

31. Preference for Associations of Persons with Disabilities Engaged in Manufacturing

1. In accordance with Article 21(1)(d) of the Proclamation, associations of persons with disabilities engaged in manufacturing shall receive a 3% price preference when competing in any tender.

2. Without prejudice to aub-article 1 of this Article, in international tenders, only the preferences authorized under Sub-Article 1(a) and (b) of Article 27 shall apply.

3. If such associations receive scores equal to those of other bidders, they shall be prioritized in the evaluation.

4. This preference applies only to legally registered associations where persons with disabilities hold at least 70% ownership, excluding employees.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

የአክሲዮን ባለቤትነት ድርሻ ቢያንስ ሰባ በመቶ (70%) በአካል ጉዳተኞች የተያዘ መሆን አለበት::

5) በዚህ አንቀጽ የተደነገገውን መብት ተጠቃሚ ለመሆን ተገቢው የአካል ጉዳተኝነት ማስረጃ ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም መቅረብ አለበት::

32. በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ የነጋዴ ሴቶች ማህበራት የሚደረግ ልዩ አስተያየት

1) የመንግስት መ/ቤቶች ከዚህ በታች የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ተከትለው በማናቸውም የማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ የነጋዴ ሴቶች ማህበራት በማምረት ለሚያቀርቧቸው የአገር ውስጥ ምርቶች ከሌሎች ተጫራቾች ጋር በሚሳተፉበት ማንኛውም ጨረታ በአዋጁ አንቀጽ 21 (1) (መ) በተቀመጠው መሠረት ልዩ አስተያየት መስጠት አለባቸው::

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በማምረት ሥራ ላይ የተደራጁ የነጋዴ ሴቶች ማህበራት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ልዩ አስተያየቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ::

ሀ/ በነጋዴ ሴቶች የተደራጁ ማህበራት በአንቀጽ 31 የተቀመጠውን ሁኔታ ሲያሟሉ 3% (ሶስት በመቶ) ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል::

ለ/ ግዥው በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚፈፀም ሲሆን አንቀፅ 27 በንዑስ አንቀጽ1 (ሀ) እና (ለ)የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈጻሚ ይደረጋል::

ሐ/ የነጋዴ ሴቶች ማህበራት ልዩ አስተያየት ተደርጎላቸው ከሌሎች ተጫራቾች ጋር እኩል ነጥብ ቢያመጡ ቅድሚያ ያገኛሉ::

33. ለቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች የሚደረግ ልዩ አስተያየት

1) የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤትን ለማቅረብ የሚሳተፉ ተጫራቾች ከሌሎች የውጭ አገር እና የአገር ውስጥ ተጫራቾች ጋር በሚሳተፉበት ማንኛውም ጨረታ በአዋጁ አንቀጽ 21 (1) (መ) በተቀመጠው መሠረት ልዩ አስተያየት ይሰጣቸዋል::

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጠቀሰው መሠረት ለቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች 5% (አምስት በመቶ) ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል::

5. To qualify for the preference, the association must submit valid certification of disability status issued by the competent government authority.

32. Preference for Women's Enterprise Engaged in Manufacturing

1. In accordance with Article 21(1)(d) of the Proclamation, preference shall be granted to Women's Enterprise engaged in domestic manufacturing when they compete in tenders, provided the conditions below are met.

2. Based on Sub-Article 1, the preferences granted to Women's Enterprise are as follows:

   a) A 3% price preference shall be granted to associations that fulfill the conditions set out in Article 31.
   b) In international tenders, only the preferences provided under Sub-Article 1(a) and (b) of Article 27 shall apply.
   c) If such associations receive scores equal to those of other bidders, they shall be prioritized in the evaluation.

33. Preference for Products of Technological Innovation

1. In accordance with Article 21(1)(d) of the Proclamation, bidders that supply products resulting from technological innovation shall be granted a preference when competing in any tender with other domestic or foreign participants.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

3) የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ ሲሟላ ነው:-

ሀ/ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቱ ለአካባቢ ጥበቃ ወይም ለማህበራዊ ልማት አስተዋፅኦ የሚያደርግ መሆን አለበት፣ ወይም

ለ/ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቱ ግዥ ከተከናወነ በኋላ የቴክኖሎጂውን ዘላቂነት ያለው አጠቃቀም ማሳየት አለበት፣ ወይም

ሐ/ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቱ በመንግሥት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ዘርፎች የስራ እድል ፈጠራ እና የክህሎት ዕድገትን የሚያበረታታ መሆን አለበት፣ ወይም

መ/ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቱ ከውጭ አገር የሚመጡ ዕቃዎችን ለመተካት የሚደግፉ እና ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ጥገኝነትን የሚቀንስ ቴክኖሎጂ መሆን አለበት፤ ወይም

ሠ/ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቱ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ እና የወጪ ንግድ ብዝሃነትን የሚያበረታታ መሆን አለበት፤ ወይም

ረ/ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቱ ለተሻለ የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ እና የዜጎች ተሳትፎን የሚደግፍ መሆን አለበት።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ረ" ከተገለፁት ቅድመ ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ የተሟሉ ስለመሆኑ አግባብነት ባለው የመንግስት አካል በሚሰጥ ማረጋገጫ ሰነድ ሊረጋገጥ ይገባል።

34. የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት ብቻ የሚሳተፉበት ግዥ

1) በአዋጁ አንቀጽ 33(6) እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 64 የተፈቀደው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግስት መ/ቤቶች በሚከተለው መሠረት የሥራ ዕድል ፈጠራ ተቋማትንብቻ በማወዳደር ግዥ መፈጸም ይችላሉ።

2) የመንግስት መ/ቤቶች ከብር 30,000,000.00 /ሰላሳ ሚልዮን ብር/ የማይበልጥ ዋጋ ያለው የግንባታ ሥራን የሥራ ዕድል ፈጠራ ተቋማትን ብቻ አግባብነት ባለው የግዥ ዘዴ በማወዳደር ሊያሰሩ ይችላሉ።

2. Subject to Sub-article (1) of this Article, a preference rate of 5% shall be granted to products of technological innovation.

3. To be eligible for the preference outlined in Sub-article (2), the product of technological innovation must meet at least one of the following criteria:

a) It contributes to environmental protection or social welfare; or
b) It demonstrates technological resilience for continued use after procurement is completed; or
c) It aligns with government priority areas for job creation and skill development;
d) It promotes import substitution in pharmaceutical or medical device sectors and reduces dependency on foreign products; or
e) It fosters a knowledge-based economy and supports diversification in foreign trade; or
f) It enhances public services and encourages national participation.

4. A competent government authority shall verify, through appropriate certification, whether the conditions set forth under Sub-article (3) (a) to (f) have been fulfilled

34. Procurement Exclusively Reserved for Job Creation Manufacturing Enterprises

1. Without prejudice to Article 33(6) of the Proclamation and Article 64 of this Directive, Public Bodies may restrict procurement to job-creation manufacturing enterprises under the following conditions.

2. Public Bodies may procure construction works valued at up to Birr 30,000,000.00 (thirty million Birr) using an appropriate procurement method exclusively from manufacturing

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

3) መንግስት መ/ቤቶች ከብር 5,000,000.00 / አምስት ሚልዮን ብር/ የማይበልጥ ዋጋ ያላቸውን ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን፣ የእንጨትና የብረታ ብረት ውጤቶችን፣ ምግብ እና የምግብ ነክ ምርቶችን የሚያመርቱና የሚያቀርቡ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተቋማትን ብቻ አግባብነት ያለውን የግዥ ዘዴ ተጠቅመው በጨረታ በማወዳደር ሊገዙ ይችላሉ።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 በተደነገገው መሠረት መንግስት መስሪያ ቤቶች ግዥዎችን መፈፀም የሚችሉት ለተመሳሳይ ግዥዎች በአንድ በጀት ዓመት ለግንባታ እስከ ብር 100,000,000.00 /መቶ ሚልዮን ብር/ እና ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን፣ የእንጨትና የብረታ ብረት ውጤቶችን፣ ምግብ እና የምግብ ነክ ምርቶችን እስከ ብር 20,000,000 (ሃያ ሚልዮን) ብቻ ነው።

5) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሠራተኞች ክበባትን በኮንትራት ለመስጠት ሲፈልጉ በዘርፉ ለተሰማሩ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት ቅድሚያ ሰጥቶ በማወዳደር ሥራውን መስጠት ይችላል።

6) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የሥራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት" ማለት የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ማህበራት፣ የጎበረት ሥራ ማህበራት እና በሌሎች ሕጎች የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት ተብለው የተለዩ አካላትን ይጨምራል።

35. የልዩ አስተያየት አፈፃፀም

የመንግስት መስሪያ ቤቶች በዚህ ክፍል የተቀመጡትን ልዩ አስተያየቶች ተፈፃሚ ለማድረግ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ከግምት ማስገባት አለባቸው።

ሀ/ በጨረታ ላይ የሚሳተፉት ተጫራቾች በዚህ ክፍል ከአንድ በላይ ልዩ አስተያየት ለማግኘት ብቁ በሚሆኑበት ወቅት ማግኘት የሚችሉት የልዩ አስተያየት ከፍተኛ የሆነውን አንዱን ብቻ በመምረጥ ነው።

enterprises that create employment opportunities.

3. Public Bodies may procure construction-related materials, wood and metal products, and food and foodstuff items valued at up to Birr 5,000,000.00 (five million Birr) using an appropriate procurement method and competitive procedures exclusively from enterprises that create employment opportunities.

4. In line with Sub-articles (2) and (3), Public Bodies may, within a single budget year, execute procurement of similar goods or works up to a cumulative value not exceeding Birr 100,000,000.00 (one hundred million Birr) for construction works, and Birr 20,000,000.00 (twenty million Birr) for construction-related materials, wood and metal products, and food and foodstuff items.

5. When outsourcing the operation of staff clubs, Public Bodies may prioritize awarding the contract to enterprises that create employment opportunities in this sector, using competitive bidding.

6. For purposes of this Article, "enterprises that create job opportunities" shall mean small, micro, and medium-sized enterprises, cooperative associations, and other entities legally recognized as job-creating organizations.

35. Execution of Preference

Public Bodies shall adhere to the following conditions when implementing the preferences provided under this Section:

a) Bidders participating in the tender process who are eligible for more than one type of preference under this Section shall be required to select and apply only one—the one with the highest rate—during the qualification stage.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ለ/ በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ፣ የሴቶች ነጋዴ ማህበራት እና የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ብቻ እርስ በርሳቸው በጨረታ በሚገናኙበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው ልዩ አስተያየት ውጪ እኩል ነጥብ ቢያመጡ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለሴቶች፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ እንደ ቅደም ተከተላቸው ቅድሚያ የሚሰጥ ሆኖ በውድድሩ ተመሳሳይ ማህበራት እኩል ነጥብ ቢያመጡ ግን በዕጣ ይለያሉ።

ሐ/ በዚህ ክፍል ለተጫራቾች የሚሰጡ ልዩ አስተያየቶች በጨረታ ሰነድ ላይ ለተጫራቾች መገለጽ አለበት።

ክፍል አራት
የግዥ ሰነዶችን ስለመያዝ እና ይፋ ስለማድረግ

36. የግዥ ሰነዶችን ስለመያዝ

በአዋጁ አንቀጽ 19 (1) እና (2) መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የግዥ ሰነዶች በግዥ የስራ ክፍል መያዝ አለባቸው።

ሀ/ ቴክኒካል እና ፋይናንሺያል ፕሮፖዛል፣

ለ/ ግምታዊ የዋጋ ዝርዝሮች፣

ሐ/ የተጫራቾች ብቃቶች እና ልምድ፣

መ/ የሂሳብ መግለጫዎች፣

ሠ/ የሂሳብ ስሌቶች፣ የቴክኒክ ግምገማ ውጤት፣ የግምገማ ሪፖርቶች እና ቃለ- ጉባኤዎች፣

ረ/ የግምገማ የውስጥ ግንኙነቶች እና ውይይቶች፣

ሰ/ በአጽዳቂ ኮሚቴዎች የተሰጠ የውሳኔ ሃሳብ እና የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቃለ-ጉባኤዎች፣

ሸ/ የውል መረጃዎች፣

ቀ/ የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች እና ምርመራዎች፣

በ/ የግዥ መዛግብት ወይም በሰራተኞች ላይ የሚወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች፣ እና

b) In tenders where small and micro enterprises, women's trading enterprises, and associations of persons with disabilities engaged in manufacturing compete and receive identical evaluation scores (excluding additional preference points), the ranking shall be determined in the following order associations of persons with disabilities; Women's trading associations, and small and micro enterprises. If the tie persists between the beneficiearies of the same category, the award shall be determined by a lottery.

c) The preferences granted to bidders under this Section shall be clearly indicated in the bidding documents made available to all participants.

SECTION FOUR

RETENTION OF PROCUREMENT RECORDS AND DISCLOSURE

36. Retention of Procurement Records

Pursuant to Article 19(1) and (2) of the Proclamation, public bodies shall retain the following procurement records within the procurement unit:

a) Technical and financial proposals,
b) Detailed cost estimates,
c) Documentation of bidders' qualifications and experience,
d) Financial statements,
e) Mathematical calculations, technical evaluation results, evaluation reports, and minutes,
f) Internal communications and deliberations related to evaluations,
g) Recommendations from endorsing committees and minutes signed by the head of the public body,
h) Contract-related documents,
i) Internal audit reports and findings,
j) Procurement files or disciplinary actions taken against employees, and

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ተ/ የመንግስት መ/ቤቶች አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ሌሎች የግዥ ሰነዶች::

37. የግዥ ሰነዶችን ይፋ ስለማድረግ

1) የመንግስት መ/ቤቶች የሚከተሉትን የግዥ መረጃዎች የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ለህዝብ ይፋ መደረግ አለባቸው፣

ሀ/ ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ እና የተጠቃለለ ዓመታዊ የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት፣

ለ/ የጨረታ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሰነድ፣

ሐ/ በአዋጁ አንቀጽ 63 ከተገለጸው ውጪ በማንኛውም የመንግስት መ/ቤቶች የሚፈፀሙ ግዥዎች የጨረታ አሸናፊው ከተመረጠና የግዥ ውል ከተፈረመ በኋላ ባሉት 5 ቀናት ውስጥ ውል የገባው ድርጅት ስም፣ የግዥው ዓይነት፣ የውል ጊዜና ዋጋ፣ እንዲሁም የአቅራቢዎች የውል አፈጻጸም የሚያሳዩ ዋና ዋና መረጃዎች፣

መ/ የተጫራቾች የቴክኒክና የዋጋ ግምገማ ውጤትና የአሸናፊ ተጫራች ማንነት፣

ሠ) በግዥ ሂደቱ ላይ አቤቱታ ቀርቦ የአቤቱታውን ሂደት የሚገልጹ ዋና ዋና መረጃዎች፣

ረ/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች መረጃዎችን፣

2) ባለስልጣኑ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም የተመዘገቡ አቅራቢዎች ዝርዝር እና በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፉ የታገዱ አቅራቢዎች ዝርዝር ለህዝብ ይፋ ያደርጋል::

3) የመንግስት መ/ቤቶች የሚያሳዩት ወይም የሚያሰራጩት ማንኛውም መረጃ ወይም መግለጫ አስተማማኝ፣ ትክክለኛ ወይም የተሟላ ስለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት አለባቸው::

38. ግዥዎችን በድረ-ገጽ ይፋ ስለማድረግ

በአዋጁ አንቀጽ 63 መሠረት ከሚፈጸሙ ሚስጢራዊ ግዥዎች ካልሆኑ በስተቀር በማንኛውም የመንግስት መ/ቤቶች የሚፈፀሙ ግዥዎች የግዥ ጨረታው አሸናፊ ከተመረጠና የግዥ ውል ከተፈረመ በኋላ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ የውል

k) Any other procurement-related documents deemed necessary by the public body.

37. Disclosure of Procurement Documents

1. Public bodies shall disclose the following procurement-related information via the electronic government procurement system:

   a) Annual procurement plan and consolidated annual procurement performance report,
   b) Bid invitations and bid documents,
   c) In addition to the requirements under Article 63 of the Proclamation, for procurements conducted by any public institution, within 5 days after the contract is signed and the winning bidder is notified, the following information shall be disclosed: the name of the contracted supplier, type of procurement, contract duration and value, and key performance data on the supplier,
   d) Evaluation results of the technical and financial proposals, and the identity of the successful bidder,
   e) For any complaints submitted regarding the procurement process, relevant information demonstrating the handling and resolution of the complaint,
   f) Any other information deemed necessary.

2. The Public Procurement and Property Authority shall publish, through the electronic government procurement system, a list of registered suppliers and suppliers debarred from participating in public procurement.

3. Public bodies must ensure that all procurement-related information they provide or disseminate is accurate, reliable, and complete.

38. Publication of Procurement Information on the Website

Except for confidential procurements conducted under Article 63 of the Proclamation, for any procurement conducted by a public body, the essential contract information must be published via the electronic

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 29th of June 2023

መረጃዎች በኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱ ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለባቸው::

ክፍል አምስት
የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት መስፈርቶች

39. ተወዳዳሪዎች ማሟላት ያለባቸው የቅድመ ብቃት መስፈርቶች

1) በአዋጁ አንቀጽ 24 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ ተወዳዳሪዎች ወደ ዝርዝር ግምገማ ከማለፋቸው በፊት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል::

   ሀ/ ግዥው የተጨማሪ እሴት ታክስ የማይመለከተው ካልሆነ በስተቀር የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ፣

   ለ/ የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና አግባብ ባለው የመንግስት ተቋም የተሰጠ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ፣

   ሐ/ ተወዳዳሪዎች የሚሳተፉት ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃን ወይም አገልግሎትን ለማቅረብ በሚሆንበት ጊዜ፣ ለኤክሳይዝ ታክስ የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያሳይ ሰርተፊኬት ማቅረብ፣

   መ/ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማያያዝ፣

   ሠ/ ተጫራቹ የተሰጠውን የጨረታ ቅጽ በአግባቡ መመላት፣

   ረ/ ላለማጭበርበር ቃል የሚገባበት ቅጽ መመላት፣

   ሰ/ ተወዳዳሪዎች በግብር ዓመቱ ተገቢውን የታክስ እና ግብር ግዴታ የተወጡ መሆኑን የሚያሳይ የታክስ ክሊራንስ፣

   ሸ/ እንዳስፈላጊነቱ የብቃት ማረጋገጫ ሰነዶች፣ ከአምራች ወይም ከአከፋፋዮች የሚሰጥ ውክልና ወይም የእሽመር ማህበር መመስረቻ ሰነድ እንዲሁም ሌሎችም አስፈላጊ ሰነዶች ተካተው መቅረብ አለበት::

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት መ/ቤቶች ጠቅላላ ዋጋቸው ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ለማይበልጡ የአንድ ጊዜ ግዥዎች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ አቅራቢዎች እንዲወዳደሩ ሊፈቅዱ ይችላሉ::

3) ተጫራቹ በሰነደ መ·ዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር በመንግስት ግዥ ላይ የሚሳተፉ

procurement system within five days of signing the contract with the winning bidder.

SECTION FIVE
PRE-QUALIFICATION CRITERIA FOR BIDDERS

39. Pre-Qualification Criteria

1. Pursuant to Article 24 of the Proclamation, before proceeding to detailed evaluation, bidders shall meet the following requirements:

   a) Valid value-added tax (VAT) registration certificate, unless the procurement is exempt from VAT,
   b) Trade registration certificate and valid trade license issued by the appropriate government authority,
   c) For procurements subject to excise tax, a valid excise tax registration certificate,
   d) Bid security in accordance with the bid document,
   e) Properly completed bid submission form,
   f) Properly completed anti-collusion declaration,
   g) Valid tax clearance certificate demonstrating the bidder's fulfillment of tax obligations for the relevant fiscal year,
   h) Documents verifying competency, including manufacturer or distributor authorization letters or consortium formation agreements, where applicable.

2. Notwithstanding Sub-article 1(a) of this Article, public bodies may allow suppliers not registered for value added tax to participate in a one-time procurement of up to ETB 500,000 (Five Hundred Thousand Birr).

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ማናቸውም የሕግ ሰውነት ያላቸው ተቋማት፣ የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበራት እንደ አንድ የቅድመ ብቃት መስፈርት በነዚሁ ተቋማት ላይ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያላቸውን ሰዎች የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 አፈፃፀም የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይገለፃል፤

ሀ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቢያንስ አስር በመቶ [10%] የሚሆነውን የድርጅቱን አክሲዮኖች ወይም የመምረጥ መብቶችን በባለቤትነት የያዙ ወይም የተቆጣጠሩ ሰዎች፤

ለ/ በሌሎች መንገዶች በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ወይም የሚቆጣጠሩ ሰዎችን ወይም

ሐ/ በባለቤትነት የተመዘገቡም ሆነ ያልተመዘገቡ ሆነው በድርጅቱ ላይ የመጨረሻ እና ውጤታማ ቁጥጥር ያላቸው ሰዎች።

5) በተጫራቾች የሚቀርቡ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብትን የሚገልጹ መረጃዎች ሀሰተኛ ያልተሟሉና ትክክለኛነት የሚጎላቸው መሆናቸው በመንግስት መ/ቤቶች ከተረጋገጠ፣ የቀረበውን የመጫረቻ ሰነድ በቅድሚያ ውድቅ በማድረግ በተጫራቹ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርቡ ይችላል።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 በተገለጸው መሠረት የቅድመ ብቃት መስፈርቶችን ያላሟሉ ተጫራቾች ወደሚቀጥለው ዝርዝር የግምገማ ደረጃ አያልፉም።

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫራቾች ከጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ውጪ ያሉ በተለያዩ ምክንያቶች የተጠየቁትን የህጋዊነት ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር አካተው ባያቀርቡም ተፈላጊ ሰነዶችን በቅድመ ግምግማ ወቅት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ካሟሉ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት የተሰጡ መሆናቸውን በማረጋገጥ በጨረታው እንዲቀጥሉ መደረግ አለበት።

40. የጥቅም ግጭት

1) ዝርዝሩ እንደ ግዥው ዓይነት በመደበኛ የጨረታ ሰነዶች የሚቀመጥ ሆኖ፣ ማናቸውም ተወዳዳሪዎች የጥቅም ግጭት ሊኖራቸው አይገባም።

3. Except where the bidder is already registered in the securities market, any legal person (including partnerships, consortiums, or joint ventures) participating in public procurement must disclose the identities of all beneficial owners.

4. For the purpose of Sub-article 3, beneficial ownership shall include:

   a) Individuals who directly or indirectly own at least 10% of the shares or who have the right to control or make decisions regarding the entity;
   b) Individuals who otherwise exercise significant influence over or control the entity;
   c) Individuals who, whether formally registered or not, ultimately and effectively control the entity.

5. If a bidder is found to have submitted false, incomplete, or misleading information regarding beneficial ownership, and such is verified by the public body, the bid may be rejected, and legal action may be initiated.

6. Bidders who do not meet the pre-qualification criteria under Sub-article 1 and 3 shall not proceed to the detailed evaluation stage.

7. Without prejudice to Sub-article 1, if bidders fail to submit required legal documents (excluding bid security) at the time of bid submission, they may be permitted to submit them during the preliminary evaluation stage, provided that the documents were issued before bid closing and all conditions are fulfilled.

40. Conflict of Interest

1. No bidder shall have a conflict of interest, as further defined in the standard bidding documents based on the type of tender.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

2) በአዋጁ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) መሰረት የጥቅም ግጭት ያላቸው መሆኑ የተደረሰባቸው ተጫራቾች ወደ ዝርዝር ግምገማ ሳይገቡ በቅድመ ብቃት መስፈርቶች ግምገማ ወቅት ውድቅ መደረግ አለባቸው::

3) አንድ ተጫራች የጥቅም ግጭት አለው ተብሎ የሚወሰደው:-

ሀ/ አሁን ወይም ከዚህ ቀደም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጨረታ ለሚገዙ ዕቃዎች፣ የማንባታ ሥራዎች፣ የምክርና እና ከምክር ውጭ አገልግሎቶች በሰነድ ዝግጅት ወይም በአማካሪነት አገልግሎት ከተሳተፈ ወይም ማንባታዎች ላይ ከተሳተፉ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ካለው ወይም ከአጋሮቹ አንዱ በመሆን በስራው ተሳታፊ ከነበረ፣

ለ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሦስተኛ አካል ጋር ባለው ግንኙነት ምክንያት መረጃዎችን በመስጠት በሌሎች ተጫራቾች እና በግዥ ፈፃሚው አካል የግዥ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የጨረታውን ሂደት ሊያዛባ የሚችል ከሆነ፣

ሐ/ በጨረታ ሂደት ወቅት ከአንድ በላይ የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ፣

መ/ ተጫራቾቹ ለአንድ የጨረታ ዓላማ አንድ ተወካይ ያላቸው ከሆነ፤

ሠ/ አንድ ተጫራች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ከሚያደርግ የመንግስት መ/ቤቱሠራተኛ ጋር የስራ ወይም የቤተሰብ ግንኙነት ያለው ከሆነ፣

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሠ) መሠረት ተጫራቹ የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ፣ በጨረታው ጠቅላላ ሂደት ውስጥ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኛ ስለነበረው ድርሻ፣ እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 49 በተመለከተው መልኩ ሠራተኛው ከግዥ ሂደቱ ራሱን ያገለለ ስለመሆኑ እና በጨረታው ሂደት ውስጥ ስለሚኖረው ተጽዕኖ ዝርዝር ግምገማ መደረግ አለበት::

5) ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የጥቅም ግጭቶች ሲፈጠሩ ተጫራቹ ያላሳወቀ ከሆነ ወይም በማንኛውም ጊዜ መ/ቤቱ ችግሩን ማወቅ ከቻለ ወይም በሚመለከተው አካል ማረጋገጥ ከተቻለ ተጫራቹን ከውድድር ውድቅ ወይም ውሉ እንዲቋረጥ ሊደረግ ይችላል::

2. Pursuant to Article 24(c) of the Proclamation, any bidder found to have a conflict of interest shall be disqualified at the pre-qualification stage and shall not proceed to detailed evaluation.

3. A conflict of interest exists where:

a) The bidder, directly or indirectly, is or has been involved in the preparation of bidding documents, consultancy services, or implementation of the procurement, or has acted as a partner in the same project in relation to the procurement of goods, construction works, consultancy and non-consultancy services,
b) The bidder has direct or indirect connections with a third party that may influence the decisions of other bidders or the procuring entity,
c) More than one bid is submitted by the same bidder or affiliated entities,
d) The same representative acts on behalf of more than one bidder in the same procurement,
e) The bidder has an employment or familial relationship with an employee of the procuring public body involved in the procurement process.

4. For cases falling under Sub-article 3(e), the detailed evaluation must assess the bidder's potential conflict of interest, the extent of involvement of the employee in the procurement, and whether the employee has recused themselves in accordance with Article 49 of this Directive.

5. If a conflict of interest is not disclosed and is later discovered and verified, the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

41. የመንግስት መ/ቤት የቀድሞ ሠራተኞች በጨረታ ስለሚሳተፉበት አግባብ

1) በአዋጁ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሰ" በተደነገገው መሰረት ጨረታ ከመውጣቱ በፊት በመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኛ የነበረ ሰው በጨረታ ሊሳተፍ የሚችለው የመጫረቻ ሰነድ ባቀረበበት ቀን መ/ቤቱን ከለቀቀ ከአንድ ዓመት በላይ ከሆነው ብቻ ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 የተቀመጡት ገደቦች በግዥው ዋጋ እና ባህሪ ላይ ሳይወሰኑ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል እና በግዥ ሂደት ውስጥ ፍትሃዊ ውድድርን ለማረጋገጥ በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ በሚወጡት ሁሉም ጨረታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በጨረታ ሂደት ውስጥ ሰነድ በማዘጋጀት ወይም በሌሎች የጨረታ ሂደቶች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ የነበረው የመንግስት መ/ቤቱ የቀድሞ ሠራተኛ በዚሁ ጨረታ ላይ ለመሳተፍ አይችልም።

4) ማንኛውም የቀድሞ ሠራተኛ ጨረታ ከማቅረቡ ወይም የጨረታ አካል ከመሆኑ በፊት በመንግስት መ/ቤቱ ውስጥ ከሰራቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት በዚህ መመሪያ አባሪ 5 የሆነውን ቅጽ በመሙላት አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የቀድሞ ሠራተኛው ከመንግስት መስሪያ ቤቱ ሠራተኞች ጋር ያለውን ማንኛውንም የግል ወይም ሙያዊ ግንኙነቶችን፣ በመንግስት አገልግሎት ወቅት ግዥ ከሚፈፀምለት ፕሮጀክት ጋር የነበረውን ተሳትፎ እና ከግዥው ጋር የተያያዙ ሚስጥራዊ መረጃዎች የሚያውቅ መሆኑን እና ሌሎች ተዛማጅ እውነታዎችን አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡ :

6) በዚህ አንቀጽ መሠረት ከዚህ ቀደም በነበረበት የመንግስት ስራ ምክንያት በመንግስት ግዥ ተሳትፎ እንዳያደርግ ክልከላ ያለበት ማንኛውም የቀድሞ ሰራተኛ የሚከተሉትን ተግባራት በመፈፀም በጨረታው መሳተፍ አይችልም፡-

procuring entity may disqualify the bidder or terminate the contract.

41. Participation of Former Public Employees in Procurement

1. In accordance with Article 24(1) (g) of the Proclamation, former public employees may participate in tenders only if they have left public service at least one year before the bid submission date.

2. The restrictions under Sub-article 1 applies to all tenders regardless of value or type, to ensure fairness and prevent conflicts of interest.

3. Notwithstanding Sub-article 1 of this Article, any former employee who was directly involved in the preparation of the bidding documents or any part of the procurement process is prohibited from participating in that specific tender.

4. Former public employees must disclose any potential conflicts of interest before participating in a tender, using Annex 5 of the Directive.

5. Disclosure under sub-article 4 of this Article must include any professional or personal relationships with current employees of the procuring entity, previous involvement in related procurement processes, access to confidential information, or other relevant factors.

6. A former public employee prohibited from participating under this Article shall not participate in the tender by:

   a) Using family members to communicate or provide advice regarding the procurement

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ሀ/ የቀድሞ ሠራተኛው ከጨረታው ጋር የተያያዘ ማንኛውንም መረጃ ወይም ምክር የሚሰጣቸውን የቤተሰብ አባላትን በመጠቀም፣

ለ/ የቀድሞ ሰራተኛው ወይም የቤተሰብ አባላቱ ዳይሬክተር፣ ባለአክሲዮን፣ አማካሪ ወይም ተቀጣሪ የሆነበትን ድርጅት በመጠቀም።

7) የመንግስት መስሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን ገደብ ለመወሰን በቤተሰብ አባል የተያዘውን የቁጥጥር፣ ተጽዕኖ እና ሚስጥራዊ መረጃ የማግኘት ደረጃን ሊገመግም ይችላል።

8) የመንግስት መስሪያ ቤቱ ሊከሰቱ የሚችሉ የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ ጥሰት ሙከራዎችን ለመለየት የውስጥ ቁጥጥር ዘዴዎችን እና የመረጃ ጠቋሚ ስርዓቶችን መተግበር አለበት።

9) ከቀድሞ ሠራተኛ ጋር ግንኙነት ያለው የቤተሰብ አባል ጨረታዎች በሚሳተፍበት ወቅት ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት በዚህ መመሪያ አባሪ 5 የሆነውን ቅጽ በመሙላት አስቀድሞ መግለፅ አለበት።

10) በዚህ አንቀጽ በተደነገገው አግባብ የትኛውንም የጥቅም ግጭት አለመግለጽ እንደ አግባብነቱ ከጨረታው ሂደት ውድቅ መሆን፣ ውል መቋረጥ፣ ወደፊት ከሚደረጉ ግዥዎች የማይሳተፉ ተጫራቾች ዝርዝር ውስጥ መግባት እና ሌሎች ባለስልጣኑ የሚወስነውን ቅጣቶች ያስከትላል።

11) ለዚህ ድንጋጌ ዓላማ **"የቤተሰብ አባል"** የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ የትዳር ጓደኛ፣

ለ/ ልጆች ፣

ሐ/ ወላጆች እና አሳዳጊ ወላጆች፣

መ/ ወንድሞች እና እህቶች፣ እና

ሠ/ የቀድሞ ሠራተኛው የገንዘብ ፍላጎቶችን ወይም ጉልህ የንግድ ግንኙነቶችን የሚጋራው ማንኛውም ግለሰብ፡

:

b) Participating through a company in which they or their family members serve as directors, shareholders, advisers, or beneficiaries

7. The procuring entity may evaluate whether a family member has access to, influence over, or control of confidential procurement information to determine whether a conflict of interest exists.

8. The procuring entity shall implement internal control mechanisms and whistleblower systems to detect violations of this Directive.

9. When a family member of a former public employee participates in procurement, any potential conflict of interest must be disclosed in advance using Form 5.

10. Failure to disclose conflicts of interest may result in disqualification from the tender process, contract termination, listing on the debarred suppliers list, and other penalties as determined by the Authority.

11. For the purpose of this Article, "family members" include:

a) Spouse,
b) Children,
c) Parents and guardians,
d) Siblings, and
e) Any person who shares the former employee's financial or business interests.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

42. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በጨረታ ስለሚሳተፉበት አግባብ

1) በአዋጁ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅት ተጠሪ ለሆነለት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ይህ የመንግሥት መስሪያ ቤት ተጠሪ ለሆነለት ሌላ የመንግስት ተቋም በሚፈጽመው ግዥ ላይ ሊሳተፍ የሚችለው በውድድር ብቻ ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመላከተው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሥራቸው ከሚገኙ የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ግዥ በሚፈጽሙበት ወቅትም ተግባራዊ ይሆናል።

ክፍል ስድስት
የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

43. <u>የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ስለማዘጋጀት</u>

1) የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚጠይቁ ግዥዎች በአዋጁ አንቀጽ 25 መሠረት ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው።

2) የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍለጎት መግለጫ በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንደግዥው ዓይነት ጠቀሜታን፣ አሠራርን፣የቴክኒክ ወይም የዲዛይን ባህርይን እና የመሳሰሉትን መሠረት በማድረግ ውድድርን እንዳይገድብ ተደርጎ መዘጋጀት አለበት፣

3) የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የውሉ አንድ ክፍል በመሆን የአቅርቦቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል፣

4) የሚፈለገው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ሥራ ወይም አገልግሎት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ግዥው እንዲፈፀምለት በሚፈለገው ክፍል ወይም ስለሚፈፀመው ግዥ በቂ ዕውቀት ባላቸው የመ/ቤቱ ባለሙያዎች እና በግዥ የሥራ ክፍሉ በጋራ መዘጋጀት አለበት፣

5) ውስብስብ ለሆኑ ግዥዎች የፍላጎት መግለጫ አዘገጃጀት ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ ያሉ ባለሙያዎችን ድጋፍ ሊጠይቁ ወይም አማካሪ ቀጥረው ሊያሠሩ ይችላሉ፣

6) በአዋጁ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 4 በተቀመጠው አግባብ ካልሆነ በስተቀር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ አገልግሎት ሰጪ እና የተመረተበትን አገር ማመልከት የለበትም።

42. Participation of Public Enterprises in Tenders

1. In accordance with Article 24(3) of the Proclamation, a public enterprise that is a subsidiary of a public body—or the public body acting as its parent—may only participate in procurement conducted by another the public body through a competitive bidding process.

2. The provision under Sub-article 1 also applies to public higher education institutions when conducting procurement from their income-generating enterprises.

SECTION SIX
TECHNICAL SPECIFICATION

43. Preparation of Technical Specification

1. In accordance with Article 25 of the Proclamation, Public Bodies shall prepare detailed technical requirement specifications for procurements that require comprehensive technical evaluation.
2. The technical requirement specifications shall be based on the needs of the end-users and must include elements such as the purpose of the procurement, operational requirements, technical or design characteristics, and other relevant parameters. These specifications must be drafted in a manner that does not restrict competition.
3. The prepared technical specification shall form an integral part of the contract and shall serve as the benchmark for verifying the accuracy and conformity of the delivered goods, works, or services.
4. The technical requirement specifications for goods, consultancy services, construction works, or other services shall be prepared jointly by the requesting unit or technical experts of the Public Body and the procurement unit.
5. For complex procurements, the preparation of technical specifications may involve the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

7) የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የመንግስት መ/ቤቱን የአሁን ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችል ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችሉ የጠቀሜታ እሴቶችን ለመግለፅ የሚያስችል እና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ እሴቶችን ያላካተተ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

8) የመንግስት መሥሪያ ቤቱ እስከተቻለ ድረስ አገራዊ ደረጃ የማውጣት እና ጥራት የማረጋገጥ ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ተቋማት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች እና የብቃት ማረጋገጫዎች በዝርዝሩ ውስጥ ሊያካትት ይችላል።

9) የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የተሟላና ትክክለኛ የመጫረቻ ሰነድ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን አለበት።

10) የመንግስት መ/ቤቱ በጨረታ ሰነዱ ያስቀመጠውን ዝቅተኛ የጥራት መመዘኛ ወይም መግለጫን መሠረት በማድረግ መገምገም አለበት።

11) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 የተደነገገው ቢኖርም በግዥ ባህሪያቸው ምክንያት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ነጥብ በመስጠት መገምገም የሚያስፈልጋቸውን ግዥዎች መሆናቸውን በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በማረጋገጥ ነጥብ በመስጠት መገምገም ይችላል።

ክፍል ሰባት
ዘላቂነት ያለው የግዥ ሥርዓትን ተፈጻሚ ስለማድረግ

44. የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና

1) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚፈጸሙ ዕቃዎችን እና የግንባታ ሥራ ዓይነቶችን ባለስልጣኑ ይወስናል፣ የዕቃዎችን እና የግንባታ ሥራዎችን ዝርዝር ለመንግሥት መ/ቤቶች በጽሁፍ ያሳውቃል።

2) መንግስት መስሪያ ቤቶች የዕቃዎች እና የግንባታ ሥራዎች ግዥን በሚፈጽሙበት ወቅት በአዋጁ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 8 ፊደል ተራ "ለ" የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና

support of external experts or consultants who are not employees of the Public Body.

6. Unless permitted under Article 25(4) of the Proclamation, technical specifications shall not reference any specific manufacturer, service provider, or country of origin.

7. The technical requirement specification shall incorporate functional features that meet both the current and foreseeable future needs of the Public Body, while excluding features that are impractical or unusable.

8. The Public Body may include, within the technical specification and qualification requirements, detailed national standards issued by authorized institutions or internationally recognized standards set by reputable global bodies.

9. The technical specification shall be comprehensive and detailed, enabling bidders to prepare accurate and complete bidding documents. It shall be included in the bid document as a distinct section.

10. The Public Body shall evaluate bids based on the minimum quality criteria or specifications set forth in the bid document.

11. Notwithstanding Sub-article 10 of this Article, if the nature of the procurement justifies it and the justification is approved by the Head of the Public Body, bid evaluation may be conducted using a scoring system.

SECTION SEVEN
IMPLEMENTATION OF SUSTAINABLE PROCUREMENT SYSTEM

44. Lifetime Cycle Cost Analysis

1. Pursuant to this Article, the Authority shall determine the categories of goods and construction works that are subject to life-cycle cost analysis and communicate the detailed list to Public Bodies in writing.

2. Public Bodies, when procuring goods and construction works under the life-cycle cost

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

መሠረት ግዥ ለመፈፀም በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን አሰራር ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሠረት የሚፈፀሙ ግዥዎች የግዥ ዕቅድ፣ የሰነድ ዝግጅት፣ የመገምገሚያ መስፈርት፣ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ፣ እና የጨረታ ግምገማ በሚካሄድበት ወቅት የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተናን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት።

4) የመንግስት መ/ቤቱ የሚፈጽማቸው ግዥዎችን በተመለከተ ተገቢውን የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና አስቀድሞ ማዘጋጀት ያለበት ሲሆን በዚህ መልኩ የተዘጋጀውን ትንተና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ተጫራቾች የሚያቀርቡትን የሕይዎት ዘመን ወጪ ትንተና ለመመዘን ጥቅም ላይ ማዋል አለበት።

5) በመንግስት መ/ቤቱ የሚዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች እና የግንባታ ሥራዎች ከመጫረቻ ዋጋው በተጨማሪ የሕይወት ዘመን ጠቅላላ ወጪዎችን ለይተው እንዲያቀርቡ የሚያስገድድ መሆን አለበት።

6) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የአንድ ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ የሕይወት ዘመን የሚወሰነው በፊዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት ይሆናል።

7) የሕይወት ዘመን ትንተና ተግባራዊ የሚደረገው ከዚህ በታች የተቀመጠውን ስሌት መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፤

የሕይወት ዘመን ወጪ = የመጫረቻ ዋጋ +የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር (ማለትም የስራ ማስኬጃ ወጪ + የጥገና እና የመለዋወጫ ወጪ+ የማስወገጃ ወጪ) - የንብረቱ ቀሪ ዋጋ።

8) ለአንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 7 አፈፃፀም፡

ሀ/ **"የመጫረቻ ዋጋ"** ማለት የዕቃዎች እና የግንባታ ሥራዎች የመጀመሪያ ግዥ ዋጋ ነው።

ለ/ **"የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር"** ማለት ዕቃው እና የግንባታ ሥራውአገልግሎት መስጠት ከጀመረበት እስከ ንብረቱ የመጨረሻ ዓመትያለውን የስራ ማስኬጅ ወጪ፣ የጥገና እና መለዋወጫ ወጪ፣የማስወገጃወጪን ያካትታል።

ሐ/ **"የሥራ ማስኬጃ ወጪ"** ማለት ለዕቃው ወይም ለሥራው የሕይወት ዘመንአስፈላጊ የሆኑየጥገና፣

analysis approach in accordance with Article 55(8)(b), shall adhere to the procedures outlined in this Article.

3. Procurements carried out under Sub-article 1 shall incorporate life-cycle cost analysis in the planning, document preparation, evaluation criteria, technical specifications, and bid evaluation stages.

4. Public Bodies shall prepare a Life Cycle Cost (LCC) analysis in advance, which shall be used as the basis for evaluating the life-cycle cost assessments submitted by bidders pursuant to Sub-article 5 of this Article.

5. The bid document shall require bidders to submit, in addition to their bid price, a separate statement of the total life-cycle costs associated with the goods or construction works.

6. The Federal Public Property Directive shall determine the expected useful life of specific goods or construction works for the purpose of this Article.

7. The life-cycle cost shall be calculated using the following formula: **Lifetime Cost = Bid Price + ∑ (Operational Costs + Maintenance + Spare Part Costs + Disposal Costs) – Residual Value**

8. For purposes of Sub-article 7:

a) **"Bid Price"** means the initial price of the goods or construction works.

b) **"Lifetime Cost Summation"** refers to the total costs incurred from the beginning of service provision to the end of the asset's useful life, including

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

የኃይል ፍጆታ እና ሌሎች ንብረቱን ከመጠቀም ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ያካትታል።

መ/ "የጥገና/ መለዋወጫ" ማለት በየወቅቱ የሚከሰቱትን ዋና ዋና ወጪዎችሲሆን እንደ ምትክ ወይም ጥገናን ያካትታል።

ሠ/ "የማስወገጃ ወጪ" ማለት በንብረቱ የሕይወት ዘመን መጨረሻ ላይ ለማስወገድ የሚወጣ ወጪ ሲሆን የንብረቱ ቀሪ ዋጋ ተቀናሽ መደረግ አለበት።

ረ/ "ቀሪ ዋጋ" ማለት ንብረቱ የሕይወት ዘመኑ ሲያልቅ ሊሸጥ የሚችለው የተገመተው ዋጋነው።

9) ተወዳዳሪው በዚህ አንቀጽ መሰረት የሕይወት ዘመን የሥራ ማስኬጃ፣ የጥገና፣ የመለዋወጫ እና የማስወገጃ ወጪዎች የሚያቀርበው የመንግሥት መ/ቤቱ የሚገዛው ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ በሕይወት ዘመኑ የሚያስወጣውን ወጪ ለማሳወቅ ዓላማ ብቻ ሲሆን ተወዳዳሪው እነዚህን ወጪዎች በማቅረቡ ብቻ የድህረ ሽያጭ የሥራ ማስኬጃ፣ ጥገና እና የማስወገድ ሥራን ለማከናወን እንደተወዳደረ ተደርጎ አይቆጠርም።

10) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው የሕይወት ዘመን ወጪ ተዓማኒነት ያለው እና በአምራች ወይም በሌሎች በሚመለከታቸው ተቋማት የተረጋገጠ መሆን አለበት።

11) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው የሥራ ማስኬጃ፣ የጥገና፣ የመለዋወጫ እና የማስወገጃ ወጪዎች ሲቀርቡ ተገቢውን የወለድ እና የቅናሽ ዋጋ ተመንን በመጠቀም ወጪዎቹ በሚወጡበት ወቅት የሚኖረውን የገንዘብ የመግዛት አቅም ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሆን አለበት።

12) የመንግሥት መስሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብለትን የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና የዋጋ ውድድር በሚያከናውንበት ወቅት እንደ ማወዳደሪያ መያዝ አለበት።

13) የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና በቂ ዕውቀት እና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች መሰራት አለበት።

operational, maintenance, spare part, and disposal costs.

c) **"Operational Costs"** refer to energy consumption, routine maintenance, and other utilization-related expenses.

d) **"Maintenance/Spare Part Costs"** refer to recurring expenses incurred over time, such as replacements and repairs.

e) **"Disposal Cost"** refers to the cost of properly disposing of the asset at the end of its useful life, with the residual value subtracted.

f) **"Residual Value"** means the estimated resale value of the asset at the end of its useful life.

9. The life-cycle costs for operation, maintenance, spare parts, and disposal submitted by bidders are used solely to estimate the total cost of ownership. Submission of these figures does not obligate the bidder to perform post-sale services unless otherwise stated in the contract.

10. The submitted life-cycle cost analysis must be credible and supported by verifiable evidence from the manufacturer or other relevant institutions.

11. Operation, maintenance, spare part, and disposal costs must be discounted using an appropriate interest rate to reflect the present value of future expenditures.

12. Life-cycle cost analysis shall be considered a competitive factor in bid evaluation and price comparison.

13. Life-cycle cost analysis shall be conducted by professionals with appropriate qualifications and experience.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

14) በዚህ አንቀጽ መሰረት በተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ የሕይወት ዘመን ትንተና ወጪዎችን የሚያሳዩ ሰነዶች ስለ ትክክለኛነታቸው በመንግስት መ/ቤቱ ሊጠየቅ እና ሊረጋገጥ ይገባል።

45. የአካባቢ ጥበቃን ታሳቢ ያደረገ መንግስት ግዥ

1) የመንግስት መ/ቤቶች የሚፈጽሟቸው ግዥዎች በአዋጁ አንቀጽ 28 መሰረት ከአካባቢ ብክለት የጸዳ፣ መልሶ መጠቀምን እና የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ከግምት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል።
2) ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቴክኖጂዎችን፣ የታዳሽ ኃይል ምንጮችን በመጠቀም ወይም ዝቅተኛ ልቀቶችን በመጠቀም የተመረቱ ምርቶችን ሊያበረታቱ የሚችሉ መስፈርቶችን በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነዶች ውስጥ ማካተት አለባቸው።
3) የመንግስት መ/ቤቶች እንደገና ጥቅም ላይ በዋሉ ቁሶች የተዘጋጁ ወረቀቶችን፣ ፕላስቲክ፣ ጎማ ወይም የግንባታ ዕቃዎችን ቅድሚያ በመስጠት ግዥ ሊፈጽሙ የሚችሉበትን አሰራር መከተል አለባቸው።
4) የመንግስት መ/ቤቶች ግዥ ከመፈጸማቸው በፊት እንደገናጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበት አማራጭ አለመኖሩን በቅድሚያማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።
5) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚፈጸሙ የዕቃዎች አይነቶችን ይወስናል፣ ዝርዝሩን ለመንግሥት መ/ቤቶች በጽሁፍ ያሳውቃል እንዲሁም በጥናት ላይ ተመስርቶ ከሌሎች ከሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆንየመንግሥት ግዥ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ስታንዳርድ እንዲወጣ ያደርጋል።

46. የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ያደረገ የመንግስት ግዥ

1) የመንግስት መ/ቤቶች የሚፈጽሟቸው ግዥዎች በአዋጁ አንቀጽ 28 መሠረት የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በዚህ አንቀጽ ሥር የተደነገጉትን ከግምት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል።

14. The Public Body shall verify and validate the credibility and accuracy of documents submitted on the basis of this Article by bidders in support of their life-cycle cost analysis.

45. Public Procurement that Considers Environmental Protection

1. In accordance with Article 28 of the Proclamation, Public Bodies shall implement procurement practices that prevent environmental pollution, promote recycling, and generate community benefits.
2. Public Bodies shall include in bid documents criteria that favor environmentally friendly technologies and products made using renewable energy and low-emission production methods.
3. Public Bodies shall adopt procurement practices that prioritize the use of paper, plastic, rubber, and construction materials manufactured from recycled content.
4. Prior to initiating procurement, Public Bodies shall verify that it is not possible to reuse existing goods.
5. The Authority shall determine which types of goods are covered under this provision, notify Public Bodies in writing, and issue binding standards through research and collaboration with relevant stakeholders.

46. Public Procurement that Considers the Interest of Society

1. Pursuant to Article 28 of the Proclamation, Public Bodies shall consider the broader social interests when carrying out procurement activities.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

2) በመንግስት መ/ቤቶች የሚፈጸሙ ግዥዎች ለአካባቢው ማህበረሰብ ያላቸውን አዎንታዊ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡ ፡

3) በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 28-34 በተደነገገው መሠረት ልዩ ትኩረት/ማበረታቻን የሚፍልጉ በማምረት ስራ ላይ ለተሰማሩ ጥቃቅን እና አነስተኛ ማህበራት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የነጋዴ ሴቶች ማህበራት፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች እና የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት የሚሳተፉበት ጨረታ የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው።

ክፍል ስምንት
የመንግስት ግዥ ስነ-ምግባር

47. ጠቅላላ

ማናቸውም በመንግሥት የግዥ ሂደት የሚሳተፉ የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኞች፣ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ፣ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ፣ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ፣ የሲስተም አስተዳዳሪ እና ተጫራቾች በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በሚወጡበት ወቅት በዚህ ክፍል የተደነገጉትን የሥነ-ምግባር ድንጋጌዎች ማክበር አለባቸው።

48. ሚስጢርን መጠበቅ

1) በግዥ ሂደት ላይ የሚሳተፉ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኞች እና ሌሎች ከስራው ጋር ቅርበት ያላቸው አካላት በሥራቸው የሚያገኙትን መረጃ ምስጢርና ደህንነት የመጠበቅ መ·ያዊ ግዴታ አለባቸው፡ ፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሚስጢራዊነታቸው እንዲጠበቅ የተደረጉት መረጃዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ የመንግስት መ/ቤቱ ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት።

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ወይም ኮሚቴ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማከናወን አለበት።

2. Procurement activities must account for their positive social, economic, and environmental impact on the local community.

3. In accordance with Articles 28–34 of this Directive, tenders involving parties that are entitled to preferential treatment—such as micro and small enterprises, persons with disabilities, women's associations, and job-creation institutions engaged in manufacturing—shall be executed in a manner that ensures community benefit.

SECTION EIGHT
PUBLIC PROCUREMENT ETHICS

47. General

All employees of a Public Body, including the Head of the Public Body, members of the Procurement Endorsing Committee, Procurement Evaluation Committee, System Administrator, and bidders participating in any public procurement process, shall at all times adhere to the code of ethics set forth in this Section when performing their duties and responsibilities as provided under the Proclamation and this Directive.

48. Confidentiality

1. All employees of a Public Body and other individuals closely involved in the procurement process have a professional duty to maintain the confidentiality and security of any information obtained through the course of their work.

2. In accordance with Sub-Article 1 of this Article, Public Bodies shall establish appropriate safeguards to ensure strict confidentiality is maintained when handling information designated as confidential.

3. For the effective implementation of Sub-Article 1 of this Article, employees or responsible

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

officials of the Public Body shall undertake the following actions:

a) Shall not disclose any information to any party that could restrict competition, provide an unfair advantage to any bidder, or harm the interests of the Public Body.
b) Shall ensure that the decisions and information of the Public Body regarding communications with suppliers during contract execution are securely managed.
c) Except in circumstances where disclosure is legally authorized and upon request by a competent authority, no information concerning bidders, the evaluation process, or any other data required to be kept confidential shall be disclosed before the results are officially announced.

49. Prevention of Conflict of Interest

1. Any employee or official who is directly or indirectly involved in the procurement process and has a potential conflict of interest related to a procurement decision shall disclose the existence of such a conflict in writing, as stipulated in the bid document, and must recuse themselves from the procurement process.

2. Where the Public Body receives information regarding a potential conflict of interest involving an employee, official, or committee member engaged in the procurement process:

   a) The individual in question shall submit a written statement concerning the alleged conflict of interest.
   b) Based on the written statement under Sub-Article 2(A) of this Article, and upon collection of any additional relevant information, it shall be determined using appropriate procedures whether the individual has a conflict of interest in relation to the procurement activity.

ሀ) ውድድርን ሊገድብ የሚችል ወይም ለተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያስጥ ወይም የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል መረጃ ለማንኛውም አካል አለመስጠት፤

ለ) የመንግስት መ/ቤቱ በውል አፈፃፀም ወቅት ከአቅራቢዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የመንግስት መ/ቤቱን ውሳኔ እና መረጃ መጠበቅ፤

ሐ) በተለየ ሁኔታ በሕግ የተፈቀደለት አካል ካልተጠየቀ በስተቀር፤ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን መረጃ እና የግምገማ ሂደት እና ሌሎች በሚስጢር መያዝ ያለባቸውን መረጃዎች ውጤቱ ከመገለጹ በፊት ለማንኛውም አካል አለማሳወቅ::

49. የጥቅም ግጭትን ስለማስወገድ

1) በግዥ ሂደት ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተሰማሩ ሠራተኞች ወይም ኃላፊ ወይም የኮሚቴ አባል ከሚሰራው ሥራ ጋር በተገናኘ የሚሰጠው ውሳኔ ከስራው ጋር የተገናኘ የጥቅም ግጭት መኖሩን በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው አግባብ በጽሁፍ በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ ራሱን ማግለል አለበት::

2) በመንግስት ግዥ ሥራ ላይ የተሳተፈ ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ወይም ከግዥ ጋር ግንኙነት ያለው የኮሚቴ አባል ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ከማንኛውም ምንጭ የመንግሥት መ/ቤቱ መረጃ ሲደርሰው፤

ሀ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በቀረበው የጥቅም ግጭት ጉዳይ ላይ አስተያየቱን በጽሁፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ "ሀ" በተሰጠው የጽሁፍ አስተያየት እና ተገቢ ነው ብሎ ባመነባቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ በማሰባሰብ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ወይም ከግዥ ጋር ግንኙነት ያለው የኮሚቴ አባል ከያዘው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ወይም እንደሌለው ይወስናል፤

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ "ለ" በተቀመጠው መሠረት የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኛው

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 4th of June 2024

ወይም ኃላፊው ወይም ከግዥ ጋር ግንኙነት ያለው የኮሚቴ አባል ከሚሰራው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሲያረጋግጥ ሠራተኛውን ወይም ኃላፊውን ወይም ከግዥ ጋር ግንኙነት ያለው የኮሚቴ አባል ከሂደቱ እንዲገለል፣ በሂደቱ ተሳትፎባቸው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ከእንደገና እንዲታዩ ያደርጋል፣ እንዲሁም የጥቅም ግጭቱን ያላሳወቀው ከማንዛቤ ጉድለት ነው ብሎ ካላመነ በስተቀር በሰራተኛው ወይም በተቋሙ ኃላፊ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።

3) በመንግሥት ግዥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያላቸው የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኞች ወይም ከግዥ ጋር ግንኙነት ያለው የኮሚቴ አባል ኃላፊዎች በግዥ ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም ሊያሳድር የሚችል ማናቸውም ዓይነት ስጦታን ከሶስተኛ ወገን መቀበል የለባቸውም።

4) በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ 3 መሠረት የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች ወይም ከግዥ ጋር ግንኙነት ያለው የኮሚቴ አባል የሚከተሉትን እና ሌሎች ተያያዥ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

ሀ/ የገንዘብ ዋጋ ያለውን ሥጦታ በተለይ ለመንግሥት መ/ቤቱ ዕጩ ተጫራች ከሆነ አካል አለመቀበል፣

ለ/ የሥራ ዕድል ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ አለመቀበል፣

ሐ/ ለግል በሚደረግ ግዥ ላይ ለመንግስት መ/ቤቱ አቅራቢ/ዕጩ ተጫራች ከሆነ አካል የተለየ የዋጋ ቅናሽ ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

መ/ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የግብዣ ፕሮግራም አለመቀበል።

c) If, pursuant to Sub-Article 2(b) of this Article, it is established that the individual has a conflict of interest, they shall be excluded from the procurement process. Any decisions in which they participated shall be reviewed, and unless it is proven that the failure to disclose the conflict was due to lack of awareness, administrative measures shall be taken.

3. Employees, officials or any committee members involved directly or indirectly in procurement are prohibited from accepting any gifts from third parties that may influence, or appear to influence, their procurement-related decisions.

4. In line with Sub-Article 3 of this Article, employees and officials of a Public Body must also observe the following precautionary measures:

a) Shall not accept gifts of monetary value, particularly from individuals or entities participating as bidders in public procurement processes.
b) Shall not accept employment offers for themselves or their family members.
c) Shall not accept special discounts or services when procuring private goods or services from bidders or suppliers involved in the Public Body's procurement.
d) Shall not accept invitations that may unduly influence their official duties.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

50. ፍትሐዊነት

1) በግዥ ሂደት የሚሳተፉ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኞች እና ሌሎች አካላት ከማንኛውም ተጽዕኖ ነፃ ሆነውተወዳዳሪዎችን በእኩልነት ማገልገል አለባቸው:::

2) በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ወይም ከግዥ ጋር ግንኙነት ያለው የኮሚቴ አባል ዕጩ ተጫራቾች እኩል የመወዳደርና ውል የመፈፀም ዕድል እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ማንኛውንም ተግባር መፈፀም የለበትም::

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈፃፀም የሚከተሉት ተግባራት መፈፀም አለባቸው፤

ሀ) በጨረታ ጥሪ ሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች በቂ መረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በጨረታው ለመሳተፍ እና ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት የሚያስችል የተሟላ እና ግልጽ መረጃ መያዙን ማረጋገጥ፤

ለ) በጨረታ ሰነዱ የተገለፀው ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርትም ሆነ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር የተወሰነ ዕጩ ተወዳዳሪን ሊጠቅም በሚችል መልኩ አለመዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ሐ) የጨረታው ውጤት ለሁሉም ተሳታፊዎች በእኩል ጊዜ መገለጹን ማረጋገጥ፣

መ) በውል ሰነድ ዝግጅት ለአቅራቢዎች የሚሰጠው ኃላፊነት ግዴታቸውን ሆን ብሎ ለማቅለል ወይም ለማክበድ ያላለመ እና አስከተቻለ ድረስ ተመሳሳይ ውል ለሚፈርሙ አቅራቢዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው ውል ሆኖ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤

ሠ) በውል አፈፃፀም ወቅት ክፍያን፣ ቁጥጥርን፣ የመረጃ ልውውጥን እና የመሳሰሉትን ተግባራት በእኩልነት ለሁሉም አቅራቢዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ::

4) የመንግስት መ/ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በሥራ አጋጣሚ የተመለከታቸውን የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የታሰቡ የሙስና ተግባራትን ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ የሚኖርበት ሲሆን የሚያደርገውም ጥቆማ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ እና እራሱንም የታሰበውን የሙስና ተግባር ሊደግፍ ከሚችል ማንኛውም ተግባር መጠበቅ አለበት::

50. Fairness

1. All employees of a Public Body and other individuals involved in the procurement process shall act impartially and remain free from any undue influence when dealing with bidders.

2. No employee or official involved in public procurement, either directly or indirectly, shall take any action that restricts bidders from having an equal opportunity to compete or to execute a contract.

3. For the implementation of Sub-Article 2 of this Article, the following measures shall be undertaken:

a) Ensure that all bidders have access to adequate information during the tendering process and that the bid documents contain complete and clear information enabling bidders to prepare responsive and eligible submissions.

b) Ensure that the requirements and evaluation criteria stated in the bid documents are not tailored in a manner that would benefit any particular bidder.

c) Ensure that tender results are announced simultaneously to all participants.

d) Ensure that contract documents do not unfairly increase or reduce the obligations of suppliers and that, where possible, uniform contract terms are prepared for suppliers entering into similar contracts.

e) Ensure that, during contract implementation, activities such as payments, supervision, and information exchange are carried out equitably and fairly among all suppliers.

4. Any employee or official of a Public Body who becomes aware of actual or suspected acts of corruption in relation to the procurement process must report such acts to the appropriate authority. Reports must be supported by evidence, and the individual shall refrain from any action that could support or facilitate the suspected misconduct.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2020

51. ግልጽነት

1) በግዥ ሂደት የሚሳተፉ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኞች እና ሌሎች አካላት የሚያከናውኖቸው ሁሉም የግዥ ሂደቶች ፍትሃዊ እና ግልጽነት ባለው መልኩ መከናወን አለባቸው፣ ይህም ለሁሉም ተጫራቾች እኩል ዕድሎችን በማረጋገጥ እና በሂደቱ ውስጥ ግልጽ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃዎችን ማሳወቅ፣ግልጽ ውድድርእንዲኖር ማድረግ እናማንኛውንም አድሎአዊ አሰራርን ማስወገድን ይጨምራል።

52. ብቃት

1) በግዥ ሂደት የሚሳተፉ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኞች እና ሌሎች አካላት ከግዥ ጋር የተያያዙ ተግባራቸውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ዕውቀት፣ ክህሎትና ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።

2) በግዥ ሂደት የሚሳተፉ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኞች እና ሌሎች አካላት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ሙያው የሚፈቅደውን ዕውቀት፣ ክህሎትና ልምድ በሥራ ላይ ማዋል አለባቸው።

3) በግዥ ሂደት የሚሳተፉ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኞች እና ሌሎች አካላት ብቃታቸውን፣ ውጤታማነታቸውን እና የአገልግሎቶቻቸውን ጥራት በየጊዜው ማሻሻል አለባቸው።

4) በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ዝርዝር ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ በግዥ ሂደት የሚሳተፉ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤቱ ሠራተኞች እና ሌሎች አካላት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም ለመንግስት ማስገኘት እንዲቻል የተሟላ የግዥ ፍላጎት ግምገማዎችን በማድረግ፣ ጨረታዎችን በትክክል በማውጣት፣ በመገምገም እና ብክነት ያለው ግዥን በማስወገድ እንዲሁም የጥራትና የአፈፃፀም መስፈርቶችን በማሟላት ግዥዎችን መፈፀም አለባቸው።

51. Transparency

1. All employees of a Public Body and others involved in the procurement process shall ensure that procurement is conducted in a fair and transparent manner, providing equal opportunities to all bidders and maintaining open, clear, and accurate communication throughout the process.

2. In accordance with Sub-Article 1 of this Article, necessary information shall be disclosed, transparent competition shall be ensured, and any discriminatory practices shall be eliminated.

52. Competence

1. All employees of a Public Body and others engaged in procurement activities shall possess the necessary knowledge, skills, and experience to competently carry out their procurement duties.

2. All such individuals shall apply their professional knowledge, skills, and experience in the execution of procurement-related responsibilities.

3. Public Body employees and other participants in the procurement process shall continuously improve their competencies, efficiency, and the quality of the services they provide.

4. All employees and other stakeholders involved in the procurement process shall perform comprehensive procurement needs assessments to ensure value for money, issue accurate tenders, evaluate bids fairly, eliminate inefficient procurement practices, and ensure compliance with quality and performance standards during contract execution on the basis of the detailed provisions of this Directive.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ምዕራፍ አራት
የግዥ ዘዴዎች

53. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

በማናቸውም የመንግስት መስሪያ ቤት ግዥ አፈጻጸም የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፣

ሀ/ ግልጽ ጨረታ፣

ለ/ በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ፣

i. የሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ፣

ii. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ፣

iii. የፍላጎት መጠየቂያ ጨረታ፡፡

ሐ/ ውስን ጨረታ፣እና

i. የተገደበ ጨረታ፣

ii. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ

መ/ በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ፡፡

ክፍል አንድ
ግልጽ ጨረታ

54. ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ

1) በአዋጁ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም የመንግስት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ አለበት፡፡

2) የመንግስት መ/ቤቶች ብሔራዊ ግልጽ ጨረታን መጠቀም የሚችሉት፡-

ሀ/ የሚፈለገውን ዕቃ፣ የግንባታ ሥራ፣ ሌሎች አገልግሎቶች እና የምክር አገልግሎት በአገር ውስጥ ብቻ ሊቀርብ የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ የገንዘብ ገደብ ሳይደረግበት፣

ለ/ ግዥው በሀገር ውስጥ ባሉ ተጫራቾች ሊሟላ የሚችል ሲሆንግምታዊ ዋጋው ከሚከተለው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን፣

CHAPTER FOUR

PROCUREMENT METHODS

53. Authorized Methods of Procurement

Any Public Body shall apply the following procurement methods in its procurement processes:

a) Open Tendering
b) Selective Tendering
   i. Two-Stage Bidding
   ii. Prequalification Tender
   iii. Request for Expression of Interest
c) Limited Tendering
   i. Restricted Tender
   ii. Request for Quotation (RFQ)
d) Direct Procurement

SECTION ONE

OPEN TENDERING

54. National Competitive Bidding

1. In accordance with Article 35 Sub-Article (2) of the Proclamation, any Public Body using procurement methods other than open tender shall maintain written documentation justifying the rationale and circumstances for selecting the alternative method.

2. Public Bodies may use national open tendering under the following conditions:

   a) When it is confirmed that the required goods, construction works, other services, or consultancy services can be procured domestically, without applying any financial threshold.
   b) When the procurement can be fulfilled by domestic suppliers and the estimated cost does not exceed the following thresholds:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

1) ለግንባታ ሥራ ዘርፍ እስከ ብር 3,000,000,000.00 (ሦስት ቢሊዮን ብር)
2) ለዕቃ ግዥ እስከ ብር 1,000,000,000.00 (አንድ ቢሊዮን ብር)
3) ለምክር አገልግሎት ግዥ እስከ ብር 90,000,000.00 (ዘጠና ሚሊዮን ብር)
4) ከምክር ውጪ የሆኑ አገልግሎት ግዥ እስከ ብር 250,000,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር)

3) ባለሥልጣኑ በሌላ አካኋን ካልፈቀደ በስተቀር፣ የመንግስት መ/ቤቶች በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥን ለመፈጸም በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ስርዓት በተዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀም አለባቸው::
4) የመንግስት መ/ቤቶች በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈጸም በባለስልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀም አለባቸው::
5) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ የሚሳተፉ ተጫራቾች የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ናቸው::
6) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 አፈፃፀም "የአገር ውስጥ ተጫራች" ማለት የተጫራቹ ወይም የአክሲዮን ባለድርሻ ባለቤቶቹ ዜግነት ከግምት ሳይገባበኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋመ እና የንግድ እንቅስቃሴ ያለው፣ የንግድ ምዝገባ፣ የታክስ መለያ ቁጥር እና የንግድ ፈቃድ ያለው ተጫራች ነው::

55. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ

1) በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ በአዋጁ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት መፈፀም አለበት::
2) የመንግስት መ/ቤቶች በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ዘዴ ግዥ ሊፈጽሙ የሚችሉት የግዥው ግምታዊ ዋጋ ከሚከተለው የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን ነው፣

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ከብር 3,000,000,000.00

1) Construction works: Up to ETB 3,000,000,000.00 (Three Billion Birr).
2) Goods: Up to ETB 1,000,000,000.00 (One Billion Birr).
3) Consultancy services: Up to ETB 90,000,000.00 (Ninety Million Birr).
4) Non-consultancy services: Up to ETB 250,000,000.00 (Two Hundred Fifty Million Birr).

3. Unless otherwise permitted by the Authority, Public Bodies shall use the standard bid documents developed and issued through the government's electronic procurement system when conducting open tendering.
4. Public Bodies shall use the standardized tender documents prepared by the Authority when conducting national competitive bidding.
5. Unless otherwise provided under the Proclamation or this Directive, only domestic suppliers shall be allowed to participate in national open tenders.
6. For the purpose of implementing Sub-Article (5) of this Article, a "**domestic supplier**" means a bidder registered and operating under Ethiopian law, possessing a valid business license, Tax Identification Number (TIN), and commercial registration certificate, irrespective of the nationality of its shareholders or owners.

55. International Competitive Bidding

1. Procurement through international open tender shall be carried out in accordance with Article 35, Sub-Article (3) of the Proclamation.
2. Public Bodies may use international open tendering when the estimated procurement value exceeds the following thresholds:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ለ/ ለዕቃ ግዥ ከብር1,000, 000,000.00

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ ከብር90, 000,000.00

መ/ ከምክር ውጪ የሆኑ አገልግሎት ግዥ ከብር 250, 000,000.00

3) የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ በተቀመጠው የገንዘብ ገደብ ውስጥ የሚያርፍ ቢሆንም የውጭ አገር ተጫራቾች ካልተሳተፉ ውጤታማ እንደማይሆን ሲታመን የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ) መሠረት በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ ሊፈጽሙ ይችላሉ።

4) በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ በሚፈጸም የዕቃ ግዥ ተሳታፊ የሚሆኑ ተጫራቾች ራሳቸው የዕቃው አምራቾች ካልሆኑ እንደ አስፈላጊነት በመስሪያ ቤቶች ሲጠየቁ የሚቀርበው ዕቃ ከአምራቹ የሚመጣ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።

5) በዓለም አቀፍ ጨረታ ሂደት የውጭ አገር ተጫራች የአገር ውስጥ ወኪል ያለው ከሆነ ወኪሉውክልና የተሰጠው መሆኑን የሚያሳይ ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ ማቅረብ፣ እንዲሁም በውክልናው የተሰጠውን የስራ ዓይነት ለይቶ መጥቀስ ይጠበቅበታል።

6) በአዋጁ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ያስገባና በዓለም አቀፍ ግዥ ተፈጻሚ የሚሆኑትን የንግድ ቃላትና ሁኔታዎችን ይወስናል፣ በየወቅቱ የሚደረጉ ማሻሻያዎችንም ያሳውቃል።

56. የዓለም ዓቀፍ ግልጽ ጨረታ አፈጻጸም

በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ከተገለፀው ዝርዝር የጨረታ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

a) Construction works: Above ETB 3,000,000,000.00 (Three Billion Birr).
b) Goods: Above ETB 1,000,000,000.00 (One Billion Birr).
c) Consultancy services: Above ETB 90,000,000.00 (Ninety Million Birr).
d) Non-consultancy services: Above ETB 250,000,000.00 (Two Hundred Fifty Million Birr).

3. When the estimated value falls within the threshold for national open tendering, but foreign participation is deemed essential due to the anticipated inefficacy of domestic suppliers, procurement may be conducted through international open tender as per Article 35(3)(b) of the Proclamation.

4. In international open tendering for goods, bidders who are not manufacturers must, when required by the procuring entity, present evidence that the goods originate directly from the manufacturer.

5. A foreign bidder that has a local representative must submit legally authenticated documentation evidencing the validity of the representation, including a clear definition of the scope of authority granted to the representative.

6. Pursuant to Article 35(6) of the Proclamation, the Authority shall, in consultation with relevant stakeholders, determine the commercial terms and conditions applicable to international procurement and shall revise and publish such terms periodically.

56. Execution of International Competitive Bidding

In addition to the tender procedures stipulated for national open tenders under this Directive, international competitive bidding shall observe the following:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

ሀ/ የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሠነዱ የሚዘጋጀው በእንግሊዘኛ ቋንቋ መሆን አለበት፣

ለ/ የጨረታ ጥሪው የመንግስት ኤለክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ላይ መውጣት አለበት፤

ሐ/ ተጫራቾች ተገቢ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጀት እንዲችሉ በዚህ መመሪያ በአባሪ ቁጥር 6 ላይ በተገለጸው መሠረት በቂ ጊዜ መሰጠት አለበት

መ/ የሚዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ የአገር ውስጥ ደረጃ የሚያሟላና እስከተቻለ ድረስ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፣

ሠ/ የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋና የጨረታ ማስከበሪያ በቀላሉ ሊመነዘር በሚችልና በዓለም አቀፍ ንግድ በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት ሊሆን ይገባል፣

ረ/ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሠ" የተገለፀው እና የተመረጠው የንግድ ቃል እንደተጠበቀ ሆኖ የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ተጫራቾች በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ሲወዳደሩ ዕቃው ከሚያርፍበት ወደብ አንስቶ እስከ መንግስት መ/ቤቱ ለማድረስ የሚከፈሉ የታክስ እና ቀረጥ፣ ኢንሹራንስ እና የማጓጓዣ ወጭዎችን እና ሌሎች ተያያዥክፍያዎችን እና ወጪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በማካተት ውድድሩ እንዲፈፀም ሊደረግ ይገባል።

ሰ/ የግዥ ፍላጎቱን ለማሟላት የውጭ አገር ተጫራቾች ከአገር ውስጥ የሚጠቀሙት ግብዓት በሚኖርበት ጊዜ ከአጠቃላይ የውሉ ክፍያ በብር ሊከፈል የሚገባው መጠን በዋጋ ማቅረቢያው ሠንጠረዥ ላይ ማመልከት ይኖርበታል።

ሸ/ በውሉ በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ሕግ ሊዳኙ ይገባል።

57. ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች

1) የውጭ አገር ተጫራቾች ካልተሳተፉበት በስተቀር በቂና ውጤታማ ውድድር ሊኖር አይችልም ተብሎ ሲታመን በአዋጁና በዚህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ለብሔራዊ እና ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተገለጹት ሌሎች አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው በማጣሪያ

a) Tender notices and documents shall be prepared in the English language.

b) Tender notices shall be published through the government electronic procurement system.

c) Bidders shall be given sufficient time to prepare their bid submissions in accordance with Appendix 6 of this Directive.

d) The prepared Statement of Requirements shall comply with domestic standards and, to the extent feasible, be acceptable by international standards.

e) Bid prices and bid securities submitted by foreign bidders shall be denominated in a freely convertible currency and in a format acceptable in international trade.

f) Without prejudice to Sub-Article (e) of this Article, both domestic and foreign bidders participating in international competitive bidding shall ensure that the quoted price includes all applicable costs from the port of entry to delivery at the Public Body's location, including but not limited to taxes, customs duties, insurance, transportation, and other related charges.

g) If foreign bidders utilize domestic inputs to fulfill the contract requirements, the portion of the contract value corresponding to local expenditures shall be expressed in Ethiopian Birr (ETB) within the Price Schedule.

h) Unless otherwise stated in the contract, any disputes arising during the execution of the contract shall be governed by Ethiopian law.

57. Other International Procurements

1. Where the participation of foreign bidders is deemed necessary to ensure effective competition, and in accordance with the Proclamation and this Directive, international procurement may be

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2025

የሚከናወን ጨረታ፣ በውስን ጨረታ እና በቀጥታ የሚፈጸም የግዥ ዘዴን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ግዥ መፈጸም ይቻላል።

2) በንዑስ አንቀጽ 1 የተለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዓለም ዓቀፍ ግልጽ ጨረታ ውጪ የሚፈጸመ ግዥዎች የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ይሆናል።

ሀ/ በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ለየግዥ ዘዴው የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ እና የገንዘብ መጠን የተሟላ መሆኑን፣

ለ/ ግዥውን ከግልጽ ጨረታ ውጭ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ መፈጸም ከጊዜ እና ከጥራት አንጻር አዋጭ መሆኑ ሲታመን፣

ሐ/ የግዥው ሂደት የግልጽ ጨረታን ሂደት እና የዚህ መመሪያ ክፍል ሶስት አንቀጽ 62 ድንጋጌዎችን ተከትሎ የሚፈጸም መሆኑን፣

መ/ ግዥውን በአገር ውስጥ ለመፈጸም ያልተቻለበት አሳማኝ ምክንያት መኖሩ ሲረጋገጥ፣

ሠ/ እስከተቻለ ድረስ የተጫራቾችን ቁጥር በመጨመር ከውድድር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ ተፈጻሚ የሚደረግ ስለመሆኑ።

ክፍል ሁለት
በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ

58. በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ አፈፃፀም

1) በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ የግዥ ዘዴ በጨረታ መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾችን ከአንድ ደረጃ በላይ በሆነ ውድድር በማጣራት እና በመጀመሪያው ደረጃ ያለፉ ተጫራቾችን ለቀጣይ ዙር ውድድር በመጋበዝ ከተጫራቾች መካከል የጨረታው አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ሲሆን፣ የቅድመብቃት ማረጋገጫ ጨረታ፣ የፍላጎት መጠየቂያ ጨረታ እና የሁለት ደረጃ ጨረታን ያካትታል።

conducted through restricted tendering, direct procurement, or selective tendering.

2. Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, international procurement methods other than open tender shall only be permitted upon verifying the following conditions:

a) The specific procurement method and applicable financial thresholds are satisfied, unless otherwise provided under the Proclamation or this Directive;
b) Conducting the procurement internationally outside open tendering is advantageous in terms of time and quality;
c) The process adheres to the principles and procedures applicable to open tendering, including the requirements of Article 62, Section Three of this Directive;
d) There is sufficient justification proving that the procurement could not be conducted domestically;
e) The procurement process maximizes competition and encourages participation by the greatest possible number of qualified bidders.

SECTION TWO
SELECTIVE TENDER

58. Execution of Selective Tendering

1. Selective tendering is a procurement method whereby interested bidders are shortlisted through a multi-stage competitive process. Only those shortlisted in the initial stage are invited to participate in the subsequent stage(s), from which the successful bidder is selected. This method includes two-stage bidding, prequalification procedures, expressions of

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

2) መሥሪያ ቤቶች በማጣሪያ ጨረታ በማውጣት ፍላጎታቸውን ሊያሟላ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበን ተጫራች በአሸናፊነት በአዋጁ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀፅ 2 ከፊደል ተራ "ሀ እስከ መ" የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች በመከተል ተጫራቾችን መምረጥ ይችላሉ።

59. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ

1) የመንግስት መ/ቤቱ ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባሕርይ አንፃር በቅድሚያ የተወዳዳሪዎችን ብቃት መሠረት ግምገማ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲያምን እንደግዥው ዓይነት ብሔራዊ ወይም ዓለም ዓቀፍ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል።

2) የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚያስፈልጋቸው ግዥዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

ሀ/ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም በባህሪው ውስብስብ የሆነ የዲዛይን፣ የማምረትና የተከላ ሥራ በአንድ ድርጅት መጠናቀቅ ያለበት የግንባታ፣ የማምረቻ መሳሪያ ወይም የቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ወይም

ለ/ የሚቀርበው ዕቃ ወይም መሳሪያ ጥራትና ጠቀሜታ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ሲሆን፣ወይም

ሐ/ የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ግዥ በመሆኑ ብቃታቸው በቅድመ ብቃት ምዘና የሚረጋገጡ ተጫራቾች ብቻ በውድድሩ ተካፋይ መሆን እንደሚገባቸው ሲታመንበት፣

3) ጨረታው የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ጥሪ መሆኑ በማስታወቂያው ላይ መገለፅ አለበት።

4) የቅድመ ብቃት ግምገማ ለማድረግ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የቅድመ ብቃት ጨረታ በባለልጣኑ

interest, and other multi-stage selection methods.

2. Public Bodies may select bidders who submit responsive bids that meet the required standards through a selective tendering process in accordance with Article 32(2)(a–d) of the Proclamation.

59. Prequalification Tender

1. Where warranted by the nature of the procurement, a Public Body may issue national or international invitations for prequalification, as applicable.
2. Procurement activities that require prequalification shall meet at least one of the following conditions:

   a) High-value or complex projects involving design, manufacturing, and installation (e.g., construction, production equipment, or technology procurement) that must be executed by a single entity;

   b) Procurement involving the supply and installation of essential and high-importance goods or equipment;

   c) Procurement that involves significant bid preparation costs, making it appropriate to limit participation to prequalified bidders verified through competence assessments.

3. The tender notice must explicitly state that it is an invitation for prequalification.
4. The tender documents prepared for pre-qualification evaluation shall be based on

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

የተዘጋጀውን የቅደመ ብቃት ጨረታ መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት በማድረግ ይሆናል። የቅድመ ብቃት መምረጫ መሥፈርት እንደግዥው ባህርይና ዓይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ተወዳዳሪ ድርጅቶቹ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት ማስረጃ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማካተት ይኖርበታል።

ሀ/ በተመሳሳይ የግንባታ ሥራ ወይም ዕቃ ማምረት ላይ ድርጅቱ ያለው ልምድ፣

ለ/ ድርጅቱ የግንባታ ሥራውን ለማከናወን ወይም ዕቃውን ለማምረት የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል፣ ማሽኖች፣ የማምረቻ አቅም እና የተሟላ መሰረተ ልማት ያለው መሆኑን፣

ሐ/ ድርጅቱ አሁን በመሥራት ላይ ያለው የግንባታ ሥራ ወይም በማምረት ላይ ያለው ዕቃ ብዛት ወይም መጠን፣

መ/ ድርጅቱ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ የሚያስችል በቂ የገንዘብ አቅም እና መልካም ስም ያለው መሆኑን፣

5) የተጫራቾች ግምገማ የሚከናወነው ለቅድመ ብቃት ማረጋገጫ በመንግስት መ/ቤቱ የተዘጋጀውን መሥፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል።

6) ለቅድመ ብቃት ውድድሩ ያመለከቱ ተጫራቾች በሙሉ የግምገማ መሥፈርቱን እስካሟሉ ድረስ ምንም ዓይነት የቁጥር ገደብ ሳይደረግ በሚቀጥለው ውድድር እንዲሳተፉ መደረግ አለበት።

7) የመንግስት መ/ቤቶች በቅድመ ብቃት ውድድር የሚሳተፉ ድርጅቶች በሽርክና ወይም በጋራ መወዳደር እንዲችሉ ሊፈቅዱ ይችላሉ። ሆኖም የቅድመ ብቃት ውድድሩን በግል ያለፉ ተወዳዳሪዎች በግዥው ሂደት የሚኖራቸውን ውድድር እንደማያጠብ በመ/ቤቱ ካልታመነ በስተቀር በጋራ ወይም በሽርክና የመጫረቻ ሰነዱን እንዲያቀርቡ መፈቀድ የለበትም።

8) በጋራ ወይም በሽርክና ለቅድመ ብቃቱ ውድድር ቀርበው ይህንኑ መሠረት በማድረግ በተካሄደ ግምገማ ለሚቀጥለው ጨረታ ያለፉና የተመረጡ ተጫራቾች በጨረታው በግል እንዲወዳደሩ አይፈቀድላቸውም።

the standard pre-qualification tender documents issued by the Authority. While the specific selection criteria may vary depending on the nature and type of procurement, the evidence required from participating organizations shall include the following:

a) Demonstrated experience in executing similar construction works or manufacturing comparable goods;

b) Proof of adequate manpower, equipment, production capacity, and complete infrastructure necessary to perform the construction works or manufacture the goods;

c) A list of ongoing construction works or goods currently being produced by the organization, including quantities or volumes;

d) Evidence of sufficient financial capacity and a positive track record demonstrating the organization's ability to fulfill its contractual obligations.

5. Evaluation shall be conducted using criteria established by the Public Body for verifying prequalification.

6. All bidders meeting the prequalification criteria shall be permitted to participate in the subsequent stage without limitation on the number of participants.

7. Public Bodies may allow participants in the prequalification stage to compete as joint ventures or consortiums. However, unless it is evident that prequalification will not restrict competition during the procurement process, submissions in joint venture or consortium form should not be permitted.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

9) የቅድመ ብቃቱ ግምገማ ውጤት እንደታወቀና በመ/ቤቱ ተቀባይነት እንዳገኘ ውጤቱ በጨረታው እንዲሳተፉ ለተመረጡትና ላልተመረጡት ተጫራቾች ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡

10) አንድ ተጫራች የቅድመ ብቃት ጨረታን ተከትሎ በወጣ ጨረታ ላይ በተደረገ ግምገማ አሸናፊ ለመሆን ቢችልም በቅድመ ብቃት ውድድር ወቅት የሰጠው መረጃ የተሳሳተ ከሆነ ወይም በቅድመ ብቃት ውድድሩ ወቅት የነበረው ብቃት ባለመኖሩ ውሉን በሚጠበቅበት ሁኔታ ለመፈጸም አለመቻሉ በድህረ ግምገማ በበቂ ሁኔታ ከተረጋገጠ የመንግስት መ/ቤቱ ተጫራቹ ውሉን እንዲፈርም ላይፈቅድ ይችላል፡፡

11) የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ውድድር ተቀባይነት ላገኙት ተጫራቾች በየአድራሻቸው የኤሌክትሮኒክ የግንኙነት ዘዴን በመጠቀም እንዲላክላቸው የሚደረግ ሲሆን፣ ቀሪው የግዥ አፈፃፀም በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ እና ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተቀመጠውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

60. የሁለት ደረጃ ጨረታ

1) በአዋጁ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለት ደረጃ የሚፈፀም ግዥ በዚህ መመሪያ እንደግዥው ዓይነት ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት ይፈጸማል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በመጀመሪያ ዙር የሚደረገው የጨረታ አፈጻጸም የሚከተሉትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ሀ/ የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ ላይ ግዥው በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም መሆኑ መገለፅ ይኖርበታል፣

ለ/ በመጀመሪያው ዙር ጨረታ የሚሳተፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ዋስትና እና ዋጋ እንዲያቀርቡ አይጠየቁም፣

ሐ/ ለግዥው የሚዘጋጀው ሰነድ የመንግስት መ/ቤቱን አጠቃላይ ፍላጎት የሚገልፅ ሆኖ አላማው ከዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ሐሳቦች መሠረት ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የሚያስችሉ አስፈላጊ

8. A joint venture or consortium that is prequalified may not submit a bid individually in the subsequent tender stage.

9. Once prequalification results are finalized and approved, the Public Body must simultaneously notify both the successful and unsuccessful applicants.

10. A contract shall not be signed with a bidder whose prequalification submission contains false information or who no longer meets the criteria upon which their prequalification was based.

11. Preparation and distribution of tender documents to prequalified bidders shall be conducted through the electronic procurement system. The remainder of the procurement process shall adhere to the national or international competitive bidding procedures set out in this Directive.

60. Two-Stage Bidding

1. Without prejudice to Article 32(2) of the Proclamation, procurements using the two-stage bidding process shall follow the procedures established in this Directive and be classified as either national or international competitive tenders

2. Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the first stage shall be conducted under the following conditions:

   a) The tender announcement shall indicate that the procurement will proceed in two stages;

   b) Bidders shall not be required to submit bid security or price proposals in the first stage;

   c) The tender document shall describe the general requirements of the Public Body and include questions and guidance to assist bidders in

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

መጠይቆችን እና መግለጫዎችን እንዲሁም ወደ ሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያልፉ ተጫራቾችን ለመለየት የሚያስችሉ መስፈርቶችን በማካተት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ላይ መውጣት ይኖርበታል፣

መ/ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበው የቴክኒክ ሐሳብ ማቅረቢያ ሰነድ በጨረታ ጥሪው በተገለፀው ቀንና ሰዓት እንዲከፈት ይደረጋል፣

ሠ/ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን ሐሳብ በመመርመር ለሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያገለግለውን የፍላጎት መግለጫ እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚገባቸውን ተጫራቾች መለየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡ :

ረ/ በግምገማው ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ከሁሉም ወይም ከተወሰኑ ወይም ከአንድ ከተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር የመንግስት መ/ቤቱ ውይይት ሊያደርግ ይችላል።

ሰ/ ከላይ በፊደል ተራ (ረ) ላይ በተገለፀው መሰረት የሚደረገው ውይይት ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሰጡትን ሐሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እና በተሻለ የዳበረ ሐሳብ ለማመንጨት ያለመ ሊሆን ይገባል።

3) በሁለተኛው ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የኤለክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም በውድድሩ ለተጋበዙ በየአድራሻቸው መላክ አለበት። በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉ አሰራሮችን ይከተላል።

ሀ/ በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያገኙ ተጫራቾች በሁለተኛው ዙር ውድድር በሚሳተፉበት ወቅት በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት የጨረታ ዋስትና እና ዋጋን ጨምሮ የመወዳደሪያ ኃሳብ እንዲያቀርቡ ይደረጋል።

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥር (ሀ) በተገለፀው መሠረት ለተመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፈው ግብዣ የጨረታ ማቅረቢያ ጊዜ እና የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ጨምሮ ሌሎች ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በግልፅ ሊያመለክት ይገባል።

preparing detailed technical proposals. It shall also outline evaluation criteria for selecting bidders to advance to the second stage;

d) Technical proposals shall be opened at the date and time specified in the invitation;

e) Evaluation of technical proposals shall lead to the formulation of the request for proposals (RFP) to be used in the second stage and the identification of eligible bidders;

f) The Public Body may hold discussions with all, some, or individual bidders on specific matters during the evaluation;

g) Discussions should aim to clarify bidders' ideas and facilitate the development of more refined and well-defined technical proposals.

3. The tender document for the second stage shall be distributed electronically to all qualifying bidders. In this stage:

a) Bidders who are accepted in the first round of bidding stage shall submit a bid proposal including bid security and price through the government's electronic procurement system while tendering in the second stage of the bidding;

b) The second-stage invitation must clearly state the bid submission deadline, bid opening date, and other relevant compliance requirements in accordance to sub-article 3 (a) of this Article.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

61. የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ

1) የመንግስት መ/ቤቶች የማማከር አገልግሎት ወይም አዕምሯዊ የሙያ አገልግሎት ስራዎችን በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት መፈጸም አለባቸው::

2) የመንግስት መ/ቤት የሚገዛው የምክር አገልግሎት ግምታዊ ዋጋ ከብር 7,000,000.00 (ሰባት ሚሊዮን ብር) የሚበልጥ ሲሆን በምክር አገልግሎቱ አቅርቦት ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የፍላጎት መጠየቂያ ጥሪ ማድረግ አለበት::

3) ተጫራቾች ፍላጎታቸውን ሊያቀርቡ የሚያስችላቸውን መረጃ እንዲያገኙ የምክር አገልግሎት ስራውን ዳራ፣ ዓላማ፣ ግብ እና የማማከር አገልግሎቱ ወሰን እና ሌሎች ለአገልግሎቱ አስፈላጊ የሆኑትን መግለጫዎች የሚዘረዝር ቢጋር ማዘጋጀት፣

4) ለፍላጎት መግለጫው የሚደረገው ጥሪ የሚከተሉትን ታሳቢ ያደረገ በመሆን አለበት::

ሀ/ የፍላጎት መግለጫ ጥሪው የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት ዓይነት፣ የሚጠበቀውን ውጤት፤ ጊዜውን፤ አማካሪው ሊኖረው የሚገባውን ብቃት፤ የስራ ልምድ እና የመሳሰሉትን የያዘ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያቀርቡት የሚገባውን መረጃ ዝርዝር እንዲሁም የሚያቀርቡበትን ቦታና ጊዜ የሚገልጽ መሆን አለበት::

ለ/ በፍላጎት መግለጫ መጠየቂያው ላይ በተቀመጠው መገምገሚያ መስፈርት መሰረት ፍላጎታቸውን ከገለፁ አማካሪዎች ውስጥ የተሻለ ብቃት ያላቸውን በመምረጥና በጨረታ ሰነዱ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎችና ተፈላጊ ነጥቦች መሠረት ፍላጎታቸውን ላቀረቡ ተጫራቾች ማሳወቅ፣

ሐ/ ፍላጎታቸውን ያሳወቁ ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት መረጃ ተገምግሞ የተፈለገውን የምክር አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ብቃት ያላቸው በቅደም ተከተላቸው መሰረት እስከተቻለ ድረስ ከሶስት ያላነሱ እና ከሰባት ያልበለጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመርጠው በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጨረታ አፈጻጸም መሠረት የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ መደረግ አለበት::

61. Request for Expression of Interest

1. Public Bodies shall procure consulting and other intellectual services in accordance with the provisions of this Article.

2. Where the estimated value of consulting services exceeds ETB 7,000,000 (seven million Birr), bidders must be invited via a Request for Expression of Interest.

3. A Terms of Reference shall be prepared describing the background, scope, objectives, and limitations of the required consulting services, enabling interested parties to respond appropriately.

4. The call for Expressions of Interest shall comply with the following requirements:

   a) The call shall clearly specify the type of consultancy services required, the expected deliverables, the timeline, the qualifications and work experience required of the consultant, and any other relevant criteria. It shall also indicate the information that interested candidates must submit, as well as the place and deadline for submission.

   b) The most qualified consultants who have submitted Expressions of Interest shall be selected based on the evaluation criteria set out in the notice. These consultants shall be notified in accordance with the conditions and requirements specified in the bidding documents.

   c) Following the evaluation of the submitted information, a minimum of three and a maximum of seven top-ranked candidates shall be shortlisted to submit full proposals in response to the Request for Proposals (RFP).

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ፊደል ተራ "ሐ" መሠረት በአማካሪዎች ብቃት ላይ ተመስርቶ የሚደረግ መረጣ ግዥር እስከተቻለ ድረስ ለመንግስት መ/ቤቱ ተፈላጊውን ጥራት እና ኢኮኖሚያዊ ጠቃሚታ በሚያስገኝና ውድድርን በሚያበረታታ መልኩ የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያን ጨረታ አፈጻጸምን ተከትሎ መፈጸም አለበት::

6) የምክር አገልግሎት ግዥር የመምረጫ ዘዴዎች ላይ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የአማካሪዎች ዝርዝር ግምገማ እና ነጥብ አሰጣጥ በዚህ መመሪያ በዝርዝር የጨረታ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ድንጋጌዎች እና ባለስልጣኑ ለዚህ ዓለማ የሚያወጣውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ ተከትሎ ይፈጸማል::

7) መ/ቤቱ የመወዳደሪ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ለተመረጡ አማካሪዎች በተመሳሳይ ጊዜ ጥሪ በአድራሻቸው መላክ አለበት:: ለግዥው የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያለ ክፍያ ሊሰጥ እንደሚገባ መ/ቤቱ ሲያምን ከጥሪው ጋር መላክ ይችላል::

8) የመንግስት መ/ቤቱ ከተመረጠው አማካሪ ጋር የሚደረገው ድርድር መሠረታዊውን የጨረታ ይዘትና የሥራ ጥራት የማይቀይር ሆኖ ስለስራው ይዘት፤ ስለአሰራር ዘዴው፤ በስራው ስለሚሰራው የሰው ኃይል እና መሳሪያ፤ ስለሪፖርት አቀራረብ እና ይዘት በመሳሰሉት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል::

9) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት የሚደረገው ድርድር የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ ወይም ለተመረጠው አማካሪ ከሌሎች ተጫራቾች አንፃር ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያሰጠው መሆን የለበትም::

10) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 ስር የተገለጹት የመረጣ ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች የጨረታ አፈጻጸም ሂደቶች በዚህ መመሪያየተገለጹትን የግልፅ ጨረታ አሠራሮች በመከተል የሚፈጸሙ ይሆናል::

11) በንዑስ አንቀጽ 12 በተገለጹት የመምረጫ ዘዴዎች ለሚፈፀሙ ግዥዎች የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ ቴክኒክ እና በዋጋ ማቅረቢያ ተለይቶ በሁለት ኤንቬሎፕ ታሽጎ መቅረብ ያለበት ሲሆን ለምክር አገልግሎቱ የሚዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት እና የሚደረገው ግምገማ በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል::

12) የምክር አገልግሎት ግዥ ለመምረጥ እንደ አግባብነቱ በጥራት እና በዋጋ ላይ፣ በሚከናወን የሥራ ጥራት ላይ፣ በቁርጥ በጀት ላይ፣ በዝቅተኛ ዋጋ ላይ፣ በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ እና አንድ አማካሪ የሚመረጥበት አሠራር ተከትሎ ተግባራዊ መደረግ አለበት::

13) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች ***በጥራት እና በዋጋ*** ላይ የሚደረግ መረጣን ተፈፃሚ ሲያደርጉ የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ወቅት

5. The selection of consultants based on their qualifications, as outlined under sub-article 4(c) of this Article, shall, to the extent possible, be conducted in a manner that ensures the required quality and economic benefit for the Procuring Entity and promotes competition.

6. Subject to the procedures stipulated for consultant selection methods, the detailed evaluation and scoring of consultants shall be conducted in accordance with the provisions of this Directive governing bid implementation, as well as the standard bidding documents issued by the Authority for this purpose.

7. The Procuring Entity shall simultaneously issue invitations to the shortlisted consultants, delivered to their official addresses. The bidding documents may be enclosed with the invitation if the Procuring Entity deems it appropriate to provide them free of charge.

8. Negotiations between the Procuring Entity and the selected consultant shall not alter the core content of the bid or the quality of the services to be rendered. Negotiations shall instead focus on aspects such as the scope of services, implementation methodology, human and material resources, and the format and content of deliverables.

9. Negotiations held in accordance with sub-article 8 shall not undermine the interests of the Procuring Entity or confer an unfair advantage to the selected consultant over other candidates.

10. Except where a different selection method under sub-article 12 is employed, other procurement procedures shall follow the open bidding process provided for in this Directive.

11. For procurement conducted under the consultant selection methods specified in sub-article 12, proposals shall be submitted in two separate envelopes: one for technical and one for financial proposals. Evaluation and selection shall follow the procedures stipulated under this Article.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት በማስገባት እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርበውን እያንዳንዱን የቴክኒክ ሐሳብ በሚገመግሙበት እና በሚያወዳድሩበት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች 100 (ከመቶ) በመያዝ መሆን አለበት፤

ሀ/ የአማካሪው ልዩ ልምድ.....ከ5 እስከ 10 ነጥብ

ለ/ በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበው የምክር ዘዴ...ከ20 እስከ 50 ነጥብ

ሐ/ በምክር አገልግሎቱ የሚሳተፉ ቁልፍ ባለሙያዎች.....ከ30 እስከ 60 ነጥብ

መ/ ዕውቀት የማሸጋገር ችሎታ.... ከ5እስከ 10 ነጥብ

ሠ/ የውጭ አገር ድርጅት ሲሆን የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ.....ከ5 እስከ 10 ነጥብ

14) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 (መ) የተቀመጠው መስፈርት እና ነጥብ ከግንባታ ሥራዎች ጋር ለተያያዙ የምክር አገልግሎቶች ተፈፃሚ አይሆንም። ሆኖም የመንግሥት መ/ቤቱ በዚህ መልኩ የሚሰጡ የምክር አገልግሎቶች ለመንግሥት መ/ቤቱ የሚያስገኘው ዕውቀት እንደ መስፈርት መታየት አለበት ብሎ ሲያምን መስፈርቱ እና መመዘኛ ነጥብን ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል።

15) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 (ሠ) የተቀመጠው መስፈርት እና ነጥብ ተፈፃሚ የሚሆነው የውጭ አገር ድርጅት በሚሳተፍበት የምክር አገልግሎት ግዥ ላይ ብቻ ነው።

16) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 ለተመለከተው የጥራት እና ዋጋ መስፈርቶች በመጠቀም መ/ቤቱ የቀረቡትን አማካሪዎች ለመምረጥ የሚከተለውን የመገምገሚያ ሂደት መከተል አለባቸው፤

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 መሰረት በቴክኒክ ብቃት ምዘና ከመቶ ከተያዘው ውጤት 70% (ሰባ ከመቶ) በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው 70% እና ከዚህ በላይ የሚያገኙት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ይከፈታል።

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ "ሀ" በቴክኒክ ግምገማ ሰባ ከመቶ (70%) እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተወዳዳሪዎች ውጤት ወደ 80% /ከሰማኒያ ከመቶ/ ተቀይሮ የዋጋ ግምገማ የነጥብ ድርሻ ከ20% (ከሃያ በመቶ) ጋር ተደምሮ ከመቶ ይያዛል።

ሐ/ የምክር አገልግሎቱ የሚገኘው ከውጭ አገር አማካሪዎች ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ለግምገማ ዓላማ ሲባል የአገር ውስጥ እና የውጭ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ የመንገዣ፣ የትርጉም፣ የጽሕፈት ሥራ ወጪን እና የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል።

12. Selection of consultancy services may be based on quality and cost, quality alone, fixed budget, least cost, consultant qualifications, or single-source selection, as appropriate.

13. When the Procuring Entity applies the quality and cost-based selection method pursuant to sub-article 12, the following criteria shall be incorporated into the tender documents and used to evaluate each technical proposal submitted:

a) Relevant experience of the consultant: 5 to 10 points
b) Proposed methodology and work plan: 20 to 50 points
c) Qualifications and competence of key experts: 30 to 60 points
d) Capacity for knowledge transfer: 5 to 10 points
e) Participation of Ethiopian professionals in the case of foreign firms: 5 to 10 points

14. The criterion under sub-article 13(d) on knowledge transfer shall not apply to consultancy services related to construction works unless the Procuring Entity deems such transfer to be of added value.

15. The criterion under sub-article 13(e) on Ethiopian participation applies only to procurements in which a foreign consultant is involved.

16. The following evaluation procedure shall apply when using the quality and cost-based selection method indicated under sub-article 13:

a) Bidders scoring less than 70% in the technical evaluation shall be rejected. Only the financial proposals of bidders scoring 70% or more shall be opened.
b) For shortlisted bidders, the technical score shall be weighted at 80% and the financial score at 20%, totaling 100%.
c) If the consultancy services are provided by domestic firms, the financial proposals may include

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2025

መ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 123 የተደነገገው የተሰበረ እና የተጋነነ ዋጋ ማጣሪያ ከተደረገ በኋላ፣ ዝቅተኛ የመጨረሻ ዋጋ ላቀረበው ዋጋ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን፣ በተነፃፃሪ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ አነስተኛ ነጥብ ይሰጣል፤ ሌሎች ተወዳዳሪዎችም የሚያገኙት ነጥብ ባቀረቡት ዋጋ ላይ በመመስረት ተሰልቶ የሚወሰን ይሆናል።

ሠ/ ለቴክኒክ ብቃት ደረጃ እና ለዋጋ የተሰጡትን ነጥቦች በመደመር በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተወዳዳሪ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል።

ረ/ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ የተገለፀውን የግዥ አፈጻጸም ሂደት በተጨማሪነት መሠረት ማድረግ ይኖርበታል።

17) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች *በሥራ ጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ* ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አገልግሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ተፈፃሚ ይሆናል፤

ሀ/ የምክር አገልግሎቱ ውስብስብና የተለየ የሙያ ብቃት የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚሁ ግዥ የተሟላ ማጣቀሻ ሰነድ ወይም ቢጋር ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ወይም ከአማካሪው የሚገኘውን የምክር አገልግሎት ዓይነት ለይቶ ማወቅ የማይቻል ሲሆን ወይም አማካሪው የራሱን የፈጠራ ችሎታ ተጠቅሞ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን፤

ለ/ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን አማካሪዎች ማግኘት አስፈላጊ በሚሆንባቸው እና የወደፊት ውጤታቸው አሳሳቢ የሚሆን ከፍተኛ ጉዳዮች ሲሆኑ፤

ሐ/ የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የሚቀርቡትን ሀሳቦች በተመሳሳይ ሁኔታ ማወዳደር አስቸጋሪ እንደሚሆን ሲታመን፤

18) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17 ለተመለከቱት መስፈርቶች መ/ቤቱ የቀረቡትን አማካሪዎች ለመምረጥ የሚከተለውን የመገምገሚያ ሂደት መከተል አለበት፤

ሀ/ ተጫራቾች የቴክኒክ እና የዋጋ የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን ለየብቻ እንዲያቀርቡ ተደርጎ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳባቸውን የያዘው ሰነድ ብቻ በመጀመሪያ እንዲከፈት ይደረጋል።

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17 መሰረት በቴክኒክ ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ያገኘው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል።

ሐ/ በቴክኒክ ግምገማው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ብቻ ያቀረበውን ዋጋ በመክፈት መ/ቤቱ ለስራው ከያዘው በጀት የማይበልጥ ከሆነ ውል ይፈርማል።

reasonable costs for transportation, translation, administrative services, and similar expenses.

d) After screening for arithmetical errors and excessive pricing in accordance with Article 123, the lowest-priced bid shall receive the highest score. Other bids shall be scored proportionally.

e) The bidder with the highest combined score for technical and financial evaluation shall be selected.

f) International open bidding for consultancy services shall follow the same procedures set out for national open bidding under this Directive.

17. The quality-based selection method under sub-article 12 may be used when:

a) The consultancy services are complex or require special qualifications, making it difficult to define the scope of services or develop reference documents.

b) The engagement of highly qualified consultants is critical, and their future performance is of strategic importance.

c) Proposals are expected to vary significantly in content and approach, making price-based comparison impractical.

18. For selection under sub-article 17, the following procedure shall apply:

a) Technical and financial proposals shall be submitted separately; only technical proposals shall be opened initially.

b) The consultant scoring highest in the technical evaluation shall be selected.

c) If the financial proposal of the top-ranked consultant is within the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

መ/ በውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያቀረበውን ዋጋ መ/ቤቱ ለስራው ከያዘው በጀት የሚበልጥ ከሆነ እና በቴክኒክ ግምገማው ውጤት ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ መ/ቤቱ ለስራው ከያዘው በጀት ጋር የሚመጣጠን ከሆነ ግዥውን ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች መፈፀም ይቻላል።

ሠ/ በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የውል ስምምነት እንደተፈረመ የሌሎች ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ሳይከፈት ለተጫራቾች ተመላሽ መደረግ አለበት።

19) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች ***በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ*** ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አገልገሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ተፈፃሚ ይሆናል፤

ሀ/ በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው፣ በትክክል ሊገለፅ የሚችል ሲሆን እና ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ጣሪያ ያለው ከሆነ ነው።

ለ/ የቴክኒክ ግምገማው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 እና 16 ባሉት ድንጋጌዎች ሥርዓቶች ተከትሎ የሚፈፀም ይሆናል።

ሐ/ ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ያቀረቡ ተጫራቾ ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል።

መ/ ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ዋጋ ያቀረበና በአጠቃላይ የቴክኒክ እና ፋይናንስ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል እንደአስፈላጊነቱም ዋጋን ያልጨመረ ድርድር ሊደረግ ይችላል።

20) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች ***በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ*** ሊጠቀሙ የሚችሉት የምክር አገልገሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ይሆናል፤

ሀ/ ይህ የመረጣ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚገዛው የምክር አገልግሎት የባለሙያውን ልዩ ችሎታ የማይጠይቅ አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸው፣ ውስብስብ ያልሆነና ስታንዳርድ ያለው ወይም በተመሳሳይና ወጥ በሆነ አሠራር ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው።

ለ/ መ/ቤቶች በዚህ የመረጣ ዘዴ ተጫራቾን ለመገምገም ሲፈልጉ ዝቀተኛውን የቴክኒክ መመዘኛ ነጥብመጠን በመወሰን በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ላይ ከተመዘገቡአቅራቢዎች ለተመረጡ ተጫራቾች በሚሰጠው የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ

budget, the contract shall be awarded accordingly.

d) If the financial proposal exceeds the budget and the second-ranked proposal is within budget, the contract may be awarded to the second-ranked consultant.

e) Once a contract is signed, unopened proposals from other bidders shall be returned.

19. The fixed-budget selection method under sub-article 12 may be used if:

a) The services are simple, clearly defined, and the budget is fixed and limited.

b) Technical evaluation is carried out according to sub-articles 13 and 16.

c) Bidders exceeding the budget limit shall be disqualified.

d) The consultant with the highest technical score and compliant financial proposal shall be selected. Negotiations may occur, provided the price is not increased.

20. In accordance with Sub-Article 12 of this Article, government agencies may apply the lowest price selection method for the procurement of consultancy services when the following conditions are met:

a) This selection method may be employed where the consultancy services are of low monetary value, do not require specialized professional expertise, are not complex, and can be delivered in a standardized or uniform manner.

b) When applying this method, the procuring agency shall establish a minimum technical qualification score, which must be explicitly stated in the request for proposals document issued to shortlisted consultants registered in the government electronic procurement system.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ላይ ይህንኑ ነጥብ በግልፅ ማመልከት አለባቸው፡
፡

ሐ/ የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ የመወዳደሪያ ሰነዶች እንዲከፈቱ በማድረግ የቴክኒክ ግምገማ መከናወን ይኖርበታል፡፡

መ/ በግምገማው ውጤት ለቴክኒክ ብቃት የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ያላሟሉ ተወዳዳሪዎች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ሠ/ በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾ የዋጋ መወዳደሪያ ሰነድ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡

ረ/ በቴክኒክ ግምገማ ውጤታቸው ለዋጋ ወድድር ያለፉት ተወዳዳሪዎች የዋጋ መወዳደሪያ ሰነድ እንዲከፈት ይደረጋል፡፡

ሰ/ በተጫራቾች የቀረበው ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

ሸ/ በቴክኒክ ግምገማ ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ካሟሉት ተወዳደሪዎች መካከል አነስተኛ ዋጋ የሰጠው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

21) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች *በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ* ሊጠቀሙየሚችሉት የምክር አገልገሎቱ የሚከትሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ተፈፃሚ ይሆናል፤

ሀ/ ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለአማካሪው የሚሰጠው ሥራ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት እና ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ ከሥራው ጋር የማይመጣጠን ወይም አስቸኳይ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት ግዥውን በውድድር መፈፀም አሳማኝ ሳይሆን ሲቀር ነው፡፡

ለ/ ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የምክር አገልግሎቱ ወጪ ከብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ሐ/ መ/ቤቱ አማካሪው ያለውን የሥራ ልምድ እና የብቃት ደረጃ እንዲገልጽ የሚጠይቅ ማጣቀሻ

c) The technical proposals shall be opened and evaluated to determine compliance with the minimum qualification requirements.

d) Bidders who fail to meet the minimum technical qualification criteria shall be disqualified from the tender process.

e) The financial proposals of bidders disqualified on technical grounds shall be returned unopened.

f) The financial proposals of technically qualified bidders shall be opened for evaluation.

g) The prices submitted by all qualified bidders shall be publicly disclosed during the financial proposal opening session.

h) The bidder offering the lowest price among those who met the technical qualification requirements shall be awarded the contract.

21. In accordance with Sub-Article 12 of this Article, selection based on consultant qualifications may be used by government agencies when the following conditions are satisfied:

a) This method is appropriate where the cost and time required to prepare and evaluate proposals are disproportionate to the scope of the consultancy services, or where the urgency of the situation renders competitive procedures impractical.

b) The total cost of the consultancy services to be procured shall not exceed Birr 1,000,000.00 (one million Birr).

c) The procuring agency shall prepare a reference or recommendation letter and send a request for expressions of interest to selected consultants, requesting them to submit information on their qualifications and experience.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ወይም ቢጋር በማዘጋጀትለዕጩ ተወዳዳሪዎች የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ መላክ አለበት::

መ/ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን የፍላጎት መግለጫ መረጃ መሰረት በማድረግ በሚከናወን ግምገማ የተሻለ ሆኖ የተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ የቴክኒክና የዋጋ ማቅረቢያ ሀሳቡን በአንድ ላይ እንዲያቀርብ በማድረግና በመደራደር በሚደረስ ስምምነት መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል::

22) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የምክር አገልግሎት ግዥን ከአንድ አማካሪ ለመፈጸም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 34 እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 66 የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው::

23) የመንግስት መ/ቤቶች በማናቸውም የመረጣ ዘዴ የአማካሪዎች ግዥ በሚፈጽሙበት ወቅት የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት፣ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርበውን እያንዳንዱን የቴክኒክ ሐሳብ በሚገመግሙበት እና በሚያወዳድሩበት ወቅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 የተደነገጉትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ መሆን አለበት::

d) The consultant deemed most qualified based on the evaluation of submitted information shall be invited to submit a combined technical and financial proposal, which shall then be subject to negotiations.

22. In accordance with Sub-Article 12 of this Article, government agencies may procure consultancy services through single-source selection only when the conditions specified under Article 34 of the Proclamation and Article 66 of this Directive are met.

23. When government agencies procure consultancy services using any of the selection methods provided under this Directive, they shall prepare the bidding documents and evaluate each technical proposal submitted by the candidates in accordance with the evaluation criteria set forth under Sub-Article 13 of this Article.

ክፍል ሶስት

ውስን ጨረታ

SECTION THREE

LIMITED TENDERING

62. የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ አፈጻጸም

1) የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት ሳያስፈልግ ቁጥራቸው ውስን ለሆኑ ተሳታፊዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አድራሻቸው በሚላኩ ግብዣ መሠረት የሚቀርቡ ተጫራቾችን በማወዳደር የጨረታ አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ነው::

2) በአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የውስን ጨረታ ግዥ ዘዴ የሚፈፀመው በተገደበ የጨረታ ወይም በዋጋ ማቅረቢያ መሆን አለበት::

62. Implementation of Limited Tender Procurement Method

1. The limited tender procurement method is a procurement approach whereby competition is conducted among a limited number of suppliers invited electronically, based on their addresses, without issuing a public tender notice.

2. In accordance with Article 33(2) of the Proclamation, the limited tender procurement method shall be executed either through restricted bidding or through the Request for Quotation method.

63. የተገደበ ጨረታ ግዥ

1) የአዋጁ አንቀጽ 33 እንደተጠበቀ ሆኖ በተገደበ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ በዚህ መመሪያ እንደግዥው ዓይነት ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል::

63. Restricted Bidding

1. In accordance with Article 33 of the Proclamation, procurement conducted through restricted bidding shall follow the procedures prescribed for national or

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

2) የተገደበ ጨረታ ለመጠቀም ከሚከተሉት አንዱ መሟላት አለበት፡፡

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር አገልግሎቱ ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝስለመሆኑ ማስረጃ ያለ እንደሆነ፣ ሁሉንም አቅራቢዎች በመጋበዝ፣

ለ/ ግዥውን ለመፈጸም የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለአንድ ጊዜ ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች በመ/ቤቱ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መመዘኛዎች ያላሟሉ ሲሆን፣

ሐ/ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆንም የሚገዛው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም አገልግሎት ጠቅላላ ግምታዊ ዋጋ በንዑስ አንቀጽ 8 ከተቀመጠው የማይበልጥ ሲሆን፣

መ/ የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 ላይ ከተቀመቀጠው በላይ ቢሆንም በዳሰሳ ጥናት ላይ ተመርኩዞ የተመረጡ ውስን አቅራቢዎችን በመጋበዝ የሆቴል አገልግሎት፣ የቢሮ እና መጋዘን አገልግሎት ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ የህንጻ ኪራይ አገልግሎቶችን መግዛት አስፈላጊ ሲሆን፣

3) የጨረታ ጥሪውን እና ለግዥው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ በውድድሩ ለተጋበዙ ተጫራቾች በየአድራሻቸው እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

4) በዚህ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) እና (ሐ) መሠረት በተገደበ ጨረታ ግዥ ለመፈጸም በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ከተመዘገቡት መካከል በዘርፉ የተሰማሩ ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች መመረጥ አለባቸው፡፡

5) የመንግስት መ/ቤቱ በተገደበ ጨረታ የሚጋበዙ ተጫራቾችን ማንነት ለሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ የለበትም፡፡

6) በተገደበ ጨረታ የተጋበዙት ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ ከጨረታ መቆያ ጊዜ ገደቡ በፊት የመጫረቻ ሰነዳቸውን ካቀረቡ ወይም በጨረታው መሳተፍ እንደማይችሉ

international open tendering, depending on the nature of the procurement.

2. Restricted bidding may be used if at least one of the following conditions is met:

a) Where the required goods, construction works, consultancy services, or other services are available only from a limited number of suppliers, all such suppliers shall be invited to bid.

b) Where an open tender has been issued at least once but no bids have been received, or the bids received fail to meet the technical specifications prepared by the Public Body.

c) Where a large number of suppliers are available, but the estimated value of the procurement does not exceed the threshold set under Sub-Article 8 of this Article.

d) Where the estimated value exceeds the threshold set under Sub-Article 8, but, based on a needs assessment, it is necessary to procure hotel services, office or warehouse rental, or building lease services, the Public Body may invite selected suppliers.

3. The tender invitation and bidding documents shall be delivered to invited bidders at their respective electronic addresses.

4. Under Sub-Articles 2(b) and (c) of this Article, restricted bidding shall only be conducted by inviting at least five suppliers who are registered and qualified in the relevant field and listed in the government electronic procurement system.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ካሳወቁ የጊዜ ገደቡ እስከሚጠናቀቅ መጠበቅ ሳያስፈልግ የመንግስት መ/ቤቱ አዲሱን የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ለሁሉም ተጫራቾች የኤሌክትሮኒክ የመንግስት የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ማሳወቅ እና እንዲገኙ በመጋበዝ ጨረታው እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል።

7) የመንግስት መ/ቤቱ የጨረታ ማስከበሪያ መጠየቅ ቁጥራቸው ውስን የሆኑትን ተጫራቾች በጨረታው ውድድር እንዳይሳተፉ ያደርጋል ብሎ ሲያምን የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ሳያስፈልግ ዕጩ ተጫራቾች በጨረታ ማስከበሪያ ምትክ የጨረታ መተማመኛ ቅጽ ፈርመው ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል።

8) በዚህ አንቀጽ መሠረት በተገደበ ጨረታ የሚፈጸም ግዥን መጠቀም የሚቻለው የሚገዛው ዕቃ፣የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም አገልግሎት የግዥው ግምታዊ ዋጋ ከሚከተለው የማይበልጥ ሲሆን ብቻ ነው።

ሀ/ ለግንባታ ሥራ ዘርፍ ግዥ .... ከብር 60,000,000.00 (ስልሳ ሚሊዮን ብር)
ለ/ ለዕቃ ግዥ ..... ከብር 12,000,000.00 (አስራ ሁለት ሚሊዮን ብር)
ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ..... ከብር 7,000,000.00 (ሰባት ሚሊዮን ብር)
መ/ ለአገልግሎት ግዥ..... ከብር 9,000,000.00 (ዘጠኝ ሚሊዮን ብር)

9) የንዑስ አንቀጽ 8 ድንጋጌ ቢኖርም የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤት በሚሆንበት የግንባታ ስራ ውል ለግንባታ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ስራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ ይሆናል።

10) በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀመው የውስን ጨረታ የምክር አገልግሎት ግዥ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጨረታ አፈጻጸም ላይ የተገለጹትን ተጨማሪ አሠራሮች መከተል ይኖርበታል።

11) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት የተቀመጠውን ጣሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ሚኒስቴሩ ሊያሻሽል ይችላል።

5. The Public Body is not required to disclose the identities of invited bidders to other suppliers.

6. If all invited bidders submit their bids before the deadline or notify their inability to participate, the Public Body may proceed to open the bids earlier than scheduled. All bidders shall be notified of the revised bid opening time and invited to attend.

7. If the Public Body believes that requiring a bid security may deter participation due to the limited number of bidders, it may accept a bid assurance form instead of a bid security.

8. Restricted bidding may only be used where the estimated value of the procurement does not exceed the following thresholds:

   a) Construction Works – Birr 60,000,000 (Sixty Million Birr)
   b) Goods – Birr 12,000,000 (Twelve Million Birr)
   c) Consultancy Services – Birr 7,000,000 (Seven Million Birr)
   d) Services – Birr 9,000,000 (Nine Million Birr)

9. Notwithstanding Sub-Article 8, where the Public Body is responsible for supplying construction materials, the construction works threshold shall still apply.

10. For consultancy services procured using a Request for Proposal under a limited tender process, the procedures governing the Request for Proposal shall be followed.

11. The Ministry may revise the threshold amounts specified under Sub-Article 8 in response to prevailing economic conditions.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

64. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ

1) በአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት መ/ቤቶች ወዲያውኑ ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ወይም ለገበያ የተዘጋጁ ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው ዕቃዎችን፣ የግንባታ ሥራዎችን ወይም የምክር አገልግሎት እና ሌሎች አገልግሎቶች ግዥን በዋጋ ማቅረቢያ ሊፈጽሙ ይችላሉ።

2) በአዋጁ አንቀጽ 33 (4) መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ሊፈጸም የሚገባው በኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓቱ ለሁሉም ተወዳዳሪዎች ክፍት በማድረግ መሆን አለበት። ሆኖም በዚህ መልኩ ግዥውን ለመፈፀም የማይቻል መሆኑ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከተረጋገጠ፣ ከሦስት ያላነሱ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ ግዥው ሊፈፀም ይገባል።

3) ከሚከተሉት የገንዘብ መጠን የማይበልጡ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀሙ ግዥዎችን ለግዥ አዕዳቂ ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚሰጠው ውክልና መሠረት እንዲፀድቁ በማድረግ ግዥ መፈፀም ይችላል።

ሀ/ ለግባታ ሥራ ዘርፍ ግዥ ..... ከብር 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ ..... ከብር 800, 000.00 (ስምንት መቶ ሺህ ብር)

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ..... ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር)

መ/ ለአገልግሎት ግዥ..... ከብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺህ ብር)

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ቢኖርም የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቱ በሚሆንበት ጊዜ የግንባታ ስራ ውል ለግንባታ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ስራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ ይሆናል።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተቀመጠውን ጣሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ሚኒስቴሩ ሊያሻሽል ይችላል።

6) የመንግስት መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ ሲፈጽም በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑት አቅራቢዎች በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ስርዓት ከተመዘገቡት ውስጥ ሆኖ ለውድድር የሚላከው ግብዣ እስከተቻለ ድረስ ቁጥራቸው ከሶስት ላላነሱ ተወዳዳሪዎች መሆን አለበት። ሆኖም ተወዳዳሪዎቹ ቁጥራቸው ከሶስት በሚያንስበት ጊዜ የመ/ቤቱን የበላይ ኃላፊን ይሁንታ ማግኘት አለበት።

64. Request for Quotation

1. Pursuant to Article 33(4) of the Proclamation, Public Bodies may procure goods, construction works, consultancy services, or other services through a Request for Quotation if the items are urgently needed, are not suitable for bulk procurement, are market-ready, or are generally available on the open market.

2. In accordance with Article 33(5) of the Proclamation, Requests for Quotation shall be conducted through the electronic procurement system, accessible to all suppliers. If the head of the Public Body confirms that this is not feasible, procurement may proceed by inviting at least three suppliers.

3. Procurements that meet the thresholds below may be conducted through Request for Quotation without approval from the Procurement Endorsing Committee. Instead, they shall be approved by the head of the Public Body or a delegated authority:

   a) Construction Works – Birr 2,000,000 (Two Million Birr)
   b) Goods – Birr 800,000 (Eight Hundred Thousand Birr)
   c) Consultancy Services – Birr 500,000 (Five Hundred Thousand Birr)
   d) Services – Birr 600,000 (Six Hundred Thousand Birr)

4. Notwithstanding Sub-Article 2, where the Public Body is responsible for providing construction materials, the threshold applicable to construction works shall apply to the procurement of such materials.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

7) በመ/ቤቱ የተጋበዙ አቅራቢዎች ማንነት ለሌሎች ለተጋበዙት አቅራቢዎች ማሳወቅ የለበትም::

8) የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማቅረቢያ ውድድሩን አፈጻጸም ፍትሐዊ ለማድረግ የሚከተለውን አሠራር መከተል አለበት:-

ሀ/ በመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ስርዓት ከተመዘገቡትውስጥ ሁሉም ተሳታፊዎች በዙር የመወዳደር ዕድል ማግኘታቸውን እና ለመ/ቤቱ ጠቃሚ የሆነ የተለየ ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር አንድ ወይም የተወሰኑ አቅራቢዎችን ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ የለበትም::

ለ/ የዋጋ ማቅረቢያ መስጠት እና ዋጋ በመወሰን ሂደት ሊፈጠር የሚችል መማላጠርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር መከተል እና ዋጋው ታክስን ያካተተ መሆን አለበት:: ሆኖም ተጫራቹ ያቀረበው ዋጋው ታክስን ያካተተ ስለመሆኑ ካልተጠቀሰ ታክስ እንዳካተተ ተደርጎ ይቆጠራል::

9) እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሆኖ ያቀረበውን ዋጋም መለወጥ አይፈቀድለትም:: ዕጩ ተወዳዳሪው በሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ በመንግስት መ/ቤቱ እና በዕጩ ተወዳዳሪው መካከል ምንም ዓይነት ድርድር ሊደረግ አይችልም::

10) በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስፈላጊነቱ ታምኖበት ውክልና የተሰጣቸው በውጭ አገር የሚገኙ ሚሲዮኖች በአንድ ጊዜ የሚፈፅሙት የግዥ መጠን ከ30,000 / ከሠላሳ ሺ/ የአሜሪካን ዶላር ያልበለጠ ከሆነ ሚሲዮኖቹ በሚገኙበት አገር በሚሰበሰብ የዋጋ ማቅረቢያ ሊፈጽሙ ይችላሉ::

11) ተቀራራቢ የጥራት ደረጃ ያላቸውና በመ/ቤቱ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደደር አሸናፊው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት ከሚያወጣው

5. The Ministry may revise the thresholds set under Sub-Article 3 in light of changing circumstances.

6. When conducting procurement through Request for Quotation, suppliers shall be selected from those registered in the electronic government procurement system. The number of invited suppliers should be at least three. If fewer than three suppliers are available, procurement may only proceed with the approval of the head of the Public Body.

7. The identities of invited suppliers shall not be disclosed to each other.

8. To ensure fairness in the quotation evaluation process, the Public Body shall:

   a) Avoid repeatedly inviting the same supplier(s), except where a specific justification exists. All registered suppliers shall be given fair rotational opportunities.
   b) Apply proper procedures to prevent manipulation during submission and evaluation. Prices shall include applicable taxes. If the bidder does not specify that taxes are excluded, the price will be deemed inclusive of taxes.

9. Each bidder may submit only one price quotation. Price revisions after submission are not permitted. No price negotiations shall take place.

10. Notwithstanding this Article, where the Ministry of Foreign Affairs authorizes it, diplomatic missions abroad may conduct local procurement through Request for

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃ ጋር አማካይ የሆነ ዋጋ መሆን አለበት።

12) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 የተደነገገው ቢኖርም ከኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃ ማግኘት የማይቻል ከሆነ እንደቅደመ ተከተሉ ከታወቀ አምራች ዋጋ ወይም ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናትውጤትጋር ተቀራራቢ የሆነና ዝቅተኛ የመወዳደሪያ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ መምረጥ አለበት።

13) የመንግስት መ/ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያለሚፈጽሙት ማናቸውም ግዥ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የዋጋ ማቅረቢያ ጨረታ ሰነድ መጠቀም አለባቸው።

14) በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸሙ ግዥዎች አቅራቢው የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ እና መ/ቤቱ ለአቅራቢው የግዥ ትዕዛዝ የሰጠበት ማስታወቂያ እንደውል ይቆጠራል። ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ መ/ቤቱ ከሚፈጽመው ግዥ ባህርይ በመነሳት ዝርዝር ውል ሊፈጽም ይችላል።

15) በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈጸም ሲባል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት አይችሉም።

16) በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸም ግዥ የተቀመጠውን ጨረታው ለተጫራቾች ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ ማራዘም አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት፣ የመንግሥት መ/ቤቱ ጊዜውን ሊያራዝም ይችላል።

65. ልዩ ፍላጎትን ለማሟላት በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3) እና (4) የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ያለ ገንዘብ ገደብ ግዥ ሊፈጽሙ ይችላሉ።

2) በአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት መ/ቤቶች ባላቸው የተለየ የሥራ ባህሪ ምክንያት

Quotation for amounts not exceeding USD 30,000 per transaction.

11. When evaluating quotations that meet quality standards, the price offered by the winning bidder shall be compared to the prevailing market reference price issued by the Ethiopian Statistical Service.

12. If no such market reference is available, the price shall be compared against known producer prices or a market analysis conducted in accordance with Authority-issued guidelines.

13. Public Bodies shall use the standard bidding document for Request for Quotation as prepared by the Authority.

14. The supplier's submitted price and the purchase order issued by the Public Body shall constitute a valid contract. However, a formal contract may be signed depending on the nature of the procurement.

15. Public Bodies may not divide a procurement into smaller components to evade the rules governing Request for Quotation.

16. The Public Body may extend the quotation submission period where necessary.

65. Procurement through Request for Quotation for Special Needs

1. Notwithstanding Article 64(2), Public Bodies may use the Request for Quotation method without a monetary limit if the conditions under Sub-Articles 2, 3, and 4 of this Article are fulfilled.

2. In accordance with Article 33(7) of the Proclamation, the Request for Quotation

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

ለሚፈጸም ግዥ ከዚህ በታች የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

ሀ/ ግዥው ለጥናት እና ምርምር የሚሆኑ ግብዓቶችወይም ለህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ወይም የቆይታ ጊዜያቸው አጭር የሆኑ ዕቃዎች ሲሆን፣ ወይም

ለ/ የሚገዙት ዕቃዎች ወይም መሳሪያዎች ምስጢራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ሲሆኑ፣ እና

ሐ/ ከጥራት፣ ከጊዜ እና ከውጤት አንጻር ግዥዎቹ በዋጋ ማቅረቢያ መፈጸም በዚህ አንቀጽ መሰረት መፈጸም አዋጭ መሆኑ በበላይ ኃላፊው ሲታመንበት፡፡

3) በአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የፌደራል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውሉ ሸቀጦችን ለአንድ ጊዜ ወይም እንደሁኔታው በማዕቀፍ ስምምነት ውል በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 አፈፃፀም የዚህ መመሪያ አንቀጽ 68 (4) ተፈፃሚ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይገባል፤

ሀ/ ከአንድ በላይ በሆኑ የአገር ውስጥ አምራቾች የሚመረቱትን እንደ ስኳር፣ፓስታ፣ዘይት እና ሻይቅጠል የመሳሰሉ የምግብ ሸቀጦች ግዥ ለመፈጸም፣

ለ/ የተለያዩ እህሎችና ጥራጥሬዎችን ከእህል ንግድ ድርጅት ወይም ሁለገብ የገበሬ ህብረት ሥራ ዩኒየኖች ግዥ ለመፈጸም፣

ሐ/ በአገር ውስጥ አምራች ኩባንያዎች የማይመረቱና በተለያዩ አስመጪና አከፋፋይ ድርጅቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የምግብ ሸቀጦችን ለመግዛት፣

መ/ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ"፣"ለ" እና "ሐ" መሠረት ግዥ ለመፈጸም በመ/ቤቱ በሚደረገው የዳሰሳ ጥናት በጊዜ ወይም በዋጋ ወይም በአቅርቦት የተሻለ መሆኑን ማረጋገጥ፣

method may be used under the following circumstances:

a) For research and study purposes, medical accessories, or items with short shelf life.
b) Where the items to be procured are confidential.
c) Where the Head of the Public Body deems the method suitable in terms of quality, timeliness, and efficiency.

3. As per Article 33(6) of the Proclamation, federal higher education institutions may procure student food supplies through Request for Quotation, either as one-time purchases or through framework agreements.

4. Without prejudice to Article 68(4), the following conditions shall apply to the implementation of Sub-Article 3:

a) For procurement of food items such as sugar, pasta, oil, and tea produced by multiple local manufacturers.
b) For procurement of food items to be distributed by wholesalers, farmers' unions, or cooperatives.
c) For procurement of food items not produced locally but imported by registered importers or distributors.
d) The Public Body must conduct a market survey to ensure the timely availability, pricing, and supply adequacy of the goods covered under Sub-Article 4(a)–(c).

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ክፍል አራት

በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ

66. በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ መሠረታዊ አሰራር

1) የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 34 መሠረት በቀጥታ ግዥ ለመፈፀም የሚሰጡት ውሳኔዎች በዚህ አንቀጽ የተቀመጡትን ሁኔታዎች መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡ :

2) በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ረ" መሠረት በዓይነት እና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበ አቅራቢመግዛት ጠቃሚ መሆኑሲታመን በአቅራቢው ፈቃደኝነት ላይ በመመሥረትና የሚከተሉትን አሠራሮች በመከተል ተጨማሪ ግዥ ለመፈፀም ይቻላል፡፡

ሀ/ በተጨማሪነት የሚታዘዘው ዕቃ፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎት ግዥ መጠን ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) መብለጥ የለበትም፣

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት ተጨማሪ ግዥ ለማዘዝ የቀድሞው ግዥ ውል ፀንቶ በሚቀይበት ጊዜ ውስጥ ወይም ውሉ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥሉት 9 (ዘጠኝ) ወራት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፣

ሐ/ በዚህ መሠረት ግዥ ሲፈጸም በመጀመሪያው ውል ከነበረው የነጠላ ዋጋ የበለጠ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አይፈቀድም፣

መ/ ከላይ በፊደል ተራ "ሐ" የተቀመጠው ቢኖርም የመጀመሪያው ውል የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ እና የዋጋ ማስተካከያ የተደረገ ከሆነ በተስተካከለው ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

3) የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሠ" በተገለጸው መሠረት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን አረጋግጠው ያልታሰቡና በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎችን ማሠራት ይችላሉ፡፡

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በተጨማሪነት እንዲሰሩ የታሰቡት ስራዎች በመጀመሪያው ውል ውስጥ መካተት ይገባቸው የነበሩ ወይም ከዋናው ስራ ጋር ቢካተቱ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚኖራቸው

SECTION FOUR

DIRECT PROCUREMENT

66. Preconditions for Direct Procurement

1. Public Bodies shall ensure that any decision made pursuant to Article 34 of the Proclamation to conduct direct procurement is based on the conditions set forth in this Article.

2. In accordance with Article 34(1)(f) of the Proclamation, a Public Body may procure additional goods, consultancy services, or other services that are similar in type and price from the same supplier that provided the original procurement, provided it is deemed beneficial to the Public Body and the following conditions are fulfilled:

   a) The additional procurement shall not exceed twenty-five percent (25%) of the total value of the original contract.
   b) The additional procurement must be ordered during the validity period of the original contract or within nine (9) months from the completion date of the original contract.
   c) While procuring in this case, the unit price shall not exceed the original price specified in the initial contract.
   d) Notwithstanding Sub-Article 2(b) of this Article, where the original contract allows price adjustment and such adjustment has been applied, the adjusted price shall prevail.

3. In accordance with Article 34(1)(e) of the Proclamation, a Public Body may undertake additional construction works that were omitted from the original

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

እና ስራዎቹን ነጣጥሎ ማሰራት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ወይም የመ/ቤቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፣

ለ/ በተጨማሪነት ወይም በዋናው ሥራ ውስጥ ያልተካተቱ አዲስ የሚሰሩ የግንባታ ሥራዎች የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% /ሠላሳ በመቶ/ የበለጠ መሆን የለበትም፣

ሐ/ በተጨማሪነት የሚታዘዙት የግንባታ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ በውል ውስጥ ሊገኝ የሚችል ከሆነ የተጨማሪው ስራ በውል ውስጥ ባለው ነጠላ ዋጋ መሠረትወይም የዋጋ ማስተካከያ የተደረገ ከሆነ በተስተካከለው ዋጋ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል። የነጠላ ዋጋው ውል ውስጥ የማይገኝ ከሆነ በድርድር ስምምነት ላይ የሚደረስበት ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን መ/ቤቱ ማረጋገጥ አለበት።

4) በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "መ" መሠረት አስቀድሞ ለተገዙ ዕቃዎች ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ተጓዳኝ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን መግዛት ሲያስፈልግ እና እነዚህን ተጓዳኝ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን ከሌላ ተወዳዳሪ መግዛት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከሚጠቀምበት ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ምክንያት ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት የግድ ሲሆንበቀጥታ ግዥ መፈጸምይቻላል።

5) የመንግስት መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሰ" መሠረት ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኝ ሲሆንየሚከተሉትን አሠራሮች በመከተል የለቀማ ግዥ መፈፀም ይቻላል።

ሀ/ ግዥውን በለቀማ መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስታወሻ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለዚህ ሥራ በኃላፊው ውክልና ለተሰጠው አካል ቀርቦ መፈቀድ አለበት።

ለ/ የመንግስት መ/ቤቶች በለቀማ ግዥ የሚፈጽሙ ብዛታቸው ከሦስት ያላነሱ ጊዜያዊ ኮሚቴ በደብዳቤ ይሰይማል። እስከተቻለ ድረስ ስለሚገዛው ዕቃ ዕውቀት ያለው ሰራተኛ የኮሚቴው አባል እንዲሆን መደረግ አለበት።

contract, provided the following conditions are satisfied:

a) The additional work must be economically beneficial when executed in conjunction with the original work, or it must have been necessary to include it in the original contract. It must also be demonstrated that executing the additional work separately would be technically or economically disadvantageous.
b) The value of the additional construction works or new works not included in the original shall not exceed thirty percent (30%) of the total value of the original contract.
c) If a unit price for the additional work exists in the original contract, the work shall be executed based on that unit price or any adjusted price. If no such price exists, a negotiated price shall be agreed upon and verified by the Public Body to ensure consistency with market rates.

4. Pursuant to Article 34(1)(d) of the Proclamation, if replacement or additional goods or services previously procured—excluding consultancy services—cannot be sourced from another supplier or service provider without incompatibility with the existing goods or services in use, the Public Body may procure such goods or services directly from the original supplier.

5. In accordance with Article 34(1)(g) of the Proclamation, when the required goods, services, or works are not available through regular suppliers, the Public Body

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

ሐ/ የተቋቋመው ጊዜያዊ ኮሚቴ ግዥውን በጋራ በመሆን ማከናወን ያለበት ሲሆን ግዥውን ለማከናወን በቂ አቅርቦት የሚኖርበትን ቦታ እና ጊዜ መምረጥ አለበት፡፡

መ/ ጊዜያዊው ኮሚቴው በጋራ በመሆን ካለው አቅርቦት የተሻለ ጥራት እና ዋጋ ያለውን ወይም ያላቸውን ሻጮች በመምረጥ ዋጋ ተደራድሮ ግዥውን ይፈፅማል፡፡

ሠ/ በግዥው አፈፃፀም ሂደት የተፈፀሙትን ግዥዎች ብዛትና ዓይነት፣ ግብይቱ የተፈፀመበትን ቦታ፣ ጊዜ፣የተከፈለውን የገንዘብ መጠን፣ የሻጮችን ሙሉ ስም እና አድራሻ፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን እንዲያካትት ተደርጎ ለዚህ ዓላማ በባለስልጣኑ በተዘጋጀው የውል ሰነድ ፎርማት ላይ ሻጮች እንዲፈርሙና እንዲያረጋግጡ መደረግ አለበት፡፡

ረ/ በለቀማ የተገዙ ግዥዎች በሚጓዝበት ወቅት እንዳይበላሹ እና እንዳይጠፉ በጥንቃቄ መያዝ እና በተቻለ ፍጥነት የሚመለከተው ክፍል እንዲረከባቸው መደረግ አለበት፡፡

ሰ/ ጊዜያዊ ኮሚቴው አጠቃላይ የለቀማ ግዥ አፈፃፀሙን የሚገልፅ ቃለ-ጉባኤ በማዘጋጀት ተፈራርሞ ሪፖርት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለዚህ ሥራ በኃላፊው ውክልና ለተሰጠው አካልማቅረብ አለበት፡፡

ሸ/ በለቀማ የሚፈጸሙ ግዥዎች ከተጠናቀቁ በኋላ የግዥ መረጃዎች የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ይፋ ለህዝብ መደረግ አለባቸው፡፡

6) የመንግስት መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሰ" መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸውን ጥቃቅን ግዥዎች ሲፈፅሙ ከዚህ በታች የተገለጹትን ሁኔታዎች መከተል አለባቸው፤

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን

may conduct direct procurement using the special shopping method under the following procedures:

a) A memorandum justifying the need for special shopping must be prepared and approved by the Head of the Public Body or their delegate.
b) An ad-hoc committee of at least three members shall be formally established. Where possible, the committee should include a staff member knowledgeable about the items to be procured.
c) The ad-hoc committee shall carry out the procurement jointly and select a suitable location and time to ensure adequate supply.
d) The committee shall select suppliers offering the best quality and price and shall negotiate prices accordingly.
e) Details of the procurement—such as the items procured, supplier names and addresses, place and time of the transaction, amounts paid—shall be documented. Suppliers must sign the standardized contract document format prepared by the Authority.
f) Purchased items must be securely stored to prevent damage or loss and promptly delivered to the designated unit.
g) The ad-hoc committee shall prepare and submit a report on the special shopping procedure to the Head of the Public Body or their delegate.
h) Upon completion, information related to the special shopping shall

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ከመፍታት ጋር የተያያዙ ጥቃቅን ግዥዎችን ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈፀም ይችላሉ። ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈፀሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን ብር) መብለጥ አይኖርበትም።

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተገለጸው ቢኖርም በውጭ አገር የሚገኙ ሚሲዮኖች በግዥ ዕቅዳቸው ሊካተቱ ያልቻሉ አጣዳፊ ግዥዎችን በአንድ የግዥ ትዕዛዝ ከ300 /ሶስት መቶ/ የአሜሪካን ዶላር ያልበለጠ ግዥ በቀጥታ ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት ለመፈፀም ይችላሉ። ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከ6 ሺህ /ስድስት ሺህ/ የአሜሪካን ዶላር መብለጥ የለበትም።

7) የመንግስት መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ቀ" መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች ለሚኖራቸው የዕቃ እና አገልግሎት ግዥ ፍላጎት ወጪን በመሸፈን ከመንግስት ባለበጀት መ/ቤት ግዥ ለመፈጸም ከዚህ በታች የተመለከቱ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

ሀ/ በሌሎች የግዥ አማራጮች ለመፈጸም አስቸጋሪ የሆነና መ/ቤቱ አዋጭ መሆኑን የሚያስረዳ በቂ ምክንያት ያለ ሲሆን፣

ለ/ ለግዥው የሚከፈለው ዋጋ ከገበያ ዋጋ አንጻር የተሻለ ሲሆን፣

ሐ/ ግዥው ተደጋጋሚ ያልሆነ ሲሆን፣

መ/ የሚቀርበው አቅርቦት ለትርፍ ተብሎ የተመረተ ምርት ወይም የሚሰጥ አገልግሎት መሆን የለበትም።

8) የመንግስት መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "በ" መሠረት ባላቸው የተለየ የስራ ባህሪ ምክንያት በውድድር ሊገኙ የማይችሉ ለጥናትና ምርምር፣ ለህክምና መሳሪያዎች አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን፣ እንዲሁም ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ግዥዎችን ከዚህ በታች የተመለከቱ ሁኔታዎች

be disclosed through the electronic government procurement system.

6. Pursuant to Article 34(1)(g) of the Proclamation, Public Bodies may conduct small-scale procurement under the following conditions:

a) For unplanned or travel-related procurements not exceeding 50,000 Birr per transaction and a cumulative annual total not exceeding 1,000,000 Birr, items may be procured from any available supplier.

b) Notwithstanding Sub-Article 6(a), diplomatic missions abroad may procure urgent items or services not included in their procurement plans, provided a single procurement does not exceed USD 300 and the annual total does not exceed USD 6,000.

7. In accordance with Article 34(1)(i) of the Proclamation, direct procurement of goods and services from another Public Body may be conducted if the following conditions are met:

a) It is difficult to execute the procurement through other methods and there is sufficient justification for cost-effectiveness.

b) The price offered is lower than prevailing market prices.

c) The procurement is non-repetitive.

d) The goods or services are not intended for profit generation.

8. Pursuant to Article 34(1)(j) of the Proclamation, Public Bodies may directly

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

የተሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ግዥውን በቀጥታ ሊፈጽሙ ይችላሉ::

ሀ/ ግዥውን ከዚህ የግዥ ዘዴ ውጭ በውድድር መፈጸም የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን፣

ለ/ ግዥው ለጥናት እና ምርምር ወይም ለመድኃኒትነት እና ለህክምና አገልግሎት የሚውል መሳሪያ እና ተያያዥ ግብዓቶች ሲሆኑ፣

ሐ/ የሚገዙ ዕቃዎች ወይም መሳሪያዎች የቆይታ ጊዜያቸው አጭር የሆኑ ወይም ምስጢራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ሲሆኑ፤

9) የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1(ተ) መሠረት ቀደም ሲል በሌላ የመንግስት መ/ቤት በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ከተገዙ ዕቃዎች ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ጋር በዓይነትና በዋጋ አንድ ዓይነት የሆኑ ግዥዎችን ለመፈጸም የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው::

ሀ/ በመንግስት መ/ቤቱ ሊፈጸም የታሰበው ግዥ ከዚህ ቀደም በሌላ የመንግስት መ/ቤት ከተፈጸመው ግዥ በመጠን ያልበለጠ፣ በዓይነትና በዋጋ አንድ ዓይነት የሆነና ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ አንጻር አዋጭ ሲሆን፣

ለ/ ቀደም ሲል በወጣው ጨረታ ተወዳድሮ ባሸነፈበትና ውል በገባበት የጥራት ደረጃ/መግለጫ/ ላይ ለውጥ ሳይደረግ መቅረብ እንዳለበት፣

ሐ/ የሚፈጸመው ግዥ ከዚህ ቀደም በሌላኛው የመንግስት መ/ቤት ከተፈጸመው የግዥ ያልበለጠ ሲሆን፣

መ/ አቅራቢው አቅርቦቱን ጨረታውን ላወጣው የመንግስት መ/ቤት አቅርቦ ካጠናቀቀ ከአንድ ዓመት በላይ ያልሆነው ሲሆን፣

10) ለዚህ ዓላማ መ/ቤቱ አስቀድሞ ግዥውን ለፈጸመው የመንግስት መ/ቤት ማሳወቅና ከሌላ የመንግስት መ/ቤት ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦ ግዥ ያልተፈጸመ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማግኘት አለበት::

procure the following items, subject to the conditions below:

a) Research-related goods and services, medical reagents, or items requiring confidentiality, if competitive bidding or other methods are not practical.
b) Equipment and supplies for research, studies, or medical services.
c) Goods with a short shelf life or items requiring confidentiality.

9. Pursuant to Article 34(1)(k) of the Proclamation, a Public Body may procure goods or services previously procured by another Public Body through open bidding under the following conditions:

a) The intended procurement is of the same type and price and does not exceed the quantity procured by the first Public Body.
b) The goods or services must meet the same specifications and quality levels.
c) The procurement quantity shall not exceed that of the previous procurement.
d) No more than one year has passed since the original contract was successfully completed.

10. For the application of Sub-Article 9, the Public Body must notify the entity that conducted the original procurement and ensure no other similar requests have been submitted.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

67. በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ ላይ ስለሚደረግ ድርድር

1) በአዋጁ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች በቀጥታ የግዥ ዘዴ ግዥ በሚፈጽሙበት ጊዜ ዋጋን ጨምሮ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ድርድርድ በማድረግ ስምምነት ላይ መድረስ ይችላሉ፡፡

ሀ/ በሚገዛው ዕቃ፣ አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ የቴክኒክ ፍላጎት ዝርዝር መግለጫዎች (specifications) ፣

ለ/ ስለ ዋጋና የክፍያ አፈጻጸም፣

ሐ/ የመዳረሻ ፕሮግራሞች እና የጊዜ ሰሌዳዎች፣

መ/ ስለ ዋስትናእና ከሽያጭ በኋላ ስለሚሰጡ አገልግሎቶች፣እና

ሠ/ ማንኛውም የመንግስት ገንዘብ ማስገኘት ያለበትን ከፍተኛ ጥቅም (value for money) ለማሳካት እናየህዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ሌሎች ሁኔታዎችን፣

2) የመንግስት መ/ቤቶች በቀጥታ የግዥ ዘዴ ድርድር በሚያደርጉበት ወቅት የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሊያሟሉ ይገባል፣

ሀ/ ግዥው በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተገለፀው መሠረት የቀጥታ ግዥ ምርጫ መስፈርትን የሚያሟላ መሆኑ፣

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ የግዥውን የተሻለ ውጤት ለማረጋገጥ የድርድሩን አስፈላጊነት በፅሁፍ ማስቀመጥ፣እና

ሐ/ የድርድሩን ዓላማ፣ ስፋት እና በመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተደራዳሪ ቡድን በመሰየም ዝርዝር የድርድር ዕቅድ ማዘጋጀት፣

3) በቀጥታ ግዥ ለመፈጸም የሚተገበር ድርድር የግዥ ውል ከመፈረሙ በፊት መካሄድ አለበት፡፡

4) የመንግስት መ/ቤቱ ከግዥው ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በግዥና ንብረት የዳበረ ልምድና ዕውቀት ያላቸው ቢያንስ ሶስት አባላት ያሉት የድርድር ቡድን ያቋቁማል፡፡

5) የድርድር ቡድኑ የግዥውን እና የድርድሩን ዓላማዎች፣ ተቀባይነት ያላቸውን ቃላት እና ቅድመሁኔታዎች የሚገልፅ የድርድር ዕቅድ በማዘጋጀት ለአቅራቢው ሊደራደርባቸው የሚችላቸውን ርዕሰ ጉዳዮች አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡

67. Negotiations on Direct Procurement

1. In accordance with Article 34(4) of the Proclamation, Public Bodies shall negotiate the following matters before entering into a direct procurement contract:

   a) Detailed technical specifications of the required goods, services, or works.
   b) Price and payment terms.
   c) Delivery timelines and schedules.
   d) Warranty and after-sales services.
   e) Considerations related to value for money and public interest.

2. Public Bodies must meet the following conditions before conducting negotiations:

   a) The procurement must qualify as direct procurement under the Proclamation and this Directive.
   b) The necessity of the negotiation must be documented in writing.
   c) A negotiation team shall be appointed and a plan prepared outlining the purpose, scope, and negotiation points.

3. Public Bodies must conduct negotiations prior to signing any procurement contract.

4. The negotiation team shall consist of at least three members with relevant procurement and property administration experience.

5. The negotiation team must prepare a negotiation plan outlining procurement objectives, acceptable terms, and issues to be discussed, and must inform the supplier of negotiable issues in advance.

6. Negotiations must be conducted transparently, inclusively, and in line with

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

6) የመንግስት መ/ቤቱ ድርድሩ ግልፅ፣ ዝርዝር፣ የሁሉም ወገኖች ግብዓቶች የተካተቱበት፣ ፍትሃዊ፣ የመንግስት ገንዘብ ከፍተኛውን ዋጋ ማስገኘቱንና ተጠያቂነትን ያረጋገጠ እንዲሁም መሠረታዊ የግዥ መርሆዎችን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል።

7) የድርድሩ ውጤት የግዥ ውሉ ከመፈረሙ በፊት በመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተመርምሮ መጽደቅ አለበት።

8) የመንግስት መ/ቤቱ ያከናወነውን የድርድር ሂደት የሚያሳዩ እና ስምምነቶችን እንዲሁም የድርድር ሂደቱን ሙሉ ዘገባ የግዥ ፋይሉ አካል አድርጎ ማስቀመጥ አለበት።

ክፍል አምስት

በልዩ ሁኔታ የሚፈፀም ግዥ

68. በልዩ ሁኔታ ግዥን ስለመፈፀም

1) በአዋጁ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ግዥውን ለመፈጸም አሳማኝ ምክንያት ሲቀርብ እና በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና በዚህ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ያልተሸፈኑ ከተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች፣ የግዥ ሰነዶች እና ቅፆች ወይም በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ ግዥን ለመፈጸም ወይም ውልን ለመፈጸም በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ሚኒስትር በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል።

2) በዚህ አንቀጽ መሠረት ተጠሪ ተቋማት ለሚኖራቸው የልዩ ሁኔታ ግዥ ጥያቄ የልዩ ሁኔታ ፈቃድ ሊሰጥ የሚገባው መ/ቤቶቹ ተጠሪ በሆኑበት ሚኒስቴር መ/ቤት ሚኒስትር ብቻ ነው።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲሁም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ የመንግሥት መ/ቤቶች በዚህ ክፍል በተደነገገው መሠረት ለሚኖራቸው የልዩ ሁኔታ ግዥ ጥያቄ ፈቃድ ሊሰጥ የሚገባው በመሥሪያ ቤቶቹ የበላይ ኃላፊ ብቻ ነው።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ የመንግሥት መ/ቤቶች በዚህ ክፍል በተደነገገው መሠረት ለሚኖራቸው የልዩ ሁኔታ ግዥ ጥያቄ ፈቃድ ሊሰጥ የሚገባው በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ኃላፊ ብቻ ነው።

procurement principles, ensuring accountability and value for money.

7. The negotiation results must be reviewed by the Head of the Public Body before signing the contract.

8. The entire negotiation process and outcomes shall be documented and retained in the procurement file.

SECTION FIVE

PROCUREMENT TO BE PERMITTED IN EXCEPTIONAL CIRCUMSTANCES

68. Procurement through Special Permission

1. In accordance with Article 30(5) of the Proclamation, where compelling reasons exist, and when the procurement method, documents, or procedures fall outside those established by law, the Minister of the respective Public Body may grant special permission.

2. The authority to grant such permission lies solely with the Minister of the relevant Public Body.

3. Notwithstanding Sub-Articles 1 and 2 of this Article, for Public Bodies accountable to the House of Peoples' Representatives or the House of Federation, the authority rests with the Head of the respective institution.

4. For Public Bodies accountable to the Office of the Prime Minister, such authority lies with the Head of the Office of the Prime Minister.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

5) በዚህ አንቀጽ መሠረት የልዩ ሁኔታ ፈቃድ ጥያቄን መርምሮ እንዲወስን ስልጣን የተሰጠው አካል የተሰጠውን ስልጣን ለተጠሪ ተቋማት ውክልና መስጠት አይችልም።

69. የልዩ ሁኔታ ፈቃድ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥ ላይ መከተል የሚገባቸው መርሆዎች

1) የልዩ ፈቃድ ጥያቄው ሊቀርብ የሚገባው የሚኒስቴር መ/ቤቶች የግዥ ጥያቄን በተመለከተ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ ሥራ ክፍል መቅረብ ያለበት ሲሆን ለተጠሪ ተቋማት የልዩ ፈቃድ ጥያቄው ለሚኒስትሩ መቅረብ ያለበት በተጠሪ መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ብቻ ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመላከተው ጥያቄ መደበኛ የግዥ ሂደቶችን ወይም መደበኛ የግዥ አሠራርን መከተል የማይቻልበትን አስገዳጅ ምክንያቶች በመዘርዘር በልዩ ሁኔታ ግዥውን ለመፈጸም ለምን እንዳስፈለገ ግልጽ እና አሳማኝ ማብራሪያመሰጠት እና በቂ ደጋፊ ሰነድመቅረብ አለበት።

3) የሚጠየቁ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች መደበኛውን የግዥ ስርዓት ተከትሎ ለመፈጸም የማይቻል መሆኑን የማረጋገጥ፣

4) የሚጠየቁ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎችና ምላሾች ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ እንዲገኝ፣ ግዥው በተያዘለት ጊዜ እንዲፈጸም ወይም ውሳኔ እንዲያገኝ በሚያስችል መልኩ በወቅቱ ምላሽ መስጠትን ያካትታል፣

5) በልዩ ፈቃድ የሚፈጸሙ ግዥዎችን አፈጻጸም መገምገም ለሚጠየቁ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች ከሚሰጡ ምላሾች በስተቀር ሌሎች መደበኛ አሰራሮችን ጠብቀው መከናወናቸውን የማረጋገጥ፣

6) የሚሰጡ ምላሾች ሚዛናዊ እና መረጃን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ለተሰጡ ምላሾችና የተሰጡ ውሳኔዎች በተቻለ መጠን ምክንያቶችን መግለጽን ይጠይቃል።

7) የሚቀርቡ የልዩ ፈቃድ መነሻ ጥያቄዎች ተገቢ መሆናቸውን አረጋግጠው የማቅረብ ኃላፊነት የግዥ ሥራ ክፍሉ ወይም የተጠሪ ተቋሙ የበላይ ኃላፊ

5. The authority to grant special permission is non-delegable and cannot be transferred to Public Bodies under their oversight.

69. Principles for Requesting and Responding to Special Permission

1. Special permission requests shall be submitted by the procurement department of the Ministry or, for subordinate Public Bodies, through their respective Head.

2. Requests under sub-article 1 of this Article must include compelling reasons and justification for why the standard procurement process cannot be followed.

3. The requests for the special procurement permission shall verify that it is difficult to follow the regular procurement procedures;

4. Special permit requests and the corresponding responses shall be handled in a timely and cost-efficient manner, ensuring that procurement is either executed within the required timeframe or a formal decision is rendered accordingly.

5. The implementation of procurements authorized under special permits shall comply with the applicable procurement standards and procedures, except for those specific elements waived under the special permit.

6. Responses to special permit requests shall be impartial, grounded in verifiable information, and, to the extent possible, accompanied by clear reasons justifying the decision taken.

7. While the primary responsibility for the preparation and submission of special permit requests lies with the procurement unit or the head of the requesting institution, all officials and experts involved in decision-making at any stage of the process

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

ኃላፊነት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በየደረጃው በሚሰጡ ውሳኔዎች የሚሳተፉ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከተሰጠው ውሳኔ ጋር በተያያዘ ተጠያቂነት አለባቸው።

70. የልዩ ፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ

1) የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች ሲቀርቡ እንደአግባብነቱ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ ሥራ ክፍል ወይም ከተጠሪ መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተረጋግጠው እና ተፈርመው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

2) የሚቀርቡ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች ግዥ ህጉን እና የአሰራር ሥርዓቱን ተከትሎ ሊፈፀም ያልተቻለበትን ምክንያት ማብራሪያዎች እና ደጋፊ ሠነዶች ማያያዝ አለባቸው።

3) የሚቀርቡ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች የአቅርቦት ወይም የአገልግሎት ጊዜ፣ ሊያወጣ የሚችለው ግምታዊ ዋጋ፣ የተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች መጠን፣ የግንባታ ሥራዎቹ የፊዚካል አፈጻጸም እና ሌሎች መረጃዎችን በግልጽ ማረጋገጥ አለባቸው።

4) ግዥውን በልዩ ሁኔታ ለመፈጸም በቀረበው አማራጭ ቢፈፀም ከጥራት፣ ከወጪና ከጊዜ አንፃር የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ማረጋገጥ አለባቸው።

5) የሚቀርቡ ማብራሪዎች እና አባሪ ማስረጃዎችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ደብዳቤውን ፈርሞ የሚያቀርበው እንደአግባብነቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ ሥራ ክፍል ወይም የተጠሪ መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ነው።

71. በልዩ ሁኔታ ፈቃድ ጥያቄ ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ስርዓቶች

1) እንደአግባብነቱ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ ሥራ ክፍል ወይም ከተጠሪ መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርቡ ማብራሪዎች እና አባሪ ማስረጃዎችን ትክክለኛነት መረጋገጥ አለበት።

2) በልዩ ሁኔታ የተሰጠው የግዥ ፈቃድ ለተፈቀደው ጊዜ እና መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

3) በልዩ ሁኔታ ለማስፈቀድ የሚቀርቡ ማብራሪያዎች እና ማስረጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተጨማሪ ማብራሪያዎች እና የሰነድ ማስረጃዎች ሊጠየቅ ይችላል፣

shall be held accountable for the decisions made in connection with the special permit.

70. Procedures for Special Permission Requests

1. The procurement department or Head of the Public Body shall verify and approve the request before submission.

2. The request must include detailed justification and, where necessary, supporting documents explaining the infeasibility of regular procedures.

3. Requests must detail delivery timelines, estimated value, scope of additional works, physical progress (if construction), and other relevant information.

4. The special procurement must be shown to provide economic and social benefits in terms of quality, cost, and time.

5. Responsibility for verifying the supporting documents lies with the procurement unit or the Head of the Public Body, who must sign and submit the request.

71. Procedures for Responding to Special Permission Requests

1. The submitted explanations and supporting documents must be verified for accuracy.

2. Special permission shall be valid only within the specified scope and timeframe.

3. Additional documentation or clarification may be requested as needed to make an informed decision.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

4) የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች የቀረቡትን ማስረጃዎች እና ማብራሪያዎችን በመመርመር ከጊዜ፣ ከጥራትና ከዋጋ አንጻር የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት የልዩ ፈቃድ ጥያቄው ይወሰናል።

5) የተፈቀዱ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች ምላሽ ደብዳቤ ለመ/ቤቱ ወይም ለመ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል እንዲያውቀው የማድረግ እንዲሁም አጠቃላይ አፈጻጸሙን በሩብ ዓመት ለባለስልጣኑ ሪፖርት ለይቶ መቅረብ አለበት።

6) የመንግሥት መ/ቤቱ ግዥውን በመደበኛው የግዥ ሂደት ለመፈጸም ከጀመረ በኋላ የግዥ ሂደቱን በማቋረጥ በልዩ ሁኔታ ግዥው እንዲፈፀም ማድረግ የለበትም።

7) በልዩ ሁኔታ ግዥውን ከመፈፀም አንፃር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች ተለይተው የታወቁ እና የተገመገሙ መሆን አለባቸው።

8) በልዩ ሁኔታ የተፈፀመው የግዥ ውሳኔ እና ሂደት በባለስልጣን መ/ቤቱ እና በሌሎች ተቆጣጣሪ ተቋማት ኦዲት ይደረጋል ።

ምዕራፍ አምስት

የግዥ ስልቶች

72. <u>የግዥ ስልት ዓይነቶች</u>

በአዋጁ አንቀጽ 36 (1) መሠረት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እንደ ግዥው ባህሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስልቶች በመጠቀም ግዥመፈጸም ይችላሉ።

ሀ/ ስትራቴጂዊ ግዥ፤

ለ/ በማዕቀፍ የሚፈጸም ግዥ፤

ሐ/ የጋራ ግዥ፤

መ/ በሊዝ ስምምነት የሚፈጸም ግዥ፤

ሠ/ በራስ ኃይል የሚፈጸሙ ሥራዎች ግዥ፤

ረ/ የተርንኪ ግዥ፤

ሰ/ የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ።

4. The evidence must be evaluated in terms of timing, cost, quality, and socio-economic benefit.

5. A copy of the response must be sent to the internal audit unit, and a quarterly performance report submitted to the Authority.

6. Once the regular procurement process has commenced, it shall not be interrupted to request special permission.

7. Risks associated with procurement under special permission must be identified, acknowledged, and assessed.

8. The Authority and other relevant oversight bodies shall audit the decision-making process and execution of procurements conducted under special permission.

CHAPTER FIVE
PROCUREMENT APPROACHES

72. Types of Procurement Approaches

In accordance with Article 36(1) of the Proclamation, depending on the nature of the procurement, Public Bodies may undertake procurement using the following approaches:

a) Strategic Procurement
b) Framework Procurement
c) Joint Procurement
d) Lease Procurement
e) Own Force Account Procurement
f) Turnkey Procurement
g) Electronic Reverse Auction

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ክፍል አንድ

ስትራቴጂያዊ ግዥ

73. የስትራቴጂያዊ ግዥ አፈፃፀም

1) መንግስት ያለበትን ኃላፊነት መወጣት ይረዳል ወይም ለአገሪቱ የተለየ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ በመንግስት የበላይ ኃላፊዎች ሲታመን በሚኒስትሩ ትዕዛዝ መሠረት ስትራቴጂክ ግዥ በማዕከል ሊፈፀም ይችላል።

2) ልዩ ሀገራዊ ጥቅም የሚኖራቸውን ግዥዎች አንዲፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጠብቆ ግዥውን ተፈፃሚ ማድረግ አለበት።

ክፍል ሁለት

በማዕቀፍ የሚፈጸም ግዥ

74. የማዕቀፍ ግዥ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1) የማዕቀፍ ግዥ ዓላማ በዋነኛነት የመንግስት መ/ቤቶች ተከታታይነት ያላቸው ፍላጎቶቻቸውን ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ መ/ቤቶች በተደጋጋሚ የሚፈለጉና በጥቅል ሊፈጸሙ የሚችሉ ተመሳሳይነት ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ከጥራት የሚገኘው ጥቅም ሳይጓደል ከዋጋ የሚገኘውንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ውጤታማ የሆነ ግዥ መፈጸም ነው።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የማዕቀፍ ግዥ አፈጻጸም እስከተቻለ ድረስ የአገር ውስጥ ተጫራቾችን ተሳትፎ በሚያበረታታ ሁኔታና አቅምን ባገናዘበ፣ እንዲሁም በአቅራቢዎች መካከል ሊፈጠር የሚችልን ኢ-ፍትሐዊነትን ሊያስወግድ በሚያስችል መልኩ ሊፈጸም ይገባል።

3) በአዋጁ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚፈጸመው በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ መሆን አለበት ሆኖም የመንግስት መ/ቤቶች ተከታታይነት ያላቸውን ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት አግባብነት ያለውን

SECTION ONE
STRATEGIC PROCUREMENT

73. Execution of Strategic Procurement

1. Strategic procurement may be conducted centrally upon the order of the Minister, where senior government officials determine that it would enable the government to fulfill its responsibilities or yield specific national benefits.

2. Any institution responsible for executing procurements that confer special national benefits shall implement such procurement in accordance with the provisions of the Proclamation and this Directive.

SECTION TWO
FRAMEWORK PROCUREMENT

74. General Provisions of Framework Procurement

1. The primary objective of framework procurement is to conduct efficient and cost-effective procurement, without compromising quality, for goods and services that are required repeatedly or in similar form by multiple Public Bodies and can be procured in bulk.

2. To implement Sub-Article 1 of this Article, the execution of framework procurement shall, to the extent possible, promote the participation of domestic bidders, consider their capacity, and ensure fairness among suppliers.

3. Pursuant to Article 60(7) of the Proclamation, framework agreements shall be established through open tender; however, Public Bodies may use other

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን ተጠቅመው የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ሊፈጽሙ ይችላሉ።

4) የመንግስት መ/ቤት በየጊዜው ተጫራቾችን በማወዳደር ግዥውን መፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የማይኖረው መሆኑን ሲረዳና በተደጋጋሚ ለሚኖረው ተመሳሳይ ፍላጎት በማዕቀፍ ግዥን በማዕከል ለመፈጸም በተቋቋመው መ/ቤት በሚፈጽማቸው ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ መሆናቸውን በማረጋገጥ የዚህን ክፍል አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ተከትሎ እስከ ሁለት ዓመት የሚቆይ በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ሊፈጽም ይችላል።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት መ/ቤቶች በቅድሚያ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ አዋጭነቱ ሲረጋገጥ የቢሮ ኪራይ አገልግሎት ውል እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ የማዕቀፍ ውል ሊፈጽሙ ይችላሉ፣

6) የዕቃና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ግዥ አፈጻጸም አዋጁን እና ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ ለግዥው በሚዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሰነድ እንዲሁም የማዕቀፍ ስምምነትን መሠረት በማድረግ መፈጸም አለበት።

75. የማዕቀፍ ግዥ አፈጻጸም

1) የመንግስት መ/ቤቶች ወይም የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል ለመፈጸም በተቋቋመው የመንግስት መ/ቤት ሊፈጸም የሚፈለገው ግዥ ፍላጎት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከሰት ወይም ትክክለኛውን የፍላጎት መጠን መወሰን የማይቻል ሲሆን ወይም የሚፈጸመው ግዥ የተለየ ባህሪ ያለው ከመሆኑ የተነሳ የመንግስት መ/ቤቱ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚፈጠር ድንገተኛ የግዥ ፍላጎት እንደሚገጥመው ሲያምን ነው።

2) የመንግስት መ/ቤቶች በማዕከል ከሚፈጸመው ማዕቀፍ ግዥ ውጭ የሚኖራቸውን የማዕቀፍ ግዥ ፍላጎት

appropriate procurement methods to satisfy their recurring needs.

4. If a Public Body determines that there is no economic benefit in regularly comparing bidders, and if the required goods or services are not included in the list of items procured centrally under a framework agreement, the Public Body may conduct a framework procurement for up to two years, in accordance with the relevant provisions of this Section.

5. Notwithstanding the provisions of sub Article 4, Public bodies may enter into a framework contract for office rental services for a period of up to five years, after conducting a preliminary feasibility study.

6. The procurement of goods and services through a framework agreement shall be conducted in compliance with the Proclamation, the provisions of this Directive concerning framework procurement, the standard bidding document, and the framework agreement itself.

75. Execution of Framework Procurement

1. Framework procurement may be undertaken by Public Bodies or by centrally established public entities where the procurement involves frequently recurring needs within a specific timeframe; the exact quantity of the requirement cannot be predetermined; or the nature of the procurement is such that the Public Body foresees sudden needs arising within a defined period.

2. Public Bodies shall fulfill their framework procurement needs excluding those handled

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

በማዕቀፍ ስምምነት መሠረት በሚደረግ ውድድር መፈጸም አለባቸው።

3) የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል የሚፈጽመው መ/ቤት እንደ ግዥው ባህሪ፣ ውስብስነት፣ አስቀድሞ ሊገመቱ የሚችሉ ድንገተኛ ፍላጎቶችን፣ አቅርቦቱ በገበያ ላይ የሚገኝበትን ሁኔታ፣ ግዥውን ለመፈጸም ተፈላጊ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ከግምት በማስገባት የማዕቀፍ ስምምነትን መጠቀም አለበት።

centrally through competitive procedures based on framework agreements.

3. The centrally established public body responsible for framework procurement shall apply framework agreements by considering the nature and complexity of the procurement, foreseeable emergency needs, market availability, and the electronic systems required for implementation.

76. በማዕቀፍ ግዥ የሚሳተፉ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1) የማዕቀፍ ግዥን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉት፣

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 59 (3) መሠረት በሁሉም የፌዴራል መስሪያ ቤቶች በተመሳሳይ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ዝርዝር የመወሰን፣ ወቅታዊ የማድረግ፣ እንዲሁም በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ድረ-ገጽ ይፋ የማድረግ፣

ለ/ ውጤታማ የማዕቀፍ ግዥ አፈጻጸም እንዲኖር የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል የሚፈጽመውን መ/ቤት አቅም የመገንባት፣ ሙያዊ ምክር እና ስልጠና የመስጠት፣

ሐ/ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የሚያወጣቸውን የወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃዎችን በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ሲስተም ላይ ተደራሽ የማድረግ፣

መ/ በማዕከል የሚፈጸሙ የማዕቀፍ ግዥዎችን አፈጻጸም በየወቅቱ የመከታተል፣የመቆጣጠርና ድጋፍ የማድረግ፣

ሠ/ የመንግስት መ/ቤቶች ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 59 (3) በሚያወጣው ዝርዝር ውስጥ የሚካተቱ የዕቃዎችና የአገልግሎቶችን ግዥ ፍላጎት ዝርዝር በማዘጋጀት እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥውን ለሚፈጽመው መ/ቤት ስለመላካቸው ቁጥጥር ያደርጋል፣

ረ/ በማዕከል በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጸምባቸው የተለዩ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችን ከባለስልጣኑ ተገቢው ፈቃድ ሳይገኝበሌሎች ተቋማትእንዳይፈጸሙ ይቆጣጠራል፣

76. Duties and Responsibilities of Parties Involved in Framework Procurement

1. The Authority shall:

a) In accordance with Article 59(3) of the Proclamation, determine and periodically update the list of goods and services commonly required by federal entities and publish the list on the government electronic procurement system.
b) Build the capacity of the centrally responsible framework procurement entity and provide technical support and training to ensure effective execution.
c) Make current market prices, as published by the Ethiopian Statistics Service, available through the government electronic system.
d) Regularly monitor, supervise, and support the central execution of framework procurements.
e) Ensure that Public Bodies submit their procurement needs for goods and services, to be included in the centrally managed list per Article 59(3) of the Proclamation, by June 30 each year.
f) Enforce that goods identified for centralized procurement under framework agreements are not procured independently by other institutions without proper authorization.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ሰ/ ለማዕቀፍ ግዥ የሚውል መደበኛ የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት፣

2) የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል ለመፈጸም የተቋቋመው የመንግስት መ/ቤት የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፣

ሀ/ ከዚህ በታች የተመለከቱትን አሰራሮች በመከተል የሁሉንም የመንግስት መ/ቤቶች ፍላጎት በማሰባሰብ የማዕቀፍ ግዥ ዕቅድ የማዘጋጀትና በዚህ መመሪያው በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለባለስልጣኑ እና ለተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች የማሳወቅ፣ እንዲሁም በመንግስት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ስርዓት ይፋ ማድረግ፣

ለ/ ከመንግስት መ/ቤቶች የሚቀርበውን ዝርዝር የግዥ ፍላጎት በግዥው ዓይነት፣ብዛት እና የጥራት ደረጃ የመለየትና የማደራጀት እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት፣

ሐ/ በዓይነት የተለዩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃ በመሰብሰብ አጠቃላይ የግዥውን ግምታዊ የገንዘብ መጠንየመወሰን፣

መ/ የሚፈለጉ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ውድድርን በሚያስፋ እና በተለያየ ደረጃ ያሉ የአገር ውስጥ አቅራቢዎችን እንዲሁም የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማትን አቅም ባገናዘበ መልኩ በሎት መከፋፈል፣ እንዲሁም የጨረታ ውጤቱ ሲታወቅ መመደብ፣

ሠ/ ከተጠቃሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎችና ፍላጎቶችን መሠረት በማድረግ በማዕቀፍ ግዥ ሊፈጸሙ የሚገቡ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በመለየት ባለስልጣኑ በሚያወጣው ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት ማሳወቅ፣

ረ/ በአዋጁ አንቀጽ 59 (3) መሠረት ባለስልጣኑ በሚያወጣቸው የዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር መሠረት የአዋጁንና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተከትሎ የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል የመፈጸም፣

ሰ/ ለየግዥው ዓይነት የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት በማድረግ የግዥውን ዓይነት፣ ግምታዊ መጠን፣ ግዥ የሚፈጸምላቸው የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣ የርክክብ ሁኔታ፣ የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቆይበት ጊዜና ሌሎች የጨረታውን ሁኔታ ሊወስኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ያካተተ የጨረታ ሰነድ የማዘጋጀት እና የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ጨረታውን ማውጣት፣

g) Prepare standard bidding documents for framework procurement.

2. The Public Body responsible for executing central framework procurement shall:

a) Prepare a framework procurement plan by collecting the needs of all Public Bodies, notify the Authority and user entities within the timeframe specified in this Directive, and publish it on the electronic procurement system.

b) Organize detailed procurement needs by type, quantity, and quality in consultation with relevant stakeholders, and prepare comprehensive technical specifications.

c) Estimate the total procurement value based on current market price data.

d) Segment required goods and services into lots to promote competition, support domestic suppliers at different levels, and encourage job creation initiatives.

e) Identify the items to be procured under the framework arrangement based on submissions from user Public Bodies and notify the Authority for inclusion in the official list.

f) In accordance with Article 59(3) of the Proclamation, Conduct the framework procurement centrally in line with the Proclamation and this Directive based on the Authority's official list.

g) Prepare and issue bidding documents that include the procurement type, estimated quantity, user Public Bodies, handover conditions, contract duration, and other tender conditions, using the government electronic procurement system.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2024

ሸ/ የቀረቡትን የመጫረቻ ሰነዶች አግባብነት ባላቸው በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት የመገምገም፣ አሸናፊዎችን የመለየት፣ የማዕቀፍ ውል የመፈጸም እና የተጠቃሚ መ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት መጠንን ከግምት ያስገባ የአቅራቢዎች ምደባ ማከናወን፣

ቀ/ በማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው እና በመንግስት መ/ቤቱ መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ጉዳዩን በውይይት ለመፍታት ጥረት ማድረግ፣

በ/ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት የአሸናፊው ተጫራች ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን የማረጋገጥ፣

ተ/ የመንግስት መ/ቤቶች በሚያቀርቡት ጥያቄ በማዕቀፍ ስምምነቱ መሰረት አቅራቢው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በሌሎች ምክንያቶች አቅርቦቱንመፈጸም ካልቻለ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በአሸናፊነት ከተመረጡት የማዕቀፍ አቅራቢዎች መካከል የአቅራቢዎቹን አቅም እና ጫና በመገምገም የአቅራቢ ለውጥ የማድረግ፣

ቸ/ የማዕቀፍ ስምምነት በወቅቱ የመፈረም፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በወቅቱ የማዕቀፍ ስምምነት መፈረም ካልተቻለ የመንግስት መ/ቤቶች ሥራ እንዳይጓተት የሚኖራቸውን ፍላጎት አግባብነት ባለው የግዥ ዘዴ በራሳቸው ግዥ እንዲፈጽሙ ይሁንታ የመስጠት፣

ኀ/ በኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዥ ሥርዓት በመጠቀም ለተጠቃሚ የመንግሥት መ/ቤቶች የአቅራቢዎች ምደባ ያደርጋል፤

ኘ/ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሠ) መሠረት የማዕቀፍ ስምምነት የፈጸሙ አቅራቢዎችን ዝርዝር እና ለተጠቃሚ መ/ቤቶች የተደረገውን ምደባ የሚያሳይ መረጃ ይፋ ማድረግ እና እንደአስፈላጊነቱ በራሱ ድረ ገጽ ላይ ተደራሽ የማድረግ፣

አ/ የአቅራቢውን የውል አፈጻጸም መከታተል፣ መገምገምና በራሱ ወይም ጥፋት ስለመፈጸሙ ከተጠቃሚ መ/ቤቶች በሚቀርብ መረጃዎች መነሻነት አርምጃ እንዲወሰድ ለባለስልጣኑ የጥፋተኝነት ሪፖርት የማቅረብ፣

ከ/ በውል አፈጻጸም ወቅት ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ ማድረግ፣ የአቅራቢዎችን አፈጻጸም ግምገማ መረጃ ይዞ ለቀጣይ ግዥ ውሳኔ እንደ ግብዓት የመጠቀም፣

h) Evaluate submitted bids in accordance with the Proclamation and this Directive, select successful bidders, execute framework contracts, and allocate suppliers according to the needs of user Public Bodies.

i) Seek to resolve disputes between suppliers and user Public Bodies through discussion.

j) Verify that the winning bid price reflects market value.

k) If a supplier is unable to perform due to force majeure or other valid reasons, assess and authorize the substitution of a supplier from among those selected under the framework agreement.

l) Ensure timely signing of framework agreements; if delayed due to force majeure, authorize user entities to procure independently using appropriate methods.

m) Allocate suppliers to user Public Bodies through the electronic procurement system.

n) Publicize the list of framework suppliers and allocation details on its website. Monitor supplier performance, assess results, and report violations to the Authority based on complaints from Public Bodies or its own findings.

o) Support user Public Bodies in contract administration and incorporate supplier

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ኘ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ ሲጠናቀቅ የውል አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ የውል ማስከበሪያው እንዲለቀቅ የማድረግ::

3) የግዥው ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉባቸው፣

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቶች ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 59 (3) በሚያወጣው ዝርዝር ውስጥ የሚካተቱ የዕቃዎችና የአገልግሎቶችን ግዥ ፍላጎት ዝርዝር እና እንደአግባብነቱ የፍላጎት መግለጫ በማዘጋጀት በየዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥውን ለሚያስፈጽመው መ/ቤት የማቅረብ፣

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) መሠረት የግዥ ፍላጎታቸውንበተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማዕከል ግዥ ለሚፈጽመው ተቋም ያላቀረቡ የመንግሥት መ/ቤቶች በማዕቀፍ ግዥው ተጠቃሚ መሆን የለባቸውም፣

ሐ/ የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል ከሚፈጽመው መ/ቤት በሚላከው የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ከተመደበላቸው አቅራቢ ጋር የተናጠል ውል የመግባት እና ውሉን የማስተዳደር፣

መ/ በማዕቀፍ ውሉ መሠረት በማዕቀፍ ስምምነቱ የተካተቱ ዕቃና አገልግሎቶችን አስቀድሞ የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል ለሚፈጽመው መ/ቤት ባሳወቀው ፍላጎት ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ አቅርቦቶች ብቻ የግዥ ትዕዛዝ መስጠትና አፈጻጸሙን የመከታተል፣

ሠ/ የሚቀርቡ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ጥራት በውሉ መሠረት የቀረቡ መሆኑን በመፈተሽ መረከብና በማዕቀፍ ውሉ መሠረት ክፍያን በወቅቱ የመፈጸም፣

ረ/ የአቅራቢውን የውል አፈጻጸም መከታል፣ መገምገም፣ አቅራቢው እንደውሉ መፈፀም ካልቻለ የመንግስት መ/ቤቱ በውሉና በሌሎች ህጎች መሠረት የሚወስደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፣

performance evaluations into future procurement decisions.

p) Conduct contract performance evaluations upon the completion of framework agreements and facilitate the release of performance securities.

3. User Public Bodies shall:

a) Submit their annual procurement needs for goods and services, along with specifications, to the central procuring entity by July 7, for inclusion in the list per Article 59(3) of the Proclamation.

b) Public Bodies that fail to submit their needs on time shall not benefit from centrally executed framework procurement.

c) Enter into separate contracts with suppliers assigned to them under the framework agreement and administer the contracts accordingly.

d) Issue purchase orders only for items included in their previously submitted needs and in accordance with the framework contract. Inspect and confirm that supplied items meet contract specifications and ensure timely payment.

e) Inspecting and Receiving the quality of goods and services provided, ensuring that they are delivered in accordance with the contract, and making timely payments in accordance with the framework contract.

f) Monitor supplier performance, take corrective measures for

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 4th of June 2024

ሰ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት በማዕቀፍ ስምምነት ውል በመግባት ግዥ መፈጸም የሚችሉት የግዥ ዕቅዳቸውን አስቀድመው የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል ለሚፈጽመው መ/ቤት ያሳወቁ መ/ቤቶች ብቻ ናቸው።

ሸ/ ተጠቃሚ የመንግሥት መ/ቤቶች በማዕቀፍ ስምምነቱ መሠረት የተመደበላቸውን የዕቃ ሞዴልን በመተው በማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ የተካተተ የሌላ ሞዴል ዕቃን ግዥ ትዕዛዝ በመስጠት የዕቃዎች ግዥ መፈጸም ሲፈልጉ በማዕቀፉ ስምምነት ላይ ባለ ዋጋ መሆኑን፣ ለመንግሥት መ/ቤቱ የተሻለ ጥቅምን የሚያስገኝ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም የሞዴል ለውጡ ካልተደረገ ግዥውን ለመፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ ግዥውን በማዕከል በሚፈጽመው አካል ሲረጋገጥ ግዥውን በዚሁ አግባብ መፈፀም ይቻላል፡

:

4) አቅራቢው በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ፣ በማዕቀፍ ስምምነቱ እና ውሉ ላይ ከተቀመጡ ግዴታዎች በተጨማሪ ሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት።

ሀ/ በአቅርቦት ወሰን ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች በውሉ መሠረት የማቅረብ፣

ለ/ በውሉ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር በውሉ መሠረት ለሚቀርቡ ዕቃዎች ለሚደርስባቸው አደጋ የመድን ዋስትና የመስጠት፣

ሐ/ ዕቃዎቹ በውሉ የተመለከተውን የፍላጐት መግለጫ የማያሟሉ ወይም የተበላሹ ወይም የጥራት ጉድለት ያለባቸው ከሆነ ዕቃዎቹን የመቀየር፣

መ/ በውሉ ላይ ከአቅርቦት በኋላ የሚፈጸም የውል ዋስትና ካለ ብልሽቱን የማስተካከል ወይም የመጠገን፣

noncompliance, and report persistent issues to the Authority.

g) Pursuant to sub article 3, letter "a" of this article, only those Public bodies that have notified their procurement plans in advance to the Public bodies that centrally executes framework procurement may make procurements by entering into a framework agreement.

h) If a Public Body seeks to switch procured goods models within the framework agreement, it may do so with the confirmation of the central procuring entity, provided the alternative model is included in the agreement, offers greater benefit, and is essential to the procurement.

4. Suppliers under the framework agreement shall, in addition to obligations under the Proclamation and contract:

a) Deliver all goods and related services in accordance with contract specifications.
b) Provide insurance coverage for delivered goods, unless stated otherwise.
c) Replace, correct, or repair any goods that are defective or do not meet contractual specifications.
d) If the contract includes a post-delivery warranty, the repair or replacement of the defect.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 7th of June 2023

ሠ/ በውሉ ሁኔታ ወይም በግዥ ትዕዛዝ ላይ በተመለከተው ወይም ከግዥ ፈፃሚው አካል በተስማሙበት ቦታ ዕቃዎቹን የማስረከብ።

77. የማዕቀፍ ግዥ ጨረታ ሥነ ሥርዓት

1) የማዕቀፍ ግዥ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን የጨረታ ሥነ-ስርዓቶችን በመደበኛ የጨረታ ሰነድ መሰረት የሚፈፀም ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሁኔታዎች ተከትሎ ተግባራዊ ይደረጋል።

2) የመንግስት መ/ቤቱ ወይም የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል ለመግዛት የተቋቋመው መ/ቤት ለማዕቀፍ ስምምነቱ ውጤታማነት ሲባል እንደ አግባብነቱ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት የኤሌክትሮኒክ የመንግስት የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም የቅድመ ጨረታ ስብሰባ ማድረግ ይገባዋል።

ሀ/ በጨረታ ማስታወቂያው ላይ የቅድመ ስብሰባ እንደሚኖር ማሳወቅ ያለበት ሲሆን ስብሰባው የሚካሄድበትን ቀንና ሰዓት እንዲሁም አድራሻ በጨረታ ሰነዱ ላይ መግለጽ ይኖርበታል።

ለ/ በቅድመ-ጨረታ ስብሰባ ጊዜ ተጫራቾች በተገቢው መንገድ ማስተናገድ እና ለሁሉም ተጫራቾች በስብሰባው የመሳተፍ እኩል ዕድል መስጠት፣ እንዲሁም ስብሰባው በውል አስተዳደር ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችንና የቅድመ ጥንቃቄ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት።

ሐ/ ከቅድመ ስብሰባው በኋላ ተጫራቾች ያሉዋቸውን ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተመለከተው አድራሻ፣ ቀንና ሰዓት መሠረት እንዲያቀርቡ ይጋበዛል።

መ/ ቅድመ ጨረታው ውይይት በቃለ-ጉባኤ ይያዛል፡ ፡ተጫራቾች በውይይቱ ውስጥ የተነሱትን ማብራሪያዎች በጨረታ ማቅረቢያቸው ማካተት ይችሉ ዘንድ የቃለ-ጉባኤው ግልባጭ የጨረታ ሰነዱ በወጣበት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት እና በመ/ቤቱ ድረ ገጽ ላይ መጫን ይኖርበታል።

e) Deliver goods to the specified location, as per contract or purchase order.

77. Tender Procedure for Framework Procurement

1. Framework procurement shall be conducted using the procedures outlined in this Directive and the standard bidding document developed for such procurements. It shall be applied under the following circumstances.
2. The Public Body, or the entity established to conduct central framework procurement, shall organize a pre-bid meeting, where appropriate, to enhance the effectiveness of the framework agreement:

a) The bid invitation shall state that a pre-bid meeting will be held and specify the date, time, and location in the bid documents.

b) Bidders shall be given equal opportunity to participate. Discussions should focus on issues related to contract implementation and matters requiring clarification.

c) After the meeting, bidders may submit written questions and requests for clarification within the timeline and address indicated in the bid data sheet.

d) Minutes of the pre-bid meeting shall be uploaded to the government electronic procurement system and posted on the website of the Public Body for bidders to review and incorporate into their submissions.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

3) የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የጨረታ ግምገማ የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

ሀ/ የጨረታ ግምገማው በዚህ መመሪያ ከተቀመጡ አሰራሮች በተጨማሪ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተከትሎ ይከናወናል፡፡

ለ/ ለውድድር የቀረቡ ተጫራቾች የህጋዊነት፣ ፕሮፌሽናል፣ ቴክኒካልና ፋይናንሻል እና ሌሎች አስፈላጊ ሠነዶች ተሟልተው መቅረባቸውን እና ተቀባይነታቸውን በመመርመር በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች አንፃር ብቁ የሆኑት እና ብቁ ያልሆኑትን ይለያል፡፡

ሐ/ በቴክኒክ ግምገማው ብቁ የሆኑ ተጫራቾች ያቀረቡትን ዋጋ መሠረት ያደረገና ባለስልጣን መ/ቤቱ በሚለያቸው የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር መሠረት የህይወት ዘመን ወጪ ትንተናን ታሳቢ ያደረገ የዋጋ ግምገማ ያደርጋል፡፡ የዋጋ ውድድሩ መካሄድ ያለበት በእያንዳንዱ ዕቃ ዓይነት መሆን አለበት፡፡

መ/ ከጨረታ ዋጋ በተጨማሪ የግዥ ፈፃሚው አካል ሰጨረታ ዋጋ ግምገማ ሌሎች ነጥቦችን ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡ እነዚህ ነጥቦች የአገልግሎቱ ባህርይ፣ አፈፃፀም፣ ቃላቶችና ሁኔታዎች ጋር ሊያያዙ ይችላሉ፡፡ ለግምገማ ጥቅም ላይ የሚውሉት ነጥቦችና የአተገባበር ዘዴዎች በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

4) በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፀውን የማወዳደሪያና የግምገማ መስፈርት በመጠቀም መሠረታዊ ወይም ዝቅተኛ የማወዳደሪያ መስፈርቶችን ካሟሉት መካከል ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች በአሸናፊነት መምረጥ አለበት፡፡

5) የማዕቀፍ ግዥን በማዕከል የሚፈጽመው መ/ቤት የጨረታውን አሸናፊዎች ከመግለጹ አስቀድሞ በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ውል ለመግባት ያላቸውን ብቃትበድህረ ግምገማ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡

6) ከዚህ በላይ ያሉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ መ/ቤቱ አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለጸው ዝርዝር አሰራር መሠረት ከአንድ በላይ የሆኑ አሸናፊዎችን ሊመርጥና የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈጽም የሚችል ሲሆን የጨረታው አሸናፊ የሚመረጠው በእያንዳንዱ ዕቃ ዓይነት ላይ በሚደረግ የዋጋ ውድድር መሠረት መሆን አለበት፡፡

3. Tender evaluations for framework procurements shall include the following:

a) Verification that bidders have submitted all required documents, and assessment of legal, professional, technical, and financial compliance. Bidders shall be categorized as qualified or unqualified based on the criteria set out in the bid document.

b) Price evaluation shall be conducted for technically qualified bidders, taking into account life-cycle cost analysis for items identified by the Authority. Each item shall be evaluated separately.

c) In addition to price, the evaluation may consider service characteristics, performance, and other factors outlined in the bid document, using predefined evaluation methods.

4. The bidder offering the lowest price among those meeting the minimum requirements shall be declared the winner, based on comparison and evaluation criteria stated in the bidding document.

5. Before announcing the award, the Public Body may conduct a post-qualification review to verify that selected bidders are capable of executing the contract.

6. Without prejudice to the above, the Public Body may select multiple suppliers for framework agreements, provided this is stated in advance in the bid documents. Price competition shall be conducted on a per-item basis.

7. The Public Body may request authorized government institutions to inspect and

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

7) የማዕቀፍ ግዥ ለመፈጸም የተቋቋመው መ/ቤት የቴክኒክ ግምገማ በሚደረግበት ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ ለውድድር የቀረቡት ናሙናዎችን ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል ፍተሻ ማስደረግና ተቀባይነት ያለው መሆኑን ማረጋገጫ ማግኘት አለበት።

78. የማዕቀፍ ስምምነት ስለመፈረም

1) የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው መ/ቤት የመንግስት መ/ቤቶችን ወክሎ አጠቃላይ የውል ስምምነት የሚፈጽምሲሆን የጨረታው አሸናፊ የሚመረጠው በእያንዳንዱ ዕቃ ዓይነት ላይ በሚደረግ የዋጋ ውድድር መሠረት ሆኖ የሚከተሉትን ግምት ያስገባ መሆን አለበት፡ :

ሀ/ በውል ስምምነት አስተዳደር ወቅት በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙ የመንግስት መ/ቤቶችን ዝርዝር፣ የማዕቀፍ ስምምነቱን የሚፈርመውን እና የሚያስተዳድረውን አካል እንዲሁም የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢዎች የሚኖራቸውን ኃላፊነት እና ግዴታ፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የግዥ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብ የሚደረግበትን፣ ክፍያ፣ ክትትል እና ግምገማ የሚደረግበትን ስርዓት፣

ሐ/ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የሚፈቱበትን ስርዓት፣

2) ለማዕቀፍ ስምምነት በወጣ ጨረታ አሸናፊ ከሆነው አቅራቢዎች ጋር እስከ ሶስት (3) ዓመታት ሊደርስ የሚችል ውል የሚፈረም ሲሆን የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል የሚከተሉትን እና ሌሎች ሁኔታዎችን በማገናዘብ እንደግዥው ሁኔታ እና እንደአሰፈላጊነቱ ከአንድ በላይ ከሆኑ ፈቃደኛ ተወዳዳሪዎች ጋር በደረጃቸው ቅደም ተከተል መሠረት ተመሳሳይ የሆነ የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈርም ይችላል።

ሀ/ የሚፈለገው የግዥ መጠን እና የተመረጠው አቅራቢ አቅም ከሚፈለገው አቅርቦት ጋር የማይመጣጠን ሲሆን፣ ወይም

ለ/ በገበያው ላይ ያሉ ተመሳሳይ አቅራቢዎች ብዛት ያላቸው ሲሆኑና የግዥ ዕድሉን ለብዙ አቅራቢዎች መስጠት ሲያስፈልግ፣ ወይም

ሐ/ የገበያው ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ በመሆኑ ምክንያት ግዥውን በቀረበው ዋጋ በቶሎ ማጠናቀቅ ሲያስፈልግ፣

certify samples submitted during the technical evaluation, as required.

78. Signing of the Framework Agreement

1. The Public Body established to execute the framework agreement shall enter into a general contract with selected suppliers on behalf of user entities. The framework agreement shall include:

   a) A list of participating Public Bodies, the entity responsible for administering the framework agreement, and the roles and responsibilities of suppliers.
   b) Procedures for issuing purchase orders, delivery modalities, payment terms, and systems for monitoring and evaluation.
   c) Mechanisms for dispute resolution.

2. The framework agreement may be signed for a period of up to three (3) years. The executing Public Body may enter into agreements with more than one bidder in order of ranking, based on the following or similar circumstances:

   a) Where the procurement requirement exceeds the capacity of a single supplier;
   b) Where many qualified suppliers exist and broad participation is desirable;
   c) Where price volatility in the market necessitates swift procurement at the awarded price.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

3) የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው መ/ቤት በአሸናፊው ዋጋ እንዲያቀርቡ በደረጃቸው ቅደም ተከተል ሌሎች ተጫራቾችን ለውል ስምምነት ሲጋብዝ የሚጋብዛቸውን አቅራቢዎች ቁጥር እና የሚያቀርቡትን መጠን/ድርሻ እንደ ግዥው ሁኔታ አይቶ ይወስናል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚፈፀም ውል፣

ሀ/ በአሸናፊ ዋጋ ለማቅረብ ፈቃደኛ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የማዕቀፍ ሥምምነት ይፈርማል፣

ለ/ በንዑስ አንቀጽ(ሀ) አፈጻጸም የአሸናፊው ዋጋ ማለት ልዩ አስተያየት ከመሰጠቱ በፊት ለውድድር ከቀረቡ ተጫራቾች መካከል ያለ ዝቅተኛ ዋጋ ነው፣

ሐ/ አሸናፊው ድርጅት ለውል ስምምነት እና ምርጫ በሚኖራቸው ጉዳዮች ላይ የምርጫ ቅድሚያ እንዲያገኝ ይደረጋል፣

መ/ የተጫራቾች ቁጥር እስካላነሰና በዋናው አሸናፊው ተጫራች ዋጋ ለማቅረብ የተስማሙ ተጫራቾች እስካሉ ድረስ የማዕቀፍ ስምምነቱ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎችን ያካተተ መሆን ያለበት ሲሆን ለጨረታው ዋና አሸናፊ የሚሰጠው ድርሻ ከጠቅላላው የውሉ መጠን 50% (ሃምሳ በመቶ) ማነስ የለበትም። ቀሪው 50% (ሃምሳ በመቶ) በአሸናፊው ተጫራች ዋጋ ለማቅረብ ከተስማሙትና እንደቅደም ተከተላቸው ለተመረጡ አቅራቢዎች የሚከፋፈል ሲሆን ዝቅተኛው ድርሻ ከውሉ ጠቅላላ መጠን ከ5% (አምስት በመቶ)ማነስ የለበትም።

ሠ/ በአሸናፊው ተጫራች ዋጋ ለማቅረብ የተስማሙ ተጫራቾች ቁጥር ከአምስት በታች ከሆነ ለአንደኛው አሸናፊ የሚሰጠው ድርሻ ከውሉ ጠቅላላ መጠን ቢያንስ 60% (ስልሳ በመቶ)ሲሆን ቀሪው ድርሻ ለተቀሩት አቅራቢዎች እንደ የደረጃቸው ይከፋፈላል። ሆኖም ዝቅተኛው ድርሻ ከውሉ ጠቅላላ መጠን ከ5% (አምስት በመቶ)ማነስ የለበትም።

ረ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሠ" የተደነገገው ቢኖርም በአሸናፊው ተጫራች ዋጋ ለማቅረብ የተስማሙ ተጫራቾች የማይገኙ ከሆነ፣ የአሸናፊው ተጫራች ስምምነትን

3. If inviting additional bidders to contract at the awarded price, the Public Body may determine the number of suppliers and the proportion of the total contract to be allocated.

4. The resulting contract shall:

   a) Be signed only with suppliers willing to supply at the winning price;
   b) Define the "winning price" as the lowest price offered before any preferences were applied;
   c) Prioritize the winning bidder in contract allocation;
   d) Include at least five suppliers, where possible. The winning supplier shall receive no less than 50% of the total contract value, and the remainder shall be distributed among other willing suppliers, with no allocation less than 5%;
   e) Where fewer than five suppliers accept the winning price, the winning supplier shall receive at least 60% of the contract value, with the rest distributed accordingly;
   f) If no other suppliers accept the winning price, the entire contract may be awarded to the winning bidder;
   g) If the winning bidder declines to sign, the next lowest bidder may be awarded the contract at the winning price.

5. The contract concluded with suppliers executing a framework agreement may have a duration of up to three years. The

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

በመጠበቅ አሸናፊው ተጫራችጠቅላላ የግዥ ፍላጎቱን በሙሉ ማቅረብ ይችላል።

ሰ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተወዳዳሪ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ሁለተኛ የወጣው ተጫራች የመጀመሪያው አሸናፊ ተወዳድሮ ባሸነፈበት ዋጋ እንዲያቀርብ መደረግ ይኖርበታል።

5) የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈጽሙት አቅራቢዎች ውል እስከሶስት ዓመት ሊቆይ የሚችል ሲሆን አቅራቢዎቹ የማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈርመው አካል የሚያስይዙት የውል ማስከበሪያ የውሉ ጠቅላላ የማቅረቢያ ዋጋ ላይ 3% (ሦስት በመቶ) ድርሻ ብቻ ይሆናል።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አቅራቢዎቹ በማዕቀፍ ግዥ ከሚፈጸምለት መ/ቤቶች ጋር በሚገቡት የተናጠልውል መሠረት በተገባው ውል ልክ10% (አስር በመቶ) የውል ማስከበሪያ ማቅረብ አለባቸው።

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት አቅራቢዎች በማዕከል የማዕቀፍ ስምምነት ሲፈጽሙ ያስያዙት የውል ማስከበሪያ የሚለቀቀው የውል ዘመኑ ሲጠናቀቅ፣ አቅራቢው በማዕቀፍ ስምምነት ዘመኑ የነበረውን የውል አፈጻፀም ሁኔታን በመገምገም እንደ ስምምነቱ የተፈፀመ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት አቅራቢዎች ከመንግሥት መ/ቤቶች ጋር በተናጠል በሚገቡት ውልያስያዙት የውል ማስከበሪያ የሚለቀቀው ከተጠቃሚ መ/ቤቶች ጋር በገቡት ውል መሠረት ሙሉ ለሙሉ ሲያቀርቡ ብቻ ነው።

9) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 የተደነገገውቢኖርም በአቅራቢው ያልተሟላው የውል ግዴታ በመ/ቤቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ተጨማሪ ወጪ እንደማያስከትል እና በአቅራቢው ችልተኝነት ምክንያት የተፈፀመ አለመሆኑ በግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች አጽዳቂ ኮሚቴ ሲታመንበት የውል ማስከበሪያው ለአቅራቢው ሊመለስለት ይችላል።

10) የማዕቀፍ ስምምት ግዥ የሚፈጽመው መ/ቤት ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የማዕቀፍ ስምምቱን ሊቋረጥ ይችላል።

ሀ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በውሉ መሠረት ግዴታውን አለመወጣቱ ሲታወቅ፣

contract security to be retained by such suppliers for the party signing the framework agreement shall be limited to three percent (3%) of the total contract value.

6. Without prejudice to Sub-Article 5 of this Article, suppliers shall provide a contract security amounting to ten percent (10%) of the contract value for each individual contract entered into with the procuring institutions implementing the framework agreement.

7. The contract security retained under Sub-Article 5 of this Article shall only be released upon the expiration of the contract term, and only after the supplier has evaluated the performance of the contract during the term of the framework agreement and confirmed that the obligations were fulfilled in accordance with the agreement.

8. The contract security retained under individual contracts concluded with government institutions pursuant to Sub-Article 6 of this Article shall only be released upon full and satisfactory delivery in accordance with the respective individual contract entered into with the user institutions.

9. Notwithstanding the provisions of Sub-Articles 7 and 8 of this Article, the contract security may be released to the supplier if the Procurement and Property Disposal Endorsing Committee determines that the supplier's failure to fulfill contractual obligations will not result in any damage or additional cost to the public institution and that the failure did not result from the supplier's negligence.

10. The framework agreement may be terminated under the following conditions:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ለ/ የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎት በግልጽና በታወቀ ምክንያት ሲለወጥ፣

ሐ/ የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ዋጋ፣ ሌሎች ሁኔታዎች እንዲሁም የገበያው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የመንግስት መ/ቤቶችን ሊጎዳ የሚችል ሰፊ ልዩነት መኖሩ ሲረጋገጥ፣

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ "ለ"እና "ሐ" መሠረት የማዕቀፍ ስምምነት እንዲቋረጥ ሲወሰን፣ የማዕቀፍ ስምምቱ የሚቋረጥበትን ምክንያት እና ተፈፃሚ የሚሆንበትን የአንድ ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፣

ሠ/ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያው ጊዜ እስከሚጠናቀቅ በውሉ ላይ የተገለጹት መ/ቤቶች ግዥያቸውን ከሌላ አቅራቢ መፈፀም አይችሉም።

79. የማዕቀፍ ውል ስለመፈረም

1) የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ከተቋቋመው አካል ጋር በመመካከር ከአቅራቢው ጋር እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ የተናጠል ውል መፈረም እና ማስተዳደር አለባቸው።

2) የመንግስት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ስምምት ግዥ እንዲፈጽም ከተቋቋመው አካል የተላለፈላቸውን የማዕቀፍ ስምምት ቅጂን በመጠቀም በስምምነቱላይ የተገለጹትን አቅርቦቶች ለመግዛት የሚያስችል የተናጠል ውል በመፈረም የግዥ ትዕዛዝ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ያስተላልፋሉ።

3) የግዥ ትዕዛዙ ወይም አቅራቢዎች ከመ/ቤቶች ጋር የገቡት የተናጠል ውል በአጠቃለይ ውሉ ውስጥ የተካተቱ መሰረታዊ የሆኑ የነጠላ ዋጋ እና ሌሎች የውል ሁኔታዎችን አይለውጥም፣ ሆኖም የመንግስት መ/ቤቱ በሚከተሉት እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ጋር የተናጠል ውል ሊፈፅም ይችላል፡

ሀ/ ዕቃው የሚቀርብበትን እና ክፍያ የሚፈፀምበትን ጊዜ ፣

ለ/ በአንድ የግዥ ትዕዛዝ የሚቀርበውን ዕቃ ብዛት ፣

a) Where the supplier has failed to meet contractual obligations;

b) Where the procurement needs of user entities have materially changed;

c) Where there is a substantial market or price shift that could adversely affect Public Bodies;

d) In the event of termination, the supplier shall be notified of the reason and given one month's notice;

e) Until the notice period expires, user Public Bodies may not procure the same goods from other suppliers.

79. Signing of the Framework Contract

1. In accordance with Article 60(5) of the Proclamation, user Public Bodies shall consult the central executing body and enter into separate contracts with suppliers for a duration not exceeding one year.
2. Using the framework agreement provided to them, Public Bodies shall sign individual contracts and issue purchase orders for the goods specified.
3. The purchase order or contract shall not alter base prices or terms but may address:

   a) Delivery schedules and payment timelines;

   b) Quantity per purchase order;

   c) Delivery location and other relevant details.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ሐ/ ዕቃው የሚቀርብበትን ቦታ እና እንዳስፈላጊነቱ ሌሎችን፤

4) መ/ቤቱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 በተገለፀው መሰረት የፈፀመውን የተናጠል ውል ቅጅ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም እንዲያስተዳድር ለተቋቋመው ተቋም መስጠት አለበት።

5) በማዕቀፍ ስምምነት አፈጻጸም ወቅት የመንግስት መ/ቤቶች የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ይኖርባቸዋል፦

ሀ/ የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጡት በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ለፈፀመው ተቋም የገለፁትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ግዥው በማዕቀፍ ስምምት የተፈፀመውን ዕቃ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ፤

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ ውስጥ የተገለፁ በመንግስት መ/ቤቶች የሚፈፀሙ ግዴታዎች በስምምነቱ መሠረት የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ፤

ሐ/ በውሉ ላይ የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮችን የማዕቀፍ ስምምነት ከሚያስተዳድረው አካል ጋር በጋራ በመሆን ለመፍታት ጥረት ማድረግ፤

መ/ የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በዋና ዋና የውል ጉዳዮች ማለትም ዕቃ ጥራት እና መጠን ማጓደል የማቅረቢያ ጊዜ አለመጠበቅ፤ በአስተሻሸግ እና በመሳሰሉት የፈፀማቸውን ጥፋቶች የማዕቀፍ ስምምነቱን እንዲያስተዳድር ላቋቋመው አካል በወቅቱ ማሳወቅ፤

ሠ/ በማዕቀፍ ስምምነት ለተካተቱ ፍላጎቶቻቸው የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጡበትን ጊዜ እና እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉትን የአቅርቦት መጠን መወሰንና ስለዝርዝር አፈጻጸሙ ግዥ የሚፈጽመውን አካል ማማከር፤

6) በማዕቀፍ ግዥ ወቅት የሚደረግ ማሻሻያ በአዋጁና በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሰረት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን፤ መሰረታዊና ዝቅተኛ የጥራት መስፈርቱን እስካሟላ እና ተያያዥ የዋጋ ጭማሪ እስካላስከተለ ድረስ እንደሁኔታው በቴክኖሎጂ ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ የምርት ለውጦችን ተቀብሎ ማስተናገድ ይቻላል።

7) የመንግስት መስሪያ ቤቶች የአቅራቢውን የውል አፈፃፀም በመገምገም የሚቀጥለውን የማዕቀፍ ውል

4. A copy of each contract signed by a Public Body shall be submitted to the central executing institution.

5. During implementation, Public Bodies shall:

a) Ensure orders correspond to their pre-submitted needs and include only items covered by the framework agreement;

b) Fulfill their obligations under the agreement;

c) Resolve disputes with supplier support from the central entity;

d) Promptly report supplier defaults to the central entity, particularly regarding product quality, delivery times, and packaging;

e) Plan the timing and quantity of orders and consult the central body for coordination.

6. Amendments shall comply with the Proclamation and this Directive. Technological variations are acceptable if they meet minimum standards and do not increase costs.

7. Public Bodies shall evaluate supplier performance before signing any new framework contracts.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ከመፈረማቸው በፊት በማዕከል ግዥውን ለሚፈጽመው ተቋም ማሳወቅ አለባቸው።

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 በተገለጸው መሠረት መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ለሚኖረው ተመሳሳይ ፍላጎት የሚከተሉትን ሁኔታዎች መከተል ይኖርበታል፦

ሀ/ የሚያካሄደው ጨረታ በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጠውን ስርዓት መከተል አለበት፤

ለ/ የሚፈርመው ውል ከሁለት ዓመታት በላይ የቆይታ ጊዜ ሊኖረው አይገባም፤ ሆኖም ከጊዜ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች አንጻር ለመ/ቤቱ የተሻለ ጠቀሜታ እንዳለው አስቀድሞ በሚደረግ የአዋጭነት ዳሰሳ ጥናት ሲረጋገጥ የቢሮ እና የመጋዘን ኪራይ አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ ውል አስከ አምስት ዓመታት ሊቆይ ይችላል።

ሐ/ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ የዋጋ ማስተካከያ ድንጋጌዎችን የተከተለ የዋጋ ማስተካከያ ሊፈቅድ እና በተፈቀደው የአፈፃፀም ስርዓት መሠረት ሊፈጽም ይችላል።

ክፍል ሦስት
የጋራ ግዥ

80. የጋራ ግዥ ቅድመ-ሁኔታዎች

1) ግዥውን በጋራ መፈጸም የሚፈልጉት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑት መስሪያ ቤቶች መሆን አለባቸው።
2) በዚህ አቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚፈጸመው ግዥ ባለስልጣኑ በማዕከል ግዥውን እንዲፈጸም ዝርዝራቸውን የሚወሰኑ ዕቃዎችን መሆን የለበትም።
3) ግዥው የሚፈጸመው መንግስት ተቋማት የጋራ ፍላጎታቸውን ለማሟላት መሆን አለበት።
4) ግዥውን በጋራ ለመፈጸም የሚፈልጉት መስሪያ ቤቶች በመጀመሪያ ሁሉንም ወክሎ ግዥውን ሊፈጽም የሚችለውን መስሪያ ቤት በመምረጥ የጋራ የስምምነት ሰነድ አዘጋጅተው መፈራረም አለባቸው።
5) የጋራ ስምምነት ሰነዱ የጋራ ግዥውን ያስፈለገበት ምክንያት እና ዓላማውን፣ በጋራ ግዥው ላይ ተሳታፊ

8. For recurring needs:

a) Procurement must follow this Directive;

b) Contracts shall not exceed two years, except for office or warehouse rentals, which may extend to five years if supported by a prior feasibility study;

c) Price adjustments are allowed as per the provisions in this Directive and shall follow approved procedures.

SECTION THREE
JOINT PROCUREMENT

80. Prerequisites for Joint Procurement

1. Joint procurement shall involve two or more Public Bodies.
2. The goods to be procured shall not include items designated by the Authority as centrally procured.
3. The purpose of the procurement shall be to meet the common needs of the participating Public Bodies.
4. Participating Public Bodies shall designate a lead entity to represent them and shall jointly prepare and sign a Memorandum of Understanding.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

የሚሆኑት መስሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ ሊገዛ የታሰበው የግዥ ዓይነት በስም፣ መጠን፣ የጨረታ ሰነድ ማን ማዘጋጀት እንዳለበት፣ የጨረታ አካሄድና የውል አፈጻጸምን በተመለከተ ያካተተ መሆን አለበት።

6) ከጋራ ግዥው አሸናፊ ተጫራች ጋር ውል እያንዳንዱ መስሪያ ቤት በተናጠል መፈጸም የሚችል መሆን አለበት፣

7) ከጋራ ግዥው የሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፣ ተመጣጣኝ ዋጋ፣ ጨረታው በተናጠል ቢደረግ ሊያስወጣው የነበረውን የጨረታ ማስኬጃ ወጪዎች ላይ የሚያስገኘው ቅናሽ፣ ግዥውን በተሻለ የሰው ሀይልና ባለሙያዎች ለመፈጸም ያለው ዕድል፣ ግዥው በጋራ ከመፈጸሙ ጋር በተያያዘ ከዋጋ አንጻር ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም በቅድሚያ ማረጋገጥ አለባቸው ።

8) ሊፈጸም የታሰበው ግዥ በእያንዳንዱ መንግስት መስሪያ ቤቶች ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ውስጥ የተካተተ መሆን አለበት፣

9) እያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት በጨረታው ሂደት ላይ ያለው የሥራ ድርሻ፣ በጥምረቱ ላይ ያለው ሚና ሙሉ ተሳትፎ ወይም በከፊል የሚለው ይወሰናል፣

10) የጋራ ስምምነቱ የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ግዥ ብቻ ይሆናል፣

11) በጋራ ግዥ የዕቃእና ሌሎች ከምክር ውጪ አገልግሎቶችን በጋራ ለመፈጸም የሚያስችል ሁኔታዎች ሲኖሩ።

81. <u>የጋራ ግዥ አፈፃፀም</u>

1) የጋራ ግዥውን እንዲመራ የሚመረጠው መስሪያ ቤት ኃላፊነት ወስዶ በጋራ ግዥ ከሚፈጽሙ መስሪያ ቤቶች የግዥ ፍላጎታቸውን በአጭር ቀናት ውስጥ ይሰበስባል፣

2) የጨረታ ሰነድ የማዘጋጀት ሥራን በተናጠል ወይም በጋራ ይዘጋጃል፣ ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶች መሪ የሆነው መስሪያ ቤት ረቂቅ የጨረታ ሰነድ አዘጋጅቶ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደርጋል፣ የመጨረሻውን

5. The Memorandum of Understanding shall include: the rationale and objective of the joint procurement; the list of participating Public Bodies; the name and quantity of items to be procured; the responsible party for preparing the bidding document; the tendering process; and contract execution procedures.

6. Each participating Public Body may sign a separate contract with the successful bidder.

7. The participating entities shall assess in advance the economic benefits of the joint procurement, including cost savings, efficiency, reduced transaction costs, better utilization of qualified personnel, and potential price advantages resulting from economies of scale.

8. The intended procurement must be included in the annual procurement plan of each participating Public Body.

9. The role and level of participation (full or partial) of each Public Body in the tender process shall be defined.

10. The Memorandum of Understanding shall apply only to the specific procurement in question.

11. Joint procurement may be applied where conditions allow for joint execution of works, goods, consultancy, or non-consultancy services.

81. Execution of Joint Procurement

1. The designated lead Public Body shall be responsible for promptly consolidating the procurement needs of all participating entities.

2. The bidding documents may be prepared separately or jointly. The lead Public Body shall draft the documents, collect comments, finalize the documents, and

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

የጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፣ በጋራ የተስማሙበትን የጨረታ ሰነድ በጥምረቱ መ/ቤቶች አጽዳቂ ያጸድቃል፣ የጨረታ ጥሪው እና የጨረታ ግምገማው መሪ በሆነው መ/ቤት ወይም ግዥውን በሚፈጽሙ አባላት መሰሪያ ቤት ከሚውጣጡ ባለሙያዎች ሊሆን ይችላል፣

3) የጨረታ ሂደቱ ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈቀደውን አካሄድ ይከተላል፣

4) አሸናፊ ድርጅቱ ከመስሪያ ቤቶች ጋር የተናጠል ውል ይፈራረማል፣

5) የውል ማስከበሪያ እና ከውል ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ቀደም ተብለው በጋራ ስምምነቱ ላይ ተጣማሪ መስሪያ ቤቶቹ በተስማሙበት አግባብ ይመራል፣

6) የአሸናፊ ተጫራቹ ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን የማጣራት እና ግዥው ካለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር ተገምግሞ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ መቅረብ ይኖርበታል፤

7) ተጨማሪ ግዥ መፈጸም የሚቻለው በመመሪያ ለተጨማሪ ግዥ የተቀመጠውን ቅድመ-ሁኔታዎችና መጠን ሲያሟላ ብቻ ነው፣

8) ይህ የግዥ ሥልት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ተከትሎ ሊፈጸም ይገባል።

ክፍል አራት

በሊዝ ስምምነት የሚፈፀም ግዥ

82. በሊዝ ስምምነት የሚፈፀም ግዥ አፈፃፀም

1) መንግስት መ/ቤቶች በሊዝ ስምምነት የሚፈጽሟቸው የኪራይ ውሎች ወጪ ሊቆጥቡ የሚችሉ፣ተለዋዋጭነት እና የቅርብ ጊዜ ቴክኖሎጂን ጠቀሜታ ሊያስገኙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

secure their endorsement by the endorsement committee representing all participants. Tender announcements and evaluations may be conducted by professionals drawn from the lead or member entities.

3. The procurement shall follow the procedure applicable to national open tendering.

4. Each participating Public Body shall enter into a separate contract with the successful bidder.

5. Performance security and related contractual matters shall be governed as agreed in the Memorandum of Understanding.

6. The price offered by the winning bidder shall be verified against market prices, and a report on the economic benefit of the procurement shall be submitted to the Authority.

7. Additional procurement may be undertaken only if it meets the criteria and volume thresholds for such procurements as defined in this Directive.

8. The procurement process shall be conducted using the government's electronic procurement system.

SECTION FOUR
PROCUREMENT BY LEASE AGREEMENT

82. Execution of Procurement Through a Lease Agreement

1. Public Bodies shall ensure that lease agreements are cost-effective, flexible, and allow access to up-to-date technologies.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

2) የመንግስት መ/ቤቶች በሊዝ ስምምነት የሚፈጽሟቸው ግዥዎች ንብረቱን በግዥ ከማሟላት ከወጪ ቆጠቢነት፣ ከአሰራር መስፈርትና ከቴክኖሎጂ ዕድገቶች አንጻር ጠቀሜታ እንደሚያስገኝ በግልጽ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

3) በሊዝ ስምምነት ውድድሩ የሚሳተፉ ተጫራቾችን ብቃት፣ ልምድ፣ የገበያ ዋጋ እና የጨረታ ሂደት በፍትሀዊነት ጠንካራ የቴክኒካል ኮሚቴ በማቋቋም ይገመግማል።

4) የሊዝ ኪራይ ውሉ የሊዙን ጊዜ፣ የሊዝ ክፍያ፣ የጥገና ሥራው በማን እንደሚከናወን፣ የጥገና ኃላፊነቶች፣ የኢንሹራንስ ሽፋን፣ አለመግባባት የሚፈታበት ዘዴን እንዲሁም ውሉ ስለሚቋረጥበት አጠቃላይ ሁኔታ ያካተተ መሆን አለበት።

5) የሊዝ ስምምነት ግዥ በዚህ መመሪያ ምዕራፍ ሰባት ስር የተዘረዘሩትን የጨረታ ሥነ ስርዓቶችንና ለእያንዳንዱ የግዥ ዘዴ የተቀመጠውን የገንዘብ ጣሪያ ገደብ ተከትሎ መሆን አለበት።

ክፍል አምስት
በራስ ኃይል የሚከናወን ሥራ

83. በራስ ኃይል የሚከናወን ሥራ ግዥ አፈፃፀም

1) የመንግስት መ/ቤት የራሱን የሰው ኃይልና መሣሪያ በመጠቀም ያለ ጨረታ ሂደት በራሱ ግንባታን ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚያከናውንበት የግዥ ስልት ሲሆን በዚህ ስልት ግዥ መፈፀም የሚቻለው ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲሟላ ነው።

ሀ/ ሊሰሩ የታሰቡት የግንባታ ሥራዎች ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ትንንሽና ተበታትነው የሚገኙ ወይም ውስብስብነት ያላቸውና በተለያዩ ምክንያቶች ሌሎች መሳተፍ በማይፈልጉባቸው ወይም ጨረታ በተደጋጋሚ ወጥቶ ተወዳዳሪ የጠፋበት ወይምሩቅ ቦታ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ምክንያት በተመጣጣኝ ዋጋ ሊሰሩ የሚችሉ

2. Public Bodies shall verify that lease-based procurements are more beneficial in terms of cost, operational efficiency, and technological advancement than direct purchases.

3. A competent technical committee shall be established to fairly evaluate the capacity, experience, market price, and bidding process of suppliers participating in lease tenders.

4. Lease agreements shall include the lease duration, lease payments, maintenance responsibilities, insurance, dispute resolution mechanisms, and conditions for contract termination.

5. Lease procurements shall follow the tender procedures outlined in Chapter Seven of this Directive and adhere to the thresholds established for each procurement method.

SECTION FIVE
FORCE ACCOUNT PROCUREMENT

83. Execution of Force Account

1. Force Account refers to procurement undertaken directly by a Public Body using its own personnel and equipment, without a competitive tender process. This method may be used only under the following conditions:

a) The intended works or services are small, scattered, or technically complex, deterring market interest; or repeated tenders have failed to attract bidders; or the works are in remote locations where capable

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2026

providers are unavailable at reasonable prices.

b) The equipment needed for the construction work may be owned or leased.

c) The scope of the work is limited to maintenance or minor tasks.

d) The contract has been terminated, and the Public Body assumes the responsibility for completing the work due to the supplier's failure.

e) Urgent works are required due to unforeseen accidents or emergencies.

2. Force Account may be used only for small-scale, urgent, or technically specific works, or where engaging contractors is impractical or uneconomical.

3. The Public Body must verify that the remaining works do not require specialized expertise and pose no risk to quality.

4. Force Account may be used only if it is more cost-effective than external contracting and the required skills and resources are available in-house. It shall not be used for large projects where competitive tendering is required to ensure value for money.

5. Prior to commencing works, the Public Body shall prepare a detailed plan outlining the scope, timeline, and implementation

ብቃቱና ልምዱ ያላቸው ድርጅቶች በጨረታው ሲሳተፉ አይችሉም ተብሎ ሲገመት፣

ለ/ ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልገው መሣሪያ በመ/ቤቱ ባለቤትነት ሥር ወይም በኪራይ የሚገኝ ሊሆን ይችላል፣

ሐ/ የሥራው ወሰን ለጥገና እና ለሌሎች አነስተኛ ተግባራት ብቻ ሲሆን፣

መ/ የውሉ መቋረጥ ሊቀር የማይችል መሆኑ በመስሪያ ቤቱ ሲረጋገጥ እና የሥራው ወይም አገልግሎቱ መቋረጡ የሚያደርሰውየሥጋት አደጋ ከአቅራቢው ይልቅ የመንግስት መ/ቤቱ ኃላፊነት ነው ተብሎ ሲገመት፣ ወይም

ሠ/ አስቸኳይ የግንባታ ሥራዎችን የሚሹ ድንገተኛ አደጋዎች ሲከሰቱ።

2) የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በራስ ኃይል የግዥ ዘዴን ሊጠቀሙ የሚችሉት ለአነስተኛ፣ አስቸኳይ ወይም በቴክኒክ ልዩ ለሆኑ ሥራዎች ወይም ሥራ ተቋራጮችን ማሳተፍ ተግባራዊ በማይሆን ወይም ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ ሁኔታ ላይ ብቻ ነው።

3) ቀሪ የግንባታ ሥራዎቹ የተለየ ልምድ እና አቅም የማይጠይቁ አለመሆናቸውን እንዲሁም የግንባታ ሥራው ላይ የጥራት ችግር ሊያጋጥም እንደማይችል ሲረጋገጥ በራስ ሀይል ግዥን ሊፈጽሙ ይችላል።

4) የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በራስ ኃይል ለመጠቀም የሚወጣው ወጪ ከሥራ ተቋራጮች ቢገዛ ያነሰ ዋጋ ያለው ከሆነ፣ ለሥራው ባህሪ የሚፈለገው ዕውቀት ወይም መሳሪያ በመ/ቤቱ የሚገኝከሆነ ብቻ ነው። ሆኖም ግዥውን ውድድር በማከናወን መፈጸም ገንዘብ ማስገኘት የሚችለውን የተሻለ ዋጋን ለማረጋገጥ አስፈላጊ በሚሆንባቸው ትላልቅ ስራዎች ወይም ፕሮጀክቶች ላይ በራስ ኃይል የሚፈጸም የግዥ ስልት ጥቅም ላይ ማዋል አይቻልም።

5) በራስ ኃይል የሚከናወን ሥራ ከመጀመሩ በፊት የመንግስት መ/ቤቶች የሥራውን ወሰን፣ የጊዜ ገደብ እና የአሰራር ዘዴን የሚገልጽ ዝርዝር የሥራ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስ እና የመሳሪያ አጠቃቀምን ጨምሮ አጠቃላይ ወጪውን መገመት፣ እና

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

ለአፈፃፀም የሚያስፈልጉ ሰራተኞች፣ መሣሪያዎች እና ሌሎች መገልገያዎች መግለጽ አለባቸው።

6) ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ሁሉም ሀብቶች፣ ሰራተኞች፣ መሳሪያዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶችን በስራው ዕቅድ መሰረት መመደብ አለባቸው።

7) የመንግስት መሥሪያ ቤቱ በራስ ኃይል የሚከናወነውን ሥራ የሚቆጣጠር የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ይሾማል።

8) በዚህ አንቀጽ መሰረት በራስ ኃይል በሚፈፀም ግዥ የሚከፈለው ክፍያ የሙያ ስምምነት ውልን በመፈረም፣ የመስሪያ ቤቱን የአሰራር ሥርዓት በመከተል እና ከገበያ ዋጋ በማይበልጥ መልኩ መሆን አለበት።

9) በራስ ኃይል የሚፈጸመው ሥራ ሂደት በየጊዜው ቁጥጥር የሚደረግበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዝርዝር አፈፃፀሙን የሚያሳዩ ሪፖርቶች ለመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ስልጣን ለተሰጠው ተወካይ መቅረብ አለባቸው።የመንግስት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ለሚፈጸም ሥራ የወጪ፣ የሀብት አጠቃቀም እና የስራ ሂደት ዝርዝር መዛግብትን ይይዛል፤ እንዲሁም በሚመለከታቸው የቁጥጥር አካላት እንዲመረመሩ በማድረግ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ አለበት።

10) የመንግስት መ/ቤት በዚህ አንቀጽ መሠረት ግዥ መፈጸም የሚችሉት ይህን ስልት ለመጠቀም የመረጡበትን ምክንያት በማስረዳት ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊ ጥያቄ በማቅረብና ፈቃድ በማግኘት መሆን አለበት።

11) የመንግስት መ/ቤቱ በራስ ሃይል የተከናወነውን የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።

ክፍል ስድስት
የተርንኪ ግዥ

84. የተርንኪ ግዥ አፈፃፀም

1) የመንግስት መ/ቤቶች የአንድ ፕሮጀክት አካል ሆነው ራሳቸውን የቻሉ የተለያዩ ጨረታዎች ሊወጡባቸው የሚችሉ ግዥዎችን አንድ ላይ በማቀናጀት በአንድ ጨረታ መፈፀሙ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ሲያምኑ የተለያዩ

procedures, including cost estimates and required human and material resources.

6. All necessary resources must be allocated in accordance with the work plan.

7. A project manager shall be assigned to oversee the implementation.

8. Payments for Force Account works shall be made under a professional services agreement, in line with internal procedures and at market prices.

9. The work shall be regularly monitored, and implementation reports submitted to the Head of the Public Body or an authorized representative. Detailed records of expenditures and workflow shall be maintained and made available for audit.

10. Force Account procurement shall be carried out only upon written request and approval by the Head of the Public Body.

11. A report on the performance of the Force Account procurement shall be submitted to the Authority.

SECTION SIX
TURNKEY PROCUREMENT

84. Execution of Turnkey Procurement

1. Public Bodies may consolidate various procurement activities under a single contract if they determine that a Turnkey arrangement is beneficial.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ግዥዎችን በአንድ ላይ በማስተሳሰር በተርንኪ ግዥ መፈፀም ይችላሉ።

2) የተርንኪ ግዥን እንደአስፈላጊነቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የግዥ ዓይነቶችን በማቀናጀት መፈፀም ይቻላል።

3) ከግንባታ ሥራ ጋር የተያያዙ ግዥዎች በተርንኪ ደረጃ ሲፈፀሙ የግንባታ ቁጥጥር ሥራው የመንግስት መስሪያ ቤቱ በሚቀጥረው አማካሪ የሚሰራ ሆኖ የተቀናጀ የሥራው አካል መሆን የለበትም።

4) የመንግስት መ/ቤቶች በተርንኪ የግዥ ስልት ተጠቅመው ግዥ ሲፈጽሙ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተፈቀዱ አግባብነት ያላቸውን የግዥ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡

5) የመንግስት መ/ቤቶች የተርንኪ ግዥን መጠቀም የሚችሉት፣

ሀ/ ሥራዎቹ ውስብስብ እና በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊጠናቀቁ የሚችሉ ሆነው በሁለት ደረጃ የግዥ ዘዴ ሊፈጸም የሚችሉ ሲሆን፣

ለ/ የግንባታ ሥራ ወይም ዕቃው የተጨማሪ ትዕዛዝን የማያስተናግድ እና የዋጋ ማስተካከያ የማይጠየቅባቸው ሥራዎች ወይም ዕቃዎች ከሆኑ፣ እና

ሐ/ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተርንኪ ግዥ እንዲውል ያዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ ተጠቅሞ ግዥ መፈጸም መቻሉ ሲረጋገጥ።

ክፍል ሰባት
የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ

85. በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ አፈጻጸም

1) የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ የመንግስት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም በመ/ቤቱ የሚጠየቀውን ዝቅተኛ ፍላጎት ስለማሟላት ብቃት ያላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች በተቀመጠላቸው የተገደበ ጊዜ ውስጥ ተደጋጋሚ በሆነ ሂደት አዲስ ዋጋ ወይም የተሻሻለ ዋጋ እያቀረቡ የሚወዳደሩበትና የኤሌክትሮኒክ ዘዴውን በመጠቀም በመ/ቤቱ የተፈለገውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት በማሟላት የመጨረሻውን ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው

2. Multiple procurement types may be combined as necessary under a Turnkey approach.

3. When Turnkey procurement involves construction, supervision shall be carried out by an independent consultant hired by the Public Body and shall not be part of the Turnkey contract.

4. The Turnkey approach shall be implemented using the relevant procurement methods permitted under the Proclamation and this Directive.

5. Turnkey procurement may be used when:

   a) The project is complex and can be completed within the set timeframe through a two-stage process.
   b) The scope of work or goods is fixed, does not permit variations, and does not require price adjustments.
   c) The standard bidding document prepared by the Authority for Turnkey procurement is applicable.

SECTION SEVEN
ELECTRONIC REVERSE AUCTION

85. Implementation of Electronic Reverse Auction Tender

1. Electronic reverse auction is a procurement method whereby pre-qualified bidders who meet minimum requirements compete electronically by repeatedly lowering their prices within a set time frame. The bidder offering the lowest price, while meeting all

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ የሚመረጥበት አሰራር ነው፡

2) የመንግስት መ/ቤቶች በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ የግዥ ዘዴ በመጠቀም የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ግዥን ለመፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 8 የተቀመጠውን ደንጋጌ የሚያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

3) የመንግስት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ስርዓት በመጠቀም በዚህ የግዥ ስልት ግዥ ለመፈጸም አቅም ያላቸው መሆኑን በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሊረጋገጥ ይህንን የግዥ ስልት መጠቀም ይችላሉ፡፡

4) በዚህ የግዥ ስልት የሚፈጸሙ ግዥዎች የገንዘብ መጠን ጣሪያ በዚህ መመሪያ ለእያንዳንዱ የግዥ ዘዴ ከተቀመጠው መብለጥ የለበትም፡፡

86. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ ሥነ ሥርዓት

1) የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ ሥነ ስርዓት ለዚህ የግዥ ስልት አግባብነት ያላቸውን በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እና በተለይም ከዚህ በታች የተመለከቱትንየተለያዩ አሰራሮችን ይከተላል፡፡

2) የጨረታ ማስታወቂያው የጨረታ ሥነ- ስርዓት ላይ ከተቀመጠው በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት፡፡

ሀ/ በጨረታው ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ ምዘገባ ዝርዝር ላይ መመዝገብ የሚችሉበትን ጊዜ

ለ/ ሊገዛ የታሰበውን ግዥ ዝርዝር ፍላጎት የሚያሳይ ግልጽና የማያሻማ መግለጫ እና እንደሁኔታው የውል ቃላትና ሁኔታዎች፣

ሐ/ የጨረታ መገምገሚያ መስፈርቶችን እና የግምገማውን ሂደት መግለጫ፣

መ/ ተጫራቾች የሰጡትን የመወዳደሪያ ዋጋ መቀነስ እንጂ መጨመር እንደማይችል፣

ሠ/ በዚህ መመሪያ የጨረታ ሥነ-ስርዓት ላይ በተቀመጠው መሰረት የጨረታ መተማመኛ ቅጽ ማቅረብ እንደሚገባ፣ እና

ረ/ ሌሎች በኤሌክትሮኒክስ ልውጥ ጨረታ አፈጻጸም መመሪያ ላይ የሚቀመጡና

technical requirements, shall be awarded the contract.

2. Public Bodies must ensure compliance with Article 36(8) of the Proclamation before using this method.

3. The Head of the Public Body must confirm that the institution has the technical capacity to execute reverse auctions through the electronic system.

4. Procurements using this method shall not exceed the thresholds set in this Directive.

86. Tender Procedure of Electronic Reverse Auction

1. The procedure shall adhere to the provisions of this Directive and the following requirements:

2. The tender notice shall include:

a) The registration deadline for interested bidders.

b) A clear and detailed description of the procurement requirement and contract terms.

c) The evaluation criteria and process.

d) A statement that bid prices may only be reduced.

e) Requirement to submit a bid guarantee in accordance with the tender procedure.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ተጫራቾች ሊያሟሉ የሚገባቸው ተፈላጊ ሁኔታዎች።

f) Other requirements as specified in the reverse auction implementation guidelines.

87. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ አቅራቢዎች ምዝገባ

1) በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ የሚሳተፉ ተጫራቾች ለዚህ ዓለማ አስቀድመው የተመዘገቡ ተጫራቾች ብቻ መሆን አለባቸው።

2) የመንግስት መ/ቤቶች ለዚህ ዓላማ በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ ለተመዘገቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚገልጽ ማረጋገጫ ወዲያውኑ ማስታወቅ አለባቸው።

3) መ/ቤቱ የተመዘገቡ ተጫራቾችን ቁጥር በቂ ውድድርን እንዲኖር ለማድረግ የማያስችል ሆኖ ሲያገኘው ወይም በኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ዘዴው ላይ የተፈጠረው እክል ውድድሩን ለማስኬድ የማያስችል ሆኖ ሲያገኘው እንደአስፈላጊነቱ ጨረታውን ሊያራዝም ወይም ሊያግደው ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

4) መ/ቤቱ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተጫራቾች መመዝገባቸው የኤሌክትሮኒክ ግንኙት ዘዴውን ሊያስተጓጉል እንደሚችል ሲያምን በውድድሩ ሊሳተፉ የሚችሉ የተመዘገቡ ተጫራቾችን ቁጥር ሊገድብ ይችላል። ሆኖም ዝቅተኛው በውድድሩ የሚሳተፉ የተመዘገቡ ተጫራቾች ቁጥር ከአምስት ማነስ የለበትም።

87. Registration of Electronic Reverse Auction Suppliers

1. Only suppliers registered in advance for reverse auctions may participate.
2. Public Bodies shall promptly confirm registration of eligible bidders.
3. If the number of registered bidders is insufficient for fair competition, or if technical issues hinder the auction process, the Public Body may extend, suspend, or cancel the tender.
4. If a large number of participants risks disrupting the electronic process, the Public Body may restrict participation to a minimum of five bidders.

88. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ የግምገማ ሂደት

1) በዚህ መመሪያ የተቀመጡት የጨረታ ሥነ ስርዓት መሠረታዊ አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆነው የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ ግምገማ የሚከተሉትን አሰራሮች መከተል አለበት።

2) የመንግስት መ/ቤቱ በውድድሩ ለሚሳተፉ ተጫራቾች እኩል የመወዳደር እና ዋጋቸውን የማቅረብ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።

3) የጨረታው ግምገማው አስቀድሞ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀው የኤሌክትሮኒክ ስርዓት አማካኝነት በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑ ተጫራቾች ተደራሽ በሆነ መንገድ ይከናወናል።

88. Evaluation Process of Electronic Reverse Auction

1. The evaluation of electronic reverse auction shall follow the procedures outlined below, while adhering to the fundamental bidding procedures set forth in this Directive.
2. The Public Body shall ensure that all participating bidders are provided with equal opportunities to compete and submit their respective prices.
3. The bid evaluation shall be conducted through an electronic system specifically designed for this purpose, in a manner that is accessible to all bidders and based on pre-established evaluation criteria.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

4) ለዋጋ ውድድር የሚመረጡ ተጫራቾች መ/ቤቱ በተፈለገው ዕቃ ወይም አገልግሎት ዘርፍ ብቃት ያላቸውን የጥራት ደረጃውን ስለማሟላታቸው በቅድመ ግምገማ የተለዩ እና የተመዘገቡ ብቻ መሆን አለበት፡፡

5) እያንዳንዱ ተጫራች በጨረታው ሂደት ወቅት የራሱን ደረጃ ከሌላው ተጫራች በአንጻራዊነት በማየት ዋጋውን ለማሻሻል እንዲያስችለው ፈጣን እና ባልተቀራረጠ ሁኔታ መረጃ በኤሌክትሮኒክ ስርዓቱ ሊደርሰው ይገባል፡፡

6) በንዑስ አንቀጽ 3 በተገለጸው ካልሆነ በስተቀር በመንግስት መ/ቤት እና በማንኛውም ተጫራች፣ እንዲሁም በተጫራቾች መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊኖር አይገባም፡፡

7) የመንግስት መ/ቤቱ የውድድሩን ሚስጢራዊነት ለመጠበቅ የማናቸውንም ተጫራች ማንነት በጨረታው ለተሳተፉ ሌሎች ተጫራቾች ማሳወቅ የለበትም፡፡

8) ለጨረታ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

9) መ/ቤቱ ውጤቱን ለተጫራቾች ከማሳወቁ አስቀድሞ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች የጨረታውን ውጤት በዚህ መመሪያ በተቀመጠው የጨረታ ሥነ ስርዓት እና አግባብነት ባለው አሰራር መሠረት ለተጫራቾች ያሳውቃል፡

ምዕራፍ ስድስት

የግንባታ ሥራ ግዥ አፈፃፀም

ክፍል አንድ

ለግንባታ ሥራ ግዥ ብቃት መስፈርቶች

89. የግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መሥፈርት

በዚህ መመሪያ ከተቀመጡት ዝርዝር መስፈርቶች በተጨማሪ፣ የግንባታ ሥራ ግዥ ለመፈጸም በሚወጣ ጨረታ ተጫራቾች የግንባታ ሥራውን መስራት የሚያስችል አቅም ያላቸው መሆኑን

4. Only those bidders who have been pre-qualified by the Public Body as meeting the required standards of quality for the goods or services in question shall be identified and registered to participate in the price competition.

5. Each bidder shall receive timely and continuous access to relevant information via the electronic system to enable them to adjust their bids by comparing their own pricing with those of competing bidders during the auction process.

6. Except as provided under Sub-Article (3), no communication shall occur between the Public Body and any of the participating bidders during the auction process.

7. To maintain the confidentiality and integrity of the auction, the Public Body shall not disclose the identity of any bidder to other bidders participating in the reverse auction.

8. The bidder who submits the lowest bid within the time period allocated for the reverse auction shall be declared the winner of the auction.

9. Prior to notifying the bidders of the final result, the Public Body shall communicate the outcome of the auction to the winning bidder, in accordance with the applicable procedures governing reverse auctions and other relevant provisions of this Directive.

CHAPTER SIX

PROCUREMENT OF CONSTRUCTION WORKS

SECTION ONE

QUALIFICATION CRITERIA FOR THE PROCUREMENT OF CONSTRUCTION WORKS

89. Qualification Criteria for Procurement of Construction Works

In addition to the detailed qualification criteria provided under this Directive, bidders participating in procurement for construction works must meet the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መስፈርቶችን መሟላት ይጠበቅባቸዋል፡ :

90. የሥራ አፈፃፀም ምዘና

1) ግዥ ፈፃሚው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቋራጮች ከዚህ በፊት በያዟቸው ወይም ባስረከቧቸው ሥራዎች ላይ ያላቸውን የሥራ አፈፃፀም መረጃን እንዲያቀርቡ ማድረግ አለባቸው።

2) እነዚህ መረጃዎች ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ ከሆነ የመንግስት መ/ቤቱ በጨረታው ግምገማ ወቅትየተጫራቹን የቀድሞ ሥራዎች በተመለከተ የውል ሰነድን ጨምሮ ሌሎች ሰነዶችን ወይም በአካል በመገኘት ተጨማሪ ማጣራትን ማከናወን እና ማረጋገጥ አለባቸው፡

91. አጠቃላይ ልምድ

1) የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ባለስልጣን በሚሰጠው ደረጃ መሠረት ከደረጃ 6 እስከ 10 ካሉት በስተቀር ሌሎች የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች በስራ ተቋራጭ፣ በሽርክና ማህበር (Joint Venture) ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት በየዘርፉ ለደረጃ 1 እና 2 የአምስት ዓመት ልምድ፣ለደረጃ 3 የሦስት ዓመት ልምድ፣ ለደረጃ 4 እና 5 የሁለት ዓመት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።

2) የውጪ ሀገር ስራ ተቋራጮች በስራ ተቋራጭ፣ በሽርክና ማህበር ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭ ደረጃ በዘርፉ ቢያንስ የ8 ዓመት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።

92. ተዛማጅ የስራ ልምድ

1) የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ባለፉት አስርዓመታት ውስጥ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር በተመሳሳይ ቢያንስ አንድ የግንባታ ስራ በስራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት የሰሩና ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው።

2) የግንባታ ሥራው ግምታዊ ዋጋ ከብር ሦስትቢሊዮን በታች ሊሆንና፣ ስራ ተቋራጮች በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠየቀውን የተዛማጅ ስራ ልምድ ዋጋ በአንድ ኘሮጀክት በሰሩት የስራ ልምድብቻ ማሟላት ካልቻሉ በአጥጋቢ እና

following requirements to demonstrate their capability to execute the proposed works.

90. Performance Evaluation

1. The Procuring Entity shall require contractors to submit information regarding their performance in previously executed or completed construction works.

2. Where such information is sourced from a third party, the Public Body shall verify its authenticity during the tender evaluation process. This includes examining contractual documents related to the contractor's prior projects, conducting supplementary checks, or confirming the information through physical site inspections.

91. General Experience

1. All domestic contractors, other than those classified by the Ethiopian Construction Works Authority under grades 6 through 10, shall meet the following minimum experience requirements: Grade 1 and Grade 2: Five years of relevant experience. Grade 3: Three years of relevant experience. Grade 4 and Grade 5: Two years of relevant experience.

2. Foreign contractors, whether acting as sole contractors, joint venture members, or subcontractors, must have at least eight years of experience in the relevant field.

92. Relevant Work Experience

1. Domestic contractors must have completed, within the past ten years, at least one construction project similar in nature to the proposed works. The contractor must have completed at least 70% of the work in a satisfactory and acceptable manner, either as a sole contractor, joint venture member, or subcontractor.

2. If the estimated value of the construction works is less than three billion Ethiopian

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቁና ሊሰራ ከተፈለገው ስራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሦስትኘሮጀክቶች ዋጋ ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል። ሆኖም የሶስቱኘሮጀክቶች የተናጠል ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የስራ ልምድ ዋጋ ከሲሶ (1/3) በታች መሆን አይኖርበትም።

3) የግንባታ ስራው ግምት ከብር ሦስትቢሊዮን በላይ ሲሆንና፣ ስራ ተቋራጮች በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠየቀውን የተዛማጅ ስራ ልምድ ዋጋ በአንድ ኘሮጀክት በሰሩት የስራ ልምድ ብቻ ማሟላት ካልቻሉ በአጥጋቢ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቁ አራት ኘሮጀክቶች ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል። ሆኖም የአራቱ ኘሮጀክቶች የተናጠል ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የስራ ልምድ ዋጋ ከሩብ(1/4) በታች መሆን አይኖርበትም።

4) የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ በጨረታሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ቢያንስ ሁለት የግንባታ ሥራዎችን በሥራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሰሩ እና ቢያንስ የሥራውን 80% (ሰማኒያ በመቶ) በአስተማማኝ እና በአጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው።

5) ተቋራጩ ያቀረበው የሥራ ልምድ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ወይም በሽርክና ማህበር አባልነት የተገኘ ሲሆን፣ በንዑስ የሥራ ተቋራጭነት የሰራው መጠን ብቻ ወይም በሽርክና ማህበሩ ካለው ድርሻ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ልምድ ብቻ በስራ ልምድነት እንዲያዝለት ይደረጋል፡

6) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተደነገገው የተዛማጅ የሥራ ልምድ መስፈርቶች ከደረጃ 6 እስከ 10 ላሉት ሥራ ተቋራጮች ተፈፃሚ አይሆኑም።

7) ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሥራ ተቋራጩ በሥራ ልምድነት እንዲያዝለት በሚያቀርበው የግንባታ ዋጋ ላይ ማስተካከያ የሚደረገው፣ ጨረታ ከሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን 28 ቀናት በፊት የነበረውን የምንዛሪ ምጣኔን ውሉ በተፈረመበት ጊዜ በነበረው የምንዛሪ ምጣኔ በማካፈል ከተሰላ በኋላ በሚገኘው ውጤት በማባዛት ነው። ማስተካከያው የሚሰላው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚሰጠውን የውጭ አገር ገንዘብ መሸጫ ዋጋ መረጃ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

8) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡

Birr, the contractor may meet the relevant work experience requirement by having completed one similar project. If this is not feasible, experience across three completed projects of similar nature may be submitted, provided the cumulative value is not less than one-third of the required threshold.

3. If the estimated value of the construction works exceeds three billion Ethiopian Birr, the contractor may meet the relevant work experience requirement through one similar project. Alternatively, experience in four completed projects of similar nature may be submitted, with the cumulative value being at least one-fourth of the required threshold.

4. Foreign contractors must have completed at least two similar construction projects within the past ten years. These projects may have been carried out as subcontractors, joint venture members, or secondary contractors, provided that at least 80% of the work was completed reliably and satisfactorily.

5. In cases where relevant work experience is based on subcontracting or joint ventures, only the portion executed directly by the contractor or corresponding to its share in the joint venture shall be considered.

6. The provisions of this Article shall not apply to domestic contractors classified as Grades 6 through 10.

7. For the purposes of tender evaluation, adjustments to project values submitted by contractors as part of their work experience shall be made using the foreign exchange rate prevailing 28 days prior to the tender closing date. The adjustment shall involve dividing the contractual value at the time of agreement by the foreign exchange rate applicable at that time and then multiplying by the prevailing rate. The foreign currency exchange rate published by the National Bank of Ethiopia shall serve as the reference.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ሀ/ "በአጥጋቢ ሁኔታ የተጠናቀቀ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 4 መሠረት እንደቅደም ተከተላቸው የሥራው 70% (ሰባ በመቶ)ወይም 80% (ሰማኒያ በመቶ) እና ከዚያ በላይ የተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ፕሮጀክት ነው።

ለ/ "በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቀ" ማለት በሥራ ተቋራጩ የተሰራው 70%(ሰባ በመቶ) እና ከዚያ በላይ ሥራ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳና የጊዜ ማራዘሚያ እንዲሁም በተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለመሰራቱ ከአሰሪ መ/ቤቱ የተሰጠ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ የቀረበበት የግንባታ ስራ ፕሮጀክት ነው።

93. የፋይናንስ አቋም

1) የስራ ተቋራጮች ያለፉት አምስት ዓመት የፋይናንስ አቋማቸውን የሚያሳይ በተመሰከረለት አዲተር የተረጋገጠ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ከተመሰረተ ከአምስት ዓመት በታች ከሆነው የሚያቀርበው የፋይናንስ ሪፖርት ከንግድ ምዝገባ ሰርተፊኬት ወይም ከንግድ ሥራ ፈቃዱ ጋር የሚናበብ ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል።

3) በስራ ተቋራጮቹ የሚቀርበው የፋይናንስ ሪፖርት ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ወይም የሂሳብ አያያዝ እና አዲት ቦርድ ከሚገኝ ሪከርድ ጋር ተመሳክሮ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል።

94. ዓመታዊ የግብይትመጠን (ተርንኦቨር)

1) የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮችን በተመለከተ ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሚወሰደው በግንባታ ላይ ካለና ከተጠናቀቀ የግንባታ ስራ ላይ የተሰበሰበ ክፍያ ዓመታዊ ተርንኦቨር መካከል ተቋራጩ ባለፉት አምስት ዓመት ውስጥ ካስመዘገበው የግንባታ ስራ ዓመታዊ ተርንኦቨር የተሻለውን በመምረጥ ሆኖ፣ስራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን የሚሰላው ሊሰራ የታሰበውን የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ፣ቀናትን ወደ ሚቀጥለው ሙሉ ወር

8. For the implementation of this Article:

a) "Substantially Completed" means a project in which at least 70% (for domestic contractors) or 80% (for foreign contractors) of the work has been completed in accordance with the prescribed project plan.

b) "Satisfactorily Completed" means a project in which at least 70% of the works have been executed by the contractor within the agreed schedule, including any approved extensions, and where a certificate of satisfactory completion, payment certificate, or other verifiable documentation from the client confirms that the required quality standards have been achieved.

93. Financial Position

1. Contractors shall submit audited financial statements covering the past five years, certified by a licensed auditor.

2. Notwithstanding Sub-Article 1, local contractors with fewer than five years of operation may submit a financial report accompanied by a valid trade registration certificate or business license.

3. The financial reports submitted shall be cross-verified with records maintained by the relevant tax authority or the Accounting and Auditing Board of Ethiopia.

94. Annual Turnover

1. For domestic contractors, the required annual turnover shall be calculated based on the highest annual turnover achieved from ongoing or completed construction works over the past five years. The required annual turnover is determined by dividing the estimated total project cost by the estimated

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈልና ውጤቱን በ0.6 በማባዛት ነው።

2) ለውጭ ሀገር የስራ ተቋራጮች እና በሽርክና ማህበር ደረጃ ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩት ስራ ተቋራጮች የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር በሚሆኑበት ጊዜ የማባዣ ቁጥር እንደቅደም ተከተላቸው 2 እና 1.2 ይሆናል።

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 አፈፃፀም፤

ሀ/ የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ተፈላጊ ዓመታዊ ተርን ኦቨር = ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ/ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር*12*0.6፤

ለ/ ለውጭ ሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ተፈላጊ ዓመታዊ ተርን ኦቨር = ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ/ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር*12*2፤

ሐ/ በሽርክና ማህበር ደረጃ ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩት ስራ ተቋራጮች የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር በሚሆኑበት ጊዜ ተፈላጊ ዓመታዊ ተርን ኦቨር= ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ/ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር*12*1.2፡

4) በጨረታ ግምገማ ጊዜ ለሚደረግ ማስተካከያ ዓላማ ለተርንኦቨር ስሌት የሚወሰደው ስራ ተቋራጩ ያቀረበው ዓመታዊ የግንባታ ስራ ተርንኦቨር መጠን፣ ጨረታ ከሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን 28 ቀን በፊት የነበረውን የምንዛሪ ምጣኔን በእያንዳንዱ በጀት ዓመት የመጨረሻ ቀን ላይ ባለው የምንዛሪ ምጣኔ በማካፈል ነው። ማስተካከያው የሚሰላው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚሰጠውን የውጭ አገር ገንዘብ መሸጫ ዋጋ መረጃ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

5) ስራ ተቋራጮቹ በሽርክና ማህበር ደረጃ ጥምረት የፈጠሩ ከሆኑ እያንዳንዳቸው የሽርክና ማህበሩ አጋር ድርጅቶች ማሟላት የሚገባቸው የተርንኦቨር መጠን ከተጠየቀው ከ25 በመቶ እና የዋናው ስራ ተቋራጭ ደግሞ ከ40 በመቶ ማነስ የለበትም።

6) የምህንድስና ዋጋ ግምት እና የግንባታው ስራ የሚፈጀውን ጊዜ የመወሰን ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም አካል የምህንድስና ዋጋውን ወይም ስራው የሚፈጀውን ጊዜ ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ያዘጋጀ ስላለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠትና ግምቱም በግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ

completion period (rounded up to the next full month) and multiplying by 0.6.

2. For foreign contractors and joint ventures involving foreign and domestic partners, the multiplier shall be 2 and 1.2, respectively.

3. For the purpose of Sub-Articles 1 and 2:

a) Required Annual Turnover for Domestic Contractors = (Estimated Cost / Estimated Completion Time in Months) × 12 × 0.6

b) Required Annual Turnover for Foreign Contractors = (Estimated Cost / Estimated Completion Time in Months) × 12 × 2

c) Required Annual Turnover for Joint Ventures (Domestic & Foreign) = (Estimated Cost / Estimated Completion Time in Months) × 12 × 1.2

4. To account for currency fluctuations, the annual turnover figures submitted by bidders shall be adjusted using the currency exchange rate applicable 28 days prior to the tender submission deadline, based on the selling rate published by the National Bank of Ethiopia.

5. In joint ventures or consortiums: Each partner must contribute at least 25% of the required annual turnover. The lead contractor must meet no less than 40% of the required annual turnover.

6. The entity responsible for preparing the engineering cost estimate and completion timeline shall certify that such estimates are reasonable and not overstated or understated. The estimate shall be reviewed by the procurement endorsing committee

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አዕዳቂ ኮሚቴ መገምገምና በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይኖርበታል፡፡

7) አማካሪው የግንባታ ሥራውን ዲዛይንና የምህንድስና ዋጋ ግምቱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚያዘጋጀው ዲዛይን፣ የሥራ መጠን እና የሥራ ዝርዝር በግንባታ ወቅት በእያንዳንዱ የሥራ መጠን ከተቀመጠው ከ15 በመቶ በላይ ወይም በታች ከሆነ እንዲሁም የማይሰሩ የግንባታ ሥራዎችን ማካተቱ ከተረጋገጠ በመንግስት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሙሉ ኃላፊነት አለበት፡፡

95. በግንባታ ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና ብቃት

1) የሥራ ተቋራጮች የጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለፀው መሠረት እንደ ግንባታ ስራው ባህርይ ብቻለስራው የሚያስፈልጉ ብቁ ባለሙያዎችን በሚፈለገው መጠን እና ስብጥር እንደሚያቀርቡ ማሳየትና ባለሙያዎቹም ለስራው በሚያስፈልጉበት ጊዜ ሁሉ በተመደቡበት ቦታ ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚያመለክት አስተማማኝ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፁት ባለሙያዎች የግንባታ ስራ ተቋራጩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ሰራተኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3) የመንግሥት መ/ቤቶች በዚህ አንቀጽ መሠረት ከሥራ ተቋራጮች የቀረበላቸው በግንባታ ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና ብቃትን የተመለከተውማስረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለፀው መሠረት መሆኑን በግንባታ ጊዜም ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

96. የግንባታ መሳሪያ ማሟላት

1) በስራ ተቋራጮች የጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለፀው መሠረት እንደ ግንባታ ስራው ባህሪ ብቻለስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ዓይነትና መጠን በሚፈለጉበት ጊዜ ሁሉ ማቅረብ እንደሚችሉ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

and approved by the head of the procuring entity.

7. If the design, bill of quantities, and specifications prepared by the consultant during the design and engineering cost estimate of the construction work are found to be 15 percent more or less than the work specified during construction, or if it is proven that they include unfinished construction work, the consultant will be fully liable for the damage caused to the government.

95. Educational Qualification and Competence of Professionals Engaged in Construction Work

1. Contractors must demonstrate, in accordance with the tender document that they have sufficient qualified professionals in the appropriate number and with the requisite expertise for the nature of the construction works. They must also provide credible evidence that such professionals will be available at their designated project sites as required.

2. The professionals may be permanent staff or temporary hires of the contractor.

3. During the construction period, government offices shall verify that the qualifications and competence of the professionals assigned to the project conform to the requirements specified under Sub-Article 1 of this Article.

96. Construction Equipment

1. Contractors shall, as per the bid document, provide evidence of their capacity to supply the necessary construction equipment in the required type and quantity at any time during project execution.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

2) የሚቀርቡት መሳሪያዎችም በስራ ተቋራጮች ባለቤትነት ስር የሚገኙ ወይም በኪራይ የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ።

97. ከአንድ በላይ ንዑሳን የግንባታ ስራዎች በተካተቱበት ግዥ ላይ የልምድ አያያዝ

1) በአንድ የጨረታ ማስታወቂያ የሚወጡ ንዑስ የግንባታ ስራዎች ቁጥር ከአንድ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ማንኛውም ተጫራች መሳተፍ የሚፈልግባቸውን ንዑስ የግንባታ ስራዎች ዓመታዊ ተርንኦቨር፣ የገንዘብ አቅምና ተዛማጅ የስራ ልምድ መስፈርት በድምር ማሟላት አለበት።

2) አንድ ተጫራች ለእያንዳንዱ ንዑስ የግንባታ ስራ የተጠየቀውን መስፈርት አሟልቶ ነገር ግን ለተሳተፈባቸው ንዑስ የግንባታ ስራዎች በድምር የሚጠየቀውን መስፈርት በማያሟላበት ጊዜ ምንም እንኳን በተናጠል ሲታይ ለየንዑስ የግንባታ ስራዎቹ የተሻለ ዋጋ ቢያቀርብም ውል ሊፈጽም የሚችለው መስፈርቶቹን ማሟላት በቻለበት ልክ ብቻ ነው።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለመንግስት መ/ቤቱ የተሻለ ጠቀሜታ ከማስገኘት አንፃር ሥራ ተቋራጩ በሰጠው ዋጋ ውል የሚገባበትን ንዑስ የግንባታ ስራ ወይም የግንባታ ስራዎች የመወሰን ስልጣን የመንግስት መ/ቤቱ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

ለተለያዩ የግንባታ ሥራ አይነቶች የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

98. ለህንፃ ግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

1) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የህንፃ ደረጃ የሚከተሉትን ይይዛል፤

ሀ) ደረጃ "ሀ" "አነስተኛህንጻ (Low-Rise Building)" ማለት ምንም ዓይነት አሳንሰር ወይም አሳንሰርን የሚተካ ከምድር ወደ ፎቅ እንዲሁም ከፎቅ ወደ ምድር

2. The required equipment may be owned by the contractor or leased through valid rental agreements.

97. Consideration of Work Experience in Procurements Involving Multiple Sub-Construction Works

1) When a tender announcement includes multiple sub-construction works, any bidder wishing to participate in any sub construction works that he intended to undertake should fulfill the respective requirements of annual turnover, financial capacity and relevant work experience.

2) A single bidder may meet the requirements for each individual small-scale construction project. However, if the bidder fails to meet the cumulative requirements for all the small-scale construction projects combined, even if they offer a better price for each individual project, the contract can only be awarded to the extent that they fulfill the requirements.

3) Subject to Sub Article 2 of this Article, in order to the Public Body will have the discretion to decide for whom the sub-construction work or construction works will be awarded and contracted with in terms of achieving the advantage of the Public Body.

SECTION TWO
MINIMUM REQUIREMENTS FOR VARIOUS TYPES OF CONSTRUCTION WORKS

98. Minimum Requirements for building Construction Work.

1) For the execution of this article the building standards shall be determined in accordance with the following Criteria:

a) Level 1 "Low-Rise Building" refers to any building that does not include an elevator or equipment facilitating

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

የሚያመላልስ መሳሪያ የሌለው ሆኖ ከምድር በላይ ከአምስት ያነሱ ፎቆች ያለው ነው።

ለ) ደረጃ "ለ" "መካከለኛ ህንጻ (Mid-Rise Building)"ማለት ከምድር በላይ ቢያንስ አምስት ፎቆች ያለው ሆኖ ከአሥራ አምስት ፎቆች በላይ የሌለው ነው።

ሐ) ደረጃ "ሐ" "ከፍተኛህንጻ (High-Rise Building)"ማለት ከምድር በላይ ቢያንስ አሥራ አምስት ፎቆች ያለው ሆኖ ከአርባ አምስት ፎቆች በላይ የሌለው ነው።

መ) ደረጃ "መ" "በጣም ከፍተኛ ህንጻ (Mega-High Rise Building)"ማለት ከምድር በላይ ቢያንስ አርባ አምስት እና ከዚያ በላይ ፎቆች ያለው ነው።

2) ለህንፃ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሰራ ከታሰበው የህንፃ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት።

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈፃፀም ሊሰራ ከታሰበው የህንፃ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ማለት በደረጃ "ሀ" ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ በደረጃ "ለ" ለመካከለኛ ህንፃ ግንባታ ስራ ተቀባይነት ይኖረዋል። በደረጃ "ለ" ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ለደረጃ "ሐ" ግንባታ ስራ ተቀባይነት ይኖረዋል። በደረጃ "ሐ" ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ለደረጃ "መ" ግንባታ ስራ ተቀባይነት ይኖረዋል።

4) ለህንፃ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ሲሆን ሊሰራ ከታሰበየህንፃ ደረጃ ጋር እኩል የሆነ ወይም የበለጠ የህንፃ ስራ ልምድ ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ ለደረጃ "መ"ግንባታ ለመስራት የሚወዳደር የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ያለው ልምድ በማናቸውም ሁኔታ ከምድር በላይ አርባ አምስት /45/ ፎቆች ያሉትን ህንፃ ከመገንባት ያነስ ልምድ ሊሆን አይገባም።

movement between floors, either from ground level to upper floors or vice versa. Additionally, it is defined as a building with fewer than five floors above ground level.

b) Level 2 "Mid-Rise Building" refers to a building with at least five floors above ground level but not exceeding fifteen floors.

c) Level 3 "High-Rise Building" refers to a building with at least fifteen floors above ground level but not exceeding forty-five floors.

d) "Mega-High-Rise Building" refers to a building with at least forty-five floors above ground level and beyond.

2) For construction works, a domestic contractor competing for the project must meet the minimum requirement of having completed construction work that is one grade lower and above the proposed project.

3) For the execution of Sub-Article 2 of this Article, a local contractor with experience in Level "1" construction work is eligible for Level "2" mid-rise building construction projects. Similarly, a contractor with experience in Level "2" construction work is eligible for Level "3" high-rise building construction projects. Furthermore, a contractor with experience in Level "3" construction work is eligible for Level "4" mega-high-rise building construction projects.

4) A foreign contractor participating in the construction works, must have experience in construction work that is equivalent to or exceeds the level of the proposed project. For example, a foreign contractor bidding for Level "4" mega-high-rise building construction must have experience in constructing buildings with at least forty-five floors above ground level. Any experience below this threshold is not acceptable

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

99. ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

1) ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሰራ ከታሰበው የድልድይ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ መሆን አለበት::ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣

   ሀ/ በህንፃ ኘሮጀክቶች ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ በድልድይ ስራ አስተማማኝ የስራ ልምድ ያለው ባለሙያ ያለው መሆኑ እና የመሬት ውስጥ ስራ ልምድ ያለው መሆኑ ተረጋግጦ አጭር ርዝመት ያለው ድልድ ይግንባታ ስራ ላይ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል::

   ለ/ አጭር ርዝመት ባለው ድልድይ ግንባታ ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ መካከለኛ ርዝመት ያለው ድልድይ ግንባታ ስራ ላይ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል::

   ሐ/ መካከለኛ ርዝመት ባለው ድልድይ ግንባታ ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ረጅምርዝመትያለውድልድይግንባታስራላይለመወዳ ደርተቀባይነትይኖረዋል::

2) ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ሲሆን የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ የሚጠየቀው የድልድይ ግንባታ ስራ ልምድ ሊሰራ ከታሰበው የድልድይ ስራ ያነሰ ሊሆን አይገባም::

3) ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ለውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ከሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪ በተወሰነ የድልድይ ዓይነት የድልድይ ግንባታ ስራ ልምድ ሊጠይቅ ይችላል::

4) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም

   ሀ/ "አጭር ርዝመት ያለው ድልድይ "ማለት ለተሽከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱ ከ25 (ሃያ አምስት) ሜትር ያነሰ ድልድይ ነው::

   ለ/ "መካከለኛ ርዝመት ያለው ድልድይ"ማለት ለተሽከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱከ 25 (ሃያ አምስት) ሜትር

99. Minimum Requirement for Bridge Construction Work.

1) For bridge construction work, a domestic contractor competing for the project must meet the minimum requirement of having completed bridge construction work that is one level lower than the proposed project.
   a) A domestic contractor with experience in building construction projects, supported by a professional with verified expertise in bridge construction and underground work, is eligible to compete for short-span bridge construction projects.
   b) A domestic contractor with experience in short-span bridge construction is eligible to compete for medium-span bridge construction projects.
   c) A domestic contractor with experience in medium-span bridge construction is eligible to compete for long-span bridge construction projects.
2) For bridge construction work, a foreign contractor competing for the project must have experience in bridge construction that is at least equivalent to, or exceeds, the level of the proposed project. Experience below the required level is not acceptable.
3) The Procuring Entity may require foreign contractors to have additional experience in bridge construction, specific to a defined type of bridge, beyond the minimum requirements.
4) For the execution of this Article
   a) "Short-Span Bridge" refers to a bridge designed to serve vehicles or other modes of transportation, with a span length of less than 25 meters.
   b) "Medium-Span Bridge" refers to a bridge designed to serve vehicles or other modes of transportation, with a span length of at least 25 meters but not exceeding 50 meters.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 6th of June 2025

የማያንስ እና ከ50 (ሃምሳ) ሜትር የማይበልጥ ድልድይ ነው።

ሐ/ "ረጅም ርዝመት ያለው ድልድይ" ማለት ለተሸከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱ ቢያንስ 50 (ሃምሳ) እና ከዚያ በላይ የሆነ ድልድይ ነው።

c) "Long-Span Bridge" refers to a bridge designed to serve vehicles or other modes of transportation, with a span length of at least 50 meters and beyond.

100. <u>የመንገድ ኘሮጀክቶች አመዳደብ በንጣፍ ዓይነት</u>

የመንገድ ኘሮጀክቶች ግዥ ሲፈፀም የሚከተሉትን አመዳደብ መሰረት በማድረግ መሆን አለበት።

1) አስፋልት ኮንክሪት፣
2) የድርብ እና ባለሶስት አስፋልት ንጣፍ፣ ወይም ደረቅ/አርማታ ንጣፍ፣
3) የጠጠር መንገድ፣
4) ከባድ ጥገና እና የመንገድ መልሶ ግንባታ፣እና
5) መደበኛና ወቅታዊ ጥገና።

100.Classification of Road Projects by Type.

When executing the procurement of road projects, it shall be based on the following classifications.

1) Asphalt Concrete Pavement
2) Double and Triple Surface Treatment or Rigid Pavement
3) Aggregate Surfacing-Gravel
4) Heavy maintenance and Road rehabilitation
5) Routine and Periodic Maintenance

101. ለመንገድ ኘሮጀክቶች የግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

1) ለመንገድ ኘሮጀክቶች የግንባታ ስራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣ ሊሰራ ከታሰበው የመንገድ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል። በመሆኑም፣

ሀ/ በአዲስ የጠጠር መንገድ ግንባታ ስራ ወይም በመንገድ መልሶ ግንባታ ወይም በከባድ የአስፋልት መንገድ ጥገና (Heavy Maintainance) የተገኘ የመንገድ ግንባታ ስራ ልምድ በአስፋልት (asphalt surfacing) ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል።

ለ/ ማንኛውም የአስፋልት ስራ ወይም እንደ አየር መንገድ ያሉ ሌሎች ተመሳሳይ የመንገድ ግንባታ ስራዎች ወይም በመንገድ ደረጃዎች ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ላይ የተገኘ ልምድ ለአስፋልት (asphalt surfacing) ፕሮጀክቶች ተቀባይነት ይኖረዋል።

ሐ/ መደበኛና ወቅታዊ ጥገና (Routine and Periodic Maintenance) የተገኘ የመንገድ ግንባታ ስራ ልምድ የጠጠር መንገድ እና የከባድ መንገድ

101. Minimum Requirements for Road Construction Projects

1) For road construction projects, a domestic contractor competing for the project must have experience in road construction that is one level lower than the proposed project to be eligible.
   a) Experience gained from new gravel road construction, road reconstruction, or heavy maintenance of asphalt roads qualifies a contractor to compete for asphalt surfacing projects.
   b) Experience gained from any asphalt work, similar road construction projects such as airport roads, or road improvement projects qualifies a contractor to compete for asphalt surfacing projects.
   c) Experience gained from routine and periodic maintenance of roads qualifies

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2021

ጥገና (Heavy Maintainance)ግንባታ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል።

መ/ በመደበኛና ወቅታዊ ጥገና (Routine and Periodic Maintenance) ግንባታ ለመወዳደር ገዥው መስሪያ ቤት ሌሎች አነስተኛ ግንባታዎችን በመስፈርትነት ሊወስድ ይችላል።

2) ለመንገድ ኘሮጀክቶች የግንባታ ስራ የሚወዳደረው የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣ የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ሊሰራ ከታሰበው የመንገድ ኘሮጀክት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ወይም የበለጠ የመንገድ ስራ ግንባታ ልምድ ሊኖረው ይገባል። እንዲሁም የሚጠየቀው የገንዘብመጠን በማናቸውም ሁኔታ ሊሰራ በታሰበው የመንገድ ስራ ከተገመተው የገንዘብ መጠንሊያንስ አይገባም።

a contractor to compete for gravel road construction and heavy road maintenance projects.

d) For routine and periodic maintenance projects, the procurement office may include other minor construction works as part of the requirements.

2) For road construction projects, a foreign contractor competing for the project must have experience in road construction that is similar to or exceeds the level of the proposed project. Additionally, the financial capacity required must not be less than the estimated cost of the proposed road construction project under any circumstance.

102. ለግድብ ግንባታ ሥራ እና ለመስኖ ግንባታ ሥራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

1) ለግድብ ግንባታ ሥራ የሚወዳደረውየአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣ የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሰራ ከታሰበው የግድብስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል። በዚህ መሰረት በአነስተኛ የግድብ ሥራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ለመካከለኛ ግድብ ግንባታ ሥራ ተቀባይነት ይኖረዋል።

2) ለመስኖ ግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣ የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሰራ ከታሰበው የመስኖስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል። በዚህ መሰረት በአነስተኛ የመስኖ ዘዴዎች የሥራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ የመስኖ ዘዴዎች ሥራ ተቀባይነት ይኖረዋል።

3) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡

ሀ/ "ትላልቅ ግድብ" ማለት ከ10 ሄክታር እና ከዚያ በላይ የሆነ የውኃ ማጠራቀሚያ ቦታ ያላቸው ግድቦች ናቸው።

102. Minimum Requirements for Dam Construction and Canal Construction Works.

1) For dam construction work, a domestic contractor competing for the project must meet the minimum requirement of having experience in dam construction that is one grade lower than the proposed project. Based on this, a domestic contractor with experience in small-scale dam construction is eligible to compete for medium-scale dam construction projects.

2) For canal construction work, a domestic contractor competing for the project must meet the minimum requirement of having experience in canal construction that is one grade lower than the proposed project. Based on this, a domestic contractor with experience in small-scale canal systems is eligible to compete for medium-scale canal construction projects.

3) For the execution of this Article

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ለ/ "መካከለኛ ግድብ" ማለት ከ3 እስከ 10 ሄክታር የውኃ ማጠራቀሚያ ቦታ ያላቸው ግድቦች ናቸው::

ሐ/ "አነስተኛግድብ" ማለት ከ 3ሄክታር በታች የሆኑ የውኃ ማጠራቀሚያ ቦታ ያላቸው ግድቦች ናቸው::

መ/ "አነስተኛ መስኖ" ማለት ከ200 ሄክታር በታች ቋሚ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ የውሃ መቆጣጠርያ እና ማሰራጫ የመሰረተ ልማት አውታሮች ያሏቸው የመስኖ ሥራዎች ናቸው::

ሠ/ "መካከለኛ መስኖ" ማለት ከ200 እስከ 3,000 ሄክታር ቋሚ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ የውሃ መቆጣጠርያ እና ማሰራጫ የመሰረተ ልማት አውታሮች ያሏቸው የመስኖ ሥራዎች ናቸው::

ረ "መካከለኛ መስኖ" ማለት ከ3,000 ሄክታር በላይ ቋሚ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ የውሃ መቆጣጠርያ እና ማሰራጫ የመሰረተ ልማት አውታሮች ያሏቸው የመስኖ ሥራዎች ናቸው::

a) "Large Dam" refers to dams with a water reservoir area of 10 hectares or more.

b) "Medium Dam" refers to dams with a water reservoir area ranging from 3 to 10 hectares.

c) "Small Dam" refers to dams with a water reservoir area of less than 3 hectares.

d) "Small-Scale Canal" refers to canal works with a water management and irrigation system serving an area of less than 200 hectares, either permanently or with potential for improvement.

e) "Medium-Scale Canal" refers to canal works with a water management and irrigation system serving an area ranging from 200 to 3,000 hectares, either permanently or with potential for improvement.

f) "Large-Scale Canal" refers to canal works with a water management and irrigation system serving an area of more than 3,000 hectares, either permanently or with potential for improvement.

ምዕራፍ ሰባት
የጨረታ ሥነ ሥርዓት

CHAPTER SEVEN
BID PROCEDURES

103. <u>የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ</u>

1) የጨረታ ጥሪው በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ለማድረግ የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት በመጠቀምእንደአስፈላጊነቱ ሰፊሽፋን ባለው ጋዜጣ ወይም በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ቢያንስ አንድ ጊዜ መውጣት አለበት::

2) የጨረታው ጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊይዝ ይገባል፡-

103. Advertisement of Bid

1. An invitation to bid shall be issued at least once through the electronic procurement system, a widely circulated newspaper, or other appropriate communication methods to ensure the participation of a sufficient number of bidders.

2. The bid advertisement shall include, at a minimum, the following information:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ሀ/ የጨረታውንማስታወቂያ ይፋ ያደረገው የመንግስት መ/ቤት ስምና የተሟላ አድራሻ፣

ለ/ የሚቀርበውን ዕቃ ወይም አገልግሎት፣ ዓይነት፣ከተቻለ ብዛት እና ርክክቡ የሚፈፀምበትን ቦታ ወይም የግንባታ ሥራውን ዓይነት እና የሚከናወንበትን ቦታ ወይም የምክር አገልግሎቱን ዓይነት እና የሚካሄድበትን ቦታ፣

ሐ/ የግዥ ዘዴውንና የጨረታ መለያ ቁጥር፣

መ/ በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያሟሏ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች፣

ሠ/ የጨረታ ሰነዱን ለማግኘት የሚከፈል ዋጋ እና ሰነዱንየሚያገኙበት ሁኔታ፣

ረ/ የመጫረቻ ሰነዱ የመጨረሻ ማስረከቢያ እና የሚከፈትበትን ቀንና ሰዓት፣

ሰ/ ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው በጨረታው አከፋፈት ላይ መገኘት የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ፣

ሸ/ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መጠን፣

ቀ/ ለተጫራቾች መገለጽ እንዳለባቸው በመሥሪያ ቤቱ የታመነባቸው ሌሎች ጉዳዮች፣

በ/ የመንግስት መ/ቤቱ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ የመሰረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

3) የጨረታው ጥሪ የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት መሰረት ጨረታው በሚካሄድበት ቋንቋ መዘጋጀት ይኖርበታል።

104. <u>የጨረታ ሰነድ</u>

የመንግስት መሥሪያ ቤቶች፣

1) በአዋጁ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ መሰረት ያደረገና በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

a) The name and address of the Public Body issuing the advertisement.

b) A description of the goods or services to be procured, including their type and quantity (where possible), and the delivery location; or, for construction works, the type and location of the work; or, for consultancy services, the type and location of service execution.

c) The procurement method and the tender reference number.

d) The eligibility requirements that participating bidders must fulfill.

e) Any applicable fee for purchasing the bidding document and the conditions for obtaining it.

f) The deadline for submission of the bid and the date and time of bid opening.

g) A notice that bidders or their authorized representatives may attend the bid opening.

h) The required amount and type of bid security.

i) Any other relevant information to be communicated to bidders by the Public Body.

j) A statement reseving the Public Body's right to cancel the bid in whole or in part.

3. The invitation to bid shall be prepared in the same language as the bidding document.

104. Bid Document

1. In accordance with Article 50(1) of the Proclamation, the bidding document shall be based on the standard bidding document issued by the Authority and shall incorporate the provisions outlined in this Directive.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

2) የጨረታ ሰነዱ በጥቅል ድምር የሚከፈል፣ በነጠላ ዋጋዎች የሚከፈል፣ በወጪ ላይ ተደማሪ ሆኖ በሚከፈልና ክሌሎች የተመረጠውን የውል አይነት በግልፅ ማስቀመጥና ለዚህ ተስማሚ የሆኑ የውል ድንጋጌዎችን የያዘ መሆን አለበት።

3) የመንግስት መ/ቤቶች ባለስልጣኑ ካዘጋጀው መደበኛ ሰነዶች ውጭ ለመጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የባለስልጣኑን ፈቃድ አስቀድመው በማግኘት የተለዩ የጨረታ ሰነድ ዓይነቶችን መጠቀም ይችላሉ።

4) የመንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ጊዜ በተጫራቾች መመሪያ እና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ምንም ለውጥ ሳያደርጉ በሌሎች የሰነዱ ክፍሎች ላይ እንደ አግባብነቱ እንደግዥው ዓይነትና ባህርይ ማሻሻያ በማድረግ ሰነዱን ማዘጋጀት አለባቸው።

5) የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚያዘጋጁትን የጨረታ ሰነድ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ተጠቅመው መሆን ይኖርበታል።

6) የጨረታ ሠነዱ ለተጫራቾች አየር ላይ ከመውጣቱ በፊት በአጽዳቂ ኮሚቴ መጽደቅ አለበት።

7) መ/ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ለጨረታ ሰነዱ ከብር ሁለት መቶ (200) ያላነሰ እና ከብር አምስት መቶ (500) ያልበለጠ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል። በማዕከል በማዕቀፍ ለሚፈጸም ግዥዎች ለጨረታ ሰነድ ከብር አምስት መቶ ያላነሰ እና ከብር ሁለት ሺ (2,000) ያልበለጠ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም የመ/ቤቱ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ ሊገድብ ይችላል ብሎ ካመነ ከክፍያ ነጻ ሊሰጥ ይችላል።

105. የተጫራቾች መመሪያ

1) ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የመደበኛ የጨረታ ሠነዶች አንዱ ክፍል ሆኖ የተዘጋጀውን የተጫራቾች መመሪያ እና የዚሁ አካል የሆነውን የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የጨረታ ሰነድ ክፍል አድርጎ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ

2. The bidding document shall clearly indicate the payment terms—whether lump sum, unit price, or reimbursable—and specify the selected contract type along with relevant contract conditions.

3. Public Bodies may use non-standard bidding documents upon obtaining prior written approval from the Authority.

4. While preparing bidding documents, Public Bodies shall not alter the Instructions to Bidders or the General Conditions of Contract, but may make appropriate modifications in other sections to reflect the specific characteristics of the procurement.

5. Bidding documents shall be prepared using the government electronic procurement system.

6. Bidding documents must be approved by the Procurement Endorsing Committee prior to issuance.

7. The Public Body may, where necessary, charge a fee for the bidding document ranging from not less than two hundred (200) Birr to not more than five hundred (500) Birr. For procurements conducted centrally under the framework procurement approach, the fee may range from not less than five hundred (500) Birr to not more than two thousand (2,000) Birr. However, where the Public Body determines that imposing such a fee may restrict bidder participation, it may exempt bidders from the payment of the fee.

105. Instructions to Bidders

1. Public Bodies shall include a section containing Instructions to Bidders and a Detailed Bid Data Sheet in the bidding

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2022

የግዥ ሥርዓቱን ተጠቅመው እንዲያገኙት ማድረግ አለባቸው።

2) ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሰነድ የተጫራቾች መመሪያ ላይ ማሻሻያ ማድረግ የማይቻል ቢሆንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ የሚደረጉት ለውጦች የሚመለከቱት የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ ላይ ይሆናል።

3) የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ የሚከተሉትን ዋና ዋና ሁኔታዎች ያካተተ መሆን አለበት፦

ሀ/ የሚገዛውን ዕቃ ወይም የግንባታ ስራ፤ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ፣ የመንግስት መ/ቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም የግዥውን የበጀት ምንጭ፣

ለ/ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ የአገር ውስጥ ተጫራቾች የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት፣ የሙያ ምስክር ወረቀት፣የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና ሌሎች መ/ቤቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ደጋፊ ሰነዶች ስለሚቀርቡበት ሁኔታ፣

ሐ/ የውጭ አገር ተጫራቾች እንደአግባብነቱ በተቋቋሙበት አገር የተሰጣቸውን የኩባንያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ማቅረብ እንዳለባቸው መጠቀሱን፣

መ/ በጨረታ ሰነዱ ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን አስመልክቶ ማብራሪያ የሚጠየቅበትን አድራሻና ጊዜ፣

ሠ/ ተጫራች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ሰነድ ይዘት ምን መሆን እንዳለበት፤በምን ቋንቋ እንደሚዘጋጅ፤ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ የሚገለጹ እና በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች እና ቅጾች ዓይነት እና ብዛት፣

ረ/ የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ ጊዜ የሚያበቃበትን እና ጨረታው የሚከፈትበትን ቀንና ሰዓት፣

ሰ/ ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚገልፅ መግለጫ፣

ሸ/ ተጫራቾች የማጭበርበር ድርጊት እና ሙስና በሚመለከት በኢትዮጵያ ህጎች የተደነገገውን የሚያከበር መሆኑን በማረጋገጥ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ሙስና ላለመፈጸም ቃል የሚገባበትን ቅጽና ሌሎች በተጫራቾች ተሞልተው እንዲቀርቡ መደረግ አለበት።

ቀ/ የዕቃዎቹ ናሙናዎች በተጫራቾች እንዲቀርቡ የሚያስፈልጉ ከሆነ ተፈላጊዎቹ ናሙናዎች የሚቀርቡበትንና እንደአስፈላጊነቱ በተጫራቾች የሚቀርብበትን ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም እነዚህ ናሙናዎች በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች

document, accessible via the government electronic procurement system.

2. The Instructions to Bidders section in the standard bidding document issued by the Authority shall not be altered; any procurement-specific amendments shall be reflected in the Detailed Bid Data Sheet.

3. The Detailed Bid Data Sheet shall include, at a minimum, the following:

a) A general description of the procurement (goods, works, consulting, or other services), the name and address of the Public Body, and the source of funding.

b) Requirements for local bidders to submit valid tax clearance, professional certificates, renewed business licenses, and other supporting documents as deemed necessary by the Public Body.

c) Requirements for foreign bidders to submit business registration or licenses issued in their country of incorporation.

d) The address and timeframe for requesting clarifications concerning the bidding document.

e) The required contents and language of the bid, the standard and additional documents to be submitted, and the number of copies required.

f) The deadline for bid submission and the date and time of bid opening.

g) A statement that bids submitted after the deadline will not be accepted.

h) A requirement that bidders submit a signed declaration form and other relevant documents affirming

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

የሚመለሱ ወይም ሊመለሱ የማይችሉ መሆናቸውን፣

በ/ ጨረታውን ለመገምገም በሥራ ላይ የሚውሉትን ዘዴዎች፣ ለዚሁ ግምገማ የሚያገለግሉትን መስፈርቶች እና እንደአስፈላጊነቱ ለመስፈርቱ የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ፣እንዲሁም ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግምገማው እኩል ቢሆኑ አሸናፊውን ተጫራች ለመለየት የመወዳዳሪዎች ሐሳብ የሚቀርብበት ሁኔታና መስፈርቶች፣

ተ/ በውል አፈፃፀም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ሁኔታ፣

ቸ/ የጨረታ ማስከበሪያ እና የውል አፈፃፀም ዋስትና መጠን፣ ዓይነት እንዲሁም እነዚህ ዋስትናዎች ፀንተው የሚቆዩበትን ጊዜ፣

ኀ/ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም የርክክቡን ቦታና ጊዜ፣

ኘ/ በአዋጁ የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት ዝርዝር አፈፃፀም የሚያመለክት መግለጫ፣

አ/ ጨረታው የቴክኒክ እና የፋይናንስ ሰነዱ ለየብቻው የሚቀርብበት ሂደት ተሞልቶ መቅረብ አለበት።

ከ/ የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ ከሆነ፣የቅድሚያ ክፍያውን መጠን እና ተቀባይነት ያለውን የዋስትና ዓይነት፣

ኸ/ ተጫራቾች በጨረታው አፈፃፀም ሂደት ቅሬታ ካላቸው በአዋጁ አንዲሁም በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት አቤቱታ እና ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳላቸው እና አቤቱታው የሚቀርብበትን ሥነ-ሥርዓት፣

ወ/ መ/ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታ ሰነዱ ከተገለጸው የአቅርቦት መጠን ላይ መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ዋጋ ሳይቀየር እስከ 20%(ሃያ በመቶ) መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚችል፣

compliance with Ethiopian anti-corruption and anti-bribery laws.

i) Requirements related to sample submission, the time and location for submission, and whether samples will be returned to unsuccessful bidders.

j) The bid evaluation method, evaluation criteria, point allocation, and procedures for identifying a successful bidder in the event of a tie.

k) Conditions for price adjustment during contract execution.

l) The required amount, form, and validity period of bid security and performance security.

m) The validity period of bid prices and the time and place for bid submission.

n) A statement regarding the application of preferences permitted under the Proclamation.

o) Whether technical and financial proposals must be submitted separately or jointly

p) If advance payment is to be made, the required security type and amount.

q) The bidders' right to lodge complaints and appeals pursuant to the Proclamation and this Directive, and the procedures for doing so.

r) The Public Body's right to increase or decrease the quantities stated in the bidding document by up to twenty percent (20%) before contract signing without altering the price offered by the winning bidder.

106. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

የመንግስት መ/ቤቶች በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 25 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 በተዘረዘሩት ሁኔታዎች

106. Technical Specification

Public Bodies shall include technical specifications in the bidding documents, prepared in accordance

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2021

መሰረት የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማካተት አለባቸው::

107. የጨረታ ቅፅና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ

1) የመንግስት መ/ቤቶች ለጨረታ በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ውስጥ በባለስልጣኑ ተዘጋጅቶ በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት የተዘጋጀውን እና እንደግዥው ባህሪ የመንግስት መ/ቤቱ ያዘጋጀውን በተጫራቾች ሊሞላ የሚገባውን የጨረታ ቅፅ፣ ወይም ሰንጠረዥ እና በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ መካተታቸው ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንባቸውን ሌሎች ቅፆችን ማካተት አለባቸው::

2) በዚህ አንቀጽ መሠረት በመንግስት መ/ቤቶች የሚዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ እንደአስፈላጊነቱ ዋጋን፣ ታክስን እና ሌሎችን ከዋጋ አቀራረብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በግልፅ ለማመልከት የሚያስችል አንዲሁም የጨረታ ግምገማን ግልጽና ቀልጣፋ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት::

3) የሚዘጋጀው የጨረታ ቅፅ በተቻለ መጠን ዕጩ ተወዳዳሪው ግልፅ የሆነ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርብ የሚያስችል፣ የጨረታ አካሄዱን መረዳቱን የሚያረጋግጥ፣ ጨረታውን የሚያደናቅፉ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ የሚከላከል እና ተጫራቹ ላቀረበው የመወዳደሪያ ሐሳብ ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ የሚያደርግ መሆን አለበት::

108. <u>አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች</u>

1) ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት መደበኛ የጨረታ ሰነድ ክፍል ሆነው የተዘጋጁትን የአጠቃላይ እና የልዩ ውል ሰነዶችን በጨረታ ሰነዱ በማካተት ለተጫራቾች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ አለበት::

2) በመደበኛ ጨረታ ሰነዱ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም:: ሆኖም አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ የሰፈሩትን አንቀጾች በማጣቀስ በአጠቃላይ የውል ሁኔታው በተፈቀደ አግባብ ብቻ ልዩ የውል ሁኔታውን እንደሚፈፀመው ግዥ ባህሪና ዓይነት ማሻሻል ይቻላል::

3) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች የሚያዘጋጁት ልዩ የውል ሁኔታ

with Article 25 of the Proclamation and Article 43 of this Directive.

107. Bid Form and Price Schedule

1. Public Bodies shall include the bid forms, price schedule, and other relevant documents in the bidding documents, as prepared by the Authority and accessed through the government electronic procurement system, reflecting the nature of the procurement.

2. The price schedule form shall clearly indicate pricing details, including, where necessary, applicable taxes and associated costs to facilitate a transparent and effective evaluation process.

3. The bid forms shall enable bidders to submit clear and comprehensive proposals, confirm their understanding of the procurement process, prevent any disruptive actions, and affirm the bidders' full responsibility for their proposals.

108. General and Special Conditions of Contract

1. Public Bodies shall include the general and special contract conditions in the bidding documents for bidders' reference.

2. General Conditions of Contract included in the standard bidding documents shall not be amended; however, Special Conditions of Contract may be tailored to the type and nature of the procurement, based on the corresponding clauses of the General Conditions.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

እንደግዥው ዓይነት ሊለያይ ቢችልም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት:-

ሀ/ የተጫራቹንና የመንግስት መ/ቤቱን ግዴታና ኃላፊነትን በግልፅ ያመለከተና በመ/ቤቱ ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሠረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ለ/ እንደአስፈላጊነቱ የውሉ አፈጻጸም የሚከተላቸውን ዋና ዋና ሂደቶች፣የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሸግ፣ የማጓጓዝ ኃላፊነት፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈፃፀም፣ የርክክብ እና የፍተሻ ሥነ-ሥርዓት፣ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አተገባበር በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል።

ሐ/ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም ለማስጠበቅ የተቀመጡ የውል ቃሎች እና ድንጋጌዎች በአግባቡ በውሉ የተካተቱ መሆኑን ማረጋገጥ።

3. Without prejudice to Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the Special Conditions of Contract shall, at a minimum, include:

a) The clearly defined obligations and responsibilities of both the Public Body and the contractor, and confirmation that the Public Body's obligations are enforceable and capable of implementation.
b) Key procedures for contract execution, including delivery timelines, packaging, transport responsibilities, price adjustment mechanisms, payment terms, inspection and acceptance procedures, performance securities, and other relevant provisions.
c) A requirement that all terms and conditions included in the contract conform to the provisions of the Proclamation and this Directive to ensure the protection of the Public Body's interests.

109. የብቃትና የግምገማ መስፈርት አዘገጃጀት

1) መንግስት መ/ቤቱ የመጫረቻ ሰነድ የሚገመገምበትን መስፈርት በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ የብቃትና የግምገማ መስፈርቶች ላይ በግልፅ ማሳየት አለበት።

2) የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት እንደ ግዥው ዓይነት የሚለያይ ቢሆንም ከሚከተሉት ሁለት መሰረታዊ የመምረጫ ዘዴዎች በአንዱ ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል:-

ሀ/ ለግዥው ተቀባይነት ያለውን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት በመወሰን፣ ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛውን ካሟሉት ተጫራቾች መካከል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 123 በተደነገገው መሠረት የተሰበረ እና የተጋነነ ዋጋ ማጣሪያ ተደርጎአነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ፣ ወይም

ለ/ ግዥውን የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ የቴክኒክ መስፈርቶችን ድርሻ በመወሰን እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንጻራዊ ክብደት በግልጽ በጨረታ ሰነዱ ላይ በማሳየትና በነዚህ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ የቴክኒክ ግምገማ በማካሄድ፣ እንዲሁም የቴክኒክ ግምገማውን ያለፉ

109. Preparation of Qualification and Evaluation Criteria

1. Public Bodies shall explicitly define the qualification and evaluation criteria in the appropriate section of the bidding document.

2. Bid evaluation shall be conducted using one of the following methods, depending on the type of procurement:

a) Establishing minimum technical requirements and selecting the lowest-priced bid that meets those requirements, after checking for abnormally low or high prices in accordance with Article 123 of this Directive;
b) Allocating scores for technical criteria to assess value for money or economic benefit, clearly stating the weight assigned to each criterion in the bidding document, conducting a technical evaluation, and then evaluating price among technically qualified bids to

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ተጫራቾችን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) በተገለፀው አሰራር መሰረት የጨረታ ዋጋ ግምገማ ከተከናወነ በኋላ በቴክኒክ እና በዋጋ አጠቃላይ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን መምረጥ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ የግምገማ ዘዴ ተፈፃሚ የሚሆነው ለምክር አገልግሎት ግዥ ብቻ ነው።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ እና ለየተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖየሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና ዘዴን መጠቀም ሲፈለግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት:-

ሀ/ የሚገዛው መደበኛ ወይም ደረጃው የታወቀ አቅርቦት በሚሆንበት ጊዜ ለመስሪያ ቤቱ ጠቃሚ የሆነ እና በተጫራቾች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የሚችል የተለየ እሴት ሊቀርብበት የሚችል መሆን አለመሆኑን፣

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ ካስቀመጠው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪነት የሚቀርብ እሴት ተጨማሪ ፋይዳ ማስገኘት አለማስገኘቱን ወይም ተጨማሪው እሴት ለመ/ቤቱ የሚሠጠውን ጥቅም ዝቅተኛነትና ከፍተኛነትን፣

ሐ/ የሚገዛው ዕቃ ደረጃ ያለወጣለት ከሆነ ተጨማሪ ፋይዳ ከመፍጠር አንፃር የፍላጎት መግለጫ በተለያየ ደረጃ ሊያሟሉ የሚችሉ ተቀራራቢ ዕቃዎች መኖር አለመኖራቸውን፣

መ/ ዕቃው ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሆኖ የአቅርቦቱ ምንጭ በመለያየቱ ምክንያት የተለያየ የመጠቀሚያ፣ የመጠበቂያና የመያዣ እንዲሁም የማስወገጃ ወጪ የሚፈልግ መሆን አለመሆኑን፣

5) የመንግስት መ/ቤቱ ተጫራቾችን ያቀረቡትን ሠነድ በዚህ አንቀጽ በተገለጹት መስፈርቶች መሠረት በመገምገም አሸናፊ የሚሆነውን ተጫራች ከለየ በኋላ የአሸናፊው ተጫራች ወቅታዊ የብቃት ሁኔታ በድሕረ ግምገማ መረጋገጥ አለበት ብሎ ሲያመን ይህንኑና ለድሕረ ግምገማ ዓላማ የሚጠቀምበትን መስፈርት በቅድሚያ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት አለበት።

6) በዚህ አንቀጽ መሰረት ለማወዳደሪያነት የሚመረጡት መስፈርቶች ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የሚሰጠውን

determine the highest combined technical and financial score.

3. The evaluation method described under Sub-Article (2)(b) shall apply only to the procurement of consultancy services.

4. Without prejudice to Sub-Articles (2)(a) and (b), where life-cycle cost analysis is to be applied, the following shall be considered:

a) Whether the item being procured offers distinguishable added value among suppliers for standardized or commonly available goods;
b) Whether the added value exceeds the Public Body's minimum requirements and provides significant additional benefits;
c) For goods without standardized specifications, whether different alternatives exist that could provide distinct value;
d) Whether the long-term use of the goods involves varying costs for operation, maintenance, storage, and disposal.

5. Upon identifying the successful bidder, the Public Body may, if necessary, verify the bidder's current qualifications through post-qualification procedures as stated in the bidding document.

6. The evaluation criteria selected must reflect the relative contribution of the goods or

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

ጠቀሜታ ለመወሰን አስተዋፅኦ የሚኖራቸው መሆኑን ለማረጋገጥ እና የግዥውን ጠቀሜታ ለመወሰን ባላቸው አስተዋፅኦ ደረጃ መሠረት አንባራዊ ክብደት እንዲሰጣቸው መደረግ አለበት።

110. ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ስለመወሰን

1) የመንግስት መ/ቤት የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን የሚከተሉትን መሠረት አድርጎ ይወስናል:-

ሀ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተቀባይነት ያለው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት፣ መረጃ ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን፣ እንደአግባብነቱ አሸሙር ወይም ሽርክና ለመመሥረት፣ ከአምራቹ የሚሠጥ ውክልና እና የመፈረም ሥልጣን ማረጋገጫ ለማግኘት እና ሌሎች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚፈጅባቸውን ጊዜ፣

ለ/ መ/ቤቱ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች በጨረታ ሰነዱ ይዘት ላይ ሊቀርቡ ለሚችሉ ጥያቄዎች ማብራሪያ ለመስጠት፣ እንዲሁም ማሻሻያ ለማድረግ የሚፈጅበትን ጊዜ፣

ሐ/ ለግዥው ናሙና ማቅረብ የሚያስፈልግ ከሆነ ናሙና ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

መ/ በተለይ የግንባታ ሥራ ግዥ በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ቦታ ጉብኝት የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 6 ላይ ከተገለጸው ቀን ያነሰ መሆን የለበትም።

services to be procured in determining their overall usefulness and value.

110. Determination of Bid Floating Period

1. The Public Body shall consider the following factors when preparing the bidding document and determining the deadline for bid submission:

   a) The time required for potential bidders to prepare a compliant bid, gather necessary information, conduct due diligence, form consortiums or joint ventures, obtain authorizations or certifications from manufacturers, and fulfill other prerequisites for participation.
   b) The time needed to respond to clarification requests submitted by bidders regarding the contents of the bidding document, including time for issuing necessary amendments.
   c) The time required to submit samples, where the procurement necessitates such submissions.
   d) The time required to visit the construction site, particularly for construction works procurement.

2. Without prejudice to Sub-article 1 of this Article, the bid floating period shall not be shorter than the minimum period specified under Annex 6 of this Directive.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

111. ስለ ናሙና አቀራረብ

1) የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወይም ከተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጨማሪነት ግዥው በተሻለ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የናሙና ምልከታ ሲኖረው መሆኑ ሲታመንበት የመንግስት መ/ቤቱ በተጨማሪነት ናሙና ሊያቀርብ ወይም እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል።

2) የመንግስት መ/ቤቱ ናሙና ራሱ አቅርቦ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለዕይታ በቀረበው ናሙና መሰረት እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፡-

ሀ/ በመንግስት መ/ቤቱ የሚቀርበው ናሙና በአንድ አምራች ወይም የንግድ ምልክት በተሠራ ዕቃ የተወሰነ መሆን የለበትም። እስከተቻለ ድረስ ተቀባይነት ያላቸው ናሙናዎች ዓይነት ለዕይታ እንዲቀርቡ ሆኖ ከቀረቡት ናሙናዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጥራት ደረጃ ያላቸው ሌሎች ዕቃዎችንም ማቅረብ እንደሚቻል ለተጫራቾች ማሳወቅ ይገባል።

ለ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙናውን በግልፅ በሚያዩበት ቦታ ላይ መደረጉን እና ተገቢ እስከሆነ ድረስ ስለናሙናው መግለጫ የሚሰጥ ባለሙያ መመደቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ሐ/ መ/ቤቱ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዕይታ ካቀረበው ናሙና በተጨማሪ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅ ከሆነ የሚዘጋጀው መግለጫ እስከተቻለ ድረስ የቀረበውን ናሙና የሚገልፅና ለዕይታ ከቀረበው ናሙና የቴክኒክ ባህርይ ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል።

3) በተሰጣቸው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መሠረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙና እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፤

ሀ/ የሚቀርቡት ናሙናዎች ዓይነት፣ ብዛት የሚቀርቡበት ጊዜ እና አኳኋን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግልፅ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል።

ለ/ ናሙናዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት መቅረብ አለባቸው፡ ፡ ሆኖም ዕጩ ተወዳዳሪው ናሙናውን በወቅቱ ልኮ ከዕጩ ተወዳዳሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት በማጓጓዝ

111. Submission of Samples

1. If the Public Body cannot adequately prepare a technical specification, or deems that reviewing samples in addition to the technical specification will improve procurement outcomes, it shall require or allow bidders to submit samples.

2. If the Public Body presents samples of the required goods for bidders to inspect and supply:

a) The samples shall not be limited to a specific manufacturer or brand. They must, as far as possible, represent acceptable quality, and bidders shall be informed that samples of equivalent quality may be supplied.
b) Samples shall be visibly displayed for inspection by bidders, and, where necessary, qualified personnel shall be assigned to explain the samples.
c) Where both technical specifications and samples are presented, the specifications must be descriptive of the sample and consistent with its technical characteristics.

3. If bidders are required to submit samples based on the technical specifications:

a) Bidders shall be provided with clear information on the type and quantity of the samples, as well as the time and manner of submission.
b) Samples must be submitted before bid opening. However, if the bidder dispatches

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ሂደት ቢዘገይ የመንግስት መ/ቤቱ የግዥውን አፈፃፀም አይጎዳም ብሎ እስካመነ ድረስ ተጨማሪ የናሙና ማቅረቢያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

4) ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን እና የማይችሉበትንም ምክንያት የመንግስት መ/ቤቱ ሲቀበለው ስለናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቅረብእንዲችሉ ሊፈቅድ ይችላል።ይህም ናሙናውን ፎቶግራፍ ወይም የተገኘውን የናሙና ክፍል ማቅረብን ይጨምራል። ሆኖም በዚህ መልኩ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚቻለው አፈፃፀሙ የተሻለውን ተጫራች በመምረጥ ሂደት ልዩነት የማያመጣ እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡

5) የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቾች የቀረቡ ናሙናዎችን በጥንቃቄ የመያዝ እና የመፈተሽ ኃላፊነት አለበት። ሆኖም ተጫራቾች ያቀረቡት ናሙና በሚመረመርበት ወቅት በዕቃው ባህሪ ምክንያት ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ካሣ አይከፈላቸውም።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው ቢኖርም በተጫራቾች የቀረቡ ናሙናዎች ከፍተሻ ጋር ከተያያያዙ ምክንያቶች ውጭ በአያያዝ እና አጠቃቀም ጉድለት ቢበላሽ፣ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ተጠያቂነት ይኖርበታል።

7) የናሙናው ምርመራ ከተደረገ በኋላ ናሙና ለተጫራቾች ተመላሽ ይደረጋሉ። ተጫራቾች ያቀረቡትን ናሙና የጨረታው ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልወሰዱ በውርስ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል።

8) በመንግስቱ መ/ቤቱ የተለየ ውሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር የአሸናፊው ተጫራች ናሙና ግዥው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ በናሙናነት ተይዞ መቆየት ያለበት ሲሆን ናሙናውም በርክክብ ወቅት ለማነፃፀሪያነት እንዲያገለግል መደረግ ይኖርበታል።

112. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ

1) ዕጩ ተወዳዳሪዎች በአዋጁ አንቀፅ 51 መሠረት በመ/ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ ላይ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄያቸውን ለመ/ቤቱ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

the sample on time but delivery is delayed for reasons beyond their control, the Public Body may grant an extension, provided that the procurement outcome will not be affected.

4. If a bidder provides satisfactory justification for not submitting a sample, the Public Body may accept documentary evidence (e.g., photographs or sample parts), provided this does not affect the determination of the most advantageous bid or result in discriminatory practices.

5. The Public Body is responsible for safeguarding and examining the submitted samples. However, it shall not be liable for loss or damage resulting from the nature of the samples or the examination process.

6. Without prejudice to Sub-article 5, if a sample is lost, stolen, or damaged due to the fault of the bidder, the Public Body shall not be held liable.

7. Samples shall be returned after examination. If not claimed within six months of the award notification, the Public Body may dispose of them.

8. Unless otherwise decided, the sample submitted by the successful bidder shall be retained until contract completion and used as a reference for conformity during delivery.

112. Clarification or Modification of the Bid Document

1. In accordance with Article 51 of the Proclamation, bidders may submit requests for clarification or amendment of the bidding document.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

2) የመንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ሰነድ ላይ ከዚህ በታች የተመለከቱ ሁኔታዎችን አሟልቶ ከማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ የሚቀርብ የማብራሪያ ወይም ማሻሻያ ጥያቄን ተቀብለው ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡

ሀ/ በዚህ መመሪያ አባሪ 11ላይ በተገለፀው መሰረት ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 40 ቀናት ለሆነ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ 21ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

ለ/ ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 30ቀናት ለሆነ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ 14 ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

ሐ/ ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 25 ቀናት ለሆነ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ 12 ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

መ/ ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 20 ቀናት ለሆነ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ 10 ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

ሠ/ ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 10ቀናት እና ከዚህ በታች ለሆነ ግዥ ጨረታው ሊዘጋ 5 ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገገው ቀን ባነሰ ጊዜ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ መ/ቤቱ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ሲቀርብ መ/ቤቱ ጨረታውን ከመክፈቱ በፊት በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሹን የጨረታ ሰነዱ ተደራሽ በተደረገበት ሥርዓት ማውጣት አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው ምላሽ ወይም ማሻሻያ ላይ ቅሬታ ያላቸው እንደሆነ ለቦርዱ ይግባኝ ለማቅረብ እንዲችሉ በአዋጁ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት መስሪያ ቤቱ ጨረታው ሳይዘጋ ማቆየት ወይም የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም አለበት፡፡

6) ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ለሚቀርብ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ የሚሠጠው ምላሽ በጽሑፍ ሆኖ የጨረታ

2. The Public Body shall respond to clarification or amendment requests submitted within the timelines below, based on the bid's floating period as defined in Annex 6:

a) For bids open for 40 days: requests must be submitted at least 21 days before bid closure.
b) For bids open for 30 days: requests must be submitted at least 14 days before bid closure.
c) For bids open for 25 days: requests must be submitted at least 12 days before bid closure.
d) For bids open for 20 days: requests must be submitted at least 10 days before bid closure.
e) For bids open for 10 days: requests must be submitted at least 5 days before bid closure.

3. The Public Body is not obliged to respond to requests that do not comply with the timeframes specified in Sub-article 2.

4. If a compliant request for clarification or amendment is received, the Public Body must respond no later than three days before the bid opening date, using the communication method stated in the bidding document.

5. Without prejudice to Sub-article 4, if a bidder has complaints regarding the response or amendment, the Public Body shall extend the bid closing date to allow time for appeal to the Appeals Board as provided under Article 51(5) of the Proclamation.

6. Responses to requests for clarification or amendment shall be provided in writing and communicated via the medium specified in the bidding document. They may also be published on the Public Body's website.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ሰነዱ ተደራሽ በተደረገበት በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት እና በመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ ማውጣት አለበት።

7) የመንግስት መ/ቤቶች ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርብላቸውን የማብራሪያ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በመ/ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የጨረታ ሰነዱን ማሻሻል ይችላሉ። የመንግስት መ/ቤቶች ማንኛውም የጨረታ ሰነዱን ይዘት የሚቀይር ማሻሻያ በተጨማሪ የጨረታ ሰነድነት የጨረታ ማስታወቂያ በወጣበት በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትላይ ማውጣት አለባቸው።

8) መንግስት መ/ቤቶች በንዑስ አንቀፅ 7 ላይ በተገለፀው መሰረት በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ ሲያደርጉና ጨረታውን ለመዝጋት በቀረው ጊዜ ውስጥ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተደረገውን ማሻሻያ አካተው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንደማይችሉ ሲገመት የጨረታ ማስታወቂያ በወጣበት በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ወይም በጋዜጣ እናበመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይየጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም አለባቸው።

9) ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዳቸው ላይ ማሻሻያ ማድረግ ሲፈልጉ የማሻሻያ ሃሳባቸውን በማሻሻል ከጨረታ መዝጊያው ቀንና ሰዓት በፊት ማስገባት አለባቸው።

113. የጨረታ ቋንቋ

1) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚዘጋጀው የጨረታ ማስታወቂያው፣ የጨረታ ሰነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ በአዋጁ አንቀጽ 23 መሰረት መሆን አለበት።

2) ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውና ደጋፊ ማስረጃዎቻቸው በጨረታ ሰነዱ ጨረታው እንዲካሄድበት ከተፈቀደው ውጭ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጁ በሚሆኑበት ጊዜ በሕጋዊ ተርጓሚ ተተርጉመው የትርጉሙ ቅጅ ከዋናው ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት።

3) የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቹ የቀረበው ሰነድ በመጀመሪያ በተዘጋጀበት እና ለጨረታው በተፈቀደው ቋንቋ ትርጉም መካከል ልዩነት እንዳለው ሲያረጋግጥ ልዩነቱ በጨረታው ይዘት ላይ መሰረታዊ

7. If the Public Body deems it necessary to amend the bidding document based on a request, the amendment shall be published on the Government Electronic Procurement System, through which the bid was advertised.

8. If an amendment significantly affects the preparation of bids, the Public Body shall extend the bid submission deadline. The extension shall be communicated using the medium specified in the bidding document and published on the e-GP system, newspapers, or the Public Body's website.

9. Bidders who wish to amend their submitted bids may do so before the bid closing date and time.

113. Language of Bid

1. The bid advertisement, bidding documents, and bid process shall be conducted in the language specified pursuant to Article 23 of the Proclamation.

2. If a bidder submits their bid and supporting documents in a language other than the one specified, an officially authorized translation shall be submitted alongside the original.

3. In case of discrepancies between the original and the translated version, if the discrepancy fundamentally alters the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ለውጥ አያመጣም ብሎ ካለመነ በስተቀር ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል።

content of the bid, the Public Body may reject the bid.

114. የመጫረቻ ዋጋ

ተጫራቾች የሚሰጡት የመጫረቻ ዋጋ በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ያልተመሰረተ፣ በጨረታው እና በውል አፈፃፀሙ ወቅት የማይለዋወጥ ፅኑ ዋጋ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

114. Bid Price

The prices quoted by bidders shall be independently determined, shall not be based on the prices of other bidders, and must remain fixed during the bid validity period and throughout the execution of the contract.

115. የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

1) የመንግስት መ/ቤቱ የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ መቆየት ያለበትን ጊዜ በጥንቃቄ በመወሰን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ማካተት አለበት። መጫረቻ ሰነድ ወይም የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለመወሰን መ/ቤቱ የሚከተሉትን ማገናዘብ አለበት፦
   - ሀ/ የግዥውን ውስብስብነት እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብዛት፣
   - ለ/ ግዥውን ለመገምገም፣ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ለማፅደቅ እና አጠቃላይ የጨረታ አፈፃፀም ሂደቱ ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ፣
   - ሐ/ የመንግስት መ/ቤቱ ተመሳሳይ ግዥዎችን በመገምገም ረገድ ያለው ልምድ፣
   - መ/ ግዥው በገበያ ላይ ያለውን የዋጋ ተለዋዋጭነት ሁኔታ፣
   - ሠ/ አቤቱታ ወይም ይግባኝ ቢነሳ እልባት ለመስጠት እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል እስከሚፈራረም ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለፀው መሰረት የመጫረቻ ሰነድ ረዘም ላለ ጊዜ ፀንቶ የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን መ/ቤቱ ካላመነ በስተቀር ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታው ከሚከፈትበት ዕለት ጀምሮ ከ45 (አርባ አምስት)ቀናትመብለጥ የለበትም።
3) የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ሂደታቸውን የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈራረም አለባቸው። ሆኖም ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ሂደቱ

115. Validity Period of Bids

1. The Public Body shall specify the bid validity period in the bidding document, considering the following:
   a) The complexity of the procurement and anticipated number of participants.
   b) The time needed for bid evaluation, endorsement, and finalization.
   c) The Public Body's experience in evaluating similar procurements.
   d) Market price volatility of the item or service.
   e) Time required to address complaints or appeals and sign the contract.
2. Unless the Authority determines that a longer bid validity period is justified pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the bid validity period shall not exceed forty-five (45) calendar days from the date of bid opening.
3. Public Bodies shall finalize the procurement process and conclude a contract with the successful bidder within the bid validity period. However, where the Authority finds that the bid validity period is set to expire before the procurement process is completed due to force majeure, it may authorize the Public Body to request the bidders to extend the bid validity period for a specified number of additional days.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ሳይጠናቀቅ ለግዥው የቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃ መሆኑን መ/ቤቱ ሲረዳ ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለተጨማሪ ቀናት እንዲያራዝሙለት መጠየቅ አለበት።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 በተመለከተው መሰረት ተጫራቾች አንዲያራዝሙ የሚጠየቁት ተጨማሪ ቀናት የመንግስት መ/ቤቱ የቀረውን የግዥ ሂደት ለማጠናቀቅ የሚበቃውን ያህል ቀናት ብቻ መሆን አለበት። ሆኖም ተጫራቾች በማንኛውም ምክንያት ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ባይሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ዋስትና መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲወጡ ይደረጋል።

5) ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ የማሻሻል የቀረበላቸውን ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች ጥያቄውን መቀበላቸውን እና የመቆያ ጊዜውን ያራዘሙት እስከመቼ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሑፍ ማረጋገጥ አለባቸው። በተመሳሳይ ሁኔታም ለዚህ ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ዋስትና መቆያ ጊዜ ማሻሻል ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 5 በተገለጸው መሰረት የጨረታ ዋስትናውን ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያላሻሻለ ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውድድር ውጭ እንዲሆን ይደረጋል።

116. የጨረታ ማስከበሪያ

1) ከምክር አገልግሎት እና ከዋጋ ማቅረቢያ ግዥ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ግልፅ ወይም ውስን ወይም የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ በጨረታው ሰነድ ውስጥ ለእያንዳንዱ ግዥ የሚጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በግልፅ መወሰንና ማመልከት አለባቸው። ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊነቱን መ/ቤቱ ካመነበት ለምክር አገልግሎት ግዥም ቢሆን ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያሲዙ ሊጠይቅ ይችላል።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት ለሚፈጸም ግዥ፣ ለኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ እና እንደ ግዥው ባህሪ እንዲሁም

4. The extension period requested in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall be limited to the number of days reasonably necessary for the Public Body to finalize the remaining stages of the procurement process. Should any bidder decline to extend the validity period for any reason, such bidder shall be disqualified from further participation in the procurement process, without forfeiture of their bid security.

5. Bidders who agree to extend the validity period of their bids shall confirm such agreement in writing, indicating the specific number of days for which the extension is granted. In addition, such bidders shall either extend the validity period of the bid security accordingly or furnish a new bid security covering the extended period.

6. Any bidder who fails to extend the validity period of their bid security in accordance with Sub-Article (5) of this Article shall be deemed to have refused to extend the validity period of their bid and shall be disqualified from the procurement process.

116. Bid Security

1. Except for procurements conducted through consultancy services and the price quotation method, Public Bodies shall clearly specify and include the bid security requirement in the bidding documents for all procurements conducted using open bidding, limited bidding, or the two-stage bidding method. However, where deemed necessary, the Public Body may require the submission of bid security for consultancy services as well, taking into account the specific nature of the procurement.

2. Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, for procurements conducted under Sub-Article (8) of Article 36 of the Proclamation, for electronic tenders, and for other procurement methods, the Public Body may, based on the urgency or nature of the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

አስቸኳይነት ለሌሎች የግዥ ዘዴዎች በጨረታ ማስከበሪያ ምትክ የጨረታ መተማመኛ ቅጽ ፈርመው እንዲያቀርቡ ሊጠየቅ ይችላል።

3) የመንግስት መ/ቤቱ የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሰረት በማድረግ ከ0.5% ያላነሰ እና2% ያለልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ወስኖ በጨረታው ጥሪው እና በጨረታ ሰነዱ ውስጥ መግለፅ ይኖርበታል። በዚህ መሠረት የሚወሰነው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከብር 2,000,000 (ሁለትሚሊዮን ብር) የበለጠ መሆን የለበትም።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተገለጸው መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ማስከበሪያ መጠንን ለመወሰን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፦

ሀ/ የሚገዛው ዕቃ/አገልግሎት የዋጋ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭ መሆን፣

ለ/ በጨረታው የሚሳተፉ በቂ ተወዳዳሪዎች መኖር፣

ሐ/ ተጫራቾች እንዲያቀርቡ የሚጠየቀው ዋስትና በጨረታው እንዳይሳተፉ እንቅፋት እንደማይሆን፣

መ/ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ እንዲሆን የሚገፋፋ፣

ሠ/ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆን ዋስትናው በመ/ቤቱ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ የሚመጥን መሆኑን፣

5) በዚህ አንቀጽ የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ምርጫው መጀመሪያ በመንግስት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት መሆን አለበት። ሆኖም በዚህ መልኩ የጨረታ ማስከበሪያው የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደተጫራቹ ምርጫ ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ፣ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሊሆን ይችላል።

6) ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ 28 ቀናት ፀንቶ መቆየት አለበት፡

procurement, require bidders to submit a signed bid security declaration form in lieu of a formal bid security.

3. The Public Body shall determine the bid security amount to be no less than 0.5% and no more than 2% of the total estimated cost of the procurement, and shall indicate this amount clearly in both the invitation to bid and the bidding documents. In any case, the bid security amount shall not exceed Ethiopian Birr 2,000,000 (Two Million Birr).

4. When determining the appropriate amount of the bid security as provided in Sub-Article (3) of this Article, the Public Body shall consider the following factors:

a) The degree of price volatility of the goods, works, or services to be procured;
b) The expected level of competition and number of prospective bidders;
c) Whether the required bid security amount may unduly discourage participation;
d) Whether the security will serve as an incentive for the successful bidder to enter into contract negotiations and execute the contract;
e) Whether the security amount is sufficient to compensate the Public Body for any loss or damage resulting from the failure of the successful bidder to sign the contract.

5. The bid security required under this Article shall be submitted through the government's electronic procurement system. The bid security may be provided in one of the following forms, at the discretion of the bidder: a certified bank payment order, an unconditional bank guarantee, or a bank-confirmed letter of credit issued by a recognized financial institution.

6. The bid security submitted by bidders shall remain valid for a minimum of twenty-eight (28) calendar days beyond the last date of validity of the bid price.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

7) የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ባንኮች የተሠጠ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በአገር ውስጥ ባንኮች ማረጋገጫ ያገኘና በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መሆን ይኖርበታል።

117. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ

ተጫራቾች የጨረታ ጥሪው ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጨረሻው የመዝጊያ ሰዓት ድረስ የጨረታ ሰነዳቸውን ማስገባት እንዲችሉ ጨረታው ክፍት ሆኖ መቆየት ይኖርበታል።

118. <u>የጨረታ አከፋፈት</u>

1) ጨረታው የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ከሆነ በማሻሻያው ላይ በተገለጸው ቀን፣ሰዓት ይሆናል። ጨረታው ሲከፈትም፡-

ሀ/ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በቀጥታ የጨረታውን ሥነ ስርዓት ሊከታተሉ በሚችሉበት ሁኔታ ይሆናል። ሆኖም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ በቀጥታ መከታተል ባይችል የጨረታውን መከፈት አያስተጓጉልም፣

ለ/ የጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ መሳተፍ የሚፈልግ የውስጥ አዲት ባለሙያ፣ የፀረ-ሙስና መኮንን እንዲሁም ማንኛውም የመገናኛ ብዙሐን ድርጅት ወኪል ወይም ሌሎች ፍላጎት እና ጥቅም ያላቸው ሰዎች በታዛቢነት መሳተፍ ቢፈልጉ የጨረታውን የአከፋፈት ሥርዓት በበየነ መረብ መከታተል እንዲችሉ ይፈቀዳል፣

ሐ/ ከግዥ ሥራ ክፍል ቢያንስ 3 ባለሙያዎች በጨረታ አከፋፈት ሂደቱ ላይ መሳተፍ አለባቸው። እስከተቻለ ድረስ የግዥው ተጠቃሚ ከሆኑ ሥራ ክፍሎችየሚወከሉ ባለሙያዎች በአከፋፈት ስነ-ስርዓቱ ላይ ሊገኙ ይችላሉ።

2) የመንግስት መ/ቤቱ የግዥ ሥራ ክፍል የጨረታውን አከፋፈት ሂደት ቃለ-ጉባዔ መያዝ አለበት። ይህ ቃለ-ጉባዔም የተጫራቾቹን ሥም፣ ያቀረቡትን ዋጋ እና በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ የተነሡ ሌሎችንም አስፈላጊ ነጥቦች የሚይዝ ይሆናል። ቃለ-ጉባዔውም በጨረታው ላይ

7. Foreign bidders shall submit bid security instruments issued by foreign banks that are certified by a domestic bank operating in Ethiopia. Such security shall be unconditional and not subject to any contingencies.

117. Submission of Bidding Document

Bidders shall be permitted to submit their bid documents from the date of the bid announcement until the specified closing date and time. The bid submission system shall remain open and accessible to bidders until the final closing deadline.

118. Opening of Bids

1. Bids shall be opened on the date and time specified in the bid announcement or as amended. During bid opening:

   a) The opening shall be conducted in a manner that allows bidders or their authorized representatives to observe the process. The absence of a bidder or their representative shall not invalidate the bid opening.

   b) An internal audit professional and an anti-corruption officer may attend the bid opening. Additionally, representatives from the media or any other interested parties may observe the process remotely via the internet, if they so desire.

   c) The bid opening shall be conducted by three professionals from the procurement unit. Where possible, experts from the requesting unit may also be present.

2. The bid opening shall be recorded in formal minutes, capturing the names of the bidders, their offered prices, and other key

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ለተሳተፉት ተጫራቾች በየአድራሻቸው ሊላክላቸው ይገባል።

3) ማንኛውም በጨረታ መክፈቻ ሥርዓት ላይ ያልተከፈተና ለተጫራቾች ያልተነበበ የመጫረቻ ሰነድ ለቀጣይ ውድድር አያገለግልም።

4) ማናቸውም ተጫራች በጨረታ መክፈቻ ሂደት ወቅት ከጨረታው ውጭ አይደረግም።

5) ማናቸውም ተጫራች በጨረታ መክፈቻ ሂደት ወቅት ከጨረታው 1 ሰዓት ቀደም ብሎ የጨረታ መክፈቻ ቁልፉን መላክ የሚኖርበት ሲሆን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መላክ ካልቻለና መ/ቤቱ ለተጫራቹ መጠበቂያ ጊዜ ብሎ በሚያሳውቀው ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ ይህ ተጫራች ያቀረበው የመጫረቻ ሰነድ አይከፈትም።

6) የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በአንድ ላይ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ከሆነ መ/ቤቶች፡-

ሀ/ እንያንዳንዱ ተጫራች ያቀረበውን የመጫረ
ሰነድ በመክፈት የተጫራቹን ስም፣
ለ/ተጫራቹ ያቀረባቸው የቅድመ ብቃት መረጃዎች
ለውሉ ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅና
መጠንና ሁኔታውን፣
ሐ/የጨረታ ማስከበሪያ ዓይነትን እና መጠን እና
መ/ማናቸውንም የተጫራቾች አንጻራዊ ደረጃቸው
ለማወቅ ይረዳቸዋል ተብለው የሚታሰበ
ሌሎች ሁኔታዎችን ማሰማት አለባቸው።

7) የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በተለያየ ሁኔታ እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ፡-

ሀ/ በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ስርዓት የቴክኒ
ሰነዱየያዘው ሀሳብ እንዲከፈት ተደርጎ የተጫራቹ
ማንነት ጨምሮ በወቅቱ ሊገለጹ የሚችሉ ነጥቦ
መሰማት አለባቸው።

information raised during the process. These minutes shall be sent to bidders at the addresses provided.

3. Any bid document not opened and read aloud during the bid opening shall not be considered in the subsequent evaluation.

4. No bidder shall be disqualified during the bid opening process.

5. Bidders participating in the government electronic procurement system shall submit their bid opening passwords one hour before the scheduled opening. If the password is not submitted on time, and the Public Body notifies the bidder of a waiting period, the bid document shall remain unopened.

6. When technical and financial documents are submitted together:

a) The names of the bidders shall be announced.

b) Submitted qualification documents, bid price, any discounts, and the type and amount of bid security shall be read aloud.

c) Other relevant details necessary for understanding the bidder's standing may also be disclosed.

7. When technical and financial documents are submitted in separate envelopes:

a) Only the technical proposal shall be opened initially, and the names and relevant details of the bidders shall be read out.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ለ/ የዋጋው ሀሳብ እስኪከፈት ድረስ ተጫራቾች በሚስጥር የያዙትን የዋጋ መክፈቻ ቁልፍ እንደያዙ ይቆያሉ::

ሐ/ በሚደረግላቸው ጥሪ መሰረት በቴክኒክ ግምገማ ያለፉ ተወዳዳሪዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ በቀጥታ በተገኙበት የዋጋ መወዳደሪያ ሀሳባቸው በግልጽ ይከፈታል::

መ/ ለዋጋ ውድድር ያለፉ ተወዳዳሪዎችን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 7 (ሐ) በተገለጸው መሰረት በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለግዥው ያቀረበውን ዋጋ የዋጋ ቅናሽ ካለው መጠኑን እና ሁኔታውን እንዲሁም ከዋጋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት::

119. የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት ግምገማ እና ማወዳደር

1) የመንግስት መ/ቤቱ ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ለቀጣዩ ዝርዝር የግምገማ ሂደት ሊያሳልፈው የሚችለው በተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በመክፈቻ ስነ-ስርዓቱ ወቅት የተከፈተ እና በአዋጁ አንቀጽ 24 እንዲሁም በዚህ መመሪያ እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን የቅድመ ሁኔታዎች ተፈላጊ ነጥቦች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው::

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግስት መ/ቤቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ የለባቸውም:-

ሀ/ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዘ፣

ለ/ በመ/ቤቱ የተጠየቁትን የሕጋዊነት ሠነዶች ያላቀረቡ ከሆነ፣

b) Bidders must keep their financial proposal passwords confidential until the financial proposals are to be opened.

c) The financial proposals shall be opened through the government electronic procurement system in the presence of those whose technical proposals have passed.

d) For bidders meeting the technical requirements, the financial proposal opening shall include the bidder's name, offered price, any discounts, and other price-related matters.

119. Preliminary Tender Evaluation and Comparison

1. The Public Body shall only proceed to detailed evaluation if the bid documents opened during the ceremony meet the preliminary conditions outlined under Article 24 of the Proclamation and this Directive.

2. Without prejudice to Sub-article 1 of this Article, the Public Body shall not allow a bidder to proceed to detailed evaluation if:

a) The required bid security is not submitted.
b) The bidder fails to submit mandatory legal documents as required.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2018

ሐ/ ሌሎች ወደ ዝርዝር ግምገማ ለማለፍ የተቀመጡ ሁኔታዎችን ያላሟላ፣

3) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ተጫራቾች በአዋጁና በጨረታ ሰነዱ የተጠየቁትን የህጋዊነት ማረጋገጫ ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ባያቀርቡም መ/ቤቱ እንደ ጥቃቅን ጉድለት በመቁጠር ከጨረታ መክፈቻ በፊት የተዘጋጀ ወይም የተሰጠ እስከሆነ ድረስ ከጨረታ መክፈቻ በኋላ እንዲያቀርብ በማድረግ ዕጩ ተጫራቹን ወደ ቀጣዩ የግምገማ ሂደት እንዲገባ ሊደረግ ይቻላል።

120. ዝርዝር ግምገማ

1) መንግስት መ/ቤቶች ተጫራቾች በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ እና በጨረታ ሰነዱ የተቀመጡ የቅድመ ብቃት ግምገማውን ያለፉ ተጫራቾች ብቻ የሚከተሉትን መስፈርቶች ተከትሎ ዝርዝር ግምገማ ማድረግ አለባቸው።

2) የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በአንድ ላይ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ሲሆን፣

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር ግምገማ ሲያከናውኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 109 መሠረት የቅድመ ብቃት መስፈርቶችን ያሟሉ ተጫራቾች በመ/ቤቱ የሚፈለገውን አነስተኛውን የጥራት መመዘኛ እና ሌሎች የተጫራቾችን ብቃት ለመገምገም በጨረታ ሰነዱ የተቀመጠ መሰረታዊ መስፈርቶችን ያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ በቅድሚያ የቴክኒክ ግምገማ ማከናወን አለባቸው።

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /ሀ/ መሰረት በመ/ቤቱ የሚፈለጉ ጥራት እና የተጫራች ብቃት መመዘኛ መስፈርቶችን ያሟሉ ተጫራቾች ብቻ የዋጋ ውድድር ማከናወን አለባቸው።

ሐ/ የመንግስት መ/ቤቱ የቴክኒክ ግምገማ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 123 ስለተሰበረ እና የተጋነነ ዋጋ የተመላከተውን ታሳቢ በማድረግ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበን ተጫራች የጨረታው አሸናፊ አድርጎ ይመርጣል።

c) The bidder does not meet the prequalification criteria set for the detailed evaluation stage.

3. Notwithstanding the provisions of this Article, if legal verification documents (excluding bid security) required by the tender are not submitted with the bid, the Public Body may consider the omission as a minor deviation and allow the bidder to submit such documents after bid opening, provided that the documents were issued before the bid closure.

120. Detailed Evaluation

1. The Public Body shall conduct detailed evaluations only for bidders who pass the prequalification stage, in accordance with the Proclamation, this Directive, and the bidding document, using the detailed evaluation criteria.

2. Where technical and financial documents are submitted together:

a) The Public Body shall conduct a detailed technical evaluation, in accordance with Article 109 of this Directive, to confirm that bidders who meet the preliminary qualifications also meet the minimum quality standards and other essential criteria as outlined in the bidding document.

b) Only bidders meeting the technical and capability criteria shall proceed to financial evaluation.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 9th of June 2023

3) የቴክኒክና የዋጋ ሠነዱ ለየብቻ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ሲሆን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዚህ መመሪያ መሰረት የቅድመ ብቃት ማረጋገጫን ያለፉ ተጫራቾችን የቴክኒክ ግምገማ ከዚህ እንደሚከተለው ማከናወን አለባቸው፡፡

ሀ/መ/ቤቱ ለቴክኒክ ግምገማ ያለፉ ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለጹ የቴክኒክ ግምገማ መስፈርቶችን ያሟሉ ስለመሆኑ መገምገምና የተገኘው ውጤት ስልጣን በተሰጠው አካል ከፀደቀ በኋላ ውጤቱን ለተጫራቾች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ መግለጽ አለበት፡፡

ለ/ የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉ ተጫራቾች የሚላክላቸው ማሳወቂያ የቴክኒክ ግምገማውን ያላለፉበት ምክንያት፣ እንዲሁም አቤቱታ ካላቸው አቤቱታቸውን ማቅረብ እንደሚችሉ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ በቴክኒክ ግምገማው ላይ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ አቤቱታው የግዥ ህጉን ተከትሎ የመጨረሻ እልባት እስኪያገኝ ድረስ የዋጋው መጫረቻ ሰነድ መክፈት የለበትም፡፡

ሐ/ አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ካገኘ በኋላ በቴክኒክ ውድድሩ ተቀባይነት ያላገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተመላሽ ይደረጋል፤

መ/ የቴክኒክ ውጤታቸው ተቀባይነት ላገኙ ተጫራቾች የሚላከው ማሳወቂያ የሚከፈትበትን ዕለትና ሰዓት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ ማሳወቂያውም በዕኩል ጊዜ እንዲደርሳቸው መደረግ እና ሁሉም ፈቃደኛ ተጫራቾች በጨረታው የዋጋ መጫረቻ ሰነድ የጨረታ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

4) በግምገማ ወቅት ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች እኩል ነጥብ ቢያገኙ በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት ለሀገር ውስጥ ምርት ወይም አገልግሎት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

c) The bidder offering the lowest evaluated price shall be selected as the winner, after verifying any unusually low or exaggerated pricing as required under Article 123 of this Directive.

3. Where technical and financial proposals are submitted separately:

a) The Public Body shall evaluate the technical proposals of prequalified bidders using the criteria in the bid document. Following approval by the Procurement Endorsing Committee, the evaluation results shall be communicated simultaneously to all bidders.

b) The notification to unsuccessful bidders shall state the reason for disqualification and inform them of their right to appeal. The financial proposals shall not be opened until any appeal is resolved in accordance with the procurement legal framework.

c) Once a final decision is made on an appeal, the bid security of bidders who did not pass the technical evaluation shall be returned.

d) Successful technical bidders shall be notified of the date and time of the financial bid opening, and sufficient notice shall be given to allow attendance.

4. If two or more bidders receive equal scores, preference shall be given to domestic goods

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመላከተው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል ነጥብ ያመጡ ወይም እኩል ተመራጭ የሆኑ ተጫራቾች በሚኖሩበት ጊዜ አሸናፊውን ለመለየት መ/ቤቱ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተወሰኑ መስፈርቶች ላይ የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል። ይህንንም ለማድረግ፡

ሀ/ እኩል የሚወጡ ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸው መስፈርቶች ቁጥር ከሦስት ያልበለጠ እና በአኃዝ ሊገለጽ የሚችል መሆን ይኖርበታል፣

ለ/ መስፈርቶቹ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተለይ በጨረታ ዝርዝር መግለጫ ላይ መገለጽ አለባቸው፣

ሐ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች እኩል መሆናቸው ሲረጋገጥ ይሄው ተገልፆላቸው መጀመሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፁት መስፈርቶች መሠረት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳባቸውን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፣

መ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ እስከተቻለ ድረስ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተገኙበት ተከፍቶ የሰጡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲነበብላቸው ይደረጋል፣

ሠ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ ተገምግሞ የተሻለ ሐሳብ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ይመረጣል፣

ረ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሠ" የተመላከተው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል የወጡት ተጫራቾች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ ባለማቅረባቸው ወይም ባቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ መሰረት በተደረገ ግምገማ በድጋሚ እኩል ቢሆኑ፣ እስከተቻለ ድረስ እኩል የሆኑት ተጫራቾች በተገኙበት አሸናፊው ተጫራች በዕጣ እንዲለይ መደረግ አለበት።

6) በጨረታ ውድድሩ ተካፋይ የሆነው አንድ ተጫራች ብቻ ከሆነ የመንግሥት መጨረታየቀረበው አንድ ተጫራች

or services in accordance with Article 21 of the Proclamation.

5. Without prejudice to Sub-article 4 of this Article, the Public Body may invite tied bidders to submit final competitive offers, provided that:

a) No more than three criteria are used for the final competition, and they must be quantitatively measurable.
b) These criteria must be clearly stated in the bidding document, particularly in the detailed bid data sheet.
c) Once a tie is confirmed, the bidders shall be asked to submit final competitive proposals based on the specified criteria.
d) The final proposals shall be reviewed under transparent conditions to ensure fairness.
e) The bidder submitting the most advantageous final proposal shall be declared the winner.
f) If a tie still exists after this evaluation, the winner shall be determined by lottery.

6. If only one bidder remains in the competition, the Public Body may declare them the winner without re-advertising the bid, provided that the final proposal is reasonable, aligns with prevailing market prices, and does not contravene the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ያቀረበው የመወዳደሪያ ሃሳብ አጥጋቢ እና ዋጋውም ተወዳዳሪ የገበያ ዋጋ መሆኑን እንዲሁም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ የሚገድቡ ምክንያቶች በጨረታ ሰነድ ላይ ያለመኖራቸውን በማረጋገጥ ድጋሚ ጨረታ ማውጣት ሳያስፈልግ የቀረበውን አንድ ተጫራች አሸናፊ ሊያደርግ ይችላሉ።

121. የዋጋ ግምገማ ስለማከናወን

1) ግዥው የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በተለያየ ሁኔታ እንዲቀርብ የተጠየቀ ሲሆን የዋጋ ውድድር የሚደረገው በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጡትን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርቶችን አሟልቶ ተቀባይነት ያገኙ የመጫረቻ ሰነዶች ብቻ ይሆናሉ።

2) ዝርዝር የዋጋ ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ተጫራቾች የሰጡት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋጋ ቅናሽ ታሳቢ ይደረጋል።

122. የሒሳብ ስህተቶችን ስለማረም

1) የመንግስት መ/ቤቱ በምርመራ ወቅት የተገኙ የሒሳብ ስህተቶችን ማረም ይችላል። እንደዚህ ያሉትን የማስተካከያ ዕርምጃዎች የመንግስት መ/ቤቱ በአስቸኳይ ለሚመለከተው ተጫራች ማሳወቅ አለበት።

2) ተጫራቹ በአዋጁ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በሒሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ የጨረታ ማስከበሪያው ተወርሶ ከጨረታው እንዲወጣይደረጋል።

3) የዚህ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለዕቃ፣ አገልግሎት እና ከምክር ውጭ አገልግሎት ግዥ የሚደረገው የሂሳብ ስሌት ተጫራቹካቀረበው የጨረታ ዋጋ ከ10(አስር በመቶ) በላይ ከሆነ ከውድድር ውጭ ይደረጋል፡

4) ግዥው በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚፈፀም ሆኖ ለግምገማ ዓላማ ሲባል በተለየ ሁኔታ እንዲቀርብ በጨረታ ሰነዱ ካልተገለጸ በስተቀር በተጫራቾች የሚቀርበው ዋጋና የሚካሄደው የጨረታ ግምገማ ታክስን ማካተት አለበት። ሆኖም በተጫራቹ ዋጋ ውስጥ ታክስ መኖሩንና አለመኖሩ ግልጽ ካልሆነ ዋጋው ታክስ እንዳካተት ተደርጎ ይቆጠራል፡

participation terms in the bidding document.

121. Financial Evaluation

1. Where technical and financial proposals are required to be submitted separately, price competition shall be limited to bids that meet the minimum technical criteria specified in the bidding document.

2. Unconditional price discounts offered by bidders shall be taken into account during financial evaluation.

122. Rectification of Arithmetic Errors

1. The Public Body shall have the right to correct any arithmetic errors identified during price evaluation, and such corrections shall be promptly communicated to the respective bidder.

2. In accordance with Article 52(3) of the Proclamation, if a bidder objects to the rectification of an arithmetic error, the bid shall be excluded from the procurement process.

3. Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, if the bidder's financial calculation exceeds ten percent (10%) of the total bid price for the procurement of goods, services, or non-consultancy services, the bid shall be excluded from the competition.

4. In international competitive bidding, unless otherwise stated in the bidding document, bid prices and evaluations shall include all applicable taxes. Where tax inclusion is unclear, the bid shall be treated as tax-inclusive.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

5) የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በተለያየ ሁኔታ እንዲቀርብ ተጠይቆ በቀረበ ጨረታ አሸናፊ ተደርጎ የሚመረጠው ተጫራች እንደ ግምገማ ዘዴው የሚወሰን ሆኖ የቴክኒክና የፋይናንስ አጠቃላይ ግምገማ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ ተጫራች ወይም የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርቶችን አሟልቶ ዝቅተኛ የመወዳደሪያ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች ይሆናል።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እንደተጠበቀ ሆኖ የግንባታ ሥራ ግዥን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 3መሰረትበግንባታ ሥራ ግዥ የተሳተፈ ማንኛውም የሥራ ተቋራጭ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሁኔታዎች አሟልቶ ከመ/ቤቱ የሚቀርብን የሂሳብ ስሌት ማስተካከያ መቀበል አለበት።

ሀ/ በመ/ቤቱ የተከናወነው የሂሳብ ስሌት ማስተካከያ በዚህ መመሪያ እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለጹ አሰራሮችን ተከትሎ የተከናወነ ሲሆን፣

ለ/ የተደረገው የሂሳብ ስሌት ተቋራጩ ካቀረበው ጠቅላላ የጨረታ ዋጋ ከ5 በመቶ የማይበልጥ ሲሆን፣

ሐ/ የሂሳብ ስሌት እርማት ከተደረገ በኋላ የተገኘው የተቋራጩ ዋጋ ከሌሎች ተቋራጮች በአንጻራዊነት ዝቅተኛ በመሆኑ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ከተገኘ፣

7) ከተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ ግድፈት ቢኖረውም በጨረታ ሰነዱ ከተዘረዘሩት ተፈላጊ ነጥቦች አንጻር ጉልህ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ የመንግስት መ/ቤቱ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል። ሆኖም ማናቸውም ልዩነት እስተቻለ ድረስ በገንዘብ ተገልጾ በጨረታው ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት።

8) በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ የሚቀመጡ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ለንዑስ አንቀጽ 7 አፈጻጸም ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ ልዩነቱ እንደ ጉልህ ልዩነት ሊቆጠር ይችላል።

ሀ/ የመጫረቻ ሰነዱ ተቀባይነት ቢያገኝ በውሉ ውስጥ የተጠቀሱ የዕቃዎችና የተያያዥ አገልግሎቶች ወሰን፣ ጥራት ወይም

5. The contract shall be awarded in accordance with the evaluation method requiring separate submissions of technical and financial proposals. The winning bidder shall either be the one with the highest combined score from both evaluations or the bidder who meets the technical criteria and offers the lowest evaluated price, as specified.

6. Without prejudice to Sub-Article (3) of this Article and Article 52(3) of the Proclamation regarding construction works:

a) Any contractor shall accept the financial adjustments proposed by the Public Body, provided such adjustments are in accordance with this Directive and the procedures set forth in the bidding document.

b) The financial adjustment shall not exceed five percent (5%) of the total bid price.

c) If, after adjustment, the contractor's bid remains competitively lower than that of other bidders, the contractor shall be declared the winner.

7. If the bid contains errors that do not constitute a material deviation from the essential requirements of the bidding documents, the Public Body may consider the bid as responsive. However, substantial deviations shall be quantified and re-evaluated.

8) If the conditions outlined in the standard bid document are met, any deviation identified in accordance to Sub-Article 7 of can be considered a major deviation.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አፈፃፀም ላይ የጎላ ልዩነት ይፈጥራል ተብሎ ሲታሰብ፣

ለ/ በውሉ ውስጥ የተጠቀሱ የግዥ ፈፃሚውን መብቶች ወይም የተጫራቹን ግዴታዎች የማዛባት እና ከጨረታ ሰነዶች ጋር ያለመጣጣም ሁኔታ ሲፈጠር፤ ወይም

ሐ/ በጨረታው ግምገማ ወቅት የታዩ መሰረታዊ ግድፈቶች እንዲስተካከሉ ተደርጎ ጨረታው ተቀባይነት ቢያገኝ በተጫራቾች መካከል ልዩነት ይፈጥራል ወይም የጨረታውን ውጤት ያስቀይራል ተብሎ ሲገመት።

a) Acceptance of the bid document leads to significant discrepancies tothe scope of goods and servives, quality, or performance expectations.

b) The contract alters the rights of the Public Body or the obligations of the bidder, creating inconsistencies with the bid documents; or

c) Fundamental errors identified during bid evaluation affect the bid's competitiveness or alter the final outcome.

123. <u>የተሰበረ ወይም የተጋነነ የጨረታ ዋጋ</u>

1) የዕቃ ግዥን በተመለከተ በተጫራቹ የቀረበው የጨረታ ዋጋ እንደቅደም ተከተላቸው ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በሚገኝ የዋጋ መረጃ፣ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የዋጋ መረጃ እንደሌለ ማረጋገጫ በሚሰጥበት ጊዜ እንደሁኔታው ከታወቀ አምራች፣ ይህም ካልሆነ ከመሥሪያ ቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መነሻ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት በሚገኘው የገበያ ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ10% (አስር በመቶ) የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ የጨረታ ዋጋ እንዲሁም የቀረበው ዋጋ ከ30% (ሰላሳበመቶ) ያነሰ ሲሆን እንደተሰበረ የጨረታ ዋጋ ይቆጠራል።

2) የምክር እና ከምክር ውጭ የሆነ የአገልግሎት ግዥን በተመለከተ ከመሥሪያ ቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መነሻ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት በሚገኘ የገበያ ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ10% (አስር በመቶ) የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ የጨረታ ዋጋ እንዲሁም የቀረበው ዋጋ ከ20% (ሃያ በመቶ) ያነሰ ሲሆን እንደተሰበረ የጨረታ ዋጋ ይቆጠራል።

3) የግንባታ ግዥን በተመለከተ በተጫራቹ የቀረበው የጨረታ ዋጋከምህንድስና ግምት ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ15% (አስራ አምስት በመቶ) የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ የጨረታ ዋጋ እንዲሁም

123. Unusually Low or Excessively High Bid Prices

1) In the procurement of goods, a bid shall be deemed an inflated bid if the offered price exceeds the prevailing market price by more than ten percent (10%) based on data from the Ethiopian Statistical Service. Where the Statistical Service confirms the absence of price data from known manufacturers, the bid shall be considered inflated if it exceeds the market price by more than ten percent (10%) as determined by a market price study conducted by the designated center upon the request of the procuring entity, and is condidered unsually low price if it is less than thirty percent (30%) below the other submitted bid prices.

2) In the procurement of consultancy and non-consultancy services, a bid shall be considered a broken bid if it is more than twenty percent (20%) lower than the market price established through a market study conducted by the designated center based on the request of the procuring entity, and is also more than twenty percent (20%) lower than other bid prices.

3) In the procurement of construction works, a bid shall be considered inflated if the price

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 27th of June 2023

በተጫራቹ የቀረበው የጨረታ ዋጋ ከምህንድስና ግምት ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ20% (ሃያ በመቶ) ያነሰ ሲሆን እንደተሰበረ የጨረታ ዋጋ ይቆጠራል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ለማወዳደሪያነት የሚውለው የምህንድስና ግምታዊ ዋጋ በግዥ ፈፃሚ የመንግስት መ/ቤቱ የተዘጋጀ እና ለግንባታው ግብዓት የሚሆኑ ሁሉም ዕቃዎች እና አገልግሎቶችበኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በሚገኘው የዋጋ መረጃ፣ የስታትስቲክስ አገልግሎት የዋጋ መረጃ እንደሌለ ማረጋገጫ በሚሰጥበት ጊዜ እንደሁኔታው ከታወቀ አምራች፣ ይህም ካልሆነ ከመሥሪያ ቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መነሻ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት የተዘጋጀ እና ቢያንስ በሦስት ወራት ውስጥ ወቅታዊ የተደረገ መሆን አለበት።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሰረት ከተጫራቹ የቀረበው ዋጋ የተጋነነ ሆኖ ሲገኝ የመንግሥት መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 26 (1(መ)) መሰረት ውል ከመፈረሙ በፊት ጨረታውን ወይም የመጫረቻ ሰነድን በማናቸውም ጊዜ ሙሉበሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግአለበት።

6) የመንግስት መ/ቤቱ በዚህ መመሪያ እና በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት ተጨማሪ ምርመራ ሳያከናውን የቀረበው የጨረታ ዋጋ የተሰበረ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ተጫራቹን ከውድድሩ ውጭ ማድረግ የለበትም።

7) የመንግስት መ/ቤቱ በቀረበው የጨረታ ዋጋ ላይ ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ እንዲያስችለው የተሰበረ የጨረታ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች ዝርዝር ማብራሪያ እና ተያያዥ ሰነዶች እንዲያቀርብ መጠየቅ አለበት።

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት መ/ቤቱ የሚጠይቀው ማብራሪያ ሌሎች በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ከሚገለጹት ነጥቦች በተጨማሪ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሊያካትት ይችላል።

ሀ/ተጫራቹ ባቀረበው ዋጋ ጥራቱንና የመ/ቤቱን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ለማመጠናቀቅ የሚያስችለው አሳማኝ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ፣

submitted exceeds the official engineering estimate by more than fifteen percent (15%), and considered broken if it is more than twenty percent (20%) below the same engineering estimate.

4) The engineering estimate used for comparison in accordance with Sub-Article (3) shall be prepared by the procuring Public Body based on price data for all inputs sourced from the Ethiopian Statistical Service. In the absence of such data, the estimate shall be based on a market price survey conducted by the designated center pursuant to a request from the procuring entity. This estimate must be updated at least once every three (3) months.

5) Where a bid is found to be excessively priced as defined under Sub-Articles (1), (2), or (3), the Public Body may, at any time prior to contract signature, reject the bid or bidding documents, in whole or in part, in accordance with Article 26(1)(d) of the Proclamation.

6) A bidder shall not be disqualified solely on the basis of a broken bid price without first conducting a thorough investigation as prescribed in this Directive and in the relevant standard bidding documents.

7) The Public Body shall request a bidder that has submitted a broken bid price to provide a detailed written explanation and supporting documentation that will allow the Public Body to conduct a proper review of the bid price.

8) The explanation requested in accordance with Sub-Article (7) may include, but is not limited to, the following:

a) Whether the bidder has a compelling reason or strategic interest in completing the contract at the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ለ/ሥራውን ማከናወን ወይም አቅርቦቱን መፈጸም የሚያስችለው የተለየ ዘዴ ያለው ስለመሆኑ፣

ሐ/ሥራውን ወይም አቅርቦቱን በዚህ ዋጋ ለመስራት ወይም ለመፈጸም የሚያስችለው የተለየ ምቹ ሁኔታ ወይም ሙያዊ መፍትሔዎች ያለው ስለመሆኑ፣እንዲሁም

መ/ ተጫራቹ ከዚህ ቀደም ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የገባቸውን ውሎች እና አፈጻጸም የሚያሳይ መግለጫ እና ሰነዶች፣

9) በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ እና በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ድንጋጌዎች መሰረት መ/ቤቱ በዚህ ረገድ የሚወስዳቸው ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆኖ መንግስት መ/ቤቱ ከተጫራቹ ማብራሪያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ10 የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ከተጫራቹ የቀረበውን ሀሳብ ተቀባይነት ስለማግኘቱ ወይም ስላለማግኘቱ ውሳኔውን ለተጫራቹ ማሳወቅ አለበት።

10) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት ከተጫራቹ የቀረበውን ኃሳብ የማይቀበለው ከሆነ የመንግሥት መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 26 (1(መ)) መሰረት ውል ከመፈረሙ በፊት ጨረታውን ወይም የመጫረቻ ሰነድን በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ አለበት።

105. <u>ያልተመጣጣነ የጨረታ ዋጋ</u>

1) ሌሎች ለዚህ አግባብ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ የሚቀመጡ አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ዋጋ ያልተመጣጣነ የጨረታ ዋጋ ሲሆን መንግስት መ/ቤቱ ለውሳኔ እንዲያመቸው ተጫራቹ ጠቅላላ ዋጋው ላይ የደረሰበትን የሚያሳይ የእያንዳንዱን ሥራ ወይም አገልግሎት ዝርዝር ዋጋ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።

2) መ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለተጫራቹ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት የቀረበው ዋጋ እና ሥራው ያልተመጣጣነ ሆኖ ሲገኝ፣ የመንግሥት መ/ቤቱ ተጨማሪ ከ5% (ከአምስት በመቶ) ያልበለጠ የውል ማስከበሪያ መጠየቅ አለበት።

proposed price in compliance with the Ministry's requirements;

b) Whether the bidder employs a different method of execution or supply that accounts for the reduced price;

c) Whether there are favorable conditions or professional solutions that enable the bidder to perform the contract at a lower cost;

d) Documents and statements evidencing the bidder's past contracts and performance over the preceding two (2) years.

9) Subject to any further decisions by the Ministry in accordance with the Proclamation, this Directive, and the standard bidding documents, the Public Body shall notify the bidder of its decision to accept or reject the justification submitted, within ten (10) working days of receiving the bidder's response.

10) If the justification is not accepted in accordance with Sub-Article (9), the Public Body may, at any time prior to signing the contract, reject the bid or the bidding document, in whole or in part, pursuant to Article 26(1)(d) of the Proclamation.

124. Unbalanced Bid Price

1. Subject to the procedures to be provided under the biding document for this purpose, if the winning bid price appears disproportionate relative to the services or goods to be provided, the Public Body may request a cost breakdown for each item or component.

2. If the breakdown confirms the disproportionality, the Public Body may require an additional performance

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 27th of June 2023

3) መ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለተጫራቹ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት የሚቀርበው ዋጋ እና ሥራው ካልተመጣጣነ ወይም ተጫራቹ ለማመጣጠን ፈቃደኛ ካልሆነ መ/ቤቱ በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ እና በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ የተገለጹ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል።

4) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ያልተመጣጣነ የጨረታ ዋጋ" ማለት በማንኛውም ጨረታ ከጠቅላላ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ውስጥ ለተወሰነ የሥራው ክፍል ከተጫራቹ የቀረበው ዋጋ ከስራው መጠን በአንጻራዊነት ሲታይ ያልተመጣጣነ ወይም እጅግ የተጋነነ ወይም እጅግ ያነሰ ዋጋ ነው።

3. If disproportionality persists or if the bidder refuses to provide clarification, the Public Body may take appropriate precautionary measures in accordance with the Proclamation, this Directive, and the standard bidding documents.

4. For the purpose of this Article,"Unbalanced bid price" refers to any price that, relative to the scope of work or service required, is excessively low, distorted, or unreasonably discounted.

125. ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ውይይት እና በመ/ቤቱ ስለሚጠየቅ ማብራሪያ

1) ጨረታ ከተከፈተ በኋላ የመወዳደሪያ ሀሳብን ለመገምገም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ከመጠየቅና ውል ከመፈፀም ጋር የተያያዙ ድርድሮችን ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር በግዥ ሂደት በማናቸውም ደረጃ ከተጫራቾ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ አይቻልም።

2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም፡-

ሀ/ በሁለት ደረጃ ጨረታ ልዩ ባህሪ ምክንያት ከተጫራቾች ጋር ውይይት፣ማድረግ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ዋጋን በማይነኩ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ መነጋገር፣ እንዲሁም

ለ/በዚህ መመሪያ መሰረት በሚከናወን ጥራትን መሠረት ያደረገ የምክር አገልግሎት ግዥ በሚከናወንበት ወቅት ፣ ከተጫራቾች ጋር ውይይት ማድረግ ይቻላል።

125. Discussions with Bidders and Clarifications Requested by the Public Body

1. No communication or relationship shall be established with bidders after bid opening, except to request clarifications necessary for bid evaluation or to discuss contract implementation.

2. Notwithstanding Sub-Article (1):
a) In two-stage bidding, discussions may be held on minor non-price-related issues due to the nature of the process.
b) For consultancy procurements where quality is a major factor, discussions are permitted in accordance with this Directive.

126. ጨረታን ማፅደቅ

1) መንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ግምገማውን የሚያከናውነው የግዥ የሥራ ክፍል ወይም

126. Endorsement of Bid

1. The Procurement unit that undertakes bid evaluation or a temporary committee established for bid evaluation, shall complete

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

እንደአስፈላጊነቱ ጨረታ ለመገምገም የተቋቋመው ጊዜያዊ ቡድን በተጫራቾች የተሠጠው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ግዥውን ለማፅደቅ ስልጣን ለተሠጠው አካል ማቅረብ አለበት፡

2) በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥውን እንዲያፀድቅ ሥልጣን የተሰጠው አካል ግዥው የመንግስት ግዥ አፈፃፀም ሥርዓትን የተከተለ እና የጨረታ ግምገማው በጨረታ ሰነዱ በተገለጸው መሥፈርት መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ ይሰጣል። ውሳኔውም ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ/ የግምገማው ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቀጣይ አፈፃፀሞች እንዲከናወኑ መፍቀድ፣

ለ/ ሪፖርቱን ባለመቀበል ግምገማው እንዲስተካከልና እንደገና እንዲከናወን ማድረግ፣ ወይም

ሐ/ እንደሁኔታው ጨረታን ለመሰረዝ በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ እና በጨረታ ሰነዱ የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ ግዥው እንዲሰረዝ፣

3) ግዥውን የሚያፀድቀው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው የግምገማ ሪፖርት ላይ ግምገማውን የሰራው ቡድን ወይም ኮሚቴ ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል።

4) በንዑስ አንቀጽ 2 /ለ/ ላይ በተገለጸው መሰረት ግዥውን የሚያፀድቀው አካል የቀረበውን የግምገማ የውሳኔ ሃሳብ ያልተቀበለ ከሆነ ምክንያቱን በመግለጽከዚህ በፊት ግምገማውን ላከናወነው ቡድን እንዲመለስ የሚያደርግ ሲሆን ገምጋሚ ቡድኑም ከአፅዳቂው አካል በተሠጠው አቅጣጫ መሰረት ግምገማውን እንደገና አከናውኖ የተስተካከለውን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም ገምጋሚ ቡድኑ ወይም ማንኛውም ገምጋሚ ቡድን አባል የግዥ አፅዳቂ አካሉ በሰጠው አቅጣጫ ወይም በግምገማ ውጤት ላይ የማይስማማ ከሆነ በግምገማ ሪፖርቱ ላይ ያልተስማማበት ሀሣብ ተገልፆ የግዥ

the evaluation within the validity period of the bids and submit the results, along with recommendations, to the authorized endorsing body for a decision.

2. Pursuant to the proclamation and this directive the authorized endorsing body shall, ensure that the procurement follows the government procurement legal framework and that the bid evaluation is in accordance with the criteria set in the bid documents, and shall make a decision. The decision may be one of the following:-

a) Approve the procurement by fully accepting the evaluation report so that subsequent procedures may proceed;
b) Reject the report and require the evaluation to be revised and re-conducted; or
c) Cancel the procurement if the circumstances set out in the proclamation, this directive, and the bid documents are met.

3. The endorsing body may request the evaluation team or committee to provide clarification on the submitted evaluation report, if necessary,

4. Pursuant to sub-article 2(b) above if the endorsing body does not accept the evaluation recommendation, it shall state the reasons and return to the evaluation team for revision, as per the direction forwarded by endorsing body the evaluation team shall undertake reevaluation and submit the revised report.

5. Nothwithstanding in Sub-article 4 above, if the evaluation team or any member of the evaluation team disagrees with the direction of endorsing body or the evaluation result, the dissenting opinion shall be recorded in the evaluation report, and the procurement shall proceed based on the decision of the endorsing body.

6. Without prejudice of this article, if a dispute arises between the endorsing committee and the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አፅዳቂ አካሉ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ግዥው እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

6) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በጨረታው ውጤት ላይ በሚቀርብ አቤቱታ መነሻነት በአጽዳቂ ኮሚቴው እና በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ መካከል ሀሳብ ልዩነት ቢፈጠር የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

127. <u>የጨረታ ውጤትን እና አሸናፊነት ማሳወቅ</u>

1) የመንግስት መ/ቤቶች የጨረታውን ዝርዝር ውጤት በአዋጁ አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ማሳወቅና የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት በመጠቀም መጫን አለባቸው፡፡

2) መ/ቤቶች የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በአንድ ላይ እንዲቀርብ ለተጠየቀ ጨረታ የሚደረገውየጨረታ ውጤት አገላለጽ በዚህ መመሪያ እንዲሁም የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በተለያየ ሁኔታ እንዲቀርብ ተጠይቆ በቀረበ ጨረታየሚደረገው የጨረታ ውጤት አገላለጽ የዚህን መመሪያ የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡

3) የጨረታው ውጤት ተጫራቾች ቅሬታ ካላቸው ለማቅረብ በሚያስችል መልኩ በዝርዝር መገለጽ አለበት፡፡

4) ለአሸናፊው ተጫራች ውል እንዲፈርም የሚላክለት የአሸናፊነት ማስታወቂያ በአዋጁ አንቀጽ 58 ከተገለጸው በተጨማሪ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቹ የቀረበውን የመጫረቻ ሐሳብ የተቀበለ መሆኑን፣

ለ/ ውሉ የሚፈጸምበትን ጠቅላላ ዋጋ፣

ሐ/ የማስረከቢያውን የመጨረሻ ቀን ፣

መ/ ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ በህጉ መሰረት የሚያስከትለውን ተጠያቂነት፣ እና

head of the Public Body regarding the complaint following the result of the bid, the decision of the head of the institution shall prevail.

127. Notification of Bid Evaluation Results and Award

1. Public Bodies shall publish detailed tender results via the electronic government procurement system, in accordance with Article 58(1) of the Proclamation.

2. Results shall be disclosed in accordance with this Directive, regardless of whether technical and financial proposals were submitted jointly or separately.

3. The results must be sufficiently detailed to allow bidders to raise objections if necessary.

4. The award notification to the successful bidder shall include:

   a) Acknowledgment of proposal receipt;
   b) The total contract price;
   c) The deadline for contract signing;
   d) Legal consequences of refusal to sign; and
   e) Any other relevant conditions.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ሠ/ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን::

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለተጫራቹ የሚላከው የአሸናፊነት ማስታወቂያ በመንግስት መ/ቤቱ እና በተጫራቹ መካከል እንደውል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም::

6) በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ውል ቢፈርምም በአዋጁና በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሰረት የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ካልቻለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ የመንግስት መ/ቤቱ በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመገምገም፣ እንዲሁምዋጋው ወቅታዊ እና አዋጭ መሆኑን በማረጋገጥ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች አሸናፊ ማድረግ ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል::

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 መሰረት ዋጋው ወቅታዊ እና አዋጭ መሆኑን ለማረጋገጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 119 የተጋነነ ዋጋን በተመለከተ የተቀመጡ ሁኔታዎችን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት::

8) የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተመላሽ ማድረግ አለበት:

ሀ/ ከአሸናፊ ተጫራቹ ጋር ውል ተፈርሞ ተጫራቹ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረበ ከሆነ፣

ለ/ የተሸናፊ ተጫራች ወይም የጨረታ ማስከበሪያውን የመጠቀሚያ ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያበቃ ከሆነ::

128. ድህረ ግምገማ

1) የመንግስት መ/ቤቶች እንደ አስፈላጊነቱ ውል ለአሸናፊው ተጫራች ከመሰጠቱ በፊት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጨረታው የቀረበውን መረጃ እና የተገቡት ግዴታዎችን ትክክለኛነት እና አዋጭነት ለማረጋገጥ ድህረ-ግምገማ ሊያካሂዱ ይችላሉ::

2) ድህረ-ግምገማው የሚያተኩረው ብልጫ ያገኘው ተጫራች በጨረታው ላይ ያሳወቀውን ህጋዊ አቋም፣ የፋይናንስ አቅም፣ የቴክኒክ እና ተዛማጅ ልምድ

5. The award notification to be sent pursuant to sub article 1 of this Article shall not constitute a binding contract between the public body and the bidder.

6. If the successful bidder refuses to sign the contract or provide the required performance guarantee, the Public Body may, after confirming price validity, award the contract to the next-ranked bidder or initiate a new tender.

7. In determining price validity under Sub-Article (6), the criteria under Article 119 of this Directive shall be used.

8. The public body shall return the bid security deposited by the bidders if it is satisfied that the following conditions are met:

a) If a contract has been signed with the winning bidder and the bidder has provided a bid security,
b) If the bid security validity period of the losing bidder or the bidder who refuses to extend the validity period of the bid security has expired.

128. Post-Qualification Evaluation

1. Public Bodies may conduct a post-qualification evaluation to verify the accuracy of information and capacity of the winning bidder before awarding the contract.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ለማረጋገጥ፤ተጫራቹ ያቀረበውን ዘዴ፣ የሥራ ዕቅድ፣ ሀብቶች እና የጊዜ ገደቦች ተጨባጭ እና ሊደረስባቸው የሚችሉ መሆናቸውን፤ተጫራቹ ያቀረበውን የዋጋ አወቃቀር ከገበያ ዋጋዎች ጋር የሚጣጣም እና የታቀደውን የሥራ ወሰን የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለመገምገም ሊሆን ይችላል።

3) የመንግስት መስሪያ ቤቶች ድህረ ግምገማውን ለማካሄድየሚከተሉትን ጨምሮ የተለያዩ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፣

ሀ/ በተጫራቹ የቀረቡ ወይም ከገለልተኛ ምንጮች የተገኙ ደጋፊ ሰነዶችን መመርመር፣

ለ/ ብቃታቸውን እና ሀብቶቻቸውን ለመገምገም የተጫራቹን ተቋማት ወይም የፕሮጀክት ቦታዎች መጎብኘት፣

ሐ/ ከተጫራቹ ቁልፍ ሰራተኞች ወይም ማጣቀሻዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣

መ/ ተጫራቹን ከጨረታቸው ጋር የተያያዙ ማብራሪያዎችን ወይም ተጨማሪ መረጃዎችን እንዲያቀርብ መጠየቅ።

4) ድህረ-ግምገማ እንደሚካሄድ፣ የድህረ-ግምገማው ወሰን እና ዘዴዎች፣ የድህረ-ግምገማ ውጤቶችን ለመገምገም የሚውሉ መስፈርቶች፣ ድህረ-ግምገማውን አለማለፍ የሚያስከትለው ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል፣ የድህረ-ግምገማው የሚካሄድበት ጊዜ፣ ተጫራቹ ከድህረ-ግምገማው ሂደት ጋር ሙሉ በሙሉ ለመተባበር ያለበትን ግዴታ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጨረታ ሰነዶች ውስጥ በግልጽ መግለጽ አለባቸው።

5) በድህረ-ብቃት ግምገማ ወቅት አሸናፊው ተጫራች በ15 ቀናት ውስጥ ተጨባጭ ሰነዶች እንዲያቀርብ ተጠይቆ ማቅረብ ካልቻለ ወይም ያቀረባቸው ሰነዶች

2. The post-evaluation may focus on verifying the winning bidder's legal standing, financial capacity, technical expertise, and relevant experience declared during the tender; the feasibility and achievability of the bidder's proposed methodology, work plan, resources, and timelines; the bidder's pricing structure to ensure alignment with market rates and adequacy for the project scope.

3. The Public Bodies may apply various methods, including the following, to conduct the post-evaluation:

   a) Reviewing documents submitted by the bidder or obtained from independent sources,
   b) Visiting the bidder's institutions or project sites to assess their capabilities and resources.
   c) Conducting interviews with the bidder's key personnel or references.
   d) Requesting the bidder to provide clarifications or additional information

4. The following shall be clearly stated in tender documents by the Public Bodies: Post-review process, the scope of the post-review, and the methods used, criteria used to evaluate post-review outcomes, the potential consequences of non-compliance with the post-review process, when the post-review will take place and the bidder's obligation to fully cooperate with the post-review process.

5. During the post-qualification evaluation process, if the winning bidder fails to submit the required supporting documents

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

የተሳሳቱ ሆነው ከተገኙ ጨረታው ውድቅ ይደረጋል፡ : በዚህ ጊዜ የግዥ ፈፃሚው አካል በሁለተኛ ደረጃ የጨረታ ሰነዱን ፍላጎቶች አሟልቶ ዝቅተኛ ዋጋ ወደ አቀረበው ተጫራች በማለፍ ብቃቱን ለማረጋገጥ በተመሳሳይ ሁኔታ በተጫራቹ ላይ አስፈላጊውን የድህረ-ብቃት ግምገማ ያከናውናል።

ምዕራፍ ስምንት

የግዥ ውል አስተዳደር እና የውል አለመግባባቶችን ስለመፍታት

129. <u>አጠቃላይ ድንጋጌዎች</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረትበመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚፈጸም ማንኛውም የግዥ ውል ወይም የውል ማሻሻያ በጽሑፍ መሆን አለበት፡

2) ውሉ በግዥ ፈፃሚው አካልና በአቅራቢው መሉ ስምምነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን የሚገባው ሲሆን ከዚህ በፊት በተዋዋዮቹ ወገኖች መካከል የነበሩት ሁሉም ግንኙነቶች፣ ድርድሮችና ስምምነቶች በዚህ ውል ይተካሉ።

3) በውሉ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣ የመንግሥት መ/ቤቶች የሚገቧቸው ውሎች በፍትሐብሔር ሕግ ስለ ውል የተደነገጉት ጠቅላላ እና የመንግስት አስተዳደር መ/ቤት ስሚያገርጓቸው ልዩ ውሎች የተደነገጉት እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚ የሚደረጉ ሲሆን ውሉ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሕጐች መሠረት የሚገዛና የሚተረጐም ይሆናል።

within 15 days or submits incorrect documents, the bid will be canceled. In such cases, the procurement entity will reassess the bid requirements and offer the contract to the next lowest-priced eligible bidder; the same post-qualification evaluation will be conducted to verify their eligibility.

CHAPTER EIGHT

PROCUREMENT CONTRACT MANAGEMENT AND RESOLVINGCONTRACT DISPUTES

129. General Provisions

1. Any procurement contract or amendment to an existing contract entered into by a Public Body pursuant to Article 61(2) of the Proclamation shall be made in writing.

2. The contract shall reflect the full and mutual agreement of the procuring entity and the supplier. It shall supersede and replace all prior communications, negotiations, and agreements between the contracting parties.

3. Unless otherwise expressly provided in the contract, the general provisions of the Civil Code governing contracts, as well as the relevant special provisions applicable to public administration, shall apply to procurement contracts entered into by Public Bodies. The contract shall be governed by, and interpreted in accordance with, the laws of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

130. <u>የግዥ ውል አዘገጃጀት</u>

1) በተወያይ ወገኖች መካከል የሚዘጋጀው የውል ሰነድ ባለስልጣኑ ያዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ ክፍል የሆኑትን አጠቃላይ እና ልዩ ልዩ የውል ሁኔታዎችን፣ እንዲሁም ሌሎች የውሉ አካል የሆኑ ሰነዶችን ያካተተና እንደአስፈላጊነቱ በህግ ባለሙያ፣ እንዲሁም በሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች አስተያየት የተሰጠበት መሆን አለበት።

2) የመንግስት መ/ቤቶች ባለስልጣኑ ካዘጋጀው የውልሰነዶች ውጭ ለመጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የባለስልጣኑን ፈቃድ አስቀድመው በማግኘት የተለዩ የውል ሰነድ ዓይነቶችን መጠቀም ይችላሉ።

3) የሚዘጋጀው የውል ሰነድ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሰረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸው ማረጋገጥአለበት፣

4) እንደአስፈላጊነቱ ሰነድ የተጫራቹንና የመንግስት መ/ቤቱን ግዴታና ኃላፊነት በግልጽ ያመላክተና በመ/ቤቱ ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሰረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥስፈላጊነቱ በህግ ባለሙያ፣ እንዲሁም በሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች አስተያየት የተሰጠ

5) የሚዘጋጀው የውል ሰነድ የአዋጁንና የዚህን መመሪያ መሠረታዊ የውል ድንጋጌዎችን፣ የሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ዋና ዋና መብትና ግዴታዎችን የያዘ፣ የመ/ቤቱን ጥቅም የሚያስጠብቅ እና የአቅራቢውን መብት ወይም ግዴታ አላግባብ የማያቀል ወይም የማያከብድ መሆን አለበት።

6) የመንግስት መ/ቤቱ የሚዘጋጁት የውሉ ሰነዶች እርስ በርሳቸው የሚመጋገቡ፣ የማይጣረሱ እና ግላጭ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

130. Preparation of Procurement Contract

1. The contract document shall incorporate standard bidding documents issued by the Authority, general and specific conditions of contract, and all other documents constituting the agreement. It shall be reviewed by legal experts and relevant units as necessary.

2. Public Bodies may, when necessary, use contract formats other than those prepared by the Authority, provided that prior approval is obtained from the Authority.

3. Obligations stipulated in the contract shall have a clear legal basis and be enforceable.

4. The contract document shall clearly outline the obligations and responsibilities of all parties and ensure these obligations are legally grounded and enforceable, with confirmation from legal experts and relevant work units.

5. The contract shall include the fundamental provisions mandated by the Proclamation and this Directive, set out the rights and duties of both parties, protect the Public Body's interests, and not exclude or impair the rights or obligations of the supplier.

6. The contract document shall be consistent, free from internal contradictions, and transparent.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2024

7) የተዘጋጀው የውል ሰነድ ውል ከመፈረሙ አስቀድሞ ለአቅራቢው መላክ ያለበት ሲሆን፣ የመንግስት መ/ቤቱ አቅራቢው የውሉ ቃላትና ሐረጎችን ለመረዳት በቂ ጊዜ የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት አቅራቢው በውል ሰነዱ ላይ የሚሰጠው አስተያየት በተዋዋይ ወገኖች የጋራ ስምምነት ሲደረስበት የውል ቃላትና ሐረጎች ውስጥ ሊካተት ይገባል።

131. <u>የውል ቅድመ ሁኔታዎች</u>

የመንግስት መ/ቤቱ ውል ከመፈረሙ አስቀድሞ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡-

ሀ/ አቅራቢው ውል ለመፈረም በአዋጁና በመመሪያው የተቀመጡ የብቃት መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ወቅታዊ ብቃት ያለው መሆኑን፣

ለ/ የሚፈጸመው ግዥ ዓይነትና መጠን፣ የውል ዋጋ፣ የአቅርቦት ጊዜ፣ በቂ በጀት እና ለውሉ አፈጻጸም ውጤታማነት እና ቅልጥፍና የሚያስፈልጉ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን፣

ሐ/ የጨረታው የአሸናፊነት ውጤት በህጉ መሰረት ለሁሉም ተጫራቾች የተገለጸና ቅሬታ ወይም ይግባኝ ቀርቦ ከሆነ የመጨረሻ እልባት ያገኘ መሆኑን፣

መ/ የውሉ ሰነድ የመ/ቤቱን የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ ውል እንዲፈርም ውክልና የሰጠውን ኃላፊ ይሁንታ ያገኘ መሆኑን።

132. ውል መፈረም

1) ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት የጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር ለዚሁ ዓላማ ተብሎ የተዘጋጀውን እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን የውል ቃሎች እና ልዩ ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሰነድ መፈራረም አለበት።

7. Prior to signature, the contract document shall be provided to the supplier, allowing sufficient time to review its contents.

8. Any feedback from the supplier on the draft contract shall be incorporated into the final version upon mutual agreement between the parties.

131. Preconditions for Contract Signing

Before signing the contract, the Public Body shall ensure the following:

a) The supplier meets the competency requirements under the Proclamation and this Directive, with up-to-date qualifications to perform the contract.

b) The procurement type and scope, contract value, delivery timeline, budget availability, and other essential prerequisites are met.

c) The bid award decision has been disclosed to all bidders as required by law, and, where no complaint or appeal has been submitted, final approval has been obtained.

d) The contract has been approved by the head of the Public Body or an authorized signatory.

132. Contract Signing

1. The Public Body shall sign the contract, incorporating agreed-upon terms, special conditions, and contractual clauses, with the successful bidder.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

2) በመንግሥት መ/ቤት እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈረመ አይቆጠርም፡ ፡

3) በመንግስት መ/ቤቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል የሚፈረመው ውል የጸና የሚሆነው ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በፊርማ ሲያረጋግጡ ብቻ ነው።

4) የመንግስት መ/ቤቱ በውል ሰነድ ላይ የሚሰፍሩ ኃላፊነቶችን እና ግዴታዎችን በጥንቃቄ መመርመር ያለበት ሲሆን በመ/ቤቱ ደረጃ ሊፈጸሙ የማይችሉ ግዴታዎችን ተቀብሎ ውል መፈረም የለበትም።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም አለበት። ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መ/ቤት የጨረታውን ወይም የቅሬታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለጸበት ቀን ጀምሮ 7 የሥራ ቀናት ከመሙላቱ በፊት የግዥ ውል መፈረም የለበትም።

6) በአሸናፊው ተጫራች እና በመንግስት መ/ቤቱ መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች ኃላፊነት በግልፅ ማመልከት ያለበት ሲሆን፣ የሚከተሉትን ጉዳዮች በተጨማሪነት ያካተተ መሆን ይኖርበታል፦

ሀ/ በውሉ የሚቀርበው ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ስራ ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች ዓይነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የሚቀርብበት አኳኋን ወይም የማስረከቢያ ጊዜውን፣ የሚከፈለውን አጠቃላይ እና የነጠላ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፣

ለ/ የውል ጊዜው መቆጠር የሚጀምርበት ቀን፣

ሐ/ የውል ማሻሻያ የሚደረግ ከሆነ የውል ማሻሻያው የሚደረግበትን አግባብ፣

2. A contract is not deemed concluded merely upon announcement of the winning bidder; it must be formally signed.

3. The contract shall only become binding when both parties sign it.

4. The Public Body shall ensure it fully understands and is capable of fulfilling the obligations outlined in the contract before signing.

5. The successful bidder shall sign the contract within 15 days from the date of award notification. The Public Body shall not sign the contract until 7 working days have passed from the notification of the award or complaint resolution.

6. The contract entered into between the Public Body and the winning bidder shall clearly define the obligations of both parties and shall include, at a minimum, the following elements:

a) A detailed description of the type, quality, quantity, method and period of delivery of the goods, construction works, consultancy services, or other services to be provided under the contract; the total and unit prices; the terms and schedule of payment;
b) The effective commencement date of the contract;
c) The procedures and conditions under which amendments to the contract may be made;
d) The responsibilities for third-party services—such as transportation, insurance, transit arrangements, and other similar services—shall be clearly

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2022

መ/ ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን እንደ ትራንስፖርት፤ ኢንሹራንስ፤ ትራንዚት እና የመሳሰሉ ተግባራትን የመከታተል እና የመፈፀም ኃላፊነት የማን እንደሚሆን መጠቀስ ያለበት ሲሆን ኃላፊነቶቹም በተሻለ ብቃት ሊፈፅማቸው በሚችል አካል እንዲሰሩ መደረግ ይኖርበታል፤

ሠ/ አቅራቢው በመጫረቻ ሰነዱ ላይ ያመለከተው የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን እና አፈጻጸማቸውን በውሉ ላይ በግልጽ ያመላከተ መሆን አለበት፤

ረ/ በውል አፈጻጸም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አካሄድ መገለጽ አለበት፤

ሰ/ ከውጭ አገር ለሚቀርቡ አቅርቦቶች ከጠቅላላው የውሉ መጠን ውስጥ በውጭ አገር ገንዘብ እና ከአገር ውስጥ ለሚቀርቡ አቅርቦቶች በብር ሊከፈለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ድርሻ ተለይቶ መገለጽ ይኖርበታል፤

ሸ/ የውል አካል የሆኑ የግዥ ሰነዶች እና በመካከላቸው ልዩነት ሲኖር የበላይነት የሚኖረውን ሰነድ፤

ቀ/ ለውል አፈጻጸም የተያዘው የውል ማስከበሪያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፤

በ/ አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፤ ምክር አገልግሎቱን፤ የግንባታ ዘርፍ ስራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ፤ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ፤ እንዲሁም፤

ተ/ በመንግስት መ/ቤቱ እና በአቅራቢው መካከል ሊኖር የሚገባውን የግንኙነት አግባብ፤ እና ሌሎች ለውሉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች።

defined and assigned to the party or parties best qualified to manage and perform such services;

e) Any price reductions, discounts, or other commercial conditions offered by the supplier in the bidding document and accepted by the procuring entity shall be explicitly incorporated into the contract, along with the terms and method of their implementation;

f) The dispute resolution mechanism to be applied in the event of disagreements during contract execution shall be clearly stated;

g) The breakdown of the contract price indicating the portion payable in foreign currency for goods or services delivered from abroad, and the portion payable in Ethiopian Birr for those delivered domestically;

h) The procurement documents that form part of the contract, and the specific document that shall take precedence in the event of inconsistency or conflict between them;

i) The conditions under which the performance security may be forfeited due to non-performance or breach of contractual obligations;

j) The consequences and penalties applicable if the supplier fails to deliver goods, consultancy services, construction works, or other services within the contractually agreed period; the required communications between the Public Body and the supplier; and any other provisions necessary to ensure proper contract performance.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

133. የተዋዋይ አካላት ኃላፊነት

1) ሌሎች በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ እና በውል ሰነዱ ላይ የተገለጹ መብትና ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አቅራቢው የሚከተሉት ኃላፊነቶች አለበት፣

ሀ/ ዕቃውን፣ አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ስራውን በውሉ ላይ በተገለጸው ዓይነትና መጠን፣ የጥራት ደረጃ፣ እንዲሁም ሌሎች ግዴታዎችን በውሉ ጊዜ ውስጥ መፈጸም፡፡

ለ/ በውሉ አፈጻጸም ወቅት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ሙሉ ኃላፊነት መውሰድ፡፡

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በስራ ላይ ላሉ ተፈጻሚ የሆኑ ህጎች ማክበርና በአዋጁ፣ በመመሪያው እና በውሉ ለተቀመጡ የሥነ ምግባር ደንቦች ተገዥ መሆን፡፡

2) ሌሎች በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ እና በውል ሰነዱ ላይ የተገለጹ መብትና ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

ሀ/ ለውሉ በአዋጁ፣ ቅልጥፋና እና ውጤታማነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፎችን፣ እገዛዎችንና ፈቃዶችን መጠየቅና እገዛ ማድረግ፣

ለ/ አቅራቢው በውሉ መሰረት ግዴታውን መወጣቱን ሲያረጋግጥ ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ መፈጸም፣

ሐ/ አቅረቢው የውል ግዴታውን እየተወጣ እንደሚገኝ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በወቅቱ መስጠት፣

መ/ የውል አፈጻጸምን አስመልክቶ ከአቅራቢው ለሚቀርብ ማንኛውም ጥያቄ በህጉና በውሉ መሰረት ፈጣን ምላሽ መስጠት፡፡

133. Responsibilities of the Contracting Parties

1. The provider shall have the following responsibilities, without prejudice to the rights and obligations under the Proclamation, this Directive, and the contract:
   a) Deliver goods, services, or construction works in the agreed type, quantity, and quality standards within the stipulated timeframe.
   b) Assume full responsibility for all acts performed during contract execution.
   c) Comply with applicable Ethiopian laws, adhere to the provisions of the Proclamation, this Directive, and maintain ethical standards throughout performance.
2. The Public Body shall have the following responsibilities to ensure that the rights and obligations specified in the proclamation, this directive, and the contract document are properly observed:
   a) Request and provide necessary support, assistance, and approvals from relevant entities to ensure the contract's validity, efficiency, and effectiveness
   b) Make timely payments upon verifying the provider's fulfillment of contractual obligations.
   c) Submit evidence confirming the provider's compliance with contractual duties promptly
   d) Provide swift responses to any inquiries from the provider regarding contract execution, in accordance with the law and the contract

Uploaded on the Website of the Ministry of Planning on the 5th of June 2025

134. ውልን ይፋ ስለማድረግ፣

1) በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚፈጸሙ ሚስጢራዊ ግዥዎች ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 63 መሰረት ዋና ዋና የውል መረጃዎችን ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለበት።

2) ባለስልጣኑ ለዚህ ዓላማ የሚያዘጋጀው ቅጽ ቢያንስ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል።

ሀ/ የውሉ ርዕስ፣

ለ/ የግዥውን ዘዴ፣ዓይነትና መጠን፣

ሐ/ የአቅራቢውን ሙሉ ስምና አድራሻ፣ እንዲሁም የተጠቃሚ ባለቤትነት መረጃዎች

መ/ የመንግስት መ/ቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ፣ እና

መ/ የግዥውን የውል ዋጋ፣ውሉ የሚጀመረበት እና የሚጠናቀቅበትን ጊዜ።

135. ውል ስለማሻሻል

1) በአዋጁ አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአቅራቢው መካከል የሚፈጸም ማንኛውም የግዥ ውል ወይም የውል ማሻሻያ በጽሑፍ መሆን አለበት።

2) በውል አፈጻጸም ወቅት እንደሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም።

3) ማንኛውም በውሉ ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች በፅሑፍና በተዋዋይ ወገኖች ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት መፈፀም አለበት። በፅሑፍ የሚደረጉት የውል ለውጦች ለቀጣይ

134. Disclosure of Contract

1. Except for confidential procurements, the Public Body shall publicly disclose key contract information as required by Article 63 of the Proclamation.
2. The disclosure form prepared by the Authority shall include at least the following:

   a) Contract title.
   b) Procurement method, type, and quantity.
   c) Full names and addresses of the supplier and its beneficial owners,
   d) Full names and addresses of the Public Body.
   e) Contract price, start date, and completion date.

135. Contract Amendment

1. Pursuant to Article 61(2) of the Proclamation, any procurement contract or amendment thereto entered into between a Public Body and a supplier shall be made in writing.
2. A contract may be amended during its performance where necessary, provided that such amendment does not adversely affect the interests of the Public Body and does not confer any undue advantage on the supplier over other bidders who participated in the same procurement process.
3. All amendments to the contract must be in writing and signed by the duly authorized representatives of both parties. Any written amendment shall be deemed an integral part of the original contract and shall form part

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

አፈጻጸም የዋናው ውል ሰነድ አካል ተደርገው ይቆጠራሉ።

4) በፅሑፍ የሚደረጉት የውል ማሻሻያዎች ተግባራዊ የሚሆኑት በተፈረመው የፅሑፍ ሰነድ ላይ ከሰፈረበት ቀን ጀምሮ ይሆናል። በግልፅ ስምምነት ካልደተረገ በስተቀር ወደ ኋላ ተመልሶ ተግባራዊ አይሆንም፡

5) በውል አፈጻጸም ወቅት በሚቀርበው ዕቃ ወይም ምርት ላይ በቴክኖሎጂ ምክንያት የሚፈጠሩ ለውጦች በውሉ ላይ ከተገለጸው የጥራት ደረጃ ያላነሰ እስከሆነ ድረስ በመንግስት/ቤቱ ወይም በአቅራቢው ጥያቄ መነሻነት በውል ማሻሻያ ሊካተቱ ይችላሉ።

6) በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት የሚደረግ ማሻሻያ አጠቃላይ የውል ዋጋ ላይ ጭማሪ የሚያስከትል መሆን የለበትም።

136. የውል ማስከበሪያ

1) በዋጋ ማቅረቢያ፣ በመንግሥት መ/ቤቱ ቁጥጥር ስር ለሚሆኑ ንብረቶች የኪራይ አገልግሎት ግዥ፣ ወጪን በመሸፈን ከመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤት ግዥ መፈፀም ሲያስፈልግ እና በለቀማ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር ለማናቸውም ሌላ የግዥ ውል የመንግስት መ/ቤቱ የውል ማስከበሪያ መቀበል አለበት።

2) የዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለዋጋ ማቅረቢያ፣ ለኪራይ አገልግሎት ግዥ እና ለለቀማ ግዥ መ/ቤቱ በዚህ መመሪያ አባሪ 8 መሰረት የውል ማስከበሪያ መተማመኛ ቅጽ ማስፈረም አለበት።

3) የጨረታው አሸናፊ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 116 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ለጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት እንዳላቸው በተገለፁት የዋስትና ዓይነቶች መሠረት ክፍያ በሚፈፀምበት የገንዘብ ዓይነት ቢያንስ የውሉን ዋጋ 10 (አስር በመቶ) በውል ማስከበሪያነት ለመንግስት መ/ቤቱ በማቅረብ ውል መፈረም አለበት።

4) የመንግስት መ/ቤቱ አቅራቢው በውሉ መሰረት ግዴታውን ሳይወጣ ቢቀር ለመውረስ እንዲያስችለው ተጫራቹ የሚያቀርበው የውል ማስከበሪያ ከውሉ ጊዜ ቢያንስ ለተጨማሪ 28 ቀናት ፀንቶ መቆየት አለበት።

of the contractual obligations for purposes of implementation and enforcement.

4. Written amendments shall take effect from the date they are incorporated into the signed contract document, unless expressly agreed otherwise. Retroactive effect shall not be presumed and must be explicitly stated in the amendment.

5. Where technological advancements lead to changes in the goods, works, or services to be supplied, such changes may be incorporated into the contract through a written amendment, upon the request of either the Public Body or the supplier. However, the substituted items or services must be of equal or superior quality to those originally specified in the contract.

6. Except as otherwise permitted under the Proclamation or this Directive, no amendment made pursuant to this Article shall result in an increase in the total contract price.

136. Performance Security

1. For procurement involving price offers, rental services of properties controlled by the Public Body, and cost-reimbursement purchases (excluding direct purchases), the Public Body shall require contract security.

2. Notwithstanding sub-article 1, for price offers, rental services, and direct purchases, the Public Body shall use a contract security confirmation form as per Appendix 8 of this Directive.

3. The winner of the bid must sign the contract by submitting at least 10 (ten percent) of the contract price to the Public Bodies according to the types of securities that are accepted as bid security in accordance with Article 116, Sub-Article 5 of this directive.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

5) የመንግስት መ/ቤቱ አቅራቢው በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥ በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት አቅራቢው ያስያዘው የውል ማስከበሪያ ሙሉ በሙሉ መውረስ ወይም በውል ማስከበሪያ መተማመኛ ቅጽ መሰረት እርምጃ መውሰድ አለበት።

6) በንዑስ አንቀጽ 6 የተገለጸው ቢኖርም በአቅራቢው ያልተሟላው የውል ግዴታ በመ/ቤቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ተጨማሪ ወጪ እንደማያስከትል እና በአቅራቢው ቸልተኝነት ምክንያት የተፈፀመ አለመሆኑ በመ/ቤቱ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሲታመንበት የውል ማስከበሪያው ለአቅራቢው ሊመልስለት ይችላል።

7) የመንግስት መ/ቤቱ በዚህ ንዑስ አንቀፅ 6 መሰረት ለወሰዳቸው እርምጃዎች የተሟላ ሰነድ በመያዝ በባለስልጣኑ ወይንም በሌላ ጉዳዩ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል ሲጠየቅ ማቅረብ እና የአሰራሩን አግባብነት ማስረዳት አለበት።

8) በንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው ቢኖርም፡-

ሀ/ ከአገር ውስጥ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ተቋራጮች ወይም መድሐኒት እና የሕክምና መሣሪያዎች አምራች ድርጅቶች ለሚፈጸም ግዥ ከታወቀ የመድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የመድን ዋስትና ቢያቀርቡ ተቀባይነት ይኖረዋል።

ለ/ የምክር አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሠማሩ አማካሪዎች በሚሰጡት የምክር አገልግሎት ሂደት ውስጥ በመ/ቤቱ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ተብሎ ሲገመት የባለሙያ የካሣ መድን እንዲሁም ለአገር ውስጥ የምክር አገልግሎት ሰጪዎች ከታወቀ የመድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የውል ማስከበሪያ እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይቻላል፣

ሐ/ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በዚህ መመሪያ በተገለጸው መሠረት በውል ማስከበሪያ ምትክ ካደራጃቸው ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።በዚህ መልኩ የሚቀርበው የድጋፍ ደብዳቤ ዋስትና የተሰጠበትን የገንዘብ መጠን በመጥቀስማህበራቱን ባደራጃቸው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የተፈረመ መሆን አለበት።

4. The security shall remain valid for at least 28 days beyond the contract period to ensure compliance.

5. Should the supplier fail to perform according to contract, the Public Body shall enforce the performance guarantee accordingly.

6. If the Public Procurement Endorsing Committee determines that the failure caused no damage or additional cost and was not due to negligence, the performance guarantee may be returned.

7. The Public Body shall retain documentation of actions taken under this provision and provide justification upon request by authorized or legal entities.

8. Additional provisions include:

a) Domestic contractors and manufacturers of pharmaceuticals and medical equipment may submit unconditional guarantees from reputable insurance companies, which shall be accepted.

b) Consultancy service providers suspected of potentially harming the Public Body may be required to provide professional liability insurance and, where appropriate, conditional performance guarantees.

c) Small and micro-enterprise associations must submit a letter of

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

መ/ የመድን አገልግሎት ግዥ ለመፈፀም በወጣ ጨረታ አሸናፊ የሚሆኑ የመድን ድርጅቶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ያስቀመጡትን ገንዘብ በውል ማስከበሪያነት ለመጠቀም ይችላሉ። ሆኖም በዚህ መንገድ ለሚያስይዙት ዋስትና በቂ መጠባበቂያ ያላቸው ስለመሆኑ ከባንኩ ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው።

9) በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ወይም በአዋጁና በዚህመመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የተያዘው የውል ማስከበሪያ አቅራቢው የውልግዴታውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ መመሰስ አለበት።

137. ውልን ተፈፃሚ ስለማድረግ

1) የመንግስት መ/ቤቶች የተለየ ሁኔታ ካላጋጠማቸው በስተቀር ከአቅራቢዎች ጋር የተደረጉ የውል ስምምነቶች በተያዘላቸው ጊዜ ውስጥ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ አለባቸው።

2) በውሉ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች በአዋጁና በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ያለው የውል ማስከበሪያ እስካላቀረበ ድረስ ውሉ ተፈጻሚ አይሆንም።

3) ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተመለከተውን ተግባራዊ ለማድረግ ውሉ የሚያስቀምጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም አለበት፦

ሀ/ ውሉ ቅደሚያ ክፍያ እንዲፈፀም የሚያዝ ከሆነ በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት አቅራቢው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንዲያሲዝ በማድረግ የቅድመ ክፍያውን በወቅቱ መፈፀም፣

ለ/ በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ ሊከፈትላቸው ለሚገባ ግዥዎች ተገቢው ፎርማሊቲ መሟላቱን በማረጋገጥ በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ሰነዱ በፍጥነት መክፈት፣

ሐ/ በመ/ቤቱ ሊፈፀሙ የሚገቡ ተጨማሪ ተግባራትን በውሉ መሰረት በወቅቱ ማከናወን።

support from the issuing institution specifying the guaranteed amount and signed by the head of the Public Body.

d) Companies providing guarantee services may use funds deposited with the National Bank of Ethiopia as performance guarantees, subject to bank confirmation.

9. Unless otherwise agreed, the party responsible for contract obligations shall return the performance security upon contract completion.

137. Implementation of Contract

1. Contracts shall be enforced within stipulated timelines except in exceptional circumstances affecting the Public Body.
2. Contract guarantees required by law or this Directive must be submitted before enforcement.
3. The Public Body shall ensure timely fulfillment of obligations, including:

   a) Providers securing priority payment guarantees and timely receipt of advance payments where applicable.
   b) Completion of formalities for bank-confirmed payments.
   c) Timely execution of additional contract obligations by the Public Body.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

4) የመንግስት መ/ቤቶች ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ በአቅራቢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው በውሉ መሰረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈፀሙን ተከታትለው ማረጋገጥ አለባቸው።

5) የመንግስት መ/ቤቶች የውሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ውሉ ተፈፃሚ መሆን የጀመረበትን ቀን መዝግበው መያዝ እና እንደ አስፈላጊነቱም አቅራቢው እንዲያውቀው ማድረግ አለባቸው።

138. <u>የውል አፈፃፀምን መከታተል</u>

1) የመንግስት መ/ቤቶች የውል አፈፃፀምን የሚከታተል አካል መለየት ወይም የውል ክትትል በተለያዩ አካላት በቅንጅት የሚፈፀም በሚሆንበት ወቅት አካላቱ ተግባራቸውን በግልፅ እንዲያውቁ ማድረግ አለባቸው፡ ፡

2) የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የመንግስት መ/ቤቱ አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን በዚህ መመሪያ አባሪ 9 ላይ በተቀመጠው ቅጽ መሰረት መከታተል አለበት።

3) በውልአፈፃፀም ክትትል ወቅት የመንግስት መ/ቤቶች በተለይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም አለባቸው።

ሀ/ ተቀባይነት የሚኖራቸውን በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ ማስተካከያ ጥያቄዎች ተቀብሎ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣

ለ/ ተገቢው አገልግሎት ከመገኘቱ በፊት የውል ማስከበሪያ፣ በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ፣ የጥራትዋስትናመጠቀሚያ ጊዜዎች እንዳያልፉ ጥንቃቄ እና ክትትል ማድረግ፣

ሐ/ የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መገንባታቸውን፣ የዕቃ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች በውሉ ጊዜ ውስጥ ለመከናወናቸው ክትትል መደረጉን እና ሪፖርት መቅረቡን፣

4. The Public Body shall monitor contract execution tasks performed by the provider for compliance.
5. The Public Body shall document the date of contract effectiveness and inform the provider accordingly.

138. Follow-up of Contract Implementation

1. Responsibility for contract monitoring shall be clearly assigned and activities made transparent.
2. The Public Body shall monitor supplier contract execution as outlined in Annex 9 of this Directive.
3. Monitoring shall include:

a) Accepting and promptly responding to requests for adjustments to bank-guaranteed payment documents.
b) Ensuring contract validation before service commencement, including monitoring guarantees and warranties.
c) Tracking construction deadlines, material deliveries, and progress reporting.
d) Exercising diligence to prevent unjustifiable claims by contractors.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

መ/ ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ከአቅራቢዎች ምንም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳይፈጠሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፣

4) የመንግስትመ/ቤት በውል አፈፃፀም ወቅት ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን መለየት እና አገልግሎቶቹ የመ/ቤቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ እና የውል አፈፃፀሙን ውጤታማነት በሚያግዝ መልኩ መሰጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

139. <u>የቅድመ ክፍያ አከፋፈል</u>

1) በመንግስት አፈፃፀም እንደአስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30 (ሠላሣ ከመቶ) የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል። የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠን በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ እና በልዩ የውል ሁኔታ ላይ መገለፅ አለበት።

2) በዋጋ ማቅረቢያ፣ በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ጨረታ ከሚፈፀም ግዥ፣ ከኪራይ አገልግሎት ግዥ፣ ወጪን በመሸፈን ከመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤት ግዥ መፈፀም ሲያስፈልግ እና እና በለቀማ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር አቅራቢዎች በውሉ መሰረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡

3) በዚህ በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተው ቢኖርም የአገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እንዲሁም የመድሀኒት እና ሕክምና መሳሪያ አምራች ኢንዱስትሪዎች በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከታወቀ የመድን ድርጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡

4) በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ በተደረገ ውል መሰረት ለሚፈፀም የቅድሚያ ክፍያ የቀረበው ዋስትና የመድን ድርጅት ሲሆን ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ከሆነ ውል ሰጪው የመንግስት መ/ቤት ውል ተቀባይ ከሆነው ሥራ ተቋራጭ ወይም አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋም ጋር የቅድሚያ ክፍያውን አጠቃቀም

4. The Public Body shall identify and ensure proper provision of third-party services related to the contract to protect its interests and ensure effective implementation.

139. Disbursement of Advance Payment

1. Up to 30% (thirty percent) of the total contract price may be paid as an advance payment based on the necessity of Public performance. The amount of advance payment to be provided shall be specified in the tender details table and the special contract conditions
2. Except for procurements conducted through price quotations, electronic reverse auctions, rental services, expenses covered by Public budgetary Body, and procurements conducted on an emergency basis, bidders are required to provide an advance payment guarantee equivalent to the advance payment requested in the contract. This guarantee may take the form of a certified payment order from a recognized bank or an unconditional bank guarantee, as chosen by the bidder
3. Notwithstanding the provisions of sub-section 2 above, domestic construction companies and pharmaceutical and medical device manufacturing industries may submit advance payment guarantees issued by recognized insurance institutions if the guarantee is conditional
4. For construction sector contracts under sub-section 3, the advance payment guarantee shall be issued by an insurance company. If the advance payment is designated for micro and small enterprises, the public Body awarding the contracts hall enter into a separate agreement with the contractor or micro and small enterprise regarding the use

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

በሚመለከት የተለየ ውል መዋዋል አለበት። ውሉም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት።

ሀ/ በውሉ መሰረት ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ የሚፈፀመው የቅድሚያ ክፍያ ለዚሁ ዓላማ በሥራ ተቋራጩ ወይም በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ ስም በሚከፈት የተለየ የባንክ ሂሣብ ውስጥ እንደሚቀመጥ፣

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" መሠረት በተከፈተው ሂሣብ ውስጥ የተቀመጠው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ወጪ ሊደረግ የሚችለው በውል ሰጪ እና በውል ተቀባዩ የጣምራ ፊርማ እንደሚሆን፣

ሐ/ በባንክ ሂሣቡ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ ክፍያ የሚፈፀመው ቀደም ሲል በወሰደው ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሠራ መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን፣

መ/ በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚከፈለው ገንዘብ ውስጥ ለመንገድ ሥራ የአገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ 50% (ሃምሳ በመቶ) እንዲሁም ለሕንጻ ሥራ የአገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ 30% (ሰላሳ በመቶ) ለመሣሪያ መግዣ ማዋል የሚችሉ መሆኑን፣ የሚገልጹ አንቀጾችን ሊይዝ ይችላል።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4(መ) በተመለከተው መሠረት መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ ከፊሉን ለመሣሪያ መግዣ እንዲያውሉ ሊፈቅድ ይችላል።።

ሀ/ የሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ በወሰደው ገንዘብ የገዛውን መሣሪያ በውሉ መሠረት ፕሮጀክቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለዕዳ መያዣነት የማያውል እና በማናቸውም መልክ ለሦስተኛ ወገን የማያስተላልፍ ለመሆኑ ማረጋገጫ የሚያቀርብ ከሆነ፣

ለ/ የሥራ ተቋራጩ የቅድሚያ ክፍያ አከፋፈል ስምምነት ከመፈረሙ በፊት በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚወስደው ገንዘብ የሚገዛቸውን መሣሪያዎች ዓይነት ለአሠሪው መ/ቤት ተቆጣጣሪ መሐንዲስ አቅርቦ መሠሪያዎቹ ለሥራው አስፈላጊ መሆናቸው ከተረጋገጠ፣

of the advance payment. This agreement shall include the following provisions.

a) In accordance with the agreement, the advance payment to the contractor or the micro and small enterprise shall be deposited into a separate bank account opened in the name of the contractor or the micro and small enterprise for this purpose.
b) Funds deposited in theaccountmentioned in clause "A" above may only be expended with the joint signature of the contracting party (provider) and (recipient).
c) For payments made to the contractor or to a small and micro enterprise from the funds deposited in the bank account, it shall first be verified that the appropriate work corresponding to the utilized funds has been completed
d) It may include provisions stating that, from the advance payment made, local contractors may allocate up to 50% for road works and up to 30% for building works to purchase equipment.

5. Pursuant this Article Sub-Article 4(d) of this Article, the Public Body may permit domestic contractors to allocate a portion of the advance payment provided to them for equipment purchases, provided the following conditions are met

a) If the contractor submits verification that the equipment purchased with the advance payment will not be used as collateral before the project's completion and will not be transferred to any third party in any form;
b) If, before signing the advance payment agreement, the contractor demonstrates to the supervising engineer of the employer that the types of equipment to be purchased with the advance payment are essential for the project;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ሐ/ መሣሪያዎቹ ከፕሮጀክቱ ባለቤት ፈቃድ ውጪ ከፕሮጀክቱ ወደ ሌላ ቦታ እንደማይንቀሳቀሱ ማረጋገጫ ከቀረበ፣

6) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ተቋራጩ በተከፈለው የቅድመ ክፍያ መሣሪያውን ስለመግዛቱ ህጋዊ ማስረጃ እንዲያቀርብ በማድረግ ማረጋገጥ አለበት።

7) በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚከፈል ገንዘብ ለመንገድ ሥራ እንዲሁም ለሕንጻ ግንባታ የሚገዙት ማሽነሪዎች በአባሪ 10ላይ የተመለከቱት ብቻ ናቸው፡

8) የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 በተመለከተው መሠረት በተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልገ መሣሪያዎቹን ወደ ፕሮጀክቱ ቦታ ካላጓጓዘ በውሉ መሰረት ሊከፈለው የሚገባው የሚቀጥለው ክፍያ አይፈፀምለትም።

9) የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጩ ወይም አነስተኛ እና ጥቃቅን ማህበራት የሚወስዱትን የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በውሉ መሠረት በየደረጃው ከሚዘጋጁት የክፍያ ምስክር ወረቀቶች ወይም በየደረጃው ከሚፈፀመ አቅርቦቶች ሂሳብ ላይ እየተቀነስ እንዲመለስ መደረግ አለበት።

140. የዋጋ ማስተካከያ

1) የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ 12 ወራት እና ከዚህ በላይ ለሚቆዩ ለግንባታ ስራዎች፣ እንዲሁም 6 ወራት እና ከዚያ በላይ ለሚቆይ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግ አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት አለበት።

ሀ/ ለግንባታ ሥራ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከስድስትወራት በኋላ ሲሆን፣ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ ደግሞ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከሶስት ወራት በኋላ ለሚኖረው የዋጋ ለውጥ ነው።

ለ/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው እንደቅደም ተከተላቸው ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት በሚገኝ የዋጋ መረጃ፣

c) If proof is provided that the equipment will not be relocated from the project site without the owner's consent.

6. The procurement Public Body shall verify, pursuant to Sub-Article 5, that the contractor presents legal proof of purchasing the equipment using the advance payment made

7. The funds paid as an advance payment for machinery purchased for roadworks and building construction are limited to those specified in Appendix 10

8. If the domestic contractor fails to transport the equipment required for the construction work to the project site using the advance payment provided under this Article (Sub-Article 6), the subsequent payment due under the contract shall not be executed

9. The advance payment received by the domestic contractor or micro small enterprise shall be deducted progressively from the payment certificates prepared at each stage or from the accounts of executed supplies, as stipulated in the contract

140. Price Adjustment

1. The Public Body shall specify in advance in the bid document that price adjustments will be made for construction projects lasting 12 months or longer, as well as for procurement activities under framework agreements lasting 6 months or longer.

a) For construction projects, price adjustments are implemented six months after the contract becomes effective, while for procurement under framework agreements, adjustments are made based on price changes occurring three months after the contract's effective date.

b) Based on this article, price adjustments shall be made in the following order of precedence: Primarily, using price

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የዋጋ መረጃ እንደሌለ ማረጋገጫ በሚሰጥበት ጊዜ እንደሁኔታው ከታወቀ አምራች፣ ይህም ካልሆነ ከመሥሪያቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ባለስልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናት በሚገኝ የገበያ ዋጋ መረጃ መሰረት ብቻ ነው።

ሐ/ የማዕቀፍ ግዥን በተመለከተ የገበያ ዋጋቸው በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ ለሆኑ ምርቶች ወይም አቅርቦቶች በውሉ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው በየሶስት ወራት ለሚኖር የገበያ ዋጋ ለውጥ ብቻ ነው።

መ/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ የሚደረገው በመ/ቤቱ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው።

2) የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶች ለተካተቱበት ግዥ በሚያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሁኔታዎች፣ በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፡-

ሀ/ ዋጋ ማስተካከያውን ተግባራዊ ለማድረግ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ያለባቸውን የመረጃ አይነት፣

ለ/ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች፣ የአቀራረብ ዘዴውን እና ከዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ዓይነትና መጠን፣

ሐ/ ሌሎች ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም ይጠቅማል ተብሎ የሚታመንባቸውን መረጃዎች እና ተጫራቾች ሊከተሉት ይገባል የሚላቸውን አሰራሮች፣

3) የመንግስት መ/ቤቱ በጨረታ ግምገማ ወቅት ለዋጋ ማስተካከያ ዓላማ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ተጫራቾች መቀበላቸውን እና ያቀረቧቸው ማስረጃዎችም ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

4) የመንግስት መ/ቤቱ እና በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በሚያደርጉት የውል ስምምነት ላይ የሚከተሉት

information available from the Central StatisticsService. If such data from the Ethiopian Statistics Service is unavailable and a confirmation of this is provided, then price data from a known local manufacturer may be used

c) For framework agreement procurement, price adjustments are applied every three months for goods or services with highly volatile market prices, unless otherwise specified in the contract.
d) Price adjustments under this clause require approval by the Public Body's procurement endorsing commeettee to take effect.

2. For items or services subject to Public Body price adjustments, the procuring public body shall clearly specify in the bidding document the following and any other relevant conditions deemed necessary for the procurement in which they are included

a) The type of information bidders shall submit with their bid documents to implement the price adjustment
b) The conditions under which the price adjustment request may be submitted, the procedure for submission, and the type and amount of evidence to be provided in relation to the price adjustment request,
c) Other information deemed necessary for the execution of the price adjustment and procedures bidders shall follow.

3. The Public Body shall verify that the bidders have accepted the preconditions set for price adjustment purposes during the tender evaluation and that the evidence they have presented is acceptable
4. The Public Body and the winning bidder shall ensure that the following conditions, along with other appropriate terms deemed reliable, are explicitly included in the contract agreement they enter into

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2025

እና ሌሎች ተገቢ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ሁኔታዎች በግልፅ እንዲካተቱ መደረግ አለበት።

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸውን ግብዓቶች በመጠቀም የሚመረቱ ዕቃዎችን ወይም አቅርቦቶችን ዝርዝር እና የማስተካከያውን አፈፃፀም፤

ለ/ ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም የመንግስት መ/ቤቱ እና አቅራቢው የተስማሙበት የሰነድ ዓይነት እና ምንጭ፤

ሐ/ ለዋጋ ማስተካከያ የሚቀርበው ማስረጃ በውሉ ላይ በተገለፀው መሰረት መሆን እንዳለበት እና ከሌላ ምንጭ የሚመጣ መረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው፤

መ/ ለአቅራቢው የሚሰጠው የግዥ ትዕዛዝ የጠቅላላ ፍላጎቱን ግምታዊ ክፍፍል መሰረት ያደረገ እስከሆነ ድረስ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት በወቅቱ ስራውን ወይም አቅርቦቱን ማከናወን ባለመቻሉ የሚፈጠረ የዋጋ መናር ማስተካከያ የሚደረግበት ስለመሆኑ፤

5) በማንኛውም ዕቃ እና ከምክር ውጭ አገልግሎት ላይ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ጭማሪ ከመጀመሪያው የውል ዋጋ 30% (ሠላሳ በመቶ) በላይ መሆን የለበትም።ሆኖም የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ከዚህ መጠን በላይ በሚሆንበት ጊዜ የመንግሥት መ/ቤቶች ጥያቄውን ለገንዘብ ሚኒስቴር እያቀረቡ አሳማኝ ሲሆን የዋጋ ማስተካከያው ሊደረግ ይችላል።

6) የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ ለተፈቀደበት ማንኛውም ግዥ ከአቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ባይቀርብም ክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው በውል ስምምነቱ በተፈቀዱ ግብዓቶች ላይ የዋጋ መቀነስ መኖር አለመኖሩን የማጣራትና የዋጋ ቅናሽ ካለም አስልቶ ከቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ ከቀነሰ በኋላ መክፈል አለበት።

7) የመንግስት መ/ቤቱ በንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት ከክፍያው ላይ ከመቀነሱ አስቀድሞ የተስተካከለውን ዋጋ ለአቅራቢው በጽሁፍ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን፣ ይህም የውል ሰነዱ አካል ሆኖ ይቆጠራል።

a) Detailed list of items or supplies produced using the inputs subject to price adjustment, and the implementation of the adjustment;

b) The type and source of the document agreed upon between the Public Body and the Supplier for the execution of the price adjustment

c) The documentation submitted for price adjustment shall be based on the criteria specified in the contract, and any information coming from other sources shall not be accepted

d) Until the procurement order issued to the supplier is based on an approximate allocation reflecting the total requirement, any price adjustment necessitated by the supplier's inability to perform the work or supply in accordance with the contractual agreement during the stipulated period shall be implemented.

5. For any item and service other than consultancy, the price adjustment increase shall not exceed 30% (thirty percent) of the original contract price. However, if a price adjustment request exceeds this limit, Public Body may submit the request to the Ministry of Finance with justification, and the adjustment may then be implemented

6. For any procurement where a price adjustment has been approved, even if the supplier does not submit a price adjustment request, when a payment request is presented, the Public Body shall verify whether there is a price reduction applicable to the contractually approved deliverables. If a price reduction exists, it shall be deducted from the submitted payment request before processing

7. The Public Body pursuant to Sub-Article 6, shall notify the provider in writing of the adjusted price before implementing the deduction. This notification shall constitute an integral part of the contract document.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

141. ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 140 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጹት ዝርዝር ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ከግንባታ ስራ ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በታች የተገለጹትን አሠራሮች ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም የሚሰላ ይሆናል።

ሀ/ ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችና በእያንዳንዱ ዋና ግብዓት ሥር ሊካተቱ የሚችሉ ዕቃዎችን ስብስብ መለየት፣

ለ/ በስራቸው የተለያዩ ዕቃዎች ስብስቦችን የያዙት ዋና ዋና ግብዓቶች፣ ከግንባታ ስራው ጠቅላላ ግብዓቶች ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በማስላት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን እና የማይደረግባቸውን መወሰን፣

ሐ/ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በሥራ ላይ ያለ የቅርብ ጊዜ ዋጋ ኢንዴክስ/ጠቋሚ አሃዝ በቀመሩ መሰረት የዋጋ ማስተካከያውን ለማስላት በመነሻነት ይወሰዳል፣

መ/ ለግንባታ ስራ ግዥ የዋጋ ልዩነት የሚሰላው በስራ ላይ ያለውን ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ/ጠቋሚ አሃዝን በመጠቀም በቀመሩ መሰረት ይሆናል፣

ሠ/ የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ለተቋራጩ የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከጠቅላላ የግንባታ ሥራው የውል ዋጋ 25% (ሃያ አምስት ከመቶ) መብለጥ የለበትም። ሆኖም የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ከዚህ መጠን በላይ በሚሆንበት ጊዜ የመንግሥት መ/ቤቶች ጥያቄውን ለገንዘብ ሚኒስቴር እያቀረቡ አሳማኝ ሲሆን የዋጋ ማስተካከያው ሊደረግ ይችላል።

141. Price Adjustment for the Procurement of Construction Works

Pursuant to Article 140 sub article 1 of this Directive, price adjustments for construction-related procurement shall comply with the prescribed conditions and be calculated according to the formula set forth in the standard bidding document, following these procedures:

a) Identify the primary inputs required for the construction work and categorize the items included under each primary input;

b) Determine the groups of items within each primary input, calculate their proportion relative to the total inputs of the construction work, and specify which inputs are eligible for price adjustments and which are not;

c) The price index reflecting recent market prices in effect prior to the tender closing date shall be the baseline for calculating price adjustments according to the formula;

d) Price differentials for construction procurement shall be calculated using the current price index applicable during the execution period, in accordance with the formula;

e) When applying price adjustments, the total adjustment granted to the contractor shall not exceed twenty-five percent (25%) of the total contract value. Should the price adjustment claim exceed this threshold, the relevant Public Body may submit a request for approval to the Ministry of Finance,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ረ/ ስራ ተቋራጩ በውል ስምምነቱ መሰረት መስራት ላልቻላቸው እና ዘግይተው ለተሰሩ የግንባታ ሥራዎች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው የግንባታ ሥራዎቹ መሰራት በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሰረት ብቻ ይሆናል።

142. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

1) በማዕከል ለሚፈፀም የማዕቀፍ ስምምነት ግዥዎች የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ሊቀርብ የሚገባው በማዕከል የማዕቀፍ ግዥን ለመፈፀም ለተቋቋመው መ/ቤት መሆን ያለበት ሲሆን መንግሥት መ/ቤቶች በተናጠል ለሚፈጽሙት የማዕቀፍ ግዥ ::

2) የመንግስት መ/ቤቶች በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ ዋጋ ማስተካከያ ሊያደርጉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፤

ሀ/ በማዕቀፍ ስምምነት መሰረት ተፈፃሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለ ከሶስት ወራት በኋላ ሊሆን ይገባል።

ለ/ በማዕቀፍ ሥምምነት ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግ የሚገባው አቅራቢው ተጠይቆቢያንስ በዓመት ሊያቀርብ ከሚገባው የውል መጠን አንድ አራተኛውን ካቀረበ በኋላ ብቻ ነው፤

ሐ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ በጨረታው መክፈቻ ጊዜ ያለ የቅርብ ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት ወይም የታወቀ አምራች ወይም መ/ቤቱ ያጠናው የገበያ ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ after which the adjustment may be implemented;

f) For delayed or incomplete construction works, price adjustments shall be calculated solely based on the prices effective during the originally planned construction period.

142. Price Adjustment for Procurement Conducted through Framework Agreements

1. Price adjustment requests related to centrally administered framework agreement procurements shall be submitted to the Public Body designated to oversee the framework procurement process. Separate procedures shall apply to purchases conducted independently by other government offices.

2. The Public Body may approve price adjustments for framework agreement procurements under the following conditions:

a) Price adjustment requests may be submitted only after three months from the effective date of the agreement;
b) Adjustments require that the supplier has delivered at least one-quarter (1/4) of the contracted annual volume before the request is submitted;
c) Adjustments shall be referenced against current market prices for the goods or services at the time of tender opening or adjustment request, as verified by the Ethiopian Statistics Service, recognized

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

የሚደረግበት ጊዜ በማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ መገለፅ አለበት::

መ/ መንግስት መ/ቤቱ በሁለቱም ዋጋዎች መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነት በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨምረ ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት::

ሠ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት ማቅረብ ሲገባው በወቅቱ ላላቀረባቸው እና ዘግይተው ለቀረቡ አቅርቦቶች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው አቅርቦቶቹ መቅረብ በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሰረት ብቻ ይሆናል::

ረ/ ለመጀመሪያ ጊዜው የሚደረገውየዋጋ ማስተካከያ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀው ቀመር መሰረት ሲሆን በጨረታ መክፈቻ ጊዜ እና የዋጋ ማስተካከያ በሚጠየቅበት ወቅት ባሉ የገበያ ዋጋዎች መካከል ያለውን ልዩነት እንደ ሁኔታው በውል ዋጋው ላይ በመጨመር ወይም በመቀነስ ነው::

ሰ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ረ" የተደነገገው ቢኖርም ከመጀመሪያው የዋጋ ማስተካከያ በኋላ ለሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፣ ቀደም ብሎ በማስተካከያየተኘው የገበያ ዋጋ ለቀጣይ የዋጋ ማስተካከያ ስሌት እንደመነሻ ዋጋ ይወሰዳል::

ሸ/ የማዕቀፍ ግዥ አቅራቢዎች ቁጥር ከአንድ በላይ ሲሆኑና የሚያቀርቡት ዕቃ ምርት መለያ ወይም የንግድ ስም የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ ለአቅራቢዎቹ የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ አንደኛ በወጣው አቅራቢ ውል የገባበት ምርት በገበያ ላይ ያመጣውን

manufacturers, or market studies conducted by the Public Body;

d) The Public Body shall calculate the price difference between the two price points and adjust the supplier's price accordingly, whether increasing or decreasing it, and the adjusted price shall remain effective until the next scheduled adjustment;

e) If the supplier delivers goods late, failing to meet the original delivery schedule, any price adjustment for such delayed deliveries shall be based solely on the prices effective at the originally scheduled delivery date;

f) The initial price adjustment shall follow a predefined formula reflecting the difference between tender-opening prices and prices at adjustment request. Subsequent adjustments shall use the most recent adjusted price as the baseline;

g) Notwithstanding paragraph (f), for any price adjustment following the initial one, the market price used in the prior adjustment shall serve as the base price for the subsequent adjustment calculation;

h) Where a framework agreement involves more than one supplier and the products supplied bear different product labels or trade names, any price adjustment granted to the suppliers shall be based solely on the price variation introduced by the product of the first contracted supplier that was brought to market.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

የዋጋ ልዩነት ብቻ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት።

ቀ/ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሸ" የተደነገገው ቢኖርም የአሸናፊው የውል ዋጋ ወይም ያለውን ልዩነት እንደ ሁኔታው በውል ዋጋው ላይ በመጨመር ወይም የገበያ ዋጋ መረጃ በተደጋጋሚ በሚጠፋበት ጊዜና ዋጋ ማስተካከያ ማድረግ በማይቻልበት ጊዜ የአሸናፊውን ድርጅት ዋጋ ተቀብለው በራሳቸው ንግድ ምልክት አቅርቦት የፈፀሙ አቅራቢዎችን ዋጋ መሰረት በማድረግ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ይቻላል።

በ/ በማዕቀፍ ስምምነት የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ አቅራቢው ጥያቄ ላቀረበበት ጊዜ ቅርብ የሆነንመረጃ በመጠቀም የሚከናወን ሲሆን በዚህ መሰረት የተስተካከለው ዋጋአቅራቢው ጥያቄ ባቀረበበት እና መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግ በወሰነው ጊዜ መካከል የሚኖረውን የዋጋ ለውጥ ታሳቢ ያደረገ ሆኖ የቅርብ ጊዜውን ዋጋ በመውሰድ መሆን አለበት።

ተ/ በዋጋ ማስተካከያው ቀመር ስሌት መሰረት የሚገኘው የተስተካከለ የውል ዋጋ ከዜሮ በታች ሲሆን ማስተካከያ በሚደረግበት ወቅት በውል ዋጋ መሰረት ማቅረብ ይቻላል: : ሆኖም በዚህ ወቅት የመንግሥት መ/ቤቱ አዋጭ አለመሆኑን ሲያምንበት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል። እንዲሁም በዋጋ ማስተካከያው መሰረትየሚኖረው ጭማሪ ከመጀመሪያው የውል ዋጋ 30% (ሠላሳ በመቶ) በላይሲሆን ውሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል:

143. ለምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

1) የመንግስት መ/ቤቱ 24 ወራት እና ከዚህ በላይ ለሚቆዩ የአገልግሎት ግዥዎች፣ ከ12ኛው ወር

i) Despite paragraph (h), where market price data is frequently unavailable or price adjustment cannot be otherwise conducted, the contract price of the winning supplier, or a variation thereof depending on circumstances, may be used as a reference by adding it to the contract price. In such cases, it is permissible to base the adjustment on the winning supplier's price for other suppliers providing goods under their own trade names;

j) Price adjustments shall be based on the most recent information available at the time the supplier submits the request. The adjusted price will be based on the data provided by the supplier, and the Public Body's consideration shall reflect the current market price;

k) If the price adjustment formula results in an adjusted contract price below zero, the adjustment may be made based on the original contract price at the time of adjustment. However, should the Public Body determine the price adjustment to be unreasonable, it may terminate the contract. Furthermore, if the price adjustment exceeds thirty percent (30%) of the original contract price, the contract may also be terminated.

143. Price Adjustment for Procurement of Consultancy Services

1. For consultancy service contracts lasting twenty-four (24) months or longer, the Public

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ጀምሮ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግ አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት አለበት።

2) በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈጻጸም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መ/ቤቱ ሲያምንበት የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል።

3) በዚህ አንቀጽንዑስ አንቀጽ የተገለጸው ቢኖርም ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከሐያከመቶ (20%)ሊበልጥ አይችልም: : ሆኖምየዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ከዚህ መጠን በላይ በሚሆንበት ጊዜ የመንግሥት መ/ቤቶች ጥያቄውን ለገንዘብ ሚኒስቴር እያቀረቡ አሳማኝ ሲሆን የዋጋ ማስተካከያው ሊደረግ ይችላል።

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው እንደቅደም ተከተላቸው ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት በሚገኝ የዋጋ መረጃ፣ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የዋጋ መረጃ እንደሌለ ማረጋገጫ በሚሰጥበት ጊዜ ከመሥሪያቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መነሻ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናት በሚገኝ የገበያ ዋጋ መረጃ መሰረት ብቻ ነው።

:

144. ርክክብ እና ፍተሻ

1) የመንግስት መ/ቤቱ አቅራቢው የሚያቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ በውሉ ላይ በተቀመጠው አግባብ ፍተሻ የተደረገበትና ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ መረከብ አለበት።

2) የመንግስት መ/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለዚህ ዓላማ የሚሆን እንደሚፈጸመው ግዥ ዓይነትና የውስብስብነት ደረጃ ጊዜያዊ የፍተሻ ኮሚቴ ማቋቋም ይችላል።

3) በንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚቋቋመው ኮሚቴ ሌሎች በውሉ የሚገለጹ ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነት እና ተግባራት ይኖሩታል።

Body shall specify in the bidding documents that price adjustments will commence from the twelfth (12th) month;

2. During contract execution, if delays in contract fulfillment arise due to causes beyond the consultant's fault, the Public Body may authorize price adjustments for the consultant;

3. Notwithstanding the foregoing, price adjustments for consultancy contracts shall not exceed twenty percent (20%) of the total contract value. Should a request exceed this limit, the Public Body shall submit the request with justification to the Ministry of Finance for approval, and adjustments may proceed upon approval;

4. Price adjustments shall be based exclusively on market price data derived from central market price studies conducted by the competent central authority, pursuant to directives issued in response to requests by relevant offices, provided that the Ethiopian Statistics Service confirms the absence of relevant price data. The process shall follow the established order of precedence.

144. Delivery and Inspection

1. The Public Body shall verify and confirm that the goods, services, or construction works delivered have been properly handed over and inspected in accordance with the contract terms and meet the required quality standards;

2. When deemed necessary, the Public Body may establish a temporary inspection committee to determine the type and complexity level of procurement for inspection purposes;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ሀ/ መፈተሸና እንደአስፈላጊነቱ ሙከራ ማድረግ፣

ለ/ የሚቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ በውሉ ላይ የተገለጸውን የጥራት ደረጃ የሚያሟላ ስለመሆኑን ፍተሻ ማድረግ፣

ሐ/ እንደምርመራው ሁኔታ ርክክብ እንዲደረግ ወይም ተመላሽ እንዲሆን የመወሰን፣

4) በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ በውሉ ላይ የተገለጸውን የጥራት ደረጃ የማያሟላ መሆኑ በኮሚቴው ከተረጋገጠ አቅራቢው በውሉ መሠረት መተካት ወይም ማስተካከል አለበት።

145. ክፍያ ስለመፈጸም

1) አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው አካል የሚያቀርበው የክፍያ ጥያቄ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች የተቀመጡ ተፈላጊ መረጃዎችን በማካተት ተገቢ የክፍያ መጠየቂያ ሰነድ በጽሑፍ ማያያዝ አለበት።

2) የግዥ ፈፃሚው አካል በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የውል ግዴታዎች መሠረት አቅራቢው ላቀረባቸው ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራዎችን በውል ዋጋው መሠረት ለአቅራቢው ክፍያ ይፈጽማል።

3) ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት እና ሌሎች አገልግሎቶች ግዥ ፈጽሞ ከተረከበ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ተገቢውን ክፍያ ለአቅራቢው መፈፀም አለበት።

4) በአዋጁና በውሉ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል ክፍያ መፈፀም የሚችለው በውሉ ውስጥ የተጠቀሱትን ግዴታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ነው።

5) የንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው አቅራቢው በውሉ ጊዜ ውስጥ ላቀረባቸው አቅርቦቶች ብቻ ሲሆን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 126 መሰረት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸውን ግዥዎች አይመለከትም።

3. The inspection committee shall, subject to fulfillment of other contractual obligations, be responsible for:

a) Conducting inspections andperforming necessary tests;
b) Verifying that the goods, services, or construction works comply with the contract's quality standards;
c) Deciding whether to require corrections or returns based on inspection outcomes;

4. Should the committee conclude that the goods, services, or construction works fail to meet the specified quality standards, the provider shall replace or rectify the deficiencies in accordance with the contract.

145. Payment Settlement

1. The supplier shall submit a written payment request to the procuring entity, including all information required under the general contract terms;

2. The procuring entity shall make payments to the supplier based on the contract price for delivered goods, related services, consultancy services, or construction works, in compliance with contractual obligations;

3. Government entities shall complete payments to suppliers within thirty (30) days after receiving the goods, consultancy services, or other procured services;

4. Unless otherwise provided by law or contract, payments by the procuring entity shall be subject to verification that contractual obligations have been fulfilled;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

6) በዚህ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤት የግንባታ ዘርፍ ስራ ግዥ ሲፈፅም ክፍያ የሚፈፀመው ግንባታውን የክንውን ደረጃ መሰረት አድርጎ እና የሚከተለውን አፈፃፀም ተከትሎ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈፀመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ እንደ ስራው ውስብስብነት ለዚህ ዓላማ ከተቀጠረ አማካሪ ወይም ከመ/ቤቱ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ ይሆናል፡፡

ለ/ የክፍያ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ከሥራ ተቋራጩ ጥያቄ በቀረበለት በ7(ሰባት) የሥራ ቀናት ውስጥ የቁጥጥር ስራውን የሚያከናውነው አማካሪ ወይም የመ/ቤቱ መሐንዲስ የምርመራውን ሥራ ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

ሐ/ የክፍያ የምስክር ወረቀት በፊደል ተራ (ለ) መሰረት ተረጋግጦ ሲቀርብ መ/ቤቱ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ተገቢውን ክፍያ ለሥራ ተቋራጩ መፈፀም አለበት፡፡

መ/ አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ከቀረበለት በኋላ ያለበቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሐ) ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ ያሳለፈ እንደሆነ በመዘግየቱ ምክንያት ተቋራጩ በመ/ቤቱ ላይ ለሚያቀርበው ማንኛውም ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ አማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት አለበት፡

ሠ/ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሰረት ከሚፈጸመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን 7% (ሰባት በመቶ) በማያገ መልክ ተቀንሶ ይያዘል፡፡

ረ/የግንባታ ስራው ሲጠናቀቅ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /ሠ/ መሰረት ከሚያዘው ገንዘብ ላይ 50% (ሃምሳ በመቶ) ለሥራ ተቋራጩ ይለቀቃል፡፡ ቀሪው 50% (ሃምሳ በመቶ) ጊዜያዊ ርክክብ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ለአንድ ዓመት የጥገና ጊዜ ተይዞ የሚቆይ ሲሆን፣ የስራ

5. Paragraph 5 applies solely to supplies delivered within the contract period and excludes price-adjusted procurements under Article 126 of this Directive;

6. Payments for government construction projects shall be made in accordance with work progress stages and require:

a) Payment shall be determined based on the project's complexity and stage of completion, as certified by a payment certificate issued by the hired consultant or the Public Body's engineer;

b) Upon request by the organization, the coordinator or engineer shall complete inspection and finalize the review process within seven (7) working days to issue the payment certificate;

c) Once the payment certificate is submitted as per item (b), the Public Body shall make payment to the contractor within thirty (30) days;

d) Should the consultant engineer fail to meet the deadline in (b) without valid justification, the Public Body shall hold the consultant engineer accountable for any subsequent additional payment claims;

e) Seven percent (7%) of each payment shall be retained as a retention amount to guarantee quality assurance of the construction work;

f) Upon completion of construction work and execution of a temporary acceptance agreement, fifty percent (50%) of the retained amount shall be released to the contractor, with the remaining fifty percent (50%) retained for a one-year maintenance period from

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ተቋራጩ ለ12 ወራት የሚቆይ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ካቀረበ የተያዘው ገንዘብ ይለቀቅለታል።

7) በግንባታ ሥፍራ ላይ ለሚገኙ የግንባታ ዕቃዎች (ማቴሪያሎች) ከዋጋቸው እስከ ስልሳ በመቶ (60%) የሚደርስ ክፍያ መፈፀም ይቻላል። ሆኖም መንግስት መ/ቤቶች የተጠቀሰውን የስልሳ በመቶ (60%) ክፍያ ከመፈፀማቸው በፊት የሚከተሉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው።

ሀ/ በግንባታ ሥፍራ ላይ ለሚገኙ ዕቃዎች ክፍያ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማናቸውም ሥራ ተቋራጭ የሚያቀርባቸው ዕቃዎች የተገዙበትን ዋጋ የሚያመለክት ደረሰኝ ትክክለኛነት በመንግስት መ/ቤቱ እና በአማካሪው መረጋገጥ አለበት።

ለ/ ክፍያ የተፈፀመበት በግንባታ ሥፍራ የሚገኝ የግንባታ ዕቃ ሥራ ላይ እንዲውል ሲደረግ የተፈፀመው ክፍያ ከሚቀጥለው ክፍያ መቀነስ አለበት።

ሐ/ በአንድ የግንባታ ሥፍራ የሚገኙ ዕቃዎችን ለሌላ የግንባታ ፕሮጀክት በግብአትነት መጠቀምም ሆነ ለሌላ የተለየ ዓላማ ማዋል አይቻልም፡

መ/ ሥራ ተቋራጩ በግንባታ ሥፍራ ላይ ለሚገኙ ዕቃዎች ክፍያ እንዲከፈለው ከሚያቀርበው ጥያቄ ጋር ዕቃዎቹ በክምችት ላይ እያሉ አደጋ ቢደርስባቸው፣ ቢሰረቁ፣ ወይም ለረዥም ጊዜ ሥራ ላይ ሳይውሉ በመቅረታቸው ቢበላሹ የጉዳቱን መጠን ለማካካስ እንዲቻል በግንባታ ሥራ መደበኛ የጨረታ ሠነድ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ድንጋጌ ላይ በተጠቀሰው አግባብ ኢንሹራንስ በመግባት ዕቃዎቹ ኢንሹራንስ የተገባላቸው መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

the date of the temporary agreement. If the contractor provides an unconditional guarantee valid for twelve (12) months, the withheld funds shall be released to them;

7. For construction materials located at the site, payment of up to sixty percent (60%) of their value may be made, subject to the following precautionary measures:

a) Any contractor requesting payment for materials located at the construction site shall have the invoice indicating the purchase price of the materials verified by the Public Body and the supervisor for accuracy.
b) When a payment has been made for construction work performed at the construction site, the payment already made should be deducted from the subsequent payment.
c) Items located at one construction site may not be used for another construction project under any circumstances, nor may they be diverted for any other purpose.
d) If a subcontractor requests payment for materials located at the construction site, and those materials are damaged, stolen, or deteriorate due to prolonged non-use while on site, the subcontractor shall provide proof that the materials were insured under the appropriate insurance coverage specified in the general contract terms for the construction work. This is to ensure compensation for the extent of the loss can be made according to the insurance policy included in the contract conditions.

Uploaded on the website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

146. ውል ማጠናቀቅ

1) የመንግስት መ/ቤት ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎችና እና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለባቸው። ለዚህም፡-

ሀ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት የሚገባውን የግንባታ ዘርፍ ስራ፣ዕቃ፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች አጠናቆ ማቅረቡን፣

ለ/ በውሉ መሰረት የተያዙ ዋስትናዎች፣ የጥራት ዋስትናዎች ተገቢው ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን፣

ሐ/ በውሉ መሰረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑን፣ ለተከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በውሉ መሠረት አገልግሎት መገኘቱን፣

መ/ ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከኢንሹራንስ፣ ከባንያዎች፣ ከአጓጓዦች፣ከጉምሩክ ባስልጣን፣ ከጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ ከባንክ እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የተያያዙ የመንግስት መ/ቤቱ ጥቅሞች መከበራቸውን እና ግዴታዎች የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፣

2) የመንግስት መ/ቤቱ ከአቅራቢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ያልተጠናቀቁ ሒሳቦችን በመዝጋት እንደአስፈላጊነቱ የውል አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ አለበት።

147. የጉዳት ካሳ

1) የመንግስት መ/ቤቱ በዚህ መመሪያ መሰረት ለዘገየ የውል አፈጻጸም በሚከተለው መሰረት እርምጃ መውሰድ አለበት፡-

ሀ/ አቅራቢው በውሉ ጊዜ ውስጥ ባልፈጸመው መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000 የጉዳት ካሳ ከክፍያው ላይ ተቀናሽ ማድረግ አለበት።

146. Contract Closure

1. The Public Body shall ensure that contracts with suppliers and related matters are completed properly and timely by:

a) Ensuring the supplier completes and delivers construction works, materials, consultancy, or other services as per contract terms;
b) Ensuring guarantees and quality assurances stipulated in the contract have been monitored and decisions made at necessary stages;
c) Confirming payments due under the contract have been completed and services rendered accordingly;
d) Verifying that the Public Body's rights and obligations relating to third parties (including insurance, companies, transporters, customs authorities, customs brokers, banks, and other service providers) are fulfilled;

2. The Public Body shall conduct contract performance evaluations as necessary and close outstanding accounts with suppliers and third parties.

147. Liquidated Damages

1. The Public Body shall impose penalties for delayed contract performance as follows:

a) If the supplier fails to complete the agreed work within the contractual timeframe, a penalty of one-thousandth

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ለ/ በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ ከውሉ ዋጋ 10% የሚበልጥ መሆን የለበትም::

ሐ/የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ የበለጠ ችግር የሚያስከትል ከሆነ የመንግስት መ/ቤቱ የመቀጫው መጠን 10% እስከሚሞላ ድረስ ለመጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ሊያቋርጥ እንደሚችል የሚገልፅ አንቀጽ ውሉ እንዲይዝ መደረግ አለበት::

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ተፈፃሚ የሚሆነው አቅራቢዎች ዘግይተው ለመንግሥት መ/ቤቶች በሚፈጽሙት ውል ላይ ብቻ ሲሆን፣ የጉዳት ካሳ ክፍያው ሊቀነስ የሚገባው ለአቅራቢው ከሚከፈለው ቀሪ ክፍያ ላይ ብቻ ነው::

3) አቅራቢው በውሉ መሠረት ዕቃውን፣ አገልግሎቱን፣ ወይም የግንባታ ሥራውን ካልፈጸመ ወይም በውሉ የተቀመጡ ሌሎች ግዴታዎችን ሳይወጣ ቢቀር የመንግሥት መ/ቤቶች የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የውል ማስከበሪያውን በመውረስ ውሉ እንዲቋረጥ ማድረግ አለባቸው::

148. ውልን ስለማቋረጥ

ዝርዝሩ በውል ስነዱ መሰረት የሚፈጸም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ለአቅራቢው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል::

ሀ/አቅራቢው ዕቃውንና ተያያዥ አገልግሎቱን፣ ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን በውሉ መሰረት ካልፈጸመ ወይም ከፍተኛ የውል አፈፃፀም ችግርን ጨምሮ ሌሎች በውሉ የተቀመጡ ግዴታዎችን ሳይወጣ ቢቀር ወይም በህግ የተከለከሉ ተግባራትን ፈጽሞ ቢገኝ ወይም መክሰሩ ወይም በዕዳ መያዙ ከተረጋገጠ፣

(1/1000) of the payment amount per day shall be deducted;

b) The total penalty shall not exceed ten percent (10%) of the contract value;

c) If delays cause operational difficulties, the Public Body may terminate the contract after issuing a warning once the penalty reaches ten percent (10%) of the contract value. Contracts shall explicitly include such termination clauses;

2. The provisions of paragraph 1 apply exclusively to contracts executed by suppliers with the Public Body, and any damages shall be deducted only from payments due to the supplier;

3. Should the supplier fail to deliver goods, services, or construction works as specified, or fail to fulfill other contractual obligations, the Public Body shall enforce this Directive, including contract termination and forfeiture of the performance bond.

148. Termination of Contract

The Public Body may terminate the contract by issuing a warning if any of the following conditions exist:

a) The supplier fails to deliver goods, related services, advisory services, or construction work as stipulated, fails to fulfill contractual obligations, commits serious performance breaches, engages in unlawful conduct, or declares bankruptcy or insolvency;

b) The Public Body determines that contract fulfillment is impossible or unnecessary due

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ ከኢኮኖሚ፣ ከበጀት ወይም ከቴክኒክና ቴክኖሎጂ ምክንያቶች አንጻር ውሉን መፈጸም የማይቻል ወይም የማያስፈልግ ሲሆን፣

ሐ/የመንግስት መ/ቤቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 145 ላይ የተዘረዘሩና ከአቅም በላይ ተብለው የተለዩ ሁኔታዎች ምክንያት አቅራቢው ውሉን ለመፈጸም እንደማይችል ሲረጋገጥ::

149. <u>ከአቅም በላይ ሁኔታ</u>

1) ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው ሊያሰኙ የሚችሉ ምክንያቶች ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፣

ሀ) ውል እንዳይፈጽም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፣

ለ) እንደ መሬት መናወጥ፣መብረቅ፣ ማዕበል፣ እና የመሳሰሉ ተፈጥሯዊ መቅሰፍቶች፣

ሐ) የጠላት፣ የውጭ አገር ወይም የአገር ውስጥ ጦርነት፣

መ) ውል የገባው ወገን መሞት ወይ ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም፣

ሠ) ውል ውል የገባው ወገን መሞት ወይ ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከወይም ውል የገባው ወገን መሞት ወይ ባልታሰበ ሁኔታ የ

ረ) በፍትሐብሔር ሕግ የተዘረዘሩ ሌሎች ከአቅም በላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፣

2) ግልጽ የሆነ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተደርገው ሊቆጠሩ አይችሉም፣-

ሀ) በተዋዋይ ፋብሪካ ወይም ስራውን ከሚያከናውንበት ባንደኛው ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ውስጥ የተደረገ የሠራተኛ አድማ ወይም የመ/ቤቱ መዘጋት፣

ለ) ለውሉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋ መወደድ ወይም መርከስ፣

ሐ) ተዋዋይ ያለበትን የውል ግዴታ አፈጻጸም ወጪ የሚያከብድበት አዳዲስ ህግ መውጣት::

to economic, budgetary, technical, or technological reasons;

c) The Public Body confirms that the supplier is incapable of fulfilling the contract due to circumstances beyond the supplier's control as listed under Article 145 of this Directive.

149. Force Majeure

1. Force majeure refers to problems beyond the parties' capacity, including but not limited to:

a) Government orders prohibiting contract execution;
b) Natural disasters such as earthquakes, lightning, floods, or similar catastrophic events;
c) International or civil war;
d) Death, unexpected severe accident, or critical illness of the contracting party;
e) For organizations, dissolution, bankruptcy, or other circumstances affecting legal standing;
f) Other force majeure instances as identified under the Civil Code;

2. Unless contractually specified otherwise, the following are not considered force majeure:

a) Labor strikes at the counterparty's factory or office;
b) Increases or decreases in prices of essential supplies for contract performance;
c) New legislation rendering contractual obligations more onerous.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

150. ማስታወቂያዎችና የፅሑፍ ግንኙነቶች

1) ማንኛውም በውሉ መሠረት አንዱ ተዋዋይ ለሌላው ወገን የሚሰጠው ማስታወቂያ በውሉ በተጠቀሰው መሠረት በፅሑፍ መሆን አለበት። በፅሑፉ የተደረገ ግንኙነት ማለት ፅሑፉ ለተቀባዩ መድረሱ ሲረጋገጥ ነው።

2) አንድ ማስታወቂያ ውጤት ሊኖረው የሚችለው ማስታወቂያው በአካል ለተዋዋዩ ሕጋዊ ተወካይ ሲደርስ ወይም በውሉ ላይ በተመለከተው አድራሻ የተላከ ከሆነ ነው።

151. የውል አለመግባባቶችን ስለመፍታት

1) ከመንግስት ግዥ ውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በአቅራቢዎች መካከል የሚፈጠር ማንኛውም አለመግባባት እስከተቻለ ድረስ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ውይይትና ስምምነት መፈታት አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም በመንግስት መ/ቤቱ እና በአቅራቢዎች መካከል የሚፈጠር ማንኛውም አለመግባባት በአዋጁ አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አግባብነት ባላቸው ሕጎች፣ በዚህ መመሪያ እና በውሉ መሠረት መፈታት አለበት።

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የመንግስት መ/ቤቱ ከጊዜና ከወጪ ቆጣቢነት አንጻር ጠቀሜታ እንዳለው ሲያምንበት በአዋጁ አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

4) የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በውል አፈጻጸም ወቅት ያጋጠማቸውን አለመግባባት ለመፍታት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የሚጠቀሙ ከሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በተቋቋሙ እና በተገቢው አካል ዕውቅና በተሰጣቸውየግልግል ዳኝነት አካላት በኩል መሆን አለበት።

5) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 አፈፃፀም ውል ፈፃሚ አካላት በሚገቡት ውል ግልግል ዳኝነት አካሉ፣ ተፈፃሚ የሚሆነውን ሕግ፣ የዳኝነት አካሉ ስብጥር፣ ዳኞች የሚመረጡበት መንገድ፣ እና ሌሎች የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች ሊካተቱ ይገባል።

150. Notifications and Written Communications

1. Any notice given by one party to another under this agreement shall be in writing as specified. Written communications shall be effective upon confirmation of receipt by the recipient;

2. A notice is effective only if physically delivered to the party's legal representative or sent to the address specified in the contract.

151. Dispute Settlement

1. Disputes arising between the Public Body and suppliers concerning contract implementation shall initially be resolved through dialogue and mutual agreement;

2. If unresolved, disputes shall be settled in accordance with applicable laws, this Directive, and the contract, as stipulated in Article 66, Sub-Article 1 of the Proclamation;

3. Notwithstanding Sub-Article 1, the Public Body may utilize alternative dispute resolution mechanisms under Article 66, Sub-Article 2 of the Proclamation when deemed beneficial for efficiency;

4. Alternative dispute resolution processes shall be conducted by legally recognized and accredited arbitration entities established under applicable laws;

5. Contracts shall include provisions specifying the arbitration body, applicable law, composition and selection of arbitrators, and procedural rules for arbitration.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ምዕራፍ ዘጠኝ

የአቤቱታ እና ይግባኝ አቀራረብና አወሳሰን ሥርዓት

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

152. አቤቱታ፣ ይግባኝ እና የጥፋተኝነት ሪፖርት አቀራረብ

1) ከመንግሥት ግዥ ጋር በተገናኘበመንግስት መንግስት ው የመንግስት መ/ቤት የተከናወነ ወይም ሳይከናወን የቀረ ተግባር ይህንን አዋጅ፣ የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅና ተያያዥ ድንጋጌዎች፣ የግዥ አፈጻጸም መመሪያዎቹንና የጨረታ ሠነዱ ላይ የተመለከቱ ሁኔታዎችን ጥሷል ብሎ የሚያምን እና በዚህም ምክንያት የደረሰበት ወይም ሊደርስበት የሚችል ጉዳት ስለመኖሩ ማሳየት የሚችል ዕጩ ተወዳዳሪ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ፣ ወይም ደግሞ በደረጃ ይግባኝ ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል።

2) ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችለው መንግስት ው መ/ቤት ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመግባቱ በፊት ብቻ ነው።

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ የመንግስት መ/ቤቱ ውል ከፈረመ በኋላ የቀረበ አቤቱታ ሊታይ ይችላል።

ሀ/ ውሉ የተፈረመው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠው የአቤቱታ እና ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት ከሆነ፣

ለ/ ውሉ የተፈረመው የመንግስት መ/ቤቱ ለቀረበበት አቤቱታ ምላሽ ከሰጠ በኋላ ውል ለመፈረም በዚህ መመሪያ የተቀመጠው ሰባት (7) ተከታታይ የሥራ ቀናት ከመጠናቀቁ በፊት ከሆነ፣

CHAPTER NINE

COMPLAINT AND APPEAL PRESENTATION AND DECISION-MAKING SYSTEM

SECTION ONE
GENERAL PROVISIONS

152. Complaints, Appeal, and Submission of an Offense Report

1. A candidate bidder who believes that there are circumstances related to a completed or ongoing procurement process of a Public Body— including concerns about this Directive, government-private partnership regulations, procurement performance directives, or tender documents— and can demonstrate actual or potential harm resulting from these circumstances, may submit complaints to the Head of the Public Body or file an appeal to the appropriate-level board.
2. Pursuant to Sub-Article 1 of this Article, the concerned party may submit complaints only before the Public Body enters into a contract with the winning bidder.
3. Notwithstanding the provision of Sub-Article 2 of this Article, complaints submitted after the Public Body has signed the contract may be considered if any of the following conditions are met:

   a) If the contract was signed before the deadline for submitting complaints and appeals stipulated in Sub-Article 1 of this Article had expired.

   b) If the contract was signed by the Public Body after responding to the submitted complaints but before the expiration of the seven (7) consecutive working days stipulated in this Directive.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ሐ/ በአዋጁና በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት የጨረታ ውጤት ለተጫራቾች ሳይገለጽ ውል የተፈረመ ከሆነ::

c) If a contract was signed without disclosing the tender results to bidders, contrary to the Proclamation and the provisions of this Directive.

ክፍል ሁለት

አቤቱታን ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ስለማቅረብ

SECTION TWO

LODGING OF COMPLAINT

153. አቤቱታን ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ስለማቅረብ

1) በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 14 እና አንቀጽ 74 በተደነገገው መሰረት ማናቸውም የበላይ ኃላፊ የመንግሥት መሥሪያቤቱ በሚፈጽመው ግዥ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን አጣርቶ ምላሽ መስጠት አለበት::

2) በመንግስት መ/ቤቱ በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ መቅረብ አለበት::

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጨረታ ሠነድ ይዘት ላይ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርብ የማብራሪያና የማሻሻያ ጥያቄ መነሻ ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የማብራሪያና የማሻሻያ ምላሾች ከሰጠበት ወይም ምላሽ መስጠት ይገባው ከነበረበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር አምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ዕጩ ተወዳዳሪው ይግባኙን በቀጥታ ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል::

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)ድንጋጌ ቢኖርም በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በሥራ አመራር ቦርድ ለሚተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ግዥው በመሥሪያ ቤቶቹ የስራ አመራር ቦርድ እንዲጸድቅ በሚኒስትሩ በልዩ ሁኔታ የተፈቀደላቸው የመንግስት መ/ቤቶች በሚፈጽሙት ግዥ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ሳያስፈልግ አቤቱታውን በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚ ቦርድ ሊያቀርብ ይችላል::

153. Lodging of a Complaint to the Head of the Public Body

1. In accordance with Article 5, Sub-Article 14, and Article 74 of the Proclamation, any Head of the Public Body shall address and respond to complaints submitted regarding procurement activities undertaken by the Public Body.
2. Complaints arising from the Public Body's completed or ongoing actions shall first be submitted to the Head of the Public Body.
3. Without prejudice to the provisions of Sub-Article 2 of this Article, if the Public Body provides clarifications or amendments in response to bidder inquiries regarding the tender document, the bidder may directly submit an appeal to the board within five (5) working days from the date the response was issued or should have been issued.
4. Notwithstanding Sub-Article 1 of this Article, for Public Bodies managed by a governing board due to their operational nature, appeals related to procurements conducted by Public Bodies specifically authorized by the Minister to require board approval may be submitted directly to the appeal review board without first being presented to the Head of the Public Body.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

154. አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ

1) በግዥ አፈጻጸም ሂደት ጉዳት ወይም በደል ደርሶብኛል የሚል ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን የመጨረሻ ውሳኔ በይፋ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አምስት (5) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ጨረታውን ላወጣው የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ አለበት። ከዚህ ጊዜ በኋላ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም።
2) ጉዳዩ አቤቱታ ባቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና ጨረታውን ባወጣው የመንግስት መ/ቤት በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት አቤቱታው ከበቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሰባት (7) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔውን እና የውሳኔውን ቅጅ አቤቱታውን ላቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እንዲደርሰው ማድረግ አለበት።
3) የጨረታው ቴክኒካል እና ፋይናንሻል መወዳደሪያ ሠነድ በተለያየ ሁኔታ እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ ተጫራቾች የመጫረቻ ሠነዳቸውን በተለያየ ሁኔታ እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፣

ሀ/ ማንኛውም ተጫራች የቴክኒክ ግምገማው አዋጁን፣ ወይም ይህንን መመሪያ ወይም የጨረታ ሠነዱን መሠረት አድርጎ አልተከናወነም የሚል ቅሬታ ካለው ቅሬታውን በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ እንደሚችል የመንግስት መ/ቤቱ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾች በሚያሳውቅበት ሁኔታ ላይ ማመልከት ይኖርበታል።

ለ/ መንግስት መ/ቤቱ የዋጋ መወዳደሪያ የያዘውን ሃሳብ ሊከፍት የሚችለው የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾች ካሳወቀ ከአምስት (5) ቀናት በኋላ ይሆናል። ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ ለአቤቱታው ምላሽ መስጠትና ምላሹን ከሰጠ በኋላ እስከ 5 የሥራ ቀናት፣ ወይም ደግሞ ለቦርዱ ይግባኝ ቀርቦ ከሆነ ቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የዋጋ መወዳደሪያ ሃሳብ

154. Timeframe for Lodging a Complaint

1. A bidder or candidate bidder who claims to have suffered harm or injustice during the procurement process shall submit complaints to the Head of the Public Body that issued the tender within five (5) consecutive working days from the date he became aware, or should have become aware, of the final decision that forms the basis of the complaint. Complaints submitted after this period will not be accepted.
2. Unless the matter is resolved by mutual agreement between the complaining bidder and the Public Body that issued the tender, the Head of the Public Body shall, in accordance with Article 74, Sub-Article 3 of the Proclamation, issue a decision and provide a copy to the complaining bidder within seven (7) consecutive working days from the date the complaint was submitted.
3. In tenders where bidders are required to submit their technical and financial proposals separately, if instructed to present their bid documents differently:

a) Any bidder who alleges that the technical evaluation was not conducted in accordance with the Proclamation, this Directive, or the tender document shall submit the complaint within five (5) working days of the Public Body's notification of the technical evaluation results.
b) The Public Body may open the price proposals only five (5) days after notifying bidders of the technical evaluation results. However, if a complaint regarding the technical evaluation is submitted to the Head of the Public Body, the price proposals shall remain unopened until a response is provided (within five working days after the response). If an appeal is lodged with the board, the price

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ሳይከፈት ማቆየት ይኖርበታል።

ሐ/ አቤቱቱታ የቀረበበት ማናቸውም ግሽር የሚጣራው ለጨረታው የተዘጃውን የጨረታ ሠነድ፣ አዋጁንና ይህንን መመሪያ መሠረት በማድረግ ብቻ ይሆናል።

c) Any procurement subject to the complaint shall be reviewed solely based on the tender document, the Proclamation, and this Directive.

155. የመንግስት መ/ቤቶች የግሽር አፈጻጸም ሂደትን ማገድ ስለመቻላቸው

1) ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መ/ቤት አቤቱታውን በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ አቤቱታው ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ የጨረታው ሂደት ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ አለበት።

2) የመንግስት መ/ቤት ለሚቀርብበት አቤቱታ የሚሰጣቸው ማናቸውም ውሳኔ እንዲሁም የውሳኔ ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግሽር ሥርዓቱ አንድ አካል ሆነው መያዝ አለባቸው።

155. Authority of the Public Bodies to Suspend the Procurement Process

1. If the Public Body verifies that the complaint was submitted within the timeframe specified in this Directive, it shall suspend the tender process until a decision on the complaint is issued.
2. Any decision made by the Public Body regarding a submitted complaint, including the reasons and circumstances, shall be considered an integral part of the procurement system.

156. የአቤቱታየሚጣራበት ሂደት እና ውሳኔ አሰጣጥ

1) የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚወስነውውሳኔ የቅሬታውን መነሻ ምክንያት፣ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውንጭብጦች፣ ትንታኔዎች፣ ከውሳኔ ላይ ለመድረስ ያስቻለውን ሕግና ምክንያት እንዲሁም ማስረጃዎችን የያዘ መሆን አለበት።

2) የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከማንኛውም ሰው ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ እንዲቀርብለት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ከማቅረቡ በፊት የሚመለከተውን ሰው ወይም አካል መጠየቅ ይችላል።

3) የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት (7) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ውሳኔ መስጠት አለበት።

4) የመንግሥት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በቀረበው አቤቱታ ውሳኔ ካልሰጠ፣ አቤቱታ አቅራቢው የ7 ቀናት ጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

156. Complaint Reviewing Process and Decision-Making

1. The decision rendered by the Head of the Public Body shall include the grounds for the complaint, the provisions requiring resolution, the legal basis and reasoning applied, and the supporting evidence.
2. If deemed necessary, the Head of the Public Body may request any individual or entity to submit evidence before issuing a decision.
3. The Head of the Public Body shall issue a decision on the complaint within seven (7) consecutive working days from the date the complaint was submitted.
4. If the Head of the Public Body fails to issue a decision within the stipulated timeframe, the appellant may submit an appeal to the board within five (5) working days after the expiration of the seven-day deadline.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ክፍል ሦስት

ለቦርዱ የሚቀርብ ይግባኝ

157. ይግባኝ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ ስለማቋቋም

1) በመንግስት መ/ቤቶች የግዥ አፈጻጸም ላይ ከአጨ ተወዳዳሪዎች ወይም ከተጫራቾች የሚቀርብለትን የይገግባኝ አቤቱታ አጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥ ቦርድ በአዋጁ አንቀጽ 67 እና በዚህ መመሪያ እንደገና ተቋቁሟል።

2) የቦርድ አባላት በሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሲሆን፣
   - ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚወክል.....ሰብሳቢ
   - ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚወክል..አንድ አባል
   - ከፍትህ ሚኒስቴር .....አንድ አባል
   - ከሙ.ያ ማህበራት.....አንድ አባል
   - ከመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚወክል.አንድ አባል
   - ከሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚወክል.አንድ አባል
   - ከንግድ ምክር ቤት የሚወክል .....አንድ አባል፣

በድምሩ ሰባት አባላት ያሉት ሲሆን፣ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚወከል አንድ የሥራ ክፍሉ ኃላፊ ወይም ባለሙ.ያ ድምጽ የሌለው አባል ሆኖ በጸሐፊነትና በአስረጂነት እንዲሰራ ይመደባል።

3) ባለሥልጣኑ የቦርዱ ጸሐፊ በመሆን ያገለግላል።
4) የቦርዱ አባላት አሰያየም በብቃት የተመሠረተ ሆኖ በግዥ፣ በምህንድስና፣ በጤና፣ በግብርና በፋይናንስ፣ ወይም በህግ ሙ.ያ ትምህርት ዝግጅት በመንግስት ግዥ አፈጻጸም በቂ እውቀትና ልምድ ያካበቱ እና መልካም ባህሪ እና ሥነ-ምግባር ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

SECTION THREE
APPEAL TO BE SUBMITTED TO THE BOARD

157. Establishment of the Board of Appeal

1. A Board of Appeal, which reviews procurement performance complaints lodged by bidders or competitors and renders decisions, is re-established under Article 67 of the Proclamation and this Directive in Public Bodies.
2. The members of the board are appointed by the Minister as follows:

   - Ministry of Finance representative Chairperson
   - Public Bodies representative — One Member
   - Ministry of Justice representative — One Member
   - Professional Association representative — One Member
   - State Owned Enterprises representative — One Member
   - Civic Society Organization representative — One Member
   - Chamber of Commerce representative — One Member

The board consists of seven members in total. Additionally, a representative from the Authority—either a department head or an expert—is appointed as a non-voting member to serve as secretary and rapporteur.

3. The Authority serves as the secretary of the board.
4. Board members shall be appointed based on competence and must possess adequate knowledge and experience in procurement, engineering, health, agriculture, finance, law, or public procurement execution. They must also have good character and ethical conduct.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

5) ማንኛውም የቦርድ አባል በዚህ ምዕራፍ መሠረት ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣት በፈጸመው ድርጊት ወይም ባለማድረጉ ምክንያት ምንም ዓይነት ክስ ሊቀርብበት አይችልም።

6) በአዋጁ አንቀጽ 67 (3) መሰረት ቦርዱ የሚኖሩት ከአንድ በላይ ንዑስ ኮሚቴዎች በግዥ አይነቶች መሰረት ወይም ይግባኝ የሚቀርብባቸውን ግዥ የሚፈጽሙአካላትን መሰረት በማድረግ ሊዋቀር ይችላል።

7) የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት አመት የሚቆይ ሲሆን፣ እንደ ሥራ አፈጻጸማቸውና የሥነ ምግባር ሁኔታቸው እየታየ ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን እንዲሰሩ ሊደረግ ይችላል።

158. ከቦርድ አባልነት ስለመሰናበት፤

1) ሰብሳቢውን ጨምሮ ማንኛውም የቦርዱ አባል በማንኛውም ጊዜ የመልቀቂያ ማመልከቻ ለሚኒስትሩ በማቅረብ ሊፈቀድለት መልቀቅ ይችላል።

2) ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም አባል ከአባልነት ሊሰበናበት ይችላል።

ሀ/ በአዕምሮ መታወክ ወይም የአካል ጉዳት ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ፣

ለ/ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኝነቱ በፍ/ቤት ከተረጋገጠ፣

ሐ/ የሥነ-ምግባር ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት ከተገኘበት

መ/ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ ወይም ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ካልተገኘ።

159. የቦርዱ ሥልጣን እና ተግባር

ቦርዱ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ አሸናፊው ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን ከማላለፍ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 69 የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል።

5. No board member shall be subject to legal action or liability for actions taken or omitted in the proper discharge of their duties under this chapter.
6. Under Article 67(3) of the Proclamation, the board may establish more than one subcommittee based on procurement categories or responsible entities.
7. The term of office for board members shall be three years, with the possibility of reappointment based on performance and ethical conduct.

158. Resignation from Board Membership

1. Any board member, including the chairperson, may resign at any time by submitting a resignation request to the Minister, subject to approval.
2. The chairperson or any member may be removed from membership under any of the following circumstances:
   a) Inability to fulfill duties due to mental incapacity or physical disability;
   b) Conviction of a criminal offense by a court of law;
   c) Breach of ethics or disciplinary standards;
   d) Failure to properly discharge responsibilities or repeated unjustified absences from board meetings.

159. Powers and Duties of the Board

In carrying out its functions, the board retains the powers granted under Article 69 of the Proclamation, except for decisions related to selecting the winning bidder or signing contracts. The board shall have the following powers:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ሀ/ መንግስት ው የመንግስት መ/ቤት በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ሥራውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ የማስተላለፍ፣

ለ/ ይግባኝ የቀረበበት የግዥ አፈጻጸም ሂደት እንዲስተካከል የመወሰን፣ የቀረበው ይግባኝ ተገቢ ሆኖ ካላገኘው ይግባኙን ውድቅ የማድረግ፣

ሐ/ ይግባኝ የቀረበበት የግዥ አፈጻጸም ሂደት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲቋረጥ የመወሰን፣

መ/ ጉዳዩን መርምሮ በይግባኙ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት የመንግስት መ/ቤቱ ክርክር ከተነሳበት የግዥ ሂደት ጋር በተያያዘ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የማገድ፣

ሰ/ እንደአስፈላጊነቱ የሰነድ ምርመራ ወይም የችሎት ስሚ ማድረግ፣

ረ/ የቀረበለትን የይግባኝ ጥያቄ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ሠነዶች፣ መዛግብት፣ ሪፖርቶች እና ማናቸውም ሌሎች ማስረጃዎች ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ከተጫራቾች እና ከሌላ ማንኛውም አካል እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣

ሰ/ ይግባኙ የቀረበው በተገቢው ጊዜና ሁኔታ መሆኑ ሲረጋገጥ ይግባኝ ለቀረበበት የመንግስት መ/ቤት የግዥ ሂደቱ ይግባይ የተባለበት ስለመሆኑና ከግዥ አፈጻጸሙ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሠነዶችና መግለጫዎች እንዲልክ፣ እንዲሁም ቦርዱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሁፍ ማስታወቂያ መላክ፣

ሸ/ ከመንግስት መ/ቤቱ የተሰጠውን ምላሽና መግለጫ፣ ተጠናቅረው የቀረቡለትን ማስረጃዎችና የይግባኝ ጭብጦች፣ ከአዋጁና ከዚህ መመሪያ አኳያ መርምሮ ውሳኔ መስጠት፣

a) To issue directives to the Public Body to perform its duties in accordance with the Proclamation and this Directive.

b) To determine adjustments to the procurement execution process under complaint, and to reject applications deemed non-compliant.

c) To order the complete or partial suspension of the procurement execution process under complaint.

d) To investigate the matter and, pending decision, issue a written notice prohibiting further procurement activities until a ruling is made.

e) To conduct document verification or hold hearings as necessary.

f) To order Public Bodies, competing bidders, applicants, or other entities to submit documents, records, reports, or other evidence necessary for decision-making.

g) If the application was timely and properly submitted, to instruct the Public Body responsible for the procurement to submit related documents and explanations and prohibit further actions until a final decision.

h) To review the response, evidence, and application in light of the Proclamation and this Directive and render a decision.

160. <u>የቦርዱ የአሰራርሥነ-ሥርዓት</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉዳዮች ቦርዱ በሚያወጣውየአሰራር ሥርዓት መመሪያ ይወሰናሉ፤

ሀ/ የቦርዱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት፣ የስብሰባጊዜ፣
ለ/ የቦርዱ ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት፣

160. The Board's Operational Procedure

The board's operational procedure directive shall determine the following:

a) Board meeting procedures and schedule,

b) Board decision-making process,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ሐ/ ይግባኝ ለቦርድ የሚቀርብበትን እና የሚጣራበትን ሥርዓት፣

መ/ ይግባኝ ላይ ስለሚደረግ ምርመራ እና ክርክር ስለሚሰማበት ሥርዓት፣

ሠ/ ማስረጃዎች የሚቀርቡበት አግባብ፣

161. ቦርዱ ስለሚሰጠው ትዕዛዝ

1) ቦርዱ ይግባኙ በሚሰማበት በማንኛውም ጊዜ የሚከተሉትን ትዕዛዞች ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሀ/ ጥያቄ ሲቀርብ ተጨማሪ ተከራካሪ ወገን ጣልቃ እንዲገባ፣

ለ/ የጉዳዩን መሰማት ለተወሰነ ጊዜ እንዲያቆይ፣

ሐ/ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት አላቸው የሚባሉ በሌሎች በህግ ሥልጣን ባላቸው አካላት እጅ የሚገኙ ወይም የተሰጡ ውሳኔዎችን ወይም የተሰጡ የምስክርነት ቃሎች ወዘተ ያሉበትን ቦታ እንዲያመለክቱ ፣

መ/ ተከራካሪ ወገኖች ለተያዘው ጉዳይ አስፈላጊ የሆነ የባለሙያ፣የቴክኒክ ወይም ሳይንሳዊ ማስረጃ እንዲያቀርቡ፣

ሠ/ ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም ተቋም ሰነድ፣ የሰውማስረጃዎች ወይም አስረጂዎች እንዲቀርቡ ወይም መርምረው ውጤት እንዲገልፁ ሊያዝ ይችላል፡፡

3) ማንኛውም የቦርዱ ትዕዛዝ በጽሁፍ ለተከራካሪ ወገኖች እና ለሚመለከታቸው አካላት መገለጽ አለበት፣ በጽሁፉም ላይ ቦታ እና ሰዓት መገለጽ ያለበት ሲሆን ማንኛውም ሰው ትዕዛዙን ማክበርና መፈጸም ይኖርበታል፡፡

4) ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የተሰጠውን ትዕዛዝ አግባብነት የለውም ወይም መሻሻል አለበት ወይም ለተወሰነ ጊዜ መቆየት አለበት ብሎ ካመነ ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣ አቤቱታውም በጽሁፍ የሚቀርብ ሆኖ ኮፒውም ለሌላኛው ወገን ተከራካሪ ከ3 ቀን በፊት መድረስ አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የሚቀርበው የጽሁፍ አቤቱታ ትዕዛዙ የሚቀርበትን፣ የሚሻሻልበትን ወይም የሚቆይበትን ምክንያት በግልጽ ማካተት አለበት፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በሚቀርበው የጽሁፍ አቤቱታ ላይ ቦርዱብይን ይሰጣል፡፡

c) Appeal submission and review process,

d) Investigation and hearing procedures,

e) Manner of evidence presentation.

161. Decision to be Made by the Board

1. The board may issue the following orders at any stage of an appeal hearing:

   a) Allow an additional interested party to intervene;

   b) Adjourn the hearing for a specified period;

   c) Request relevant decisions, testimonies, or documents held by other legally authorized entities;

   d) Compel competing parties to submit expert, technical, or scientific evidence;

   e) Order submission of any human or documentary evidence essential for a fair decision.

2. The board may compel entities to submit documents, present witnesses or evidence, or conduct investigations and report findings.
3. All orders issued by the board shall be communicated in writing to concerned parties and specify place and time. Compliance is mandatory.
4. Any party believing an order invalid, requiring amendment, or suspension may complain to the board in writing, providing a copy to the opposing party at least three days prior to review.
5. The written complaint shall explicitly state reasons for invalidation, amendment, or suspension.
6. The board shall rule on the written complaint.
7. If a party fails to comply with the board's order, the board may terminate the matter,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

7) ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በቦርዱ የተሰጠውን ትዕዛዝ ካልፈጸመ ቦርዱ እንደ አግባብነቱ ጉዳዩ እንዲቋረጥ ወይም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተከራካሪ ወገን በሌለበት ክርክሩ እንዲቀጥል ወይም የተጠቀሰው ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው ሊወሰን ይችላል።

162. ቦርዱ ውሳኔውን እንደገና ስለሚያይበት አግባብ

ማናቸውም ሰው ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ለፍርድ ቤት ቅሬታውን አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት፣ ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያት ጥያቄውን ለቦርዱ በማቅረብ የተሰጠው ውሳኔ እንደገና እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፤

ሀ/ የመጨረሻው ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሰነድ ወይም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃልን፣ መደለያንወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት በማድረግ ሲሆንና አቤት ባዩም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጎ ለማወቅ አለመቻሉን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፣

ለ/ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ተግባሮች መፈፀማቸው ቢገለጽ ኖሮ ለፍርዱ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማስረዳት ከቻለ፤

ሐ/ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች መፈጸማቸውን የሚያረጋግጥ ትክክለኛ ማስረጃ ጋር የይግባኝ አቤቱታውን በሚቀርብበት አግባብ መቅረብ አለበት።

መ/ አመልካቹ ያቀረበውን አቤቱታ ግልባጭ ለሌላኛው ወገን እንዲደርሰው በማድረግ መከራከሪያ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠት ክርክሩ የሚሰማበትን ቀን ቀጠሮ መወሰን አለበት።

ሠ/ ቦርዱ ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባዋል ወይም አይገባውም በማለት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል። በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ አይቻልም።

163. ይግባኝ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ስለማቅረብ

1) በአዋጁ አንቀጽ 81 መሰረት ቦርዱ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 84 መሰረት ባለስልጣኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚችለው በሕግ ትርጉም ረገድ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ብቻ ነው።

proceed without the non-compliant party, or rule evidence inadmissible.

162. Circumstances under which the Board Reviews Its Decision

Before appealing a board decision or order to court, a person may request the board to reconsider its decision on the following grounds:

a) The final judgment, decision, or order was based on documents prepared fraudulently or submitted falsely, false testimony, forged evidence, or criminal conduct, provided the party could not reasonably have identified the fraud before the judgment.
b) If such fraudulent or false conduct is demonstrated, it may constitute sufficient grounds for modifying or overturning the judgment, provided evidence is submitted.
c) The request for reconsideration must be submitted with valid evidence proving these grounds, following prescribed procedures.
d) The applicant's complaint shall be served on the opposing party, and a hearing date set for submission of arguments.
e) The board shall decide whether to reconsider its judgment. This decision is final and not subject to appeal.

163. Submission of an Appeal to a Regular Court

1. Pursuant to Article 81 of the Proclamation, any interested party dissatisfied with a decision issued by the Board or the Authority under Article 84 of the Proclamation may appeal to the Federal Supreme Court solely on matters

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

2) በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ቀጥሎ ባሉት 15 (አስራ አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።

ምዕራፍ አስር

የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት እና የሚጣራበት ሥርዓት

164. ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርብ የጥፋተኝነት ሪፖርት

በመንግስት ግዥ አፈጻጸም ሂደት የመንግስት መ/ቤት በተጫራቾች ወይም በአቅራቢዎች ሕገ ወጥ የሆነ ወይም ሕጋዊ ጥቅሜን የሚጎዳ ድርጊት ተፈጽሞብኛል ብሎ ሲያምን በጨረታ ሠነዱ ወይም በውል ስምምነቱ መሠረት የሚወሰዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለባለሥልጣኑ የጥፋተኝነት ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

165. የጥፋተኝነት ሪፖርት አቀራረብ

1) ባለሥልጣኑ የመንግስት መ/ቤቶች በተጫራቾች ወይም በአቅራቢዎች ላይ የሚያቀርቡትን የጥፋተኝነት ሪፖርት በሚከተሉት ሁኔታዎች አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል።
2) ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት በመንግስት ግዥ የተሳተፈ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ በተሳተፈበት ግዥ የሚመራበት ህግ ከሚያዘው ውጭ መፈረሙን ውል ለመፈረም ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ ማጭበርበሩን፣ ሀሰተኛ ሠነድ ለውድድር ማቅረቡን፣ መመሳጠሩን፣የሙስና ተግባር መፈጸሙን እና ወይም የገባውን የውል ግዴታ አለመፈጸሙን፣ማሳየት ከቻለ በጥፋት ፈጻሚው ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ሊያቀርብ ይችላል።
3) ባለሥልጣኑ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ሪፖርት ፍሬ ሃሳብ በመግለጽ በዝርዝር ያለውን ማስረጃና ማብራሪያ በሰባት (7) ተከታታይ

concerning legal interpretation of the Board's decision.

2. An interested party dissatisfied with the Board's decision may file an appeal to the Federal Supreme Court within fifteen (15) working days from the date the decision is issued.

CHAPTER TEN
OFFENSE REPORT PRESENTATION AND REVIEW SYSTEM

164. Submission of Offense Report to the Authority

Where, during the execution of a procurement process, a Public Body identifies unlawful acts or actions by bidders or suppliers that harm legitimate interests—and provided that any measures taken are consistent with the tender documents or contract agreements—it shall submit a misconduct report to the Authority.

165. Presentation of an Offense Report

1. The Authority shall examine and decide upon misconduct reports submitted by Public Bodies concerning bidders or suppliers under the following circumstances:
2. A Public Body may submit a misconduct report against a bidder or supplier involved in a public procurement process, demonstrating that the party has violated procurement laws, refused to sign a contract after being awarded, colluded with others, submitted false documents, engaged in corrupt practices, or failed to fulfill contractual obligations.
3. The Authority shall notify the bidder or supplier against whom an offense report has been filed, provide the substance of the report, and require the submission of a

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ መላክና አፈጻጸሙን መከታተል አለበት።

4) ባለሥልጣኑ ከመንግስት መ/ቤቱ እንዲሁም ከተጫራቹ ወይም ከአቅራቢው የቀረበለትን መግለጫና ማስረጃዎች ከአዋጁ፣ ከዚህ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ፣ከጨረታ ሠነዱ እንዲሁም ከግዥ ውሉ አኳያ በማጣራት የጥፋተኝነት ሪፖርቱ በቀረበ በአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን የጥፋተኝነት ሪፖርት ላቀረበው የመንግስት መ/ቤት እና የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት አቅራቢ ወይም ተጫራች እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት መላክ አለበት።

written response and evidence within seven (7) consecutive working days. The Authority shall monitor compliance with this requirement.

4. The Authority shall review the statements and evidence submitted by both the Public Body and the bidder or supplier in accordance with the Proclamation, procurement implementation directives, tender documents, and contract provisions. A decision must be rendered within fifteen (15) working days and communicated to the reporting Public Body, the reported party, and other relevant entities as necessary.

166. ባለሥልጣኑ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች

1) ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የግዥውን የግምገማ ውጤት ሆን ብሎ ለማዛባት ወይም ለማስለውጥ በጨረታው ሂደት ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መፈጸሙ ከተረጋገጠ እንደሁኔታው ከሁለት አመት ላላነሰ ጊዜ ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት በሚያወጣው የመንግስት ግዥ ላይ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል።

ሀ/ የሙስና ተግባር ማለትም በግዥ ሙያ ላይ ለተሰማራ ባለሙያ ወይም ኃላፊ ጉቦ ወይም ማባበያ ወይም ማንኛውንም ዋጋ ያለው ነገር መስጠቱን በማስረጃ ሲረጋገጥ፣

ለ/ የማጭበርበር ማለትም ሐሰተኛ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ሠነድ ማቅረቡ ወይም በባለሥልጣኑ ታጎዶ እያለ የአገዳ ጊዜውን ሳያጠናቅቅ በሌላ የንግስት ግዥ ጨረታ ላይ ተካፍሎ መገኘቱ፣ ወይም ከውል ውጭ ጥራት የጎደለው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ፣ ወይም የምክር አገልግሎት፣ እውነተኛ ወይም ትክክለኛ አስመስሎ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

166. Decisions to be Issued by the Authority

1. If it is confirmed that a bidder or supplier engaged in any of the following actions with the intent to distort or manipulate the procurement evaluation process or contract administration, the entity shall be barred from participating in public procurement for a minimum of two (2) years and shall have its supplier registration revoked:

a) Corrupt practices, including offering bribes, inducements, or anything of value to a procurement professional or official, as substantiated by evidence.

b) Collusion, including the submission of fraudulent documents, participation in tenders while under suspension, or supply of substandard or non-compliant goods, services, or works under misrepresentation.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ሐ/ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር ተመሳጥሮ ዋጋን በመወሰን መ/ቤቱ ከነጻ ውድድር ማግኘት የሚችለውን ጥቅም ማሳጣቱ ሲረጋገጥ፣

መ/ ከመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ከውሉ ውጭ የሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

ሠ/ በግዥ ሥራ ላይ የተሰማራ ባለሙያ ወይም ኃላፊ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መጉዳትን ወይም ለመጉዳት ማስፈራራት (መዛቱን) ወይም ማስገደዱ ሲረጋገጥ፣

ረ/ ቀደም ሲል በባለስልጣኑ የተጣለበትን ቅጣት ከፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ ዕገዳ የሚስከትል ጥፋት መፈጸሙ ሲታወቅ፣

2) ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸሙ ሲረጋገጥ፣ እንደጥፋቱ ክብደት እየታየ ከስድስት ወራት ያላነሰ እና ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በማንኛውም የመንግስት ግዥ ላይ እንዳይሳተፉ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፣

ሀ/ በገባው ውል መሰረት አቅርቦቱን ወይም አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን ባለማጠናቀቁ፣ ወይም አቅርቦቱን ጀምሮ በማቋረጡ ምክንያት በመንግስተ መ/ቤቱ ላይ የገንዘብ ኪሳራ ወይም የስራ መጓተት ወይም የጥቅም ማጣት ካስከተለ፣

ለ/ በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ መሆኑ በፅሁፍ ተገልጾለት ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት መ/ቤቱ ግዥውን ከሌላ ተጫራች በመፈጸሙ በመንግስት መ/ቤቱ ኪሳራ ወይም የስራ መጓተት ካስከተለበት፣

ሐ/ ከዚህ ቀደም (ከሶስት ዓመት ወዲህ) ሌላ ጥፋት ፈጽሞ ከባለሥልጣኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የነበረ ሆኖ አሁን የቀረበበት ሌላ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጥ የግዥ አፈጻጸም ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ፣

3) ማንኛውም ተጫራች ወይ አቅራቢ የሚከተሉት ጥፋቶች መፈጸሙሲረጋገጥ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፣

c) Price fixing through collusion with other bidders, thereby denying the Public Body the benefits of free competition.

d) The provision of unauthorized goods, services, or works in collusion with Public Body staff.

e) Causing or threatening harm, or coercing a procurement official or professional.

f) Repeating a penalizable offense within two years of a prior penalty being imposed and enforced.

2. If a supplier or provider is found to have committed any of the following acts, it shall be barred from public procurement participation for a period between six months and two years, proportionate to the severity of the offense, and its registration shall be revoked:

a) Failure to perform or complete the contracted goods, services, consultancy, or works, leading to financial or operational harm to the Public Body.

b) Refusal by the selected bidder to sign the contract after award, resulting in procurement from another bidder and consequent loss to the Public Body

c) Repeating procurement violations despite having been previously warned within the past three years.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

ሀ/ ውል ገብቶ አቅርቦቱን ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራውን በውሉ በተቀመጠው ጊዜ ሳይሆን ዘግይቶ በማቅረቡ ምክንያት በመ/ቤቱ ሥራ ችግር መፍጠሩ፣

ለ/ በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ ተመዝግበው ከሚገኙ አቅርቢዎች መፈጸሙ እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥ ለሚፈጸም ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ፕሮፎርማ እንዲሰጥ ተጠይቆ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑ ከተረጋገጠ

ሐ/ የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበበት ተጫራች ወይም አቅራቢ በማምረት ሥራ ላይ የተሰማራ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበር፣ ወይም የአካል ጉዳተኞች ማህበር፣ ወይም የነጋዴ ሴቶች ማህበር ወይም የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶችን የሚያቀርብ ከሆነና ጥፋቱን የፈጸመው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ፣

መ/ ተጫራቹ ወይም አቅራቢው ከምርት ልዩነት ወይም ከውጪ ምንዛሬ እጥረት ጋር ተያይዞ ከድርጅቱ አቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እንደገጠመው ከሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያቀረበ እንደሆነ፣

4) ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ በተዘረዘሩት ቅጣቶች መሰረት የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ ለሁሉም የፌዴራል መ/ቤቶች፣ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ኮሌጆችና ማዕከላት፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲደርሳቸው ይደረጋል፣ በባለስልጣኑ የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ፖርታልና ድረ-ገጽ ላይ እንዲሰፍር ይደረጋል።

5) ባለሥልጣኑ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች ተጫራቹ ወይም አቅራቢው በፈጠረው ችግር ምክንያት የደረሰባቸው ኪሳራ በግዥ ውላቸው እና አግባብነት ባለቸው ሌሎች ህጎች መሰረት መጠየቅ ይችላል።

6) የመንግስት መ/ቤቶች የሚያቀርቡት የጥፋተኝነት ሪፖርት የተሟላ ማስረጃ የሌለው እንዲሁም ሪፖርቱን ካቀረቡ በኃላ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል

3. The Authority may issue a warning in the following circumstances:

a) Delay in delivering goods, services, consultancy, or works after contract signature, causing operational challenges.

b) A registered provider's refusal to submit a proforma when requested by a Public Body.

c) First-time violations committed by micro and small enterprises, disability associations, women entrepreneurs' associations, or entities providing technological innovations.

d) When non-performance is due to external factors beyond the supplier's capacity, such as technological differences or foreign currency shortages, as confirmed by a third party.

4. The Authority's decision under this Article shall be communicated to all federal institutions, higher education institutions, regional and city administrations, and published on the Authority's electronic procurement platform and website.

5. The Authority's decision shall be binding. Public Bodies may claim damages incurred due to supplier or provider actions as per the contract and applicable laws.

6. If the misconduct report lacks adequate evidence, or if the Public Body fails to provide the additional information requested by the Authority, the case shall be closed.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

ተጨማሪ መረጃና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ከባለስልጣኑ ተጠይቀው በወቅቱ ካላቀረቡ ባለስልጣኑ ክሱን ይዘጋል።

167. ባለስልጣኑ ውሳኔውን እንደገና ስለሚያይበት አግባብ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ ከ3 እስከ 6 የተደነገገው ቢኖርም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በስምምነት እልባት የሚሰጡበት፣ የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበበት ድርጅት ጥፋቱን ተቀብሎ ግዴታውን ሲወጣ ወይም ጥፋቱን ሲያርም ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚወስናቸው ውሳኔዎች ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል።

ሀ) ክሱን ተገቢውን መረጃ በማየት መዝጋት፣

ለ) የሚቀርቡ መረጃዎችን በማጣራት እገዳውን ማንሳት፣

ሐ) የሚቀርቡ መረጃዎችን በማጣራትና ውሳኔውን በድጋሚ በማየት ቅጣቱን ማቅለል፣

መ) የመጀመሪያውን ውሳኔ የሚያስቀየር ባለመኖሩ ቅጣቱን የሚያጸና ውሳኔ፣

2) ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 84መሰረት የቀረበለትን የጥፋተኝነት ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ሂደት በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የተፈጸመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ጉዳዩን ለመመርመር እና እርምጃ ለመውሰድ በሕግ ስልጣን ለተሰጠው የህግ አስፈጻሚ አካል ያሳውቃል፡

168. <u>መረጃን ስለማቅረብ</u>

ባለስልጣኑ በአዋጁ መሰረት የቀረበለትን የጥፋተኝነት ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ሂደት በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የተፈጸመ መሆኑን ሲረዳ አግባብነት ላለው የመንግስት አካል መረጃ መስጠት አለበት።

167. Circumstances Under Which the Authority Reviews Its Decision

1. Notwithstanding Sub-Articles 3 to 6 of Article 84 of this Directive, if the parties involved reach a mutual resolution, or if the offender remedies the issue, the Authority may issue one of the following decisions:
   a) Close the case based on verified evidence.
   b) Lift the suspension after confirming the remedy.
   c) Modify the penalty after reassessing the evidence.
   d) Uphold the original penalty without change.
2. If, upon reviewing an offense report under Article 84 of the Proclamation, the Authority determines that the act constitutes a criminal offense, the matter shall be referred to the competent law enforcement body.

168. Submission of Evidence

Upon determining that the act described in the offense report constitutes a criminal offense, the Authority shall forward the relevant information and evidence to the appropriate government body for investigation and legal action.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ምዕራፍ አስራ አንድ
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

169. ለመንግሥት መ/ቤቶች ስለሚቀርብ የሒሳብ ሰነድ

ባለስልጣኑ በአዋጁ መሰረት የቀረበለትን የጥፋተኛነት ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ሂደት በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የተፈጸመ መሆኑን ሲረዳ አግባብነት ላለው የመንግስት አካል መረጃ መስጠት አለበት።

170. የተሻሩ መመሪያዎች

1) በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ አሠራር፣ልማድ ወይም ሰነድበዚህ መመሪያ ተሽሯል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው በተጨማሪ የሚከተሉት መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፤

ሀ/ የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ እና የዚሁ መመሪያ ማሻሻያ የሆኑት መመሪያ ቁጥር 258/2013፣ መመሪያ ቁጥር 260/2013፣ እና መመሪያ ቁጥር 264/2013ን ጨምሮ የመመሪያው ሁሉም ማሻሻያዎች፤

ለ/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምግብ ግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 221/2013፤ እና

ሐ/ የፌዴራል ኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ መመሪያ ቁጥር 814/2013።

171. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተጀመሩ የግዥ ሂደቶች፣ ውሎች እና የግዥ አቤቱታዎች በነባሩ መመሪያ መሠረትፍፃሜ ያገኛሉ።

CHAPTER ELEVEN
MISCELLANEOUS PROVISIONS

169. Submission of Financial Documents to Public Bodies

If a Public Body requires an audit report to be submitted for participation in a tender under this Directive, the report must be prepared by a certified auditor or auditing firm licensed by the Accounting and Audit Board.

170. Repealed Directives

1. Any directive, procedure, or document inconsistent with the provisions of this Directive is hereby repealed.

2. In particular, the following directives are repealed:

a) The Federal Government Procurement Execution Directive and all its amendments, including Directive Nos. 258/2013, 260/2013, and 264/2013.

b) Directive No. 221/2013 on Food Procurement for Higher Education Institutions.

c) Directive No. 814/2013 on Federal Electronic Government Procurement and Disposal of Property.

171. Transitory Provisions

Procurement processes, contracts, and complaints initiated before the effective date of this Directive shall be finalized in accordance with the prior directive.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

172. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ይፋዊ ድህረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስአበባ _____ ቀን ____2017 ዓ.ም.

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር

172. Effective Date of the Directive

This Directive shall come into force on the date of its publication on the Ministry of Finance's official website following its registration with the Ministry of Justice.

Addis Ababa .....Date .....2017 E.C

Ahimed Shide

Minister of Finance

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አባሪ-1

የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢና ፀሐፊ ዋና ዋና ኃላፊነቶች

1.1 የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነቶች

የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የኮሚቴውን የስብሰባ ቀንና ሰዓት ይወስናል፣ ስብሰባውን ይመራል፡፡
2. ከጨረታ ሂደት ጋር የተያያዙ ተግባራት የመንግስት ግዥ አዋጅና መመሪያውን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

1.2 የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ኮሚቴ ፀሐፊ ኃላፊነት

የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ኮሚቴ ፀሐፊ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚመደብ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ማንኛውንም የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ይመዘግባል፣ ኮሚቴው የተሟሉ ሠነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣ በጥንቃቄ ይይዛል፡፡
2. በውሳኔ አሠጣጥ ሂደት ከአቅራቢዎች ጋር የተደረገ ውይይት ካለ በቃለ-ጉባዔ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡
3. ከኮሚቴው ሰብሳቢ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት አጀንዳ ያዘጋጃል፡፡
4. የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ስብሰባዎች ድምፅ

1.3 የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

1. የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ኮሚቴ ሊሰበሰብ የሚችለው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ሲሆን ውሣኔ የሚተላለፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡
2. የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ኮሚቴ በውሳኔ አሰጣጥ ወቅት እኩል ድምጽ በሚኖረው ጊዜ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
3. በድምፅ አሰጣጥ ወቅት በሃሳብ የተለየ አባል ሲኖር የተለየበት ምክንያት በቃለ-ጉባዔው እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

Annex – 1

Key Responsibilities of the Chairperson and Secretary of the Procurement and Property Disposal Committee

1.1 Responsibilities of the Chairperson of the Procurement and Property Disposal Committee

The Chairperson of the Procurement and Property Disposal Committee, designated as the senior official of the Committee, shall have the following responsibilities:

1. Convene meetings of the Committee by determining the date and time, and preside over such meetings.
2. Ensure that all activities of the tender process are conducted in accordance with the Public Procurement Proclamation and this Directive.

1.2 Responsibilities of the Secretary of the Procurement and Property Disposal Committee

The Secretary of the Procurement and Property Disposal Committee, designated as the senior official of the Committee, shall have the following responsibilities:

1. Record minutes of all Committee meetings, ensure complete documentation is maintained, and safeguard all related records with due diligence.
2. Where consultations with suppliers occur during the decision-making process, document such interactions in the meeting minutes and retain them securely.
3. Prepare the agenda for each meeting in accordance with the instructions of the Chairperson.

1.3 Meeting Procedures of the Procurement and Property Disposal Committee

1. The Committee may conduct a meeting only when more than half of its members are present. Decisions shall be adopted by a majority vote.
2. In the event of a tie in votes, the decision supported by the Chairperson shall prevail.
3. If a member dissents from the majority opinion, the reason for such dissent shall be recorded in the minutes.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አባሪ-2

<u>ከግዥ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የሚጠበቅ ሙያዊ ስነ-ምግባር፣</u>

ማንኛውም ከግዥ ሥራ ጋር በተገናኘ በጊዜያዊነት የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ አባል የሚሆኑ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ግምገማ ማከናወን የሚችሉት በቅድሚያ በዚህ አባሪ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በማክበርና በፊርማቸው መስማማታቸውን በማረጋገጥ መሆን ይገባዋል፡፡

1. የጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ከግል ጥቅማቸው ጋር የተተያያዘ እና ኃላፊነታቸውን በትክክል እንዳይወጡ የማድረግ ውጤት ያለው ወይም የዚህ አይነት ውጤት ሊያስከትል የሚችልን ማናቸውም ሁኔታ ከግምገማው ጋር በተያያዘ አለመፈጠሩን ማረጋገጥ፣
2. ከግዥ ግምገማው ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ስጦታ አለመቀበላቸውን ማረጋገጥ፣
3. ከግዥ ፈፃሚው አካል በጽሑፍ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር መረጃውን ለሦስተኛ ወገን አሳልፈው መስጠት አለመስጠትና ከሥራው ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያገኙትን መረጃ በምስጢር መጠበቅ፣
4. ከተጫራቾች የሚቀርብን የመጫረቻ ሠነድ ያለምንም አድሎ እና ልዩነት መመዘን እና ውጤቱን አለማዘባት፣
5. በግምገማ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በጨረታ ሠነድ ዝግጅትም ሆነ ዋና ዋና የፍላጐት መግለጫ ዝግጅት ወቅት ያልተሳተፈ መሆኑን ማረጋገጥ፣
6. ከላይ ከተዘረዘሩት አንዱን መከሰቱን ካረጋገጠ የጊዜያዊ ኮሚቴ አባሉ ለወከለው የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ እራሱን ማግለል አለበት፡፡ ሆኖም እራሱን የሚያጋለው የኮሚቴ አባል እራሱን ከስራ ለማሸሽ መሆን ግን የለበትም፡፡

ስለሆነም የኮሚቴው አባላት ከላይ የተዘረዘሩትን አንብበው መስማማታቸውን በፊርማቸው ያረጋግጣሉ፡
፡

የኃላፊው/የባለሙያው ስም _____ የሥራ መደብ _____ አድራሻ _____ የስልክ _____ የኢ-ሜይል _____ቀን _____

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

Annex – 2

Professional Ethics for Procurement Officers and Experts

Officials or experts appointed as temporary members of a procurement evaluation committee shall confirm their understanding and acceptance of the following ethical standards by signing this declaration prior to conducting any evaluation activities:

1. Confirm that there is no actual or potential conflict of interest related to the evaluation, and that their professional judgment will not be influenced by personal interests.
2. Affirm that they have not accepted, and will not accept, any form of gift, either directly or indirectly, that could influence the procurement evaluation process.
3. Undertake to maintain strict confidentiality, refraining from disclosing any procurement-related information to third parties unless expressly authorized in writing by the Procuring Entity.
4. Conduct bid evaluations impartially and without discrimination, and avoid any improper handling or manipulation of evaluation results.
5. Confirm that none of the evaluation committee members were involved in preparing the bidding documents or drafting key terms of reference.
6. If any of the above conditions are not met, the concerned committee member must immediately notify the responsible authority of the Public Body in writing and withdraw from participation. A committee member may not seek withdrawal merely to avoid responsibilities.

Declaration of Compliance

I hereby confirm my agreement to the above ethical principles:

Name of Official/Expert: .....
Position: .....
Address: .....
Telephone: .....
Email: .....
Date: .....

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

አባሪ - 3

ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዋና ዋና ኃላፊነቶች

1.1 ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ኃላፊነቶች

ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ እንደግዥው አይነት እና አስፈላጊነት በጊዜያዊነት በመቤቱ የበላይ ኃላፊ በደብዳቤ የሚሰየሙ ሆኖ ኮሚቴውን እንዲመራ የተወከለው ሰብሳቢ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴው ግምገማውን የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን ተከትሎ መፈጸሙንና በሲስተሙ የተሰጡትን ተጨማሪ ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣቱን ያረጋግጣል፡፡
2. ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴው የግምገማ ሥራው የሚጀምርበትን ቀንና ሰዓት `ይወስናል፣ በተወሰነው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የግምገማ ስራውን ይመራል፡፡
3. ከግምገማው ሂደት ጋር የተያያዙ ተግባራት የመንግስት ግዥ አዋጅና መመሪያውን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
4. ማንኛውንም ከግምገማው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሠነዶች እና መዛግብቶች በጥንቃቄ ተይዘው መገምገማቸውን ያረጋግጣል፡፡
5. እንደ ግዥው ውስብስት የግምገማው ጊዜ የሚያጥርና የሚረዝም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የግዥ ግምገማዎች እስከ አራት ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው የግምገማው ሪፖርት ለግዥ ሥራ ክፍል መቅረቡን ያረጋግጣል፡፡



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2022

Annex – 3

Key Responsibilities of the Chairperson of a Temporary Procurement Evaluation Committee

1.1 Responsibilities of the Temporary Procurement Evaluation Committee Chairperson

A temporary procurement evaluation committee shall be established as needed, based on the nature and complexity of the procurement. The Chairperson of the committee shall be appointed in writing by the Head of the Public Body. The Chairperson shall have the following responsibilities:

1. Ensure that the evaluation is carried out in accordance with the requirements of the government's electronic procurement system and that any additional responsibilities assigned through the system are fully discharged.
2. Set the date and time for the commencement of evaluation activities and supervise the evaluation process as scheduled.
3. Ensure that the evaluation complies with applicable procurement laws and directives.
4. Carefully review all documents and records relevant to the evaluation to ensure the accuracy and reliability of the assessment.
5. Depending on the complexity of the procurement, confirm whether the evaluation period should be extended or shortened; in all cases, the evaluation must be completed within four weeks and the report submitted to the procurement unit accordingly.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

አባሪ - 4

የጨረታ መተማመኛ ቅጽ

ሀ. የግዥ አይነትና የግዥ መለያ ቁጥር----------

ለ. የግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ስም----------

ሐ. የማህበሩ/ የድርጅቱ ሕጋዊ ስም----------

መ. የማህበሩ/ የድርጅቱ የአሁን አድራሻ----------

ሠ. የማህበሩ/ የድርጅቱ መሪ ሕጋዊ ስምና የአሁን አድራሻ----------

ረ. የማህበሩ/ የድርጅቱ አባላት ብዛት በቁጥር ----------

ማህበሩ/ድርጅቱ የሚገባቸው ግዴታዎች፣

እኛ ከላይ ስማችን የተጠቀሰው ማህበር/ድርጅት ከላይ በተጠቀሰው የግዥ መለያ ቁጥር በወጣው ጨረታ ላይ የተሳተፍን ሲሆን በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር-- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ "ለ" መሰረት በጨረታ ማስከበሪያ እና በውል ማስከበሪያ ምትክ የድጋፍደብዳቤከአደራጅን አካል የገንዘብ መጠን በመጥቀስ እና በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በማስፈረም ያቀረብን ሲሆን በተጨማሪም ይህንን መተማመኛ ቅጽ ሞልተን ያቀረብን ሲሆን፣

(ሀ) መ/ቤቱ በጨረታ ሰነዱ ያስቀመጣቸውን ግዴታዎችመርምረንሁሉንምያለምንምተቃውሞተቀብለናል፣

(ለ) በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የሰፈሩትን መስፈርቶችን እናሟላለን፡፡

(ሐ) ከታች የተዘረዘሩትን ነገሮች ያቀረብነውም ከሌሎች ተወዳዳሪዎችና ተጫራቾች ጋር ውይይት፣ ግንኙነት ወይም ስምምነት ሳናደርግ በግላችን ብቻ ነው፡፡

I. የጨረታ ዋጋዎች
II. የጨረታ ማቅረቢያ ሃሳብ
III. ዋጋን ለማውጣት የተጠቀምንባቸው ዘዴዎችና ነጥቦች

(መ) በመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ጥፋተኛ ናችሁ ተብለን ከመንግሥት ግዥ አልታገድንም፡፡

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

(ሠ) እኛ አልከሰርንም ወይም በመክሰር ላይ አይደለንም።

(ረ) በኢትዮጵያ የታክስ ህግ መሠረት የሚፈለግብንን ታክስ የመክፈል ግዴታችንን ተወጥተናል፡

(ሰ) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 5 ስለማጭበርበርና ስለሙስና የተመለከተውን አንብበን ተረድተናል። ስለሆነም በጨረታ ሂደትም ሆነ በውል አፈፃፀም ጊዜ በእንደዚህ ዓይነት ድርጊት የማንሳተፍ መሆኑን እናረጋግጣለን።

(ሸ) የምዝበራና የማጭበርበር ድርጊት አልፈፀምንም፣ ከማንኛውም ተጫራች ጋር አልተመሳጠርንም።

(ቀ) ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት እንዳላችሁ እንረዳለን።

(በ) ከጨረታው ጋር በተገናኘ የሰጠነው መረጃ በአጠቃላይ እውነትና የተረጋገጠ ሲሆን መ/ቤቱን የሚያሳስቱ እና ውሸት ሆነው ቢገኙ መንግስት በሚያወጣቸው ጨረታዎች እንዳንሳተፍ መ/ቤቱ እንደጥፋተኛነት በመቁጠር ሪፖርት ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በማቅረብ ከመንግስት ግዥዎች ብንታገድ የማንቃወም፣

መሆናችንን እና ከላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ማሟላታችንን እንዲሁም በ----------ምትክ ባቀረብነው የመተማመኛ ቅጽ መሰረት መጠየቅ የምንችል መሆኑን በፊርማችን እናረጋግጣለን።

ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ----------

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

Annex – 4

Bid Security Declaration Form

a) Type of Procurement and Procurement Identification Number: _____

b) Name of Procuring Entity: _____

c) Legal Name of the Association/Organization: _____

d) Current Address of the Association/Organization: _____

e) Legal Name and Address of the Leader of the Association/Organization: _____

f) Number of Members in the Association/Organization (in numeric form): _____

Declaration and Acknowledgment of Obligations

We, the undersigned association/organization, confirm our participation in the tender referenced above. Pursuant to Article 30(2)(b) of the Federal Public Procurement Directive No. ___/2025, we have submitted a letter of support from our parent organization, specifying the financial commitment and duly signed by its head, in lieu of bid security and performance guarantee. We also submit this signed declaration as further assurance of our commitment.

We confirm the following:

a) We have reviewed and accepted all obligations set out in the tender documents.
b) We satisfy all conditions stated in the bid document.
c) We have submitted the following items independently, without any communication oragreement with other bidders:
    I. Bid prices
    II. Bid submission proposal
    III. Pricing methodology and evaluation criteria
d) We have not been barred from public procurement, even where allegations of misconduct exist.
e) We are not subject to any criminal prosecution.
f) We have complied with our tax obligations under Ethiopian law.
g) We have read and understood Article 5 of the General Conditions of Contract regarding collusion and corruption, and we commit to refrain from such practices.
h) We affirm that we have not engaged in corruption or collusion, nor have we conspired with any bidder.
i) We acknowledge the right of the Procuring Entity to cancel the tender, in whole or in part.
j) All information submitted by us is true and accurate. If any part of our submission is found to be false or misleading, we understand that the Procuring Entity may report us

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

to the Public Procurement and Property Administration Authority, and we may be blacklisted. We will not challenge such action.

By signing below, we affirm our existence as a legal entity, our commitment to the above conditions, and our liability in accordance with this declaration and the substituted guarantee for bid security or performance bond.

Name: .....

Title/Responsibility: .....

Signature: .....



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አባሪ - 5

<u>የመንግስት መ/ቤት የቀድሞ ሰራተኞች በጨረታ ስለሚሳተፉበት አግባብ</u>

ማንኛውም የቀድሞ ሠራተኛ የመጫረቻ ሰነዱን በመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ከመሙላቱ በፊት ወይም የጨረታ አካል ከመሆኑ በፊት በመንግስት መ/ቤቱ ውስጥ ከሰራቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት እንዳይኖር በቅድሚያ ይህንን ቅጽ በመሙላት አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

በመንግስት መ/ቤቱ የቀድሞ ሠራተኛ የሚሰጥ መረጃ፣

1. በተቋሙ ስራ የጀመረበት ጊዜ----------
2. ተቋሙን የለቀቀበት ጊዜ----------
3. ከጨረታው ጋር በተገናኘ ምንም አይነት የጥቅም ግጭት የለብኝም።
4. በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የሰፈሩትን መስፈርቶችን አሟላለሁ።
5. ጨረታውን በተመለከተ የሰጠሁት መረጃ ትክክለኛ ነው።

ከጨረታው ጋር በተገናኘ የሰጠሁት መረጃ በአጠቃላይ እውነትና የተረጋገጠ ሲሆን መ/ቤቱን የሚያሳስቱ እና ውሸት ሆኖ ቢገኝ ከዚህ የጨረታ ሂደት ውጪ እንደምሆን በተጨማሪም መንግስት በሚያወጣቸው ጨረታዎች እንዳልሳተፍ መ/ቤቱ እንደጥፋተኛነት በመቁጠር ሪፖርት ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በማቅረብ ከመንግስት ግዥዎች ብታገድ የማልቃወም መሆኑን እና ከላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ማሟላቴን እንዲሁም ከዚህ መስሪያ ቤት ከለቀቅሁ ከአንድ ዓመት በላይ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ----------

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

Annex – 5

Declaration Form for Former Public Body Employees Participating in Tenders

Any former employee of a Public Body must complete this form prior to participating in a tender or completing procurement documents on the electronic government procurement system, in order to proactively disclose any potential conflicts of interest related to prior employment.

Information to be Provided by the Former Public Body Employee:

1. Date of employment commencement at the institution: _____
2. Date of departure from the institution: _____
3. I declare that I have no conflict of interest concerning the procurement process.
4. I meet all eligibility requirements outlined in the tender document.
5. The information I have provided concerning this tender is complete and accurate.

I affirm that the above declarations are true and accurate. Should any information be found to be false or misleading, I understand that I may be excluded from the procurement process and reported to the Public Procurement and Property Administration Authority for appropriate action, including disqualification from future public procurements. By signing below, I further confirm that more than one year has passed since my departure from the Public Body.

Name: _____
Position Held: _____
Signature: _____

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አባሪ - 6

1. <u>ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ</u>

1.1 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 በተገለፀው መሰረት ዝቅተኛ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ጊዜ በሚከተለው አኳኋን ይወሰናል፡፡

ሀ/ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት በመጠቀም የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ጊዜ የግዥውን ዓይነት እና የግዥውን የተሳትፎ ሽፋን በተለይም ውስብስብ የሆኑ እና ያልሆኑ ግዥዎችን በመለየት ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን መወሰን አለባቸው፡፡

ተራ ቁጥር	የግዥው ዓይነት	ውስብስብነት	ግልጽ ጨረታ		የተገደበ ጨረታ		ዋጋ ማቅረቢያ (በኤሌክትሮኒክ)
			ዓለም አቀፍ	ብሔራዊ	ዓለም አቀፍ	ብሔራዊ	
1	የግንባታ ዘርፍ ሥራ	ውስብስብ	40	25	40	25	
		ውስብስብ ያልሆነ	30	20	30	20	
2	ዕቃ	ውስብስብ	30	20	30	20	
		ውስብስብ ያልሆነ	25	10	25	10	
3	ሌሎች አገልግሎቶች	ውስብስብ	40	25	40	25	
		ውስብስብ ያልሆነ	25	10	25	10	
4	የምክር አገልግሎት • የፍላጎት መግለጫ (EOI) • የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ	ውስብስብ	10	7			24 ሠዓት
		ውስብስብ ያልሆነ	7	5			
		ውስብስብ	40	25	30	25	
		ውስብስብ ያልሆነ	25	10	20	10	

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

ለ/ ውስብስብ ያልሆነ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥ የሚባለው በዚህ አባሪ ቁጥር ተራ ቁጥር 1.2 የተመለከተው ዓይነት ግዥ ነው።

ሐ/ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ በሚፈጸም ግዥ የመጫረቻ ሰነድ የማቅረቢያ ጊዜ የግዥው ዓይነት፣ አስቸኳይነት፣ ውስብስብነት፣ የአቅራቢዎቹ የተሳትፎ ሽፋን እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ከላይ በሰንጠረዥ ከተገለፀው ከ24 ሠዓት በታች ማድረግ አይፈቀድም። ሆኖም ግዥው አንድ አቅራቢ በሚሆንበት ጊዜ የመጫረቻ ሰነድ የማቅረቢያ ጊዜውን በመስሪያ ቤቶች ይወሰናል፡

መ/ ግዥው የሚፈፀመው የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴን መሠረት በማድረግ በሚሆንበት ጊዜ

1. በመጀመሪያ ደረጃ እንደግዥው ዓይነት በተራ ቁጥር 1.1 (ሀ) በተመለከተው መሠረት በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ወይም በአገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ለሚፈጸም ውስብስብ ግዥ የተፈቀደው ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ወይም የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበት የመጫረሻ ጊዜ ተፈፃሚ ይደረጋል።
2. በሁለተኛው ደረጃ በመንግስት መስሪያ ቤቱ በውድድር ተሳታፊ እንዲሆኑ የተመረጡት የተወሰኑ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር ተጫራቾች ለሚሳተፉበት የተገደበ ጨረታ በተራ ቁጥር 1.1 (ሀ) ለተገደበ ጨረታ የተፈቀደው ዝቅተኛ ጊዜ ተፈፃሚ ይደረጋል።

ሠ/ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በተራ ቁጥር **1.1 (ሀ) ላይ የተገለጸው ዝቅተኛ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ጊዜ** መሆኑን በመረዳት እንደግዥው ዓይነት እና የገበያው ሁኔታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንደአስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ የሆኑ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጡ ይችላሉ።

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

1.2 በዚህ አባሪ ተራ ቁጥር 1.1 (ለ) መሠረት ውስብስብ ያልሆኑ ግዥዎች ዝርዝር፣

ዕቃዎች	የግንባታ ሥራዎች	የምክር አገልግሎት	ሌሎች አገልግሎቶች
• ለገበያ የተዘጋጁ የጽህፈት መሳሪያዎች • ለገበያ የተዘጋጁ የዕዳት ዕቃዎች • ለገበያ የተዘጋጁ ኮምፒዩተሮችና ተጓዳኝ ዕቃዎች • ለገበያ የተዘጋጁ ፕሪንተሮች • ለገበያ የተዘጋጁ የቢሮ መገልገያዎች • የመኪና ጎማ • ለገበያ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ መለዋወጫዎች (ለምሳሌ የተሸከርካሪ የቢሮ መገልገያ ማሽኖች • ለገበያ የተዘጋጁ የኤሌክትሪክ፣ ኤሌክትሮኒክስና ኤሌክትሮ ሜካኒካል ዕቃዎች • ለገበያ የተዘጋጁ የቢሮ መገልገያ ማሽኖች (ለምሳሌ ፋክስ፣ ፎቶ ኮፒ፣ መጠረጊያ ማሽን)	• የህንጻ ዕድሳት • የቀለም ቅብ ሥራ • የጊዜያዊ ቤቶች ሥራ • የአጥር ሥራ • የቢሮ መከፋፈል (ፓርትሽን) ሥራ	• ዝርዝር የጥናት አካሔድ (Methodology) ማቅረብ የማይጠይቁ አገልግሎት ግዥዎች፣	• የህትመት • የተሽከርካሪ ጥገና • የመሳሪያዎችና ዕቃዎች ኪራይ • የቢሮ ዕቃዎችና የቢሮ ማሽኖች ጥገና • የትራንስፖርት ኪራይ • የሆቴልና መስተንግዶ • የባንክ እና የኤሌክትሪክ ጥገና • የሥልጠና • የአዲት አገልግሎት • የጥበቃ እና የጽዳት • የግዥ አገልግሎት • የግቢ ማስዋብና ማስተካከል • የቢሮ ማስዋብ • የቢሮ ኪራይ

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

• የግንባታ ዕቃዎች (ለምሳሌ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ አሸዋ፣ ቧንቧ፣ ቀለም፣ እንጨት፣ ምስማር) • የምግብ ጥሬ ዕቃ እና የተዘጋጀ ምግብ • ነዳጅና ልዩ ልዩ ቅባቶች • ለገበያ የተዘጋጁ ልብሶች፣ ጨርቆችና ጫማዎች • ለገበያ የተዘጋጁ መድሐኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች • ኬሚካሎች እና ሬኤጀንቶች • መጽሐፍት እና ጆርናሎች			

- "ለገበያ የተዘጋጁ" ማለት ለተጠቃሚው ሕዝብ ፍላጎት ተብለው የሚመረቱ ስታንዳርድ የገበያ ዕቃዎች ሲሆኑ ለግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ በተለየ ሁኔታ የሚመረቱትን አይጨምርም::
- ግዥ ፈጻሚው አካል ዝርዝር የጥናት አካሄድ የማያስፈልጋቸውን ውስብስብ ያልሆኑ የምክር አገልግሎቶች ዓይነት የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት የሚኖረውን የጥናት ባሕርይ በማየት ይወሰናል::

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

Annex – 6

Bid Validity Period and Submission Timeframes

1. Period During Which the Tender Remains Open for Participation
1.1. In accordance with Article 109(2) of this Directive, the minimum period for preparing and submitting procurement documents is determined as follows:

a) When using the electronic government procurement system, Public Bodies shall differentiate between complex and non-complex procurements, applying the following table based on procurement type and scope of participation:

S. No.	Procurement Type	Complexity	Open Tender (Days)	Restricted Tender (Days)
			Int'l	Nat'l
1	Construction Works	Complex	40	25
		Non-Complex	30	20
2	Goods	Complex	30	20
		Non-Complex	25	10
3	Other Services	Complex	40	25
		Non-Complex	25	10
4	Consultancy Services	Complex EOI	10	7
		Non-Complex EOI	7	5
		Proposal	40	25
		Non-Complex	25	10

b) "Non-complex procurement" refers to procurement types listed under Serial No. 1.2 of this annex.
c) For procurements using price offers, the minimum bid submission period shall be no less than 24 hours, unless it involves a sole supplier.
d) In two-stage tenders:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

- The first stage shall observe the minimum periods outlined in 1.1(a).
- In the second stage, restricted tender timelines as per 1.1(a) shall apply to shortlisted bidders.

e) Public Bodies may extend the minimum submission periods reasonably, based on market conditions and the nature of the procurement.

1.2. List of Non-Complex Procurements (As per Serial No. 1.1(b)):

Goods:

- Standard stationery and sanitary materials
- Standard computers, printers, office machines and accessories
- Tyres and spare parts (vehicles and office equipment)
- Electrical, electronic, and electro-mechanical items
- Construction materials (cement, steel, water pipes, paint, wood, nails)
- Basic foodstuffs and processed foods
- Petroleum products and lubricants
- Ready-made garments and footwear
- Standard medicines and medical equipment
- Chemicals and reagents
- Books and journals

Construction Works:

- Building maintenance
- Painting works
- Temporary housing and fencing
- Office partitions

Consultancy Services:

- Assignments not requiring in-depth studies

Other Services:

- Printing, transport, vehicle maintenance, office equipment repair
- Equipment and goods leasing

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

- Hotel, plumbing, electrical repair, training, audit, security, sanitation
- Procurement services, landscaping, office decoration, office rental

Note: "Standard" refers to commonly available, off-the-shelf goods not produced for specialized or custom orders. Non-complex consultancy assignments are those that, based on the terms of reference, do not demand deep or extensive studies.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

አባሪ - 7

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 116 መሠረት በተጫራቾች የሚሞላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና፣

የግዥው መለያ ቁጥር.....(የጨረታ መለያ ቁጥር ይግባ)

ለ.....(የግዥ ፈጻሚው የመንግስት መ/ቤት ሙሉ ስም ይግባ)

/የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ/ ከአሁን በኋላ "ተጫራች" እየተባለ የሚጠራው በግዥ መለያ ቁጥር .....(የግዢ መለያ ቁጥር እና የዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች..... (አጭር መግለጫ ይግባ) ከአሁን በኋላ ጨረታው እየተባለ የሚጠራውን ለማቅረብ በ...../የጨረታ ማስረከቢያ ቀን...../.....ወርና.....ዓ.ም.....አስገባ/ የተጻፈውን ጨረታ ያስገባን ስለሆነ እኔ ...../የድርጅቱ ስምና ባለቤት ወይም የመፈረም ሥልጣን ያለው ኃላፊ ስም አስገባ/ ከዚህ በታች የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና/ የጨረታ ዋስትናው መጠንና የገንዘቡት ዓይነት በቃላት እና በቁጥር ግልጽ/ ሙሉ ኃላፊነት ድርጅቱ የሚወስድ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

የዋስትና ሰጪው የተለመደ ማህተብ ተደርጎበት/ዋስትናው የሚቆይበት የቀን ብዛት በቁጥር፣ በወር ወይም በዓመት መሆኑ ተለይቶ ይገለፅ/ ይታሸጋል።

የሚከተሉትን ግዴታዎች በመረዳት ተፈጻሚ ለማድረግ ተስማምቻለሁ።

ሀ/ በጨረታ ሠነዱ የተገለጸው የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን ካለፈ በኋላ ወይም በመጫረቻ ሠነዱ የተገለጸው የጨረታ ዋጋ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ከጨረታው አራሴን ላለማግለል፣ ወይም

ለ/ በመጫረቻ ሠነዱ የተገለጸው የመጫረቻ ዋጋ ጸንተ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የግዥ ውል አንድፈርም የቀረበልኝን የጽሁፍ ጥያቄ በመቀበል ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ለመሆን፣ ወይም

ሐ/ በጨረታው ውድድር አሸናፊ በመሆኔ ውል አንድፈርም እና የውል ማስከበሪያ አንዳስይዝ ስጠየቅ የውል ማስከበሪያውን ለማስያዝ ፈቃደኛ ለመሆን፣ እና ከላይ በፊደል ተራ ሀ እስከ ሐ እና በጨረታ ሠነዱ የተገለጹትን ሌሎች ተግባራት ባልፈጽም የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በሚያቀርበው የጽሁፍ ጥያቄ ከላይ የተገለጸውን የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ለመ/ቤቱ ወዲያውኑ ለመክፈል ተስማምቻለሁ።

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2018

ይህ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታው ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ በተጨማሪ ለ28 ቀናት በህግ ፊት ጸንቶ ይቆያል። ይህን ዋስትና በተመለከተ ከተጠቀሰው ጊዜ ዘግይቶ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡
፡

ስም.....(ጨረታውን የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስምና ሕጋዊ ሥልጣን ይግባ)

ፊርማ .....(ስምና ማዕረጉ ከላይ የተጠቀሰው ሰው ፊርማ ይግባ)

ወይም (ወኪል ከሆነ ጨረታውን ለመፈረም ህጋዊ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሙሉ ስምና ፊርማ ይግባ)

ቀን..... (የተፈረመበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት ይግባ)

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

Annex – 7

Bid Security Form (Pursuant to Article 116 of the Directive)

Procurement Identification Number: _____
For: [Insert Name of Procuring Public Body]

We, [Insert Bidder's Full Legal Name], hereinafter "the Bidder," in respect of Procurement Identification Number _____ and the procurement of [Insert Brief Description], hereinafter "the Bid," confirm by this signed declaration that we have fulfilled the following bid security requirements:

I, [Insert Name of Authorized Representative], acting on behalf of the Bidder, hereby affirm that:

- The amount and form of the bid security are explicitly stated in both words and numbers.
- The bid security is valid for [Insert validity period: days/weeks/months].
- The original signed and sealed bid security has been affixed with the Bidder's official stamp.

We further undertake the following obligations:
a) Not to withdraw from the bidding process during the bid validity period.
b) To sign a contract upon receipt of award notification and within the bid validity period.
c) Upon award, to sign the contract and submit performance security as required.

Failure to comply with the above obligations will result in forfeiture of the bid security amount to the Procuring Public Body without dispute.

This guarantee remains valid for 28 calendar days beyond the expiry of the bid validity period. Claims submitted after the expiry of this period shall be rejected.

Name of Authorized Person: _____
Position/Capacity: _____
Signature: _____
Date: _____

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2023

አባሪ - 8

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 136 መሠረት በተጫራቾች የሚሞላ የውል ማስከበሪያ ዋስትና፣

ቀን----------የግዥመለያቁጥር:- ----------

ለ:---------- *[የግዥ ፈፃሚ አካል ሙሉ ስም ይግባ]*

<u>የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ</u> (ከዘህ በኋላ "አማካሪ" እየተባለ የሚጠራ) በቀን---------- ወር___ ዓ.ም.____ በተፈረመው ውል ቁጥር----------(ካሁን በኋላ "ውል" እየተባለ የሚጠራው) መሠረት *የአገልግሎቶች ዝርዝር ይገለጽ* *(----------)* ለማቅረብ ግዴታ የገቡ ሲሆን፣

በተጠቀሰው ውል ውስጥ እርስዎ አማካሪው ለገቡበት የውል ግዴታ ይሆንዎ ዘንድ *የዋስትና አይነት ይገለጽ* *(----------)* ከታወቀ ዋስትና ሰጭ መጠኑ ለተጠቀሰው ገንዘብ የውል ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያቀርቡ አጥብቀው የጠየቁ ስለሆነ፡፡

እኛ ከዘህ በታች ፊርማችንን ያኖርንና ህጋዊ አድራሻችን----------
<u>የዋሱ ሙሉ ስም ይግባሕጋዊ የመኖሪያ አድራሻው</u> *(ሙሉ የዋሱ አድራሻ ይግባ)*፣ የሆንን (ካሁን በኋላ "ዋስ" እየተባለን የምንጠራው) ለአማካሪው ዋስትና ለመስጠት የተስማማን ስለሆነ፣

ስለዚህ እኛ አማካሪውን በመወከል እስከ *የዋስትናው የገንዘብ ዓይነትና መጠኑ በአሀዝ እና በፊደል ይግባ* (----------) ለሚደርስ ዋስትና ተጠያቂ መሆናችንንና አማካሪው ውሉን መጣሱን በመግለጽ የክፍያ ጥያቄ በጽሑፍ እንደቀረበልን ያላንዳች ማስረጃና ክርክር ክፍያ ለተጠየቀበት ምክንያት እስከ *የዋስትናው መጠን በአሀዝና በፊደል ይግባ* ---------- የሚደርስ ለመክፈል ግዴታ እንገባለን፡፡

ይህ ዋስትና የሚፀናው እስከ ቀን---------- ወር---------- ዓ.ም----------ድረስ ይሆናል፡፡

ይህ ዋስትና በዓለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት እትም ቁ. 458 መሰረት ለደንበኞች በጥያቄ የሚሰጥ አንድ ዓይነት ዋስትና ነው፡፡

ስም----------(ጨረታውን የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስምና ሕጋዊ ሥልጣን ይግባ)

ኃላፊነት:----------[ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ኃላፊነት ይግባ]

ፊርማ .....(ስምና ማዕረጉ ከላይ የተጠቀሰው ሰው ፊርማ ይግባ)

ዋስትናው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው አካል---------- [የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ]

ቀን---------- (የተፈረመበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት ይግባ)

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2021

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

Annex – 8

Performance Security Form (Pursuant to Article 136 of the Directive)

Date: _____

Procurement Reference No.: _____

To: [Insert Name of Procuring Entity]

Whereas [Insert Name of Consultant], hereinafter referred to as "the Consultant," has entered into Contract No. _____ dated _____ for [Insert List of Services to Be Delivered] (hereinafter "the Contract"), and the Consultant is required to provide performance security, we, [Insert Name and Full Address of Guarantor], hereinafter "the Guarantor," undertake to guarantee the performance obligations of the Consultant.

We hereby guarantee payment of up to [Insert Amount and Currency in Words and Figures] upon the Procuring Entity's written demand, stating that the Consultant has breached contractual obligations, without the need to provide proof or engage in dispute resolution.

This Guarantee shall remain valid until [Insert Validity Date: Day/Month/Year].

This Guarantee is issued in accordance with International Chamber of Commerce publication No. 458.

Name of Authorized Signatory: _____

Position: _____

Signature: _____

Representing: _____

Date: _____



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

አባሪ-9

<u>የመንግስት መ/ቤቶች የውል አፈጻጸምን የሚከታተሉበት ቅጽ</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 137 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የፈጸሟቸውን የግዥ ውል ስምምነቶች በውሉ መሰረት እየተከናወኑ መሆናቸውን መከታተል እና አፈጻጸማቸውን መገምገም አለባቸው።

1. ውሉ የተፈረመበት ቀን እና ለምን ያክል ጊዜ ጸንቶ እንደሚቆይ፣
2. የተዋዋዮችን ዋና ዋና ግዴታዎችን፣
3. የውል ማስከበሪያው ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣
4. አቅራቢው በሚሰጠው የግዥ ትዕዛዝ መሠረት አቅርቦቱን እየፈጸመ ስለመሆን አለመሆኑ፣
5. የውል ስምምነቱ በተያዘለት ጊዜ ካልተጠናቀቀ ተጨማሪ የውል ጊዜ መስጠት አስፈላጊ ስለመሆን አለመሆኑ መወሰን፣
6. ተጨማሪ የውል ጊዜ የሚሰጠው ሆኖ ሲገኝ አቅራቢው የውል ማስከበሪያውን ለተጨማሪ ቀናት ማራዘም እንዲችል ማደፍረግ፣
7. አቅራቢው በውሉ መሠረት መፈጸም ካልቻለ በመመሪያው መሠረት ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ በሚመለከት ለመንግስት ወርስ ማድረግ ወይም አሳማኝነቱ በአጽዳቂ ኮሚቴው ሲታመንበት ተመላሽ ማድረግ፣
8. የአቅራቢውን የአፈጻጸም ደረጃ ግምገማ በማድረግ የተጠቃለለ የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

Annex – 9

Contract Performance Monitoring and Evaluation Form

(Pursuant to Article 137(2) of the Directive)

Public Bodies shall monitor and assess procurement contract execution based on this standardized format, which includes the following elements:

1. Contract effective date and duration
2. Principal obligations of both parties
3. Performance security validity period
4. Whether the supplier performed in accordance with the purchase order
5. Determination of the necessity of contract extension due to incomplete performance
6. Enforcement of an extension of the performance security where contract duration is extended
7. Enforcement or release of performance security based on evaluation findings
8. Preparation of a consolidated performance report after supplier evaluation



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

አባሪ - 10

<u>በቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ የሚገዙ ማሽነሪዎች፣</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 138 ንዑስ አንቀጽ 7 ለአሸናፊው ተጫራች በሚፈቀድ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ለመንገድ ሥራና ለሕንጻ ግንባታ ሥራ የሚገዙ ማሽነሪዎች ዝርዝር፣

ተ.ቁ	ለመንገድ ሥራ የተፈቀዱ የግንባታ መሣሪያዎች	ለሕንጻ ግንባታ ሥራ የተፈቀዱ መሣሪያዎች
1	ቡል ዶዘር	ኤክስካቫተር
2	ፍሮንት ኢንድ ሎደር	ሀይድሮሊክ ብሬከር
3	ሞቶር ግሬደር	ክሬይን
4	ትሬንች ኤክስካቫተር	ታወር ክሬይን
5	ባክሆይ	ዶዘር
6	ግሪድ ሮለር	ተራክ ሚክሰር
7	ቫይብራቶሪ ሮለር	ሎደር
8	ወተር ቦውሰር	ዳምፕ ትራክ
9	ዳምፕ ተራክስ	ስካፎለዲንግ
10	ትራክ ዊዝ ትሬለር	ፎርምወርክ
11	ሎቤድ ሀኡሊንግ ተራክ	ፍሮንት ኤንድ ዳምፐር
12	ቤትውመን ዲስትሪቢውተር	ኮምፓክተር ወይም ሮለር
13	ስቴሽነሪ ሂተር	ባክሆ
14	ፔቨር ፎር ቤዝ ኮርስ	ክሬሸር
15	አስፓልት ፔቨር	ጀኔሬተር
16	ሰልፍ ፐሮፒልድ ችፕ ስፒረደር	ተራክ ዊዝ ትሬለር
17	ሚካኒካል ብሩም	

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th of June 2025

Annex – 10

List of Machinery to Be Purchased with Advance Payment
(Pursuant to Article 138(7) of the Directive)

For Road Works:

1. Bulldozer
2. Front-End Loader
3. Motor Grader
4. Trench Excavator
5. Backhoe
6. Grid Roller
7. Vibratory Roller
8. Water Bowser
9. Dump Trucks
10. Truck with Trailer
11. Hauling Truck
12. Bitumen Distributor
13. Station Heater
14. Base Course Paver
15. Asphalt Paver
16. Self-Propelled Chip Spreader
17. Mechanical Broom

For Building Construction:

1. Excavator
2. Hydraulic Breaker
3. Crane
4. Tower Crane
5. Dozer

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023

6. Truck Mixer
7. Loader
8. Dump Trucks
9. Scaffolding
10. Formwork
11. Front-End Dumper
12. Compactor/Roller
13. Backhoe
14. Crusher
15. Generator
16. Truck with Trailer



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of June 2023